የጸጋውንና የበረከቱን ምሥጢር ማወቅና ማመን ራሱ በረከት ነው፡፡ የመጀመሪያው ሰማያዊና መንፈሳዊ በረከት እግዚአብሔር ከሁሉ አስቀድሞ የአባ ዘሮች ከእርሱ ርቀውና ጠፍተው እንዳይቀሩ በልጁ አማካይነት ወደ ራሱ መጥራቱና መምረጡን የሚያመለክት ነው፡፡ ሐዋርያው " ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን"(ኤፌ. 1፥4) በማለት የተናገረው ቃል እኛ ሰዎች በእግዚአብሔር ዘንድ ምን መሆን እንደሚገባን ወይም በክርስቶስ ወደፊት የምንሆነውን የመጨረሻውን ዓላማችን ያስረዳናል፡፡ መቼም ሰው በጥንተ ፍጥረቱ በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠረ ስለሆነ ሰው ፈጣሪውን ይመስላል (ዘፍ.1፥26)፡፡ ስለሆነም እርሱ ቅዱስ እንደሆነ ሰውም ቅዱስ መሆን ይገባዋል (1ኛጴጥ.1፥15-16)፡፡ ነገር ግን ሰው በሠራው በደል የተነሣ ንጽሐ ጠባይዕ ስላደፈበት ፈጣሪውን መምሰል ተስኖታል፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ ሰዎችን ነውር የሌለባቸው ቅዱሳን አድርጐ ወደራሱ ሊያቀርባቸው በፊቱም ሊያቆማቸው፥ በፍቅርም ሊያ ኖራቸው ማሰቡንና በልጁም አማካይነት ይኸንን እንደሚፈጽመውና እን ፈጸመው ከላይ የተጠቀሰው ኃይለ ቃል ያስገነዝበናል፡፡ እንግዲህ የመጀመሪያው መንፈሳዊ በረከት እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳንና ለመቀደስ ብሎ በልጁ አማካ ይነት ያቀደውና ያደረገው ሰማያዊ ጥሪና ምርጫ ነው፡፡ በተለይም "ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ" ተብሎ ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን የተነገረውን ታላቅ ምሥጢር ያመለክተናል (ኤፌ.5፥27-32)፡፡ ምክንያቱም በክርስቶስ በመመረጣችን ነው ነውር የሌለን ቅዱሳን ሆነን ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ የምንችለው፡፡ ቤተ ክርስቲያንም የቅዱሳን ማኅበር ናትና፡፡ በክርስቶስ የመጣልን ሰማያዊ ጸጋና በረከት ለቅድስናውና ለፍቅሩ የበቃን ሊያደርገን ይችላል፡፡

የሰው ልጅ ሊደሰትበት የሚገባ የመጀመሪያ ደስታው በእግዚአብሔር መጠራትና መመረጥ ነው፡፡ የጌታ ደቀ መዛሙርት ተልዕኳቸውን ፈጽመው ሲመለሱ በተሰጣቸው ሥልጣን አጋንንት ስለ ተገዙላቸው ደስ ብሏቸው ነበር፡፡ ጌታ ግን "መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፤ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ" ብሏቸዋል (ሉቃ.10፥17-20) ይህም የሚያሳየው ከሥራቸው በፊት በእግዚአብሔር መመረጣቸው ሊያስደስታቸው እን ደሚገባ ነው፡፡ መመረጥም ታላቅ ዕድልና ሰማያዊ በረከት ስለሆነ ይህ ጸጋ የተ ሰጣቸው ሁሉ በእውነት ደስ ይበላቸው፡፡

## (2) የጸጋ ልጅነት (ሀብተ ወልድና)

ሁለተኛው ሰማያዊና መንፈሳዊ በረከት የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን የሚያስገነዝበን ነው፡፡ ይህም እግዚአብሔር "በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ" ስለ ወሰነን ነው (ኤፌ.1፥5)፡፡ ቅዱሳን እንዲሆኑ የመረጣቸውን፥ ልጆቹ እንዲሆኑ በልጁ አከናውኗቸዋል፡፡ የልጅነት ማዕርግ ታላቅ ጸጋ ነው፡፡ ለእግዚአብሔር ልጅ የመሆን መብት የተገኘው በክርስቶስ እንደሆነ ተጽፏል፡፡ ክርስቶስን "ለተቀበሉት ሁሉ . . . በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተ ወለ ዱም" (ዮሐ.1፥12-13)፡፡ ከእግዚአብሔር ተወለዱ የምንለው በክርስቶስ አምነው ከውኃና ከመንፈስ ሲወለዱ ማለት ሲጠመቁ ነው፡፡ ያን ጊዜ በጸጋ መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ አዲስ ሰው አዲስ ፍጥረት ይሆናሉ፤ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ፡፡



የጸጋ ልጅነት ማግኘት ታላቅ ሰማያዊ በረከት ነው፡፡ ሰው ሁሉ የእግዚአ ብሔር ልጅ አይባልም፡፡ ሰማያዊ ጸጋ የተሰጣቸው ብቻ ናቸው ለእግዚአብሔር ልጅነት ዕድል ያገኙት፡፡ "የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፥ እንዲሁም ነን . . . ወዳጆች ሆይ፤ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፥ ምን እንደምንሆን ገና አልተ ገለጠም፡፡ ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን፡፡ በእርሱም ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንጹሕ እንደሆነ ራሱን ያነጻል (1ኛዮሐ.3፥1-3)፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች "የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ . . . ወሰኗልና፤ እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፤ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፤ የአጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው" እንደ ተባለው ለልጆቹ በክብር ላይ ክብር በበረከት ላይ በረከት ጨምሮላቸዋል (ሮሜ.8፥29-30)፡፡ ከባሕርይ ልጁ ከክርስቶስ ጋር አብረው ወራሾች እንዲሆኑ በቸርነቱ እንዲሁ አድርጐላቸዋል (ሮሜ.8፥17)፡፡ "በውድ ልጁም እንዲያው የሰ ጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ" (ኤፌ.1፥6)፡፡

## (3) ከኃጢአትና ከሞት የመዳን ጸጋ (ሀብተ ድኂን)

ሦስተኛው ሰማያዊ በረከት ለመዳናችን መሠረት የሆነውና ሌሎቹንም በረከት እንድናገኝ ያደረገልን የጌታችን የማዳኑ ሥራ ነው፡፡ "በውድ ልጁም፥ እን ደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ሥርየት" (ኤፌ.1፥7) የተባለው ኃይለ ቃል ታላቁንና አማራጭ የሌለውን የመዳናችንን ጸጋና በረከት ባጭሩ ይገልጽልናል፡፡ ልጁ በሥጋ ወደ እኛ መጥቶ በእኛ ፈንታ ነፍሱን ቤዛ አድርጐ ባይሰጥልንና በደሙ ባይክስልን ኖ ሮ ለበደላችን ሥርየት፥ ለኃጢአታችን ምሕረት ባለማግኘት በበረከት ምትክ መርገም፥ በሕይወት ምትክ ሞት፥ በዘላለም ደስታ ምትክ የዘላለም ስቃይ ዕድል ፈንታችን ሆኖ ይቀር ነበር፡፡ ጌታችን በሰውነቱ ኃጢአታችንንና ሞታችንን ወስዶ በሕማማቱና በሞቱ ኃጢአታችንን አስወግዶልናል፥ ሞታችንን ደምስ ሶልናል፥ ትን ሣኤ ሙታንን ሰጥቶናል፡፡ ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆናችን ያገኘነውና የምናገኘው ጸጋና በረከት እጅግ ታላቅና ድንቅ ነገር ነው፡፡ " እግዚአብሔር . . . በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን . . . ከእርሱ ጋር አስነሣን በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ሥፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን" (ኤፌ.2፥4-7)፡፡

በደሙ ፈሳሽነት ያገኘነውን የመዳን ጸጋና በረከት ሁልጊዜ እንድናገኘው ጌታ በጸሎተ ኀሙስ ሥርዓተ ቁርባንን ሠርቶልናል፡፡ በየዘመኑ የሚነሡት ሰዎች ሁሉ ለትውልደ ትውልድ ይህን የመዳን ጸጋና በረከት እንዲያገኙ ምሥጢረ ቁርባንን ይፈጽማሉ፡፡ እንዲህ በማድረጋቸውም የመዳን ጸጋና በረከት የተቀ በሉበትን ክቡር ሞቱን "ጌታ እስኪመጣ ድረስ" ይመሰክራሉ (1ኛቆሮ.11፥21)፡፡ በጌታ ሞት የተገኘው የኃጢአት ሥርየት በየዘመኑ ለሚነሡት ሁሉ ይህ ጸጋና በረከት እንዲዳረስ ምሥጢረ ጥምቀትን መሥርቶልናል፡፡ በጥምቀትና በንስሐ የኃጢአት ሥርየትን እናገኛለን፡፡ ይህም ታላቅ በረከት ነው፡፡ በጠቅላላው ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ስለ መሠረተልን ከክርስቶስ ልዩ ልዩ ጸጋና በረከትን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እናገኛለን፡፡ "ጸጋውንም በጥበብና በአእምሮ ሁሉ አበ ዛልን" (ኤፌ.1፥8)፡፡

## (4) በክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ማዕከልነት ተጠቃሎ ስለ ሚገኘው የአንድነትና የሰላም በረከት

በኃጢአት ምክንያት በጥላቻ፥ በክፋትና በድንቁርና የተለያየውን ዓለምና እንዲሁም እያረጀና እየፈረሰ የሚገኘውን ሥነ ፍጥረት ሁሉ በሐዲስ ተፈ ጥሮ በክርስቶስ እንደገና ሊፈጥረው በልቡናው ያሰበውን ታላቅ ምሥጢር ... እንደገለጠው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አስረድቶናል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ይህም በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ በተከሠተው መከራና ፈተና ለሚሠቃየው ዓለ
ማችን ታላቅ የምሥራች ቃል ነው። እንግዲህ አራተኛው ሰማያዊ በረከት
ለዘመናት ተሰውሮ የነበረውን የእግዚአብሔርን ፈቃድና እቅድ አውቆና አም
የጸጋውና የበረከቱ ተካፋይ መሆን ነው። ሐዋርያው ሲጽፍ "በክርስቶስ
ለማድረግ እንደ ወደደ እንደ አሳቡ፥ የፈቃዱን ምሥጢር አስታውቆናልና፥
በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ
በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው" ብሎ የተናገረው ኃይለ ቃል በኤፌሶን መልእክ
ለተነሡት ፍሬ ነገሮች ሁሉ መክብባቸው ነው፥ ለሰማያዊ በረከት ሁሉ
ማእከላቸውና ማጠቃለያቸው ነው (ኤፌ.1፥9-10)። እግዚአብሔርንና ሰውን
በማስታረቅ፥ ሰላምን በምድር በማምጣት፥ በእሥራኤልና በአሕዛብ መካከል
የነበረውን የጥል ግርግዳ በማፍረስ፥ በብሔር፥ በቋንቋ፥ በዘር፥ በቀለም
በሌላም ነገሮች ተለያይተው የነበሩትን ሁሉ አንድ ሕዝብ የእግዚአብሔር
ወገኖች እንዲሆኑ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያኑ የተደረገውንና እየተደረ
ያለውን ታሪካዊ ክንውን ሁሉ ያካተተው ይህ የአራተኛው በረከት ምሥጢር
ነው። ሥራውም ገና እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ይቀጥላል። በሰማይ ያሉትን
መላእክትንና በምድር ያሉትን ሰዎች ሁሉ ጠቅልሎ የሚገዛ ክርስቶስ ነው። ዓለ
ምን የሚያበጣብጠውን ኃጢአት በማስወገድ ጌታ በእርሱ ያመኑትን ሁሉ አዳ
ናቸው፤ የዳኑትን ወገኖቹን ደግሞ በፍቅርና በሰላም በአንድነት በቤተ ክርስቲያን
ሰበሰባቸው።

"ሁሉ በእርሱ /በክርስቶስ/ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ
እርሱ አልሆነም" (ዮሐ.1፥3) እንደ ተባለው እግዚአብሔር ይህን ወደ ም
ያን አደረገ ሲባል ቃሉ፥ እጁ፥ ክንዱ፥ ኃይሉ፥ ጥበቡ በተባለው በልጁ
በክርስቶስ እንዳደረገው አምነን ይኸን ሁልጊዜ እንደ መመሪያ ቃል መያዝ አለ
ብን። እግዚአብሔር የሠራው ሁሉ በክርስቶስ የተሠራ ነው፤ በክርስቶስ
የተፈጸመው ሁሉ እግዚአብሔር የፈጸመው ነው፤ ሁለቱ አይለያዩም፤ አንድ
ናቸው። ምንም በተለየ አካሉ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ ሥጋ ቢለብስና
በአርአያ ገብር በትሕትና ቢገለጥ በመለኮት በባሕርይ በሕልውና ሦስቱም አንድ
ናቸው። ስለዚህ በአንድ ቦታ እግዚአብሔር ክርስቶስን ከሙታን አስነሣው
ወይም በሌላ ቦታ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ የሚል ቃል ብናነብ ሁለቱ
የሚቃረኑ ሳይሆኑ ሁለቱም አንድ ናቸው። ምክንያቱም የሞተው የክርስቶስ
ሥጋ ነው። አስነሺው ደግሞ መለኮት ነውና። በመለኮት ሦስቱም አንድ ስለሆ
ኑ አብ አስነሣው ወይም ወልድ የተዋሐደውን ሥጋ አስነሣው ወይም መንፈስ
ቅዱስ አስነሣው ቢባል አስነሺው ያው አንድ መለኮት ስለሆነ ልዩነት አያ
መጣም (ሮሜ.8፥9-11 ትርጓሜውን ተመልከት)። ወልደ እግዚአብሔር
ክርስቶስ በአምላክነቱ በመስቀል ላይ ሳለ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው ከለየ
በኋላ እንደገና ሁለቱንም በማገናኘት ለሦስት ቀን በመቃብር ያደረውን ሥጋውን
እንዳስነሣው እናምናለን። ክርስቶስ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ነው።
እዚህ ላይ መንፈስ የተባለው ባሕርየ መለኮቱ ነው። "ሞተ በሥጋ ወሐይወ
በመንፈስ፡ በሥጋ ሞተ በመለኮት ተነሣ" ይላልና (1ኛጴጥ.3፥18 ትርጓሜውን
ተመልከት)።

እግዚአብሔር በሰማይም በምድርም ያለውን ሁሉ አጠቃሎ የሚገዛው
በልጁ ነው። እግዚአብሔር ኃይሉንና ሥልጣኑን፥ መግቦቱንና ረድኤቱን፥
ጸጋውንና በረከቱን ሁሉ የሚገልጠው በልጁ ስለሆነ ይኸንን ለማከናወን ልጁን
ወደ ዓለም ላከ። ልጁም በመስቀሉ ዓለምን አዳነ፤ ወደ ላይም ከፍ ከፍ ሲል
ሁሉንም ወደራሱ ሰበሰበ (ዮሐ.12፥32-33)። "እምከመ ተለዐልኩ እምድር
እስሕብ ኵሎ ኀቤየ ያለው ሊፈጸም" ከሰማይ ወርዶ ከመሬት ከፍ ብሎ "በመካ
ከል ተሰቅሏል። ኀሩይ ማዕከለ እግዚአብሔር ወሰብእ ሁኖ እንዳስታረቀን
ለማጠየቅ አስታራቂ በመካከል ነውና ቁሞ ተሰቅሏል፤ ምድርን በኪደተ እግሩ
እንደ ቀደሰ አየራትን ለመቀደስ" [illegible]



ትርጓሜውን ተመልከት)። በሰማይና በምድር መካከል ክርስቶስ በመስቀሉ
ቤዛ ሆኖልን ለሁላችንም እርቅና ሰላምን አስገኘልን። በአንድ እግዚአ
ብሔርና በሰው መካከል ያለው አንድ መካከለኛና አስታራቂያችን እርሱ
ክርስቶስ ብቻ ነውና (1ኛጢሞ.2፥5-6)። እግዚአብሔር በእርሱ ሰውን ብቻ
ቀደሰ ሳይሆን ምድርንና አየራትን በጠቅላላው ሥነ ፍጥረትን ሁሉ እንደ ቀደሰ
ያስተውላለን። ሥነ ፍጥረት ሁሉ ከጥፋት መዳንን ይጠባበቃልና (ሮሜ.8፥19-
22)። እኛም በክርስቶስ " ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር
እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን" (2ኛጴጥ.3፥13)።

እግዚአብሔር ክርስቶስን "ከሙታን ሲያስነሣው ከአለቅነትና
ከሥልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይና በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር
ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ደግሞ ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ሥፍራ
በቀኙ" እንዳስቀመጠው ሐዋርያው ይገልጣል (ኤፌ.1፥21)። ጌታ ቅድመ
ተዋሕዶ በአብ ዕሪና እንደነበረ ቢታወቅም ይህ የተነገረው፡ አካላዊ ቃል ስለ
ተዋሐደው ሥጋ ነው ማለት "ስለ ሥጋ እንግድነት" ነው (መዝ.109፥1
ትርጓሜውን ተመልከት)። እግዚአብሔር "በክርስቶስ ባደረገው ሥራ የብርታቱ
ችሎት ይታያል፤ ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት ከሁሉም በላይ ራስ እን
ዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው። እርስዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእር
ሱ መላቱ ናት" (ኤፌ.1፥21-23)።

ክርስቶስ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ዛሬም ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር
በመሆን እርሱ ራሱ የጀመረውን ሥራ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ረድኤት እያካ
ሄደ ነው (ማቴ.28፥19-20)። በክርስቶስ የመጣው ድኅነት ጸጋና ሰማያዊ
በረከት በእርሱ ላመኑት ሁሉ እየተሰጠ ይቆያል። በመጨረሻው የፍርድ ቀን
በዳግም ምጽአት በሰማይም በምድርም ያለው ሁሉ ተጠቃሎ በአንድ አገዛዝ
በአንድ መንግሥት ሥር ይሆናል። የእግዚአብሔርና የክርስቶስ መንግሥት
በሁሉ ዘንድ ይታወቃል። ዐመፀኛው መልአክ ከነሠራዊቱ ይመታል፤ እርሱና
የእርሱም ተባባሪዎች ሁሉ የዘላለም ስቃይ ወዳለበት ሥፍራ ይጣላሉ። ከእን
ግዲህ ወዲያ የእግዚአብሔር ወገኖች ከፈጣሪያቸው ጋር በፍቅርና በሰላም
በደስታም ይኖራሉ። እግዚአብሔርም ሁሉ በሁሉ ይሆናልና፤ ለመንግሥቱም
ፍጻሜ የለውም (ሉቃ.1፥33)።

## (5) ርስት መንግሥተ ሰማያትን መውረስ (ሀብተ ሕይወት ዘለዓለም)

አምስተኛው ሰማያዊ በረከት በአጠቃላይ እግዚአብሔር ለሰዎች ልጆች
የሰጠው የተስፋውን ቃል ያመለክታል። ስለ ተስፋው መፈጸም ሐዋርያው
ሲናገር /እግዚአብሔር/ "እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሠራ እንደ እርሱ አሳ
ብ አስቀድመን የተወሰንን በክርስቶስ ደግሞ ርስትን ተቀበልን። ይኸውም፥
በክርስቶስ አስቀድመን ተስፋ ያደረግን እኛ ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ
ነው" ብሏል (ኤፌ.1፥11-12)። የእግዚአብሔር በረከት በብዙ ዓይነት
ይተረጐማል። በረከተ ሥጋና በረከተ ነፍስን የሚሰጥ የነፍስና የሥጋ ፈጣሪ እር
ሱ ነውና። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ለእሥራኤል ዘሥጋ ለአባታቸው ለአ
ብርሃም በገባለት የተስፋ ቃል መሠረት ምድረ ርስትን አውርሷቸዋል። እነር
ሱም ከዓለም ሕዝብ ሁሉ ተለይተውና ተቀድሰው የእግዚአብሔር ርስት ሆነዋል
(ዘጸ.19፥4-6)።ሁለቱም እንደ ሁኔታቸው በየበኩላቸው በእግዚአብሔር የተከናወ
ኑና ከእርሱ የተሰጡ ጸጋና በረከት ናቸው። ፍጻሜያቸው ግን ለእሥራኤል
ዘነፍስ የተደረገው የመዳን ጸጋና የተሰጠው ሰማያዊ ርስት ነው። ተስፋ መን
ግሥተ ሰማያትን ይኸውም የዘላለም ሕይወትንና የማያልፈውን እውነተኛ
ደስታን ማግኘት የመጨረሻውና ታላቁ ሰማያዊ በረከት ስለሆነ ከሰው ልጆች
የመፈጠርና የመኖር ዓላማና ግብ ጋር የተያያዘ እንደሆነ እናስተውላለን።

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ ክርስቲያን በዚህ ዓለም እንደ እንግዳና እንደ መንገደኛ እንጂ እንደ ዘላለም ቤቱ አድርጐ በመቁጠር ተደላድሎ በደስታ መኖ ይገባውም፡፡ ሐዋርያው እንዳለ፦ "እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፥ ከዚያም የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ጠባበቃለን" (ፊልጵ.3፥20)፡፡

ከላይ እንደ ተጠቀሰው እሥራኤል ከዓለም ሕዝብ ተለይተው ራሳቸው የእግዚአብሔር ርስት በመሆናቸው ምክንያት ምድረ ርስትን እንደ ሱ እንዲሁም ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ለራሱ "ለርስቱ ወገን" (1ኛጴጥ.2፥9-10) ስለሆኑ ሰማያዊ ርስት ተሰጥቷቸዋል፡፡ ክርስቲያኖች ለእርሱ የተቀደሰ ማደሪያው ርስቱ መሆናችን ሲረጋገጥ እግዚአ ብሔር ደግሞ ለእኛ ማደሪያ የሚሆነውን ሰማያዊ ርስት ይሰጠናል፡፡ ለእርሱ ማደሪያው ርስቱ ካልሆንን ለእኛም የሚሆን ማደሪያ ርስት አናገኝም፡፡ ስለዚህ ከዓለማዊ ሕዝብና አኗኗር ራሳችንን ለይተን ለእግዚአብሔር ብቻ ማደሪያ እን ድንሆን በንጽሕና በቅድስና መኖር ይገባናል (1ኛቆሮ.6፥19-20)፡፡ ም ያቱም እርሱ ቅዱስ እንደሆነ ማደሪያው ሰውም ቅዱስ መሆን ያስፈልገዋል (1ኛጴጥ.1፥15-16)፡፡

## (6) የርስታችን መያዣ "ዐረቦነ መንፈስ ቅዱስ" (ጸጋ መንፈስ ቅዱስ)

ለእሥራኤል ብቻ ተጠብቆ የነበረው ሰማያዊ በረከት ሁሉ ዛሬ በክርስቶስ ለአሕዛብ ሁሉ እንደ ተሰጠ ሐዋርያው ሲገልጽ "እናንተም ደግሞ የእውነት ቃል፥ ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል፥ ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አ ምናችሁ፥ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታተማችሁ" ብሏል፡፡ በክርስቶስ ላመኑት የዓለም ሕዝብ ሁሉ በነቢያት የተነገረው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ለሁሉም እንደ ተሰጠ የሚገልጽ ነው (ኢዩ.2፥28-32)፡፡ ይህንንም ከአምስተኛው ጋር በማያያዝ የምናጠናው ስድስተኛው ሰማያዊ በረከት ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ እርሱም ከተስፋው ቃል ጋር ከሰማያዊ ርስት ጋር ተያይዞ የሚሰጥ የእብና የወልድ የባሕርይ ሕይወታቸው ስለሆነ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ከራሱ በረከትነት በተጨማሪ የሌሎቹም ጸጋና በረከት ሁሉ ማረጋገጫቸው ማኅተማቸው ነው፤ በተለይም የሰማያዊ ርስታችን መያዣ (አረቦን) እንደሆነ እናምናለን፡፡ ስለዚህም ሐዋርያው እንዲህ ብሏል፦ "እርሱም /መንፈስ ቅዱስ/ የርስታችን መያዣ ነው፥ ለእግዚአብሔር ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ፥ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል" (ኤፌ.1፥14)፡፡

እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ላይ አድሮ ይኖራል፤ እነር ሱም የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ቤተ መቅደስ ሆነዋል (1ኛ ቆሮ.6፥19-20)፡፡ ስለዚህ ራሳችንን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ አድርገን በማመን በጎውን ነገር እን ፈጽም ክፋውን እናስወግድ፡፡ ሐዋርያው እንደመከረን "... ክፉ ቃል ከአ ፋችሁ ከቶ አይውጣ፡፡ ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ" (ኤፌ.4፥29-30)፡፡

## (7) ከእግዚአብሔር የተሰጠን ፍቅር (ሀብተ ተፋቅሮ)

የመዳናችን ምሥራች፥ የርስታችን የመንግሥተ ሰማያት መሰጠትና ማናቸውም "በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አ ባት ይወርዳሉ፡፡ ለፍጥረቱ የበኩራት ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ ወለደን" ልጆቹም አደረገን (ያዕ.1፥17-18)፡፡ ይህን ሁሉ ያደረገልን "እግዚአ ብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ፥ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ" ነው



(ኤፌ.2፥4-5)፡፡ ስለዚህም እግዚአብሔር ፍቅር መሆኑን አውቀናል (1ኛዮሐ. 4፥7-16)፡፡ ይህም የምሥራች ቃል ስለሆነ በፍቅሩ አምነው የሚኖሩ ክርስቲያኖች የልቡና ሰላምና ደስታ አይለያቸውም፡፡ ምሕረት ከሌለው ከጨካኙ ከዲያብሎስ ግዞት ነፃ ወጥተን በክርስቶስ አዳኝነት ታላቁን የእግዚአብሔርን ፍቅር ከማግኘት የበለጠ ምን ነገር አለ? እንግዲህ ሰባተኛው ሰማያዊ በረከት የእግዚአብሔር ፍቅር ነው፡፡ እግዚአብሔር ለመረጣቸውና ለወደዳቸው ሁሉ ይህንን የፍቅሩን ጸጋና በረከት በልቡናቸው ውስጥ እንዲኖር አድርጓል፡፡ ፍቅሩ በልቡናችን እንዲያድር ያደረገው የሰጠን የተስፋው ቃል የማይቀርና እውነተኛ መሆኑን ከመመስከር ጋር ነው፡፡ ስለዚህ ነው "በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም" የተባለው (ሮሜ.5፥5)፡፡

የሺህ ፍልጥ ማሠሪያው ልጥ እንዲሉ የሰማያዊ በረከት ሁሉ ማሳ ረጊያው የእግዚአብሔር ፍቅር ነው፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር የክርስቶስ ፍቅር ስለሆነ "ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቀቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፥ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ" አእም ሮውን እሱ ባለቤቱ ይስጠን (ኤፌ.3፥18-19)፡፡ እንግዲህ በክርስቶስ ፍቅር እን ኑር፤ በፍቅሩ ሆነን በነፍሳችንም በሥጋችንም እናገልግለው፡፡ ክርስቲያን ስሙ እንደሚያመለክተው በክርስቶስ አምኖ የተጠመቀ ከእርሱም ጋር አንድ እንዲሆን በመንፈስ ቅዱስ የታተመ ስለሆነ በዚህ ዓለም ሳለ አሁን በሥጋው በሚኖርበት ኑሮው የክርስቶስ መሆኑን በተግባር መመስከር ይገባዋል፡፡ ይህን ካልፈጸመ ክርስቲያንነቱ በምን ይታወቃል? የክርስትና ቃል ኪዳኑስ፥ የክርስትና ማኅተሙስ የት ላይ ነው?

## 2. ክርስቲያን "የኢየሱስን ማኅተም" በሥጋው ተሸክሞ ይኖራል

"የኢየሱስ ሕይወት ... በሥጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁልጊዜ የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን እንዞራለን፡፡ የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሚሞት ሥጋችን ይገለጥ ዘንድ እኛ ሕያዋን የሆንን ከኢየሱስ የተነሣ ዘወትር ለሞት አልፈን እን ሰጣለንና" (2ኛቆሮ.4፥10-11)፡፡

በመግቢያው ላይ ክርስቲያናዊ ሕይወታችንና ምግባራችን ሁሉ በክርስቶስ ላይ እንደ ተመሠረተ የጠቀስነው ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ሁለን ተናችን ለክርስቶስ የተሰጠ መሆኑን አምነን ክርስቲያናዊ ሕይወታችንን ማለት መላው ሰውነታችንን "እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕ ት" አድርገን ማቅረብ የሚገባን መሆኑን ለማመልከት ነው (ሮሜ.12፥1-2)፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሰውነቱን ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጐ ለማቅረብ የቻለው መላ ዘመኑን ራሱን ክዶ መስቀሉን ተሸክሞ ሕይወቱን ለክርስቶስ ሲል አሳልፎ በመስጠቱ ከሚወዳቸው የሥጋ ወገኖቹና ከእነርሱም ባሕልና ሃይማኖት ተለይቶ ከክርስቶስ ጋር መሞትን በመምረጡ ነው፡፡ ስለዚህም ነው "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ" ያለው፡፡ ቀጥሎም "እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው" ብሏል (ገላ.2፥20)፡፡

የሐዋርያት ተከታዮችም ሐዋርያትን በመምሰል (1ኛቆሮ.11፥1) የሐዋርያትን ትምህርትና ትውፊት በመከተል ለክርስቶስ ሲሉ ራሳቸውን ሕያውና ቅዱስ መሥዋዕት በማድረግ እስከ ሞት ድረስ በታማኝነት ኖረዋል፡፡ ምንም ወደ ኋላ ሳይሉና ሳይወላውሉ ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ለክርስቶስ ብቻ ያስገዙ ስለሆነ በአኗኗራቸውም፥ በሥራቸውም፥ በሚያደርጉት በማናቸውም ነገር ሁሉ ክርስቶስን ያንፀባርቃሉ፡፡ መስተዋት በፊቱ የቀረበውን ነገር ሁሉ በውስጡ [illegible] እነርሱም ወደ እርሱ የቀረቡ ስለሆነ እርሱም ወደ

www.ethiopianorthodox.org

እነርሱ የቀረበ ስለሆነ ከክርስቶስ በቀር የሚወዱትና የሚያመልኩት፥ የሚያስ ምሩትና የሚመሰክሩት ስለሌለ በልባቸው ውስጥ የጌታቸውና የአዳኛቸው ሥዕል ተቀርጿል፡፡ ስለሆነም እነርሱ የክርስቶስ ምስክሮች በመሆናቸው እግዚአብሔ የሚያውቁትና ስለ እርሱም የሚመሰክሩት በክርስቶስ ስም ብቻ ነው፡፡ ም ያቱም እነርሱ እንዲያው በደፈናው በአጠቃላይ ስለ እግዚአብሔር ህልው (መኖር) ብቻ ቢመሰክሩ ኖሮ አይሁድም ሆኑ ግሪኮች ሌሎችም የሃይማኖ ሰዎች ነገሩን እንደእየራሳቸው እምነት በራሳቸው ይትበሃል ይተረጉሙ እንጂ የክርስቲያን ሃይማኖት ምንነትና ዓላማ ባልታወቀም ነበር፤ ደም እስ ማፍሰስ የደረሰ ተቃውሞም ባልተነሣም ነበር፡፡ ነገር ግን ሰውን ለማዳን ሰ በሆነው በእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ በክርስቶስ ስም በመኖራቸውና በመሰ ቸው በመመስከራቸውም የክርስትና ሃይማኖት ከሌሎቹ ተለይታ የራሷ ቅርጽ ይዘት ኖሯት በየክፍለ ዓለሙ ሁሉ እንድትቋቋም አድርገዋል፡፡ እነዚህ የክ ስቶስ ምስክሮች (ሰማዕታት) በፍጹም እምነትና ፍቅር ሕይወታቸውን በክርስቶ ላይ የመሠረቱ ስለሆነ የክርስቶስን መስቀል ተሸካሚዎች በመሆን በዓላው ነገሥታት ፊት ስለ ስሙ በመመስከር ራሳቸውን ለእሳት ለስለት ለአራዊት አሳ ልፈው ሰጥተዋል፡፡

## አግናጥዮስ "ቴዎፎሮስ" - የአምላክ [ስም] ተሸካሚ

እያንዳንዱ ክርስቲያን ማንነቱ የሚታወቀው የክርስቶስ መሆኑ የሚያስረዳው በክርስትና ስሙ በመጠራቱ ሳይሆን የክርስቶስን መከራ መስቀል ተሳታፊ ሆኖ በመኖርና ማንነቱንም በተግባር በመመስከር ነው፡፡ ማንነቱም የሚረጋገጠው በሥጋው ስለ ክርስቶስ ብሉ ጸዋትወ መከራን በመቀበል፥ "የኢየ ሱስን ማኅተም" በሥጋው ተሸክሞ እስከ መጨረሻው ታግሦ በታማኝነት በመገኘት፥ እስከ ዕለተ ሞቱም በጌታው ቃል ኪዳን ጸንቶ በመኖርና በማገልገል ይሆናል፡፡ የኢየሱስ ማኅተም ማለትም መከራ መስቀሉ ማለት ነውና፡፡ እን ዲህ ዓይነቱ ክርስቲያን በመንፈስም በሥጋም ጌታውን የሚከተልና የሚመስል ስለሆነ ጸዋሬ ክርስቶስ (ክሪስቶፎሮስ) ጸዋሬ አምላክ (ቴዎፎሮስ) ይባላል፤ ይህም ማለት በውስጥ በአፍአ በልቡናውም በሥጋውም ስመ አምላክን የተሸከመ ማለት ነው፡፡ እንደ ቅዱሳን ሐዋርያት ይህንን በተግባር የፈጸመውን ሐዋርያዊ የቤተ ክርስቲያን አባት "ምጥው ለአንበሳ" ለአንበሳ የተሰጠ የተባለውን ቅዱስ አግ ናጥዮስን በአንክሮ እናስታውሰዋለን፡፡ እርሱ ራሱን ቴዎፎሮስ (ጸዋሬ አምላክ) አ ምላክን የተሸከመ በማለት ይጠራ ነበር፡፡

ይኸው ቅዱስ፥ አማኞች ሁሉ ክርስቶስን እንዲመስሉት እግዚአብሔርን እንዲመስሉት ያስተምር ነበር፡፡ እውነተኛ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር መሆን የሚቻለው እንደ ጌታ ሕማማትንና ሞትን በመቀበል እንደሆነ ሰማዕትነትን ለመቀበል ወደ ሮም በሚሄድበት ጊዜ በጻፈው መልእክቱ ገልጾታል፡፡ ክርስቲያናዊ ሕይወት ያለማቋረጥ ዘወትር ክርስቶስን መምሰልና በየደረጃውም ወደ እርሱ በእርሱ ማደግ ማለት እንደሆነ ከትምህርቱና ከሕይወቱ ለመረዳት እንችላለን፡፡ "ሥጋዊ የሆኑት /ሰዎች/ መንፈሳዊ ነገሮችን ማድረግ፥ መንፈሳዊ የሆኑትም /ሰዎች/ ሥጋዊ ነገሮችን ማድረግ አይችሉም . . . ነገር ግን እናንተ በሥጋ የምታደርጉት እንኳ መንፈሳዊ ነው፥ ምክንያቱም የምታደርጉት ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስለሆነ" ነው በማለት ለኤፌሶን ክርስቲያኖች ጽፎላቸዋል፡፡ ቀጥሎም "እናንተ ጓደኞቹ የሆናችሁ መንገደኞች ናችሁ፡፡ ከእናንተም ጋር እግዚአብሔርን ተሸክማችኋል፥ መቅደሱንም ተሸክማችኋል፥ ክርስቶስንም ተሸክማችኋል፥ የተቀደሰውንም ተሸክማችኋል እንደዚሁም በሁሉም መንገድ በኢ የሱስ ክርስቶስ ትእዛዛት አጊጣችኋል" እያለ ያስተምራቸው ነበር፡፡ በዚህም ጥቅ ሱ ላይ ነው ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርና የክርስቶስ የቅድስናው ማለት የመን ፈስ ቅዱስም ተሸካሚዎች መሆናቸውን [illegible]



መንፈስ ቅዱስ ስም በሚጠመቁበት ጊዜ ያገኙትን ጸጋ ያመለክታል፡፡

የክርስቲያን ሕይወቱ የራሱ ሳይሆን የእግዚአብሔር ነው፤ በነፍሱም በሥጋውም የእግዚአብሔር ማኅደርና መቅደስ ሆኗል (ሮሜ. 14፥7-8፤ 1ኛቆሮ. 3፥16፤ 6፥19-20)፡፡ ማኅደሩን በአዳሪው መጥራት የተለመደ ስለሆነ እያንዳንዱ ክርስቲያን ቴዎፎሮስ ተብሏል፡፡ በዚህም ቃል ክርስቲያናዊ ሕይወቱ ይገለጣል፤ ይወ ሰናል፡፡ ከእንግዲህ ወዲያ የክርስቲያን ሕይወት በሰው ሕይወት ዙሪያ ሳይሆን በእግዚአብሔር ዙሪያ ብቻ ያማከለ ወይም ያተኮረ ይሆናል፡፡ ስለዚህም ተራው የሰው ሕይወት በውስጣችን ባደረው መለኮታዊ ኃይል ይለወጣል በማለት ከታች በግርጌ ማስታወሻ የጠቀስነው መጽሔት ያብራራል፡፡ የክርስትና ሕይወትም ዓላማው ከግቡ የሚደርሰው በዚህ ሁኔታ በመለኮታዊ ኃይል እየተሻሻለና እየታደሰ፥ እየተለወጠና እያደገ ሄዶ "እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ" (1ኛጴጥ.1፥15-16) ብሎ ያለውን ፈጣሪውን በመምሰል የቅድስናው ሕይወትና የመለኮታዊ ክብሩ ተካፋይ ለመሆን ነው (2ኛ ጴጥ.1፥4)፡፡

አማኞች "በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በፍቅር የእግዚአብሔር አብ ማኅተምን" መሸከማቸውን ቅዱስ አግናጥዮስ ከገለጸ በኋላ ይቀጥልና "በእርሱ (በክርስቶስ) በኩል በእርሱ ሕማም (ማለት የእርሱን ሕማም በመቀበል) በፈቃደኝነት ለመሞት ካልመረጥን የእርሱ ሕይወት በእኛ ውስጥ የለም" ብሏል፡፡ ይህም ማለት የእርሱን ሕማምና ሞት በሥጋችን ለመቀበል መዘጋጀት እንዳለብን ያመለክተ ናል፡፡ አለበለዚያ ለምድራዊና ለሥጋዊ ሕይወታችን ሳስተን ስለ ክርስቶስ መመስከ ርን ፈርተን በመደበቅና በመሸሽ የምንኖር ከሆነ የክርስቶስ ሕይወት በእኛ ውስጥ የለም፡፡ "መስቀሉን የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም" ያለ ውንና ዳግመኛም "ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና፤ ስለ እኔ ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን እርሱ ያድናታል" በማለት ጌታ የተናገረውን ቅዱስ አግናጥዮስ በቃል አስተምሯል በተግባርም ፈጽሞታል (ማቴ.10፥38፤ ሉቃ.9፥24)፡፡

በ107 ዓ.ም. ገደማ በአንጾኪያ ክርስቲያኖች ላይ ስደት ተነሥቶ በነበ ረበት ጊዜ ቅዱስ አግናጥዮስ የአንጾኪያ ሊቀ ጳጳስ በመሆኑና በክርስትና ሃይማኖቱም ጠንካ ራ አቋም ምክንያት ተይዞ ትራጃን በተባለው ዓላዊ ንጉሥ ፊት ቀርቦ ነበር፡፡ ንጉ ሡም፦ "ማነው ቴዎፎሮስ" (አምላክን የተሸከመው) ብሎ ቢጠይቀው "በልቡ ውስጥ ክርስቶስ ያለው እርሱ ነው" በማለት መልሶለታል፡፡ ዓላዊው ንጉሥም፦ "ታዲያ አን ተ በውስጥህ ያን የተሰቀለውን ተሸክመሃልን?" በማለት መልሶ ጠየቀው፡፡ ቅዱስ አግ ናጥዮስም፦ "በእርግጥም እንደዚሁ ነው፤ ምክንያቱም 'በእነርሱ እኖራለሁ፥ በእነር ሱም (በመካከላቸውም) እመላለሳለሁ' ተብሎ ተጽፏልና" በማለት ጥያቄውን መለ ሰለት፡፡ ከዚህም በኋላ ዓላዊው ንጉሥ ትራጃን የሚከተለውን የፍርድ ውሳኔ አስተ ላለፈ፦ "በውስጡ ያን የተሰቀለውን መሸከሙን ያረጋገጠው አግናጥዮስ በወታደሮች ታሥሮ ወደ ታላቋ ሮም (ከተማ) በመሄድ እዚያም ለሕዝቡ መደሰቻ በአራዊት እን ዲበላ አዘናል፡፡" በዚህ ትእዛዝ መሠረት በ110 ዓ.ም. አካባቢ በሮም ከተማ በሰማዕት ነት አርፎአል[72]፡፡

## ሰማዕትነት ያለ ደም

የጥንቱ ዓይነት ሰማዕትነት በጊዜያችን የለም፥ ዘመነ ሰማዕታትም አል ፏል ቢባልም ዛሬም መልኩን ለውጦ በተዘዋዋሪ መንገድ አለ፡፡ እርግጥ ነው ዛሬ እሳት ስለቱ፥ ለአራዊት መሰጠቱ ባይኖርም እውነተኛ ክርስቲያኖች ፈታኝ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ማለፋቸው አልቀረም፡፡ ስለ ክርስትና እምነታቸው ይልቁንም

[72] Christian Orient: An Indian Journal of Eastern Churches, Christian Orient Trust, Kottayam, Kerala, India, (Sep. 1996) pp. 119-127. በዚህ በእንግሊዝኛ ክርስቲያን ኦሪየንት በተባለው ስለ ምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት በየጊዜው እየታተመ በማውጣው የሕንድ መጽሔት ውስጥ እንደ ተጻፈው በግሪክ Theophoros (ጸዋሬ አ ምላክ) Christophoros (ጸዋሬ ክርስቶስ) በእንግሊዝኛ God– bearer, Christ – bearer ተብሎ ተተርጉሟል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

ስለ መልካም ሥነ ምግባራቸውና ጠባያቸው፥ ስለ መንፈሳዊ ተጋድ[illegible] በጠቅላላው ስለ ክርስቲያናዊ ሕይወታቸው ጽናት ብዙ ፈተናና መከራ የተ[illegible] እንዳሉ እናውቃለን፡፡ እንደ እነዚህ ያሉት የዘመናችን ሰማዕታት ናቸው፤ [illegible]ት ዘእንበለ ደም (ሰማዕት ያለ ደም) ይባላሉ፡፡ በሥጋ መከራን ከመ[illegible] የሚሸሹ ግን ክርስቲ ያናዊ ሕይወታቸውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መ[illegible] እንዲጉሳቆል አድርገው ታል፡፡ ከላይ እንደ ጠቀስነው የክርስቶስን [illegible] መስቀል በሥጋችን ለመሸከም ቁር ጠኛ ኀሊና ኖሮን በፈቃደኝነት ካል[illegible] ነው የክርስቶስ ሕይወት በእኛ ውስጥ አይ ኖርም፡፡ ክርስቲያናዊ ሕ[illegible] ማለትም በእኛ ውስጥ የሚገኘውን የክርስቶስን ሕይወት መኖር የሚያመለ[illegible] ነው፡፡ ይህንንም ሕይወት የምናገኘው በነፍሳችንም በሥጋችንም ክርስ[illegible] በመምሰል በተለይም እንደ እርሱ በሥጋችን መከራን በመቀበል ትእዛ[illegible] በመፈጸም ይሆናል፡፡ የጌታን ትእዛዝ የማይፈጽም አርአያውንም የማይ[illegible] "የኢየሱስን ማኅተም" በሥጋው አልተሸከመም፡፡

እንግዲህ ክርስቶስን መምሰል ከቅዱስ ጳውሎስ ትምህርትና ሕይወት ተ[illegible] ናል፡፡ እኛ የእርሱንና የቅዱሳን ሐዋርያትን የቤተ ክርስቲያን አባቶችንም ት[illegible] ርትና ትውፊት በመከተል እነርሱን እንምሰላቸው፡፡ እነርሱ "የኢየሱስን ማኅተ[illegible]" በሥጋቸው በመሸከማቸው ተገገርነታቸው ለክርስቶስ ብቻ ነው፡፡ እነርሱ በመ[illegible] ዘመናቸው ሕይወታቸውን በሰማዕትነት መፈጸማቸው ብቻ ሳይሆን መላው እድ[illegible] ቸውን የክርስቶስ እንጂ የራሳቸው ወይም የሌላ አለመሆናቸውን በሥጋቸው መ[illegible] ሲቀበሉ በመኖራቸው ተገገርነታቸውን በክርስቲያናዊ ሕይወታቸው በተግ[illegible] መስክረዋል፡፡ "የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ [illegible] ሰቀሉ" የተባለውን የፈጸሙና እኛም የክርስቶስ የሆንነው ሁሉ ይህንኑ እንድንፈጽ[illegible] ታዘናል (ገላ.5፥24)፡፡ ሐዋርያውም "የኢየሱስን ማኅተም በሥጋዬ ተሸክሜአለሁ" ማለቱ የክርስቶስ መሆኑንና ስለእርሱም ሕማምና ሞትን በሥጋው በመቀበል ፍጹ[illegible] ተገገርነቱን ያመለክታል (ገላ.6፥17)፡፡ እንግዲህ እኛ በወርቀ ደሙ በዋጋ የተገዛ[illegible] የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ነን እንጂ የራሳችን አይደለንም፡፡ ስለዚህም ሥጋ የጌ[illegible] ነው ጌታም ለሥጋ ነው እንደ ተባለው ሥጋችን የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እን[illegible] ደሆነ አውቀንና አምነን በሥጋችን እግዚአብሔርን እናክብረው (1ኛቆሮ.6፥13-20)፡፡

## 3. የክርስቲያን ሕይወት የክርስቶስ ሕይወት ነው፡፡

በክርስቶስ ክርስቲያን በወልድ ውሉድ (ልጆች) የተባልን ክርስቲያኖች ሁሉ ሕይወታችን በክርስቶስ ነው፡፡ የቀደመውን አኗኗሩን ትቶ ክርስቲያን የሚኖረው በክርስቶስ የሕይወት መንፈስ ስለሆነ በነፍስም በሥጋም የሚኖረው ሕይወት የክርስቶስ ሕይወት እንደሆነ ከቅዱስ ጳውሎስ ተምረናል፡፡ ሐዋርያው "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ" ሲል የቀደመው ሕይወቱ፥ በፈሪሳውያን እምነትና ሥርዓት መኖሩ ያበቃለት መሆኑን ይገልጻል፡፡ ከዚህም አያይዞ "እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል" በማለት የተናገረው ኃይለ ቃል በአንድ በኩል እንደ ሞተ ሰው ሆኖ በሌላ በኩል ደግሞ እንደሚኖር ሆኖ ያመለክተናል፡፡ "ሕያው ሆኜ አልኖርም" በማለቱ ሐዋርያው ቀድሞ ሳውል ተብሎ በሚጠራበት ጊዜ ያሳለፈው ኑሮው እንደ ቀረ፥ የሚወደውን ምድራዊ ነገር ሁሉ እንደ ተወ፥ ከበደልና ከኃጢአት ሥራ ሁሉ እንደ ሞተ ሰው መሆኑን ያስረዳል፡፡ "ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል" በማለቱ ደግሞ በቀረውና በተረሳው፥ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሎ በሞተው አሮጌው ሕይወቱ ምትክ ከሙታን በተነሣው በክርስቶስ የትንሣኤ ሕይወት በትንሣኤ ልቡና እንደሚኖር ያስገነዝበናል (ሮሜ.6፥5-11)፡፡ ሐዋርያው "አሁን በሥጋ" የሚኖርበትን ኑሮ ሲገልጽ፦ "በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው" ብሏል (ገላ.2፥20)፡፡ ሐዋርያው እንደ ቀድሞው አኗኗሩ ሳይሆን አሁን በሥጋው በምድር ላይ የሚኖረው ሕይወት በሚወደውና በአዳነው በክርስቶስ ላይ በአለው የእምነትና የፍቅር ሕይወት ነው፡፡



"አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር" ገፍፎ ከክርስቶስ ጋር አንድ ሆኖ [illegible]ጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን [illegible]" ለብሶ አዲሱ ሰውነታችን (ክርስቲያናዊ ሕይወታችን) ማለት አዲሱ [illegible]ወታችን "ከክርስቶስ ጋር ተሰውሯል" የተባለው እውነት ነው (ቆላ.3፥1-[illegible])፡፡ ምክንያቱም በምሥጢረ ጥምቀት በጸጋ መንፈስ ቅዱስ ከክርስቶስ [illegible] አንድ ሆነናል፤ በሕይወቱም በሞቱም በትንሣኤውም እርሱን እንመስለዋለን ([illegible].6፥1-11፤ ኤፌ.2፥5-7)፡፡ ስለ ኃጢአታችን በመስቀል ላይ በሥጋው እንደ [illegible] እኛም ለኃጢአት ሞተናል፤ በሥጋችን መከራ በመቀበል ከኃጢአት [illegible]ተናል (1ኛጴጥ.4፥1-2)፡፡ እርሱ ከሙታን እንደ ተነሣ እኛም በአዲስ [illegible]ወት ተወልደን በትንሣኤ ልቡና ተነሥተናል፤ በዓለም ፍጻሜም የሙታን [illegible]ሣትን ተስፋ እናደርጋለን፡፡ አሁን የምንኖረው ሕይወት የክርስቶስ ነው ([illegible]ኛቆሮ.5፥14-15፤ ፊልጵ.1፥21፤ ገላ.2፥20)፤ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ሆነናል ([illegible]ኛቆሮ..5፥17፤ ገላ.6፥15)፡፡ እምነታችንም ሕይወታችንም ሥር ሰዶ በእግዚአ[illegible]ሔር የባሕርይ ልጅ በክርስቶስ ላይ ተመሥርቷል፡፡ "እንግዲህ ጌታን ክርስ[illegible]ስ ኢየሱስን እንደ ተቀበላችሁት በእርሱ ተመላለሱ፤ ሥር ሰዳችሁ በእርሱ ታ[illegible] እንደ ተማራችሁም በሃይማኖት ጽኑ፥ ምስጋናም ይብዛላችሁ" (ቆላ.2፥6-[illegible])፡፡ እርሱ መንገድም እውነትም ሕይወትም ነውና በእርሱ እንጽና ([illegible]ሐ.14፥6)፡፡ ከእርሱ በቀር መንገድም እውነትም ሕይወትም የለም፡፡ ስለዚህ [illegible]ከራውን ሁሉ በመታገሥ ከእርሱ ጋር በእውነትና በፍቅር በመንፈስ ቅዱስ [illegible]የተመራን በእርሱ ቃል እንኑር፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረን፦ "ለክርስቶስ [illegible]ንጌል እንደሚገባ ኑሩ፡፡ በአንድም ነገር እንኳ በተቃዋሚዎች አትደንግጡ፤ [illegible]ህም ለእነርሱ የጥፋት፥ ለእናንተ ግን የመዳን ምልክት ነው፥ ይህም ከእግዚአ[illegible]ሔር ነው፤ ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቷ ችኋልና" (ፊልጵ.1፥27-29)፡፡

## ጌታ ሰው የሆነበት ዓላማ
## ለእኛ ደኅንነትና ቅድስና

የክርስቲያን ሕይወት ጌታ ወደዚህ ዓለም በመምጣት ሰው የሆነበትን ምክንያትና ዓላማ ሁሉ የተከተለ መሆን ይኖርበታል፡፡ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ሰው የሆነበት ምክንያት ሰዎችን ለማዳን እንደሆነ በአንቀጸ ሃይማኖት ተገልጿል፡፡ ይህም ሰዎችን የማዳንና የማጽደቅ ዓላማ ግቡን የሚመታው በጌታ ትምህርት መሠረት እሱን በማመንና በስሙ በመጠመቅ ትእዛዙንም በመጠበቅ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ እነዚህን ሁሉ በቅድሚያ የፈጸመ ሆኖ መገኘት ይገባዋል፡፡ ያለ እምነትና ምግባር ክርስቲያናዊ ሕይወት የለም፡፡ ጌታ ወደ ዓለም ሊያድነን በመምጣቱ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ታላቅ ፍቅር ለማወቅና እግዚአብሔር ማለትም ፍቅር መሆኑን ከቅዱሳት መጻሕፍት ቃል ለመረዳት ችለናል፡፡ ስለሆነም በእንዴት ያለ ታላቅ ፍቅር የወደደንን አምላክ ከሁሉም በላይ በመውደድና በፍቅሩም እየኖርን ሰውንና እግዚአብሔርን በፍቅር ማገልገል ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን እጅግ አስፈላጊና የክርስቶስም ለመሆናችን ልዩ መታወቂያችን ነው (1ኛዮሐ.4፥7-21፤ ዮሐ.3፥16፤ 13፥35)፡፡

የጌታ መምጣት ለቅድስና ሕይወትና ለመልካም ሥራ ሁሉ አብነት ሆኖናል፡፡ ጌታ ሐዋርያትን ያስተማራቸው በቃል ብቻ አይደለም በተግባርም ምን መሆንና እንዴት መኖር፥ ምን ማድረግና እንዴት ማገልገል እንደሚገባቸው አስረድቷቸዋል፡፡ ለምሳሌ በጸሎተ ኀሙስ ማታ የደቀ መዛሙርቱን እግር በማጠብ ትኅትናን በቃል ብቻ ሳይሆን በገቢርም አስተምሯቸዋል፤ እርሱንም አብነት አድርገው እንዲፈጽሙት አዟቸዋል (ዮሐ.13፥4-17)፡፡ ጌታ ራሱን የፍቅር አብነት አድርጎ ሲናገር፦ "እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት" ብሏል (ዮሐ.15፥12)፡፡ ጌታ መስቀሉን [illegible] እኛም እርሱን አብነት አድርገን መስቀሉን ተሸክመን

www.ethiopianorthodox.org

እንድንከተለው አስተምሮናል (ማር.8፥34)፡፡ እርሱን አብነት አድርገን ዕለት ዕ
ለት መስቀሉን ካልተሸከምን የእርሱ ተከታዮች ልንሆን አንችልም (ሉቃ.9፥23፤
ማቴ.10፥38)፡፡ "እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ" እንደ ሰጠ እኛም እርሱን አ
ብነት አድርገን "ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰ
ይገባናል" (1ዮሐ.3፥16)፡፡ ስለዚህ እርሱ ለእኛ አብነት ሆኖ ያደረገውን ሁሉ
በአግባቡ ማድረግ ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን ወሳኝና አስፈላጊ ነው፡፡ ያለበለዚያ
ክርስቲያናዊ ሕይወታችን በወረቀት ላይ ተነድፎ በጽንስ ሐሳብነቱ እንደተ
እቅድ ይቆጠራል፡፡

ጌታ አምላክ ሰው የሆነበት የመጨረሻው ምክንያትና ዓላማ (የእኛን
ኃጢአት አስወግዶ ካዳነን በኋላ) የእርሱን ቅዱስ ሕይወት ተካፋይ ሊያደርገን፤
ክብሩን ሊያወርሰን፥ የዘላለም ደስታን ሊሰጠን፥ መንግሥተ ሰማያትም ሊያገባን
እንደሆነ እናምናለን፡፡ ስለዚህም የጌታ የባሕርይ ሕይወቱ የጸጋ መንፈስ ቅዱስ
ተካፋይ እንደሆንን አውቀን ክርስቲያናዊ ሕይወታችንን በተስፋው ቃል
ማጠናከር ይገባናል፡፡ ወልድ በተለየ አካሉ ከእኛ ከሰዎች ጋር በነፍስ
በሥጋም በመዛመዱ ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለን፡፡ በእርሱም ያለን
ኅብረት ከአብና ከመንፈስ ቅዱስም ጋር ማለት ከቅድስት ሥላሴ ጋር ኅብረት
እንዲኖረን ያደርገናል፤ በዚህም የክርስቲያኖች ማኅበር ማለት የቤተ
ክርስቲያን አንድነት ይጠናከራል (ዮሐ.17፥20-21)፡፡ "ኅብረታችንም ከአብ
ጋር ከልጁም ከኢየሱስ ጋር ነው" (1ኛዮሐ.1፥3)፡፡ የክብሩም ወራሾች
ለመሆናችን ቅዱስ ጳውሎስ አስረድቶናል፦ "ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤
ማለት የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፥ አብረንም እንድንከብር አብረን መከራ ብን
ቀበል ከክርስቶስ ጋር አብረን ወራሾች ነን" (ሮሜ.8፥17)፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ
ጴጥሮስም በዓለም ውስጥ ከሚገኘው ክፉ ምኞትና ጥፋት አምልጠን ወደ ታላቅ
ክብርና ተስፋ መሸጋገራችንን ያመለክተናል፦ "ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው
ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ፥ በእ
ነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋ ሰጠን" (2ኛ
ጴጥ.1፥4)፡፡

## *የክርስቲያናዊ ሕይወት ሂደትና እድገት በሦስት ደረጃ*

እንግዲህ የክርስቲያናዊ ሕይወት መንገድና መጨረሻው ከላይ እንደ
ተገለጸው ከሆነ ዛሬ የእያንዳንዳችን ክርስቲያናዊ ሕይወት ከምን ላይ እንዳለ
በየጊዜው መገምገም አስፈላጊ ነው፡፡ በመሠረቱ ክርስቲያናዊ ሕይወት በሂደት
ላይ ያለ በመንፈሳዊ ተጋድሎ ኃይል ወደፊት የሚንቀሳቀስ፥ ተስፋችን ወደ አለ
በት ቦታ የሚገሠግሥ ሰማያዊ ጉዞ ነው፡፡ እንደ ማናቸውም ተንቀሳቃሽ ነገር
የጉዞው መነሻና መድረሻ አለው፡፡ የአሮጌው "ሰዋችን" (ሮሜ 6፥6) ሕይ
ወት አክትሞ አዲሱ ሰው በጸጋ እግዚአብሔር ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ እን
ቅስቃሴው ይቀጥላል፡፡ ጉዞ ያልነው ከመንፈሳዊ ልደት እስከ ዘላለማዊ ሕይወት
በአንድ ክርስቲያን ልቡና ውስጥ ያለውን ውጣ ውረድና መንፈሳዊ እንቅስቃሴ
የሚገልጽ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ወደፊት ሌላ ጊዜ ወደኋላ የሚሄድበት፥ አንድ
ጊዜ ወደ ላይ ሌላ ጊዜ ወደታች የሚወርድበትና የሚወጣበት፥ ጊዜ አለ፡፡ ምና
ልባት ሁለት እርምጃ ወደፊት ሄዶ ወደ ኋላ አንድ ርምጃ የሚሄድ ወይም
በተቃራኒው ሁናቴ የሚንቀሳቀስ ይኖራል፡፡ ይህ በክርስቲያናዊ ሕይወት ውስጥ
የሚታይ እንቅስቃሴ ቢሆንም በተቻለ መጠን ተስፋ ሳይቆርጡ በእግዚአብሔር
ረድኤት መንፈሳዊ ጉዟችንን መቀጠል አለብን፡፡ በዚህ ዓለም ውስጥ የክርስ
ቲያን ጉዞ የመናኝ ጉዞን ይመስላልና ወደ ፈቅዶ የገባበት ስለሆነ ክርስቲያን
በመንገድ ላይ በሚያጋጥመው ፈተናና ችግር መሰቀቅ አይገባውም፡፡ ምናልባት
ወደ ፈቅዶ መንፈሳዊ ጉዞውን ያልጀመረ ክርስቲያን ካለ በዘፈቀደ በስም
የሚኖር ስመ ክርስቲያን ስለሆነ
ውስጥ የለም፡፡

www.ethiopianorthodox.org



ከላይ እንደ ጠቀስነው ክርስቲያናዊ ሕይወት በሂደት እያደገ ሊሄድ የሚችል ቢሆንም አንዳንዴ ወደ ኋላ የሚሄድበትን ሳንቆጥር በአጠቃላይ የክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት በሦስት ዋና ዋና ደረጃዎች ይከፈላል፡፡ እነርሱም የወጣንያን፥ የማዕከላውያንና የፍጹማን ክርስቲያናዊ ሕይወት ናቸው፡፡ ወጣንያን ማለት ከታችኛው ደረጃ የሚገኙ አማኞችን ገና ክርስቲያናዊ ሕይወታቸውን የጀመሩትን ያመለክታል፡፡ በክርስትና መሠረተ ትምህርት ላይ የሚገኙትን ከንዑስ ክርስቲያንነት ደረጃ ጀምሮ ያሉትንና አዲስ የተጠመቁትንም እንደዚሁም ገና በትምህርተ ክርስትና እውቀት ያላደጉትን፥ በእምነትና በምግባር ያልጸኑትን ሁሉ ያካትታል፡፡ በክርስትና እውቀታቸው ይልቁንም በሃይማኖታቸው የበቁ፥ ምግባርና ትሩፋት የሚሠሩት፥ በመንፈሳዊ ገድላቸው ከራሳቸው አልፈው ለሌላ የሚተርፉት ክርስቲያኖች ደግሞ በከፍተኛው የዕድገት ደረጃ የደረሱ ናቸው፡፡ ይህ የፍጹምነት ደረጃ ስለሆነ ቅዱሳንን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡ በሁለቱ ደረጃዎች መካከል የሚገኙት ማዕከላውያን ይባላሉ፡፡ እንግዲህ በወጣኒ ደረጃ ያለው ወደ ማዕከላዊ ደረጃ፥ ማዕከላዊ የደረሰው ወደ ፍጹማን ደረጃ ለመድረስ በጸጋ እግዚአብሔር አጋዥነት ሁሉም በበኩሉ መንፈሳዊ እንቅስቃሴውን ከመቀጠልና መንፈሳዊ ተጋድሎውን ከመፈጸም መቆጠብ የለበትም፡፡

ለእያንዳንዳችን ጸጋውን የሰጠን እግዚአብሔር ሁላችን በአንድነት ሆነን ወደ ሙሉና ፍጹም ወደ ሆነው ክርስቲያናዊ ሕይወት በልጁ በክርስቶስ እንድንደርስ ፈቃዱ ነው፡፡ የክርስቲያን መንፈሳዊ እድገቱ ራስ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስ በማደጉ እንጂ አቅጣጫውን ስቶ በሌሎች አስመሳይ የትምህርት ዓይነቶች እየተመሩ የሚይዙትንና የሚጨብጡትን በማጣት "ወዲያና ወዲህም" እየተንሳፈፉ እንደ "ሕፃናት መሆን" አይገባም፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደሚከተለው ያስተምረናል፡

> "ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን የክርስቶስን ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንፃ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኰል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህም እየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደፊት አይገባንም ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ" (ኤፌ.4፥12-15)፡፡

እንግዲህ የክርስቲያን ሕይወት እድገት በክርስቶስ እንደሆነ ተረዳን፡፡ በክርስቶስ ለማደግ ደግሞ በክርስቶስ መኖር ያስፈልጋል፡፡ በክርስቶስ መኖር ማለት ደግሞ ምን ማለት እንደሆነ ምሥጢሩን አውቀን ከእግዚአብሔር ቃል ተምረን በሥራ መተርጐም ይገባናል፡፡

## *በክርስቶስ መኖር በሕገ ወንጌል በተፋቅሮ መኖር ነው*

ክርስቶስ የወይን ግንድ ነው፤ ክርስቲያኖች በግንዱ ላይ አብቅለውና አብበው የሚያፈሩ ቅርንጫፎች ናቸው (ዮሐ.15፥1-6)፡፡ ቅርንጫፎቹ ከግንዱ ተለይተው መኖር አይቻላቸውም፡፡ ክርስቲያኖችም በኑሯቸው ከክርስቶስ ጋር ሁልጊዜ በአንድነት ካልኖሩ ሕይወትም አይኖራቸውም፤ ከግንዱ እንደ ተለዩ ቅርንጫፎች ደርቀው ይወድቃሉ፤ ለማገዶም ወደ እሳት ይጣላሉ፡፡ ከእርሱ ጋር አንድ በመሆን እስከ መጨረሻው ከጸናን መልካም ፍሬን በማፍራት ለራሳችንም ለሌላውም እንሆናለን፡፡ እንግዲህ "እግዚአብሔር አብን በእርሱ እያመሰገናችሁ፥ በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ ኢየሱስ
ስም አድርጉት" በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ የተግባር መመሪያውን ሰጥቶናል

እኔም በእርሱ ፡ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል" ብሎናል (ዮሐ.15፥5)።

እኛ በክርስቶስ፥ እርሱ ደግሞ በኛ መኖር ማለት ምን ማለት ነው፤ ጌታችን በመጀመሪያ "በእኔ ኑሩ" ካለ በኋላ (በምሳሌም ካስረዳ በኋላ) ይህ ምን ማለት እንደሆነ ምሥጢሩን ሲገልጽ፦ "በፍቅሬ ኑሩ" ማለቱ እንደሆነ አስረ ቶናል። ስለዚህ በእርሱ መኖር ማለት በፍቅሩ መኖር ማለት ነው። "በፍቅሬ ኑሩ" ያለውን ደግሞ እንዴት በሥራ እንተረጉመዋለን? ብለን ብንጠይቅ ጌታ ለሐዋርያቱ ስለዚሁ ጉዳይ ያስተማራቸውን በመጥቀስ እንደሚከተለው መልስ እናቀርባለን፦

> "በፍቅሬ ኑሩ። እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደ ጠበቅሁ በፍቅሩም እንደምኖር ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ። ደስታዬም በእናንተ እንዲሆን ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን ነግሬአችኋለሁ። እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በእርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት። ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከማኖር ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም። እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ ናችሁ። . . . አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እንዲሰጣችሁ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኋችሁ። እርስ በእርሳችሁ እንድትዋደዱ ይህን አዛችኋለሁ" (ዮሐ.15፥10-17)።

እንግዲህ በክርስቶስ ፍቅር መኖር ማለት ትእዛዙን መጠበቅ ማለት ነው፤ ሕገ ወንጌልን መፈጸም፥ በሕገ ተፋቅሮ መኖር ማለት እንደሆነ ግልጽ ነው። ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በመጀመሪያ የተራራውን ስብከት (ማቴ.5-7) መሠረት በማድረግ በክርስቶስና በክርስቶስ የፍቅር ትእዛዝ አኗኗር ክርስቲያናዊ ሕይወታችን ምን መምሰልና ምን መሆን እንደሚገባው እንገልጻለን። ሕገ ወንጌል እንደ ሕገ ኦሪት ትእዛዝን የምታውጅ ብቻ ሳትሆን ትእዛዙን ለመፈጸም የሚያስችል የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ረድኤት ያለባት ናት። ስለዚህም ወንጌል የጸጋ ሕግ ትባላለች። በክርስቶስ ጸጋ የጽድቅና የደኅንነት ሕይወት ስላለን ክርስቲያናዊ ሕይወታችን በሕገ ወንጌልና በጸጋ መንፈስ ቅዱስ የጸና ይሆናል። እንግዲህ በተራራው ስብከት መሠረትነት ሕገ ወንጌልን ከአንቀጸ ብፁዓን ጀምረን በአጭር በአጭሩ ከተመለከትን በኋላ በክርስቶስ እምነት ያገኘነው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ረድኤት ምን እንደሆነ ከቅዱሳት መጻሕፍት ቃልና ከምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን እንደሚከተለው ለማጥናት እንሞክራለን። በመጀመሪያ ስለ አንቀጸ ብፁዓን እንመልከት።

## ለ) ክርስቲያናዊ ሕይወት በብፁዓን ተስፋና ምግባር

ክርስቲያናዊ ሕይወታችንና ምግባራችን በአጠቃላይ ሃይማኖታችንና መን ፈሳዊ ዓላማችን ሁሉ በእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ላይ ተመሥርቷል። ስለሆነም የክርስቶስ ወንጌል በአንቀጸ ብፁዓን ላይ በተገለጸው የተስፋ ቃል ይጀምራል። ያለ ተስፋ፥ ሃይማኖትም ሆነ ምግባርም ሊኖር አይችልም። የሃይማኖት አባ ታችን አብርሃም ከትውልድ አገሩ ወጥቶ ወደ ማያውቀው አገር የመጣው በተስፋ ነበር። ከተስፋው አንዱ አብርሃም በእንግድነት ይኖርባት የነበረችውን ምድረ ርስትን ለዘሩ እንደሚያወርስ ከእግዚአብሔር ተነግሮት ነበር (ዘፍ.15፥7-21)። ይህች የተስፋ ምድር ለእውነተኛው ለአማናዊው ሀገረ ሕይወት ለገነት ለመንግሥተ ሰማያት ምሳሌ ነበረች። ጌታችንም የአንቀጸ ብፁዓን ትምህርቱን ሳይጀምር በፊት መንግሥተ ሰማያት እንደ ቀረበችና የተስፋው ቃልም እንደተፈጸመ አብሥሮናል (ማቴ.4፥17)። ስለሆነም በአንቀጸ ብፁዓን ክርስቲያናዊ ሕይወታቸው የቀናና በጐ ምግባር ያላቸው እውነተኛ አማኞች የሚ ሰጣቸው ምድራዊ ርስት ሳይሆን መንግሥተ ሰማያት መሆኑ ተገልጿል።

የክርስቲያኖች የመጨረሻ ዓላማና ግብ በመንግሥተ ሰማያት [illegible]

www.ethiopianorthodox.org



[illegible]ና ችግር የሌለበት ዘላለማዊ ደስታ ነው፤ ጠብና ክርክር፥ ክፋትና ተንኮል [illegible]የበጣብጠው ኑሮ ሳይሆን ዘላለማዊ ሰላምና እረፍት፥ ፍቅርና ደስታ የሰፈ[illegible] ሕይወት ነው። በክርስቶስ ጸጋ የሚገኘው፥ ኃጢአትና ሞት የሌለበት [illegible]ማዊ ሕይወት እግዚአብሔር ለሚወዱት አዘጋጅቶላቸዋል። "ዓይን [illegible]ው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት [illegible]ጀው ተብሎ እንደተጻፈ እንዲህ እንናገራለን" (1ኛቆሮ.2፥9)። እንግዲህ [illegible]ው ወራሾች የሆኑት የእውነተኛ ክርስቲያኖች ሕይወት፥ ጠባይና አመለካ[illegible] ምግባርና ትሩፋት ምን ዓይነት እንደሆነ በአንቀጸ ብፁዓን ማለት በአሥሩ [illegible]ጊል ብፁዓን ተገልጧል። (ስለ አንቀጸ ብፁዓን የተዘጋጀውን ሰንጠረዥ [illegible]ግቢያው ውስጥ ተመልከት)

## አሥሩ ብፁዓንን በመምሰል እንኑር

1. የመጀመሪያ ብፁዓን "በመንፈስ ድሆች" የተባሉት ናቸው። በመንፈስ ድሆች የተባሉት እነማን እንደሆኑ እናስተውል። በቁሙ ድሆች አላለም፤ የዚህ ዓለም ሀብት ንብረት የሌላቸውን ነዳያንን ብቻ ማለት አይደለም፤ በእርግጥ እነሱንም ይጨምራል። ነገር ግን "በመንፈስ ድሆች" ስላለ ሀብት ያላቸውንና የሌላቸውን አጠቃሎ መንፈሳዊ አቋማቸውንና አመለካከታቸውን ይገልጻል። ስለሆነም ትሕትናቸውን ብቻ የሚያመለክተን ቃል ነው። በመንፈስ ድሆች የተባሉት ሀብት ወይም ሥልጣን ወይም እውቀት ወይም ሌላ ስጦታ ሲኖራቸው ሳለ ባላቸው ነገር ሳይታበዩና ሳይመኩ ምንም እን ደሌላቸው ነዳያን ራሳቸውን በመቁጠርና ያላቸው ሁሉ የእግዚአብሔር መሆ ኑን አውቀው ራሳቸውን ዝቅ የሚያደርጉ ትሑታን ስለሆኑ ብፁዓን ማለት ንዑዳን ክቡራን ተብለዋል። ትዕቢት ከእግዚአብሔር ያርቃል፤ ትሕትና ግን ወደ መንግሥተ ሰማያት ያገባል። ስለዚህ የትዕቢተኞችን ክፉ መንፈስ እየተዋጋን የትሑታንን የተቀደሰ መንፈስና አኗኗር መከተል ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው። የብፁዓን ምግባራቸው ትሕትና፥ ተስፋቸው መንግሥተ ሰማያት ነውና።
2. "የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው" ተብሎ የተነገረላቸው ስለ ራሳቸውና ስለ ባልንጀራቸው ኃጢአት የሚያዝኑ የሚተክዙ ናቸው። ይህም ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው ሞትን የሚያመጣ የዓለም ኀዘን ሳይሆን ወደ መዳን የሚያደርሰው ይኸውም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ የንስሐ ኀዘን ነው (2ኛቆሮ.7፥9-11)። በእግዚአብሔር መጽናናትን የሚያገኙ እንደነዚህ ያሉ ተነሳሕያን ስለሆኑ በእውነት ብፁን ይባላሉ። እነርሱ በሆነው ባልሆነው የሚያዝኑ ሳይሆኑ ሞተ ወልደ እግዚአብሔርን ግፈ ሰማዕታትን እያሰቡ ያዝናሉ። የኀዘን አጸፋው ደስታ ነውና መጽናናትን አግኝተዋል። ስለዚህ አሁን የምታዝኑ ሁሉ የክርስቶስ የተስፋ ቃል ይፈጸማልና ደስ ይበላችሁ። የብፁዓን የመጀመሪያ ምግባራቸው የንስሐ ኀዘን ሲሆን ተስፋቸው ደግሞ የዘላለም ደስታ ነው።
3. "የዋሆች ብፁዓን ናቸው" የተባለው በልባቸው ቂም በቀል የሌላቸው ገ ሮችና ቅኖችን የሚያመለክት ነው። እንደ እነዚህ ያሉት ሰማያዊ ርስትን ያገ ኛሉ። እንደነዚህ ያሉት ዓመፅን የማያውቁ ኃዳግያን በቀል የሆኑ ከየውሃት ጠባይዓዊ የደረሱ ንዑዳን ክቡራን ናቸው። ጌታ የዋህና ትሑት ስለ ሆነ የእርሱን አርአያ በመከተላቸው ተስፋ መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ነውና ደስ ሊላቸው ይገባል።
4. "ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው" የተባለው ስለ ጽድቅ ሲሉ ኃጢአትን በመዋጋት ፈቃዳተ ነፍስን ለመፈጸም የሚራቡትንና የሚጠ ሙትን ያመለክታል። እነርሱም ስለሚበሉትና ስለሚለብሱት ባለመጨነቅ [illegible]ብሔርን መንግሥትና ጽድቁን የሚፈልጉ ናቸው።

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ በአንድ በኩል ስለ ጽድቅ የሚራቡና የሚጠሙ ማለት የሚ... ማለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ጽድቅን የሚራቡ ማለት የቃለ እግዚ... ብሔር ረሃብ ስለሆነ የሁለቱንም የነፍስና የሥጋን ረሃብና ጥም ያሳያ... ዋጋቸውም ነፍስንና ሥጋን ለመመገብ የሚችል እግዚአብሔር በበረከ... ሥጋና በበረከተ ነፍስ ያጠግባቸዋል፡፡ "አንድም ለፍቅሩ የሚ... ሰዎች ንዑዳን ክቡራን ናቸው፡፡ ጸምአት ነፍስየ ለከ" -- ነፍሴ አን... ተጠማች ይላል (ማቴ.5፥6 ትርጓሜውን ተመልከት)፡፡ የወንጌል ብፁ... ከምግባራቸው አንዱ እግዚአብሔርንና ጽድቁን አጥብቀው መፈለግ መ... ነው፤ ተስፋቸው የልቡና እርካታና የዘላለም ደስታ ነው፡፡

5. "የሚምሩ ብፀዑን ናቸው፥ ይማራሉና" የተባለው "ቢበድሉ ማሩ... ቢበደሉ ይቅርታ" ማድረግ በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋን ያሰጣል፡፡ የበ... ሉንን ይቅር ማለት ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትን ያስገኛልና፡፡ ስለዚ... ነው በአቡነ ዘበሰማያት ጸሎታችን "በደላችንን ይቅር በለን እኛም የበ... ሉንን ይቅር እንደምንል" በማለት ዘወትር የምንለምነው፡፡ "ለሰዎች ኃጢአ... ታቸውን ይቅር ብትሉ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላ... ኋልና፤ ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም ኃጢአ... ታችሁን ይቅር አይላችሁም" (ማቴ.6፥14-15)፡፡

የሚምሩ ማለት የሚያዝኑ የሚራሩ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ምሕረት... ከእግዚአብሔር ያገኛሉና፡፡ እንግዲህ ምሕረትን የሚያደርጉ ምሕረት... ያገኛሉ፡፡ ምሕረትን በሦስት ወገን እንረዳዋለን፡፡ "ምሕረት ሥጋዊ... ምሕረት መንፈሳዊና ምሕረት ነፍሳዊ አለ፤ ምሕረት ሥጋዊ ቀዶ ማልበስ... ቆርሶ ማጉረስ . . . ነው፡፡ . . . ምሕረት መንፈሳዊ ክፉውን ሃይማኖት... ክፉውን ምግባር በጎ ምግባር በጎ ሃይማኖት መስሎት ይዞት ሲኖር መክሮ አስ... ተምሮ ክፉውን ሃይማኖት አስትቶ በጐውን ማስያዝ ክፉን ምግባር አስት... በጐውን ማሠራት ነው፡፡ ምሕረት ነፍሳዊ መጥዎተ ርእስ ነው" (ማቴ.5፥7 ትርጓሜ ወንጌል ተመልከት)፡፡ የብፁዓን ምግባር ይቅርታ ማድረግ ስለሆ... ነ ተስፋቸው ደግሞ ሰማያዊ ይቅርታና ምሕረት ማግኘት ይሆናል፡፡

6. "ልበ ንጹሐች ብፁዓን ናቸው፥ እግዚአብሔርን ያዩታልና" የተባለው በንስሐ ከኃጢአት ከበደል ንጹሐን የሆኑ፥ ከቂም ከበቀል የራቁ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ማለት ነው፡፡ ቂም በቀል ያለበት ሰው እግዚአብሔርን ማየት ይቅርና ጸሎቱም በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት የለውም፡፡ በአን... ጽሖ መንፈስ ከንጽሐ ልቡና የደረሱ እግዚአብሔርን የማየት ፈጣሪያቸውን በእርግጠኝነት የማወቅ ዕድል ተሰጥቷቸዋልና ሁልጊዜ ደስተኞች ናቸው፡፡ የወንጌል ብፁዓን አመለካከት፥ ጠባይና ምግባር በንጽሕናና በቅድስና የተሞላ ስለሆነ ተስፋቸው እስከ ነፅሮተ ሥሉስ ቅዱስ ማዕርግ ይደርሳል፡፡

7. "የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው" የተባሉት ሰውን ከሰው ጋር ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር በማስታረቅ እርቅና ሰላምን የሚያስገኙ ናቸው፡፡ በቤት በጐረቤት ተጣልተውና ተቀያይመው ተለያይተው የሚኖሩትን ሰዎች ከያሉበት ፈልገው ወጥቶ ወርዶ የሚያስማማና የሚያስታርቅ ሰው ታላቅ ክርስቲያናዊ ምግባርን ፈጽሟል፡፡ "ሰው ሰርቶ ቀምቶ ከፈጣሪው ጋር የሚጣላ የሚበላው የሚለብሰው እንጂ ቢያጣ ነው ብለው የሚበላውን የሚለብሰውን ሰጥተው ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስታርቁ ባለጠ... ጐች ንዑዳን ክቡራን ናቸው፡፡ ሰውን በንስሐ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያ... ስታርቁ ቀሳውስት ንዑዳን ክቡራን ናቸው፡፡" እነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ፡፡ ምክንያቱም "ጌታ በመስቀል ተሰቅሎ ወደ መቃብር ወርዶ ሰውን ከእግዚአብሔር ...



ቁልቁለቱን ወርደው በማስታረቃቸው ይመስሉታልና" (ትርጓሜ ወንጌል)፡፡ የማስታረቅ ሥራ የሚፈጽሙ ክርስቲያኖች በምግባር ጌታቸውን መስለውታልና ተስፋቸውና ማዕርጋቸው ከፍ ያለ ነው፡፡

8. "ስለጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው" የተባሉት እውነትንና ጽድቅን ለማወቅ ወይም ለማስተማር ወይም በምናኔና በንስሐ ምክንያት አገራቸውን ጥለው የተሰደዱ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ እግዚአብሔርና ጽድቁን ለመፈለግ ሲሉ ከዓለማዊ ኑሮና ከክፉ ግብር ራሳቸውን የለዩትን ሁሉ ይመለከታል፡፡ በተለምዶ ከያዙት ዓለማዊ ኑሯቸው ወጥተው ወደ መንፈሳዊ ዓለም ገብተው ትሩፋት ገድል ለመሥራት በቅተዋል፡፡ የሰው ሀገሩ ምግባሩ ነውና ስለጽድቅ ሲሉ መከራ የተቀበሉት ሁሉ ሀገረ ሕይወት ገነት መንግሥተ ሰማያት ለእነርሱ ተሰጥታለች፡፡

9. "በእኔም ምክንያት ሲነቅፏችሁና ሲያሳድዷችሁ ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ" የተባሉት በአጠቃላይ በክርስቶስ ስም መከራን የሚቀበሉ ሁሉ ናቸው፡፡ እንደነዚህ ያሉት ዋጋቸው በሰማያት ታላቅ ስለሆነ ደስ እንዲላቸውና ሐሤትም እንዲያደርጉ ጌታ ደቀ መዛሙርቱን አስተምሯቸዋል፡፡ ከእነርሱ በፊት የነበሩትንም ነቢያትን እንደዚሁ ያሳድዷቸው ስለነበር በመከራው እንዲታገሡ በተስፋውም እንዲደሰቱ ማጽናኛውን ሰጥቷቸዋል፡፡ ዛሬም በክርስቶስ ስም መከራ የሚቀበሉ ሁሉ ለነቢያትና ለሐዋርያት የተሰጠውን ዋጋ የመንግሥተ ሰማያት ደስታን ይቀዳጃሉ፡፡

10. "እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፥ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል፡፡ እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና፡፡ . . . ይህን ብታውቁ፥ብታደርጉትም ብፁዓን ናችሁ" የተባሉት የክርስቶስን አርአያ ተከትለው ፍቅርና ትሕትናን በተግባር የሚፈጽሙት ናቸው (ዮሐ.13፥14-17)፡፡ ክርስቶስ ሰውን ሁሉ እንደ ወደደና ለጠላቶቹም እንደ ጸለየላቸው እኛም እንዲሁ ማድረግ ይገባናል፡፡ እርሱ ትሑትና ታጋሽ እንደሆነ እኛም እርሱን አብነት አድርገን እርሱን መምሰልና በግብር መከተል ይኖርብናል፡፡ እንደዚህም ካደረግን ክርስቲያናዊ ሕይወታችን በእምነትና በጽድቅ ሥራ ይጠናከራል፤ የመንግሥተ ሰማያት ወራሾች እንሆናለን፡፡

አሥሩ ብፁዓን ጌታን ከሚከተሉት አምስት ገቢያ ሕዝብ ተለይተው በእግር ብቻ ሳይሆን በግብርም የሚከተሉትን ደቀ መዛሙርቱን ይመለከታል፡፡ "እናንተ የምድር ጨው ናችሁ . . . እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ" ብሎ ጌታ የተናገረው ለአሥሩ የወንጌል ብፁዓን ነው፡፡ እነርሱ በክርስቲያናዊ ሕይወታቸውና በበጐ ምግባራቸው አልጫውን ኅብረተሰብ ሊያጣፍጡና ጨለማውን ዓለማችንንም በሃይማኖት ብርሃናቸው በመልካም አርአያቸው የክርስቶስ ብርሃን ለሁሉም እንዲያበራ ለማድረግ የሚችሉበት የጸጋ ኃይል ተሰጥቷቸዋል፡፡ ስለዚህ የአሥሩን ብፁዓን ፈለግ የምትከተሉ ሁሉ "መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ" (ማቴ.5፥13-16)፡፡

www.ethiopianorthodox.org

## ሐ) ክርስቲያናዊ ሕይወት በሕገ ወንጌል

በክርስቶስ እምነትና በአንቀጸ ብፁዓን ላይ የተመሠረተው ክርስቲያናዊ ሕይወታችን በሕገ እግዚአብሔር መጠናከር አለበት፡፡ የክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣት ሕጉን ለመፈጸምና ለማጠናከር እንጂ ለማፍረስ አ ደለም (ማቴ.5፥17-20)፡፡ ሕግ ስንል ሕገ ልቡናን ሕገ ኦሪትንና ሕገ ወንጌልን ማለታችን ነው፡፡ ሦስቱም ሕግጋት የእግዚአብሔር ናቸው፡፡ በሕገ ኦሪት የተጻፈው አሥሩ ቃላት በተፈጥሮ ልቡናችን የሚገኘው ዓይነት እንደሆነ ለማወ ብንፈልግ ሕግ ሳይሰጣቸው በሕግ የሚኖሩት የአሕዛብን የሞራል ማለት የሥ ነ ምግባር ታሪክ መጥቀስ ይቻላል (ሮሜ.2፥14-15)፡፡ ሕገ ልቡናን በሕገ ኦሪት እንዳጠናከረው ሕገ ኦሪትን ደግሞ ጌታ በሕገ ወንጌል ፍጹም አድርጐታል (ማቴ.5፥17-48)፡፡ እንግዲህ አንዳንድ ወገኖች እንደሚያደርጉት በእምነት ወይም በጸጋ አመካኝቶ ሕግን ትቶ መኖር ከክርስቲያናዊ ሕይወት ውጭ መ ኑን በጌታ ቃል እናረጋግጣለን፡፡ ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ሕግን በእምነት እንሽራለን? አይደለም፤ ሕግን እናጸናለን እንጂ" ያለው (ሮሜ.3፥31)፡፡ የእምነታችን ጌታና ባለቤት ክርስቶስ ሕግን ካጸና ዘንድ በሕግ መኖር ክርስቲያናዊ ግዴታችን ይሆናል፡፡

ሕግ በራሱ "ቅዱስ ነው ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት" (ሮሜ.7፥12)፡፡ ስለሆነም ክርስቲያናዊ ሕይወታችን ሕግን ለመፈጸም በምናደርገው ጥረትና መንፈሳዊ ተጋድሎ ይገመገማል፡፡ ሕግ ይህን አድርግ ያንን አታድርግ እያለ በማወጅ በደላችንንና ኃጢአታችንን ቆጥሮ ቆጥሮ እየመዘገበብንና እየዛተብን ያስታውቀናል እንጂ የጽድቅ ሥራ እንድንሠራ አ ይረዳንም፡፡ እንዲያውም በሕግ ተላላፊነታችን የተነሣ በሕግ መሠረትነት ፍርድ ያጸናብናል፤ ይቀጣናል፡፡ ስለዚህ በሕግ ፊት የተገሠጽን ሁላችን በታላቅ ትሕትና ወደ ክርስቶስ ጸጋ እንድንቀርብ ይገባናል፡፡ ስለ ባሕርያችን ደካማነት የተነሣ ስለ እኛ ሕግን ሁሉ ፈጽሞ ከኃጢአታችን በደሙ ያዳነን ክርስቶስ እን ደሆነ አምነን በእርሱ ሕግን እንደ ፈጸምን ስለሚቆጠር በእርሱ ጸጋና ረድኤት ሕግን ለመፈጸም እንበረታታለን፤ በእርሱም ጸጋ ሥር ስለሆንም ኩነኔ የለብንም (ሮሜ.8፥1-4)፡፡ በሕግ ያላገኘነውን ደኅንነትና ጽድቅ በክርስቶስ ተሰጥቶናል፤ በሕገ እግዚአብሔርም እንድንኖር የሚያስችለንን ጸጋ መንፈስ ቅዱስን በእርሱ ተቀብለናል፡፡ እግዚአብሔር በሕጉ ያዘዘውን በጸጋው እንድንፈጽመው ያስችለናል፡፡ ኃይልን በሚሰጠን በክርስቶስ ሁሉን እንችላለን (ቆላ.4፥13)፡፡

### ጠቅላላ የኦሪት ሕጐች በሦስት ዐበይት ክፍሎች

ሕግን የሰጠው ጌታ ሕግን ሁሉ በመዋዕለ ሥጋዌው ፈጽሞታል፡፡ "ሕግንና ነቢያትን . . . ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም . . . ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፡ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ" በማለት ጌታ የተናገረው ይህ ቃል የሚያስረዳን በአንድ በኩል በአ ጠቃላይ ከኦሪት ሕጐች መካከል የሚሻር እንደ ሌለና ሁሉም መፈጸም እን ዳለበት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ "ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ" የሚለው ሐረግ ከብሉይ ኪዳን ሕግ መካከል ትንቢታቸው ተፈጽሞ በሌላ የአዲስ ኪዳን ሕግ የሚተኩ መሆኑን ያመለክታል፡፡ እንግዲህ ይህን ለመረዳት የምንችለው በአ ጠቃላይ የኦሪትን ሕግ በሦስት ወገን ወይም ክፍል ከፍለን በማሳየት ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል የኦሪቱ የሃይማኖትና የሥነ ምግባር ሕግ ሲሆን ሁለተኛው የኦሪት ካህናትንና የኦሪት መሥዋዕትን ሕግና ሥርዓት ይመለከታል፡፡ ሦስተኛው በጥንቷ የእሥራኤል መንግሥት ይሠራበት የነበረው ለሀገሪቱ እንደ ፍትሐ ብሔርና እንደ ወንጀለኛ መቅጫ የሚያገለግለው ሕግና ሥርዓት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡



የመጀመሪያው ክፍል አሥሩ ቃላትንና ሌሎችንም የሥነ ምግባር ማለት የግብረ ገብ (የሞራል) ሕጐችን ያካተተ ነው፡፡ አሥሩ ቃላት በሕገ ወንጌል ተጠናክሮ የክርስቲያኖች ሁሉ ሕግና ደንብ ሆኖ ይሠራበታል፡፡ ሁለተኛው ክፍል ግን በክርስቶስ ሊቀ ካህናትነትና በክርስቶስ መሥዋዕትነት ፍጻሜ አግኝ ቷል፡፡ የኦሪት የእንስሳት መሥዋዕት በክርስቶስ ሥጋና ደም ማለት በምሥጢረ ቊርባን ተተክቷል፡፡ የኦሪት ክህነትም በጌታ ሊቀ ካህናትነት በወንጌል ካህናት በሐዋርያትና በተከታዮቻቸው ተፈጽሟል፡፡ ሦስተኛው ክፍል እንደ ፍትሐ ብሔ ርና እንደ ወንጀለኛ መቅጫ የመሳሰሉት የኦሪት ሕጐች በሌሎች መሰል ሕጐች የተተኩ ሳይሆኑ አብያተ ክርስቲያናት እንደሚገኙበት ብሔር ወይም ሀገር የተለ ያዩ ናቸው፡፡ ክርስቲያኖች ሁሉ በያሉበት ሀገር ብሔራዊ ሕግ ይተዳደራሉ፤ ለመንግሥት ባለሥልጣኖችም ይገዛሉ (ሮሜ.13፥1-7)፡፡ ሕገ ወንጌልን መሠረት ያደረጉ ሕገ ቤተ ክርስቲያንና ልዩ ልዩ የቀኖና መጻሕፍት አሉ፡፡ እነዚህም ለክርስቲያኑ ሕዝብ የመንፈሳዊና የማኅበራዊ ኑሮ ሕግና ሥርዓት፥ ደንብና መመሪያ በመሆን ያገለግላሉ፡፡

እንግዲህ ሕገ ኦሪት ስንል ከላይ የተጠቀሱትን ሦስቱን ክፍሎች ያጠቃ ልላል፡፡ ከነዚህም የመጀመሪያው ክፍል ታላቁ ሕግ አሥሩ ቃላትና ሌሎችም የሥነ ምግባር ወይም የግብረ ገብ ሕግና ደንቦች ሁሉ ለክርስቲያኖች የዕለት በዕ ለት መመሪያ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ የሕግ አፈጻጸሙም እንደ ጸሐፍት ፈሪሳ ውያን አፍአዊ ማለት ውጭ ውጩን ወይም ላይ ላዩን በግብዝነት ሳይሆን ውስጥ ውስጡን ወደ ልባችን ገብቶ ከዚያ በመነሣት በእውነተኝነትና በቅን መን ፈስ በሙሉ ኃይላችን ቃሉን በሥራ ላይ በማዋል ነው፡፡ ጽድቃችን ከጸሐፍትና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ መንግሥተ ሰማያት ልንገባ የማንችል መሆናችንን ጌታ አስተምሮናል (ማቴ.5፥17)፡፡ ከኦሪት ጽድቅ የወንጌል ጽድቅ እንዲበልጥ ጌታ ሕገ ኦሪትን በሕገ ወንጌል ፍጹም አድርጐ ሰጥቶናል፡፡ ወፈጸመ ሕገ ርትዕ በሕገ ትሩፋት ማለት ከሚገባውና ከቀጥተኛው የሕግ ሥራ በላይ አብልጦ አት ርፎ በጐ መሥራትን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም ኢትቅትል በኢታምዕዕ ኢት ዘሙን በኢትፍቱ አጽንቷቸዋል፤ ትርጉሙም፦ አትግደል የሚለውን አት ቆጣ፥ አታመንዝር የሚለውን አትመኝ በማለት አጠናክሮታል፡፡ እንግዲህ እነዚ ህና ሌሎችም በስድስቱ ቃላተ ወንጌል እንደ ሚከተለው በአጭሩ ተገልጸዋል (ማቴ.5፥21-48)፡፡ (ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ከኦሪት ጋር ያለውን ንፅፅር ለማሳ የት የተዘጋጀውን ሰንጠረዥ በመግቢያው ውስጥ ተመልከት)

### ስድስቱ የኦሪት ትእዛዛት በስድስቱ ቃላተ ወንጌል ሲተረጐሙ

1. "ለቀደሙት፦ አትግደል እንደ ተባለው ሰምታችኋል፤ የገደለ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል. . . " በማለት ጌታችን የኦሪቱን ሕግ ከጠቀሰ በኋላ ፍጹም የሆነችውን የወንጌልን ሕግ በአንፃሩ ያስቀምጣል፡፡ "እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ ደንቆሮ የሚለው ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል"፡፡ እንግዲህ ሕገ ወንጌል እንደዚህ ናት፡፡ አትግደል ያለውን ክፉ ድርጊት አለማድረግ ብቻ ሳይሆን ከድርጊቱ በፊት ያለውን ክፉ ሐሳብና ስሜት መቆጣጠር ይገባል፡፡ አትግደል ያለው ቊጣንና ስድብን ጭምር ይከለክላል፡፡ ስድብ ምን ያህል ክፉ ነገር እንደሆነ አውቀን እን ጠንቀቅ፡፡ መንግሥተ ሰማያትን ያህል ተስፋ አስቀርቶ የገሃነመ እሳት ቅጣትን የሚያመጣብንን ይህንን ቊጣና ስድብን በታላቅ ትዕግሥትና አርምሞ እን ቆጣጠረው፡፡ በየጊዜውና በየወቅቱ በክርስቶስ ስምና ፍቅር በምናደርገው የጸሎት ኃይል እየታገዝን ክርስቲያናዊ ሕይወታችንን ከቊጣና ከስድብ ኃጢአት የነጻ እን ዲሆን ያልተቋረጠ ጥረት እናድርግ፡፡ ስለ እውነት ጉዳይ በተገቢው መንገድ

www.ethiopianorthodox.org

የምትቆጡ ብትኖሩ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው፦ "ኃጢአትንም አታድ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፥ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት . . . ማናቸ በጐ ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይውጣ፡፡ ለቤዛም ቀን የታተ ሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ፡፡ መራርነትና ንዴት ቁጣ ጩኸትም መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ፡፡ እ በርሳችሁ ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፥ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እ ዳላችሁ ይቅር ተባባሉ" (ኤፌ.4፥26-32)፡፡

2 "አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል፡፡ <u>እኔ ግን እላችኋለሁ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመ ዝሯል</u>፡፡ . . ." በሕገ ኦሪት አታመንዝር የሚለው የኃጢአት ድርጊት በወን ሕግ ሴትን አይቶ መመኘት በልብ ማመንዘር ስለሆነ ሴትን አይቶ መመኘ ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡ አይቶ መመኘት እንጂ ያለ ምኞት ማየት በለ ማመንዝር አይደለም፡፡ ሆኖም ለክፉ ምኞት ላለመጋለጥ ርእይን (ማየትን) መቆ ጣጠር ያስፈልጋል፡፡ ይልቁንም በዛሬው ጊዜ ሱባኤ እንደገባ ጾመኛ ማናቸው ክርስቲያን የዓይን ጾምን ማዘውተር ይገባዋል፡፡ ዓይናችን ምክንያተ ስሒት እ ዳይሆንብን ክፉውን ከደጉ ለይተን የማየት ልምድ ይኑ ረን፡፡ አለበለዚያ ሁለ የዓይን ዐዋጅ ይሆንብንና በአእምሮ ፍርድ መመራታችን ቀርቶ በእይታ ብቻ እንድንነዳ ይሆናል፡፡ ይህም ለስሜታችንና ለምኞታችን ብቻ ተገዢዎች እን ሆን ያደርገናል፡፡ ስለዚህ ከላይ የተጠቀሰው ሕገ ወንጌል ከድርጊቱ በፊ የሚመጣውን ክፉ ሐሳብና ስሜት የዝሙት ምኞት እንድንቆጣጠረው ያስ ስበናል፡፡ የበጎም የክፉም ነገር መነሻው የልባችን ስሜት የሕሊናችን ሐሳብ ስለሆነ ክፉ አስተሳሰብና ርኩስ መንፈስ በዚያው በኩል የሚመጣ መሆኑን ተገ ዝበን በእግዚአብሔር ጸጋና ረድኤት የልባችንን በልባችን ውስጥ ውስጡ መታገል አለብን፡፡ ጌታ እንዳለው "ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ ዝሙት ፥መስረቅ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ መጐምጀት፥ ክፋት፥ ተንኰል መዳራት፥ ምቀኝነት፥ ስድብ፥ ትዕቢት፥ ስንፍና ናቸውና ይህ ክፉው ሁሉ ከውስጥ ይወጣል፤ ሰውንም ያረክሰዋል" (ማር.7፥21-23)፡፡ እንግዲህ የሚያ ሰናክለን ከሆነ ዓይናችንን እንድናወጣው እጃችንን እንድንቆርጠው የታዘዘው ለኃጢአት ምክንያት የሆነውን ነገር ሁሉ ሳናመነታ በቁርጠኝነት ከእኛ እን ድናርቀው ወይም እኛ እንድንርቀውና እንድንሸሸው፥ ከልቡናችን መዝገብ እን ድናስወጣውና ከሐሳባችን እንድናስወግደው መታዘዛችንን ያመለክታል፡፡

3 "ሚስቱን የሚፈታት ሁሉ የፍችዋን ጽሕፈት ይስጣት ተባለ፡፡ <u>እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አ መንዝራ ያደርጋታል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል</u>፡፡" በሙሴ በኩል የተሰጠው የኦሪት የጋብቻ ሕግ መፋታትን ይፈቅዳል፤ ብዙ ሴቶችንም ማግባት አይከለከልም፡፡ በወንጌል ግን መፋታት የሚቻለው በዝሙት ምክንያት ብቻ ነው፡፡ ከአንድ በላይ ማግባትም የተከለከለ ነው፡፡ አንድ ወንድ በአንዲት ሴት አንዲት ሴት በአንድ ወንድ ጸንቶ መኖር በሕገ ወንጌል ተደን ግጓል፡፡ ሁሉም ክርስቲያን ሕጉን የመጠበቅና የማስጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡ ክርስቲያናዊ ሕይወትም የሚለካበት አንዱ መመዘኛ ይህ የወንጌል ሕግ ነው፡፡ ስለዚህ ምእመናን ሁሉ በጋብቻ እንዲወሰኑና ምሥጢረ ተክሊልም እንዲፈጽሙ እናት ቤተ ክርስቲያናችን ከአደራ ጭምር ታሳስባለች፤ በጋብቻም ውስጥ ያሉት እስከሞት ድረስ ከኑሮ ጓደኞቻቸው ጋር በክርስቶስ ፍቅር ተዋደውና ተቻችለው አንድ በአንድ ጸንተው እንዲኖሩ ትመክራለች፡፡

4."ደግሞ ለቀደሙት፦ በውሸት አትማል ነገር ግን መሐላዎችህን ለጌታ ስጥ እንደ ተባለ ሰምታችኋል፡፡ <u>እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ከቶ አት ማሉ</u>፤. . ." መሐላ በኦሪት የሚከለከለው በውሸት ነገር ብቻ ሲሆን ነው (ዘሌ. ፲፱፥12፤ ዘፀ.20፥7፤ ዘዳ.5፥11፤ ያዕ.5፥12)፡፡ በወንጌል ግን መሐላ ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡ በሰማይም በምድርም በሀገርም በራስም በሌላ ሰውም በሌላ ዘርም መማል አይገባም፡፡ ጠብ ክርክርን ለማስቀረትና የተደበቀውን እውነት ለማውጣት በፍርድ ቤት ቃለ መሐላ መስጠት ይፈቀዳል፡፡ ከዚህ በስተቀር በማን ኛውም ጊዜና ቦታ በንግግርና ጨዋታ መካከል መማልና መገዘት ከክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ውጭ ነው፡፡ ታዲያ ለምንድነው ክርስቲያኖች በየመንገዱ የእግዚአ ብሔርን፥ የእመቤታችንን፥ የመላእክትን፥ የቅዱሳንን፥ የአባትና የእናትን ስም የሚጠሩ በየሰዓቱ የሚምሉት? ይህን በዘልማድ የሚፈጸመውን አነጋገርና አኗ ኗር አሻሽለን እውነተኛውንና የታረመውን ክርስቲያናዊ ጠባይ እና ንግግር መከተል ይገባናል፡፡ እንግዲህ "ፈጽማችሁ አትማሉ" በማለት ጌታ ያዘዘውን ለመፈጸም እንትጋ፤ ለሌሎችም አብነት እንሁናቸው፤ አንደበታችንንም መቆጣ ጠር እንልመድ እንዲያው አፋችን እንዳመጣው ሳናስብና ሳንገምት መናገርና የሆነውም ላልሆነውም ለቀልዱም ለቁም ነገሩም ለሐሰቱም ለእውነቱም መማልና መገዘት በውጭ ባሉትና በተቃዋሚዎቻችን ዘንድ የሚያስንቅንና የሚያዋርደን ነው፡፡ ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው፦ "ዘመኑን እየዋጃችሁ፥ በውጭ ባሉት ዘንድ በጥበብ ተመላለሱ፡፡ ለእያንዳንዱ እንዴት እንድትመልሱ እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ ሁልጊዜ፥ በጨው እንደ ተቀመመ በጸጋ ይሁን" (ቆላ.4፥5-6)፡፡ እንግዲህ እንደ ወንጌሉ ቃል እውነቱን እውነት፥ ሐሰ ቱን ሐሰት፥ የሆነውን በአዎንታ አዎን አዎን በማለት ያልሆነው በአሉታ አይደ ለም አይደለም በማለት ነገራችንን እንቋጨው፤ "ከነዚህም የወጣ" ግን ጌታ እን ዳለው፦ "ከክፉው /የተገኘ/ ነው፡፡" ከመማልና ከመገዘት ብቻ አይደለም የተከለከልነው ከክፉው ነገር ሁሉ አንደ በታችንን መቆጣጠር ይኖርብናል፡፡ አን ደበቱን መቆጣጠር የተወ ክርስቲያን ሁሉ ክርስቲያናዊ ሕይወቱን ትቷል ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ማንም አንደበቱን ሳይገራ ያለልጓም ልቅ አድርጐ ከተወው ውጤቱ አደገኛ ይሆናል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ እንዳለው፦

> "አንደበትም እሳት ነው፡፡ አንደበት በብልቶቻችን መካከል ዐመፀኛ ዓለም ሆኗል ሥጋን ሁሉ ያሳድፋልና፥ የፍጥረትንም ሩጫ ያቃጥላል፥ በገሃነምም ይቃ ጠላል፡፡ የአራዊትና የወፎች የተንቀሳቃሾችና በባሕር ያለ የፍጥረት ወገን ሁሉ በሰው ይገራል ደግሞ ተገርቷል፤ ነገር ግን አንደበትን ሊገራ ማንም ሰው አይ ችልም፤ የሚገድል መርዝ የሞላበት ወላዋይ ክፋት ነው፡፡ በእርሱ ጌታንና አብን እንባርካለን፤ በእርሱም እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠሩትን ሰዎች እን ረግማለን፤ ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣሉ" (ያዕ. 3፥6-10)፡፡

እንግዲህ በእግዚአብሔር ረድኤት ቁም ነገር ለማድረግ ይቻላልና በክርስቶስ ስም በመጸለይ የክርስቶስን አርአያ በመከተል በየዕለቱ አንደበታችንን ከመቆጣጠር አንቆጠብ፡፡ "ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፤ ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህና ከቃልህም የተነሣ ትኰ ነናለህ" (ማቴ.12፥36-37)፡፡

5. "ዓይን ስለ ዓይን ጥርስም ስለጥርስ እንደ ተባለ ሰምታችኋል፡፡ <u>እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ክፉውን አትቃወሙ</u>፤ . . ." "ዓይን ስለ ዓይን" ማለት ዓይን ቢጠፋ ዓይን ይጥፋ፥ ጥርስ ቢሰበር ጥርስ ይሰበር በማለት ኦሪት ታውጃለች፡፡ ወንጌል ግን ክፉውን አትቃወሙት፤ ክፉውን ሰው በክፉ ነገር ድል አትንሱት ክፉውን ግብር በክፉ ግብር አታጥፉት ትላለች፡፡ እንዲያውም "ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙ ርለት፤ እን ዲከስህም እጀ ጠባብህንም እንዲወስድ ለሚወድ መጐናጸፊያህን ደግሞ ተውለት . . ." በማለት ወንጌል አዲስ የማኅበራዊ ኑሮ ሥነ ምግባር መሥርታለች፡፡ ለአንዳንድ ወገኖች ክርስቲያኖች በክፉዎች መሰደብ፥ መመታት፥ መደብደብ፥ መከራ መቀበልና መገደል የክርስቲያኖች ዕድል ፈን ታ መስሏቸዋል፡፡ አንዳንድ የገነር መደብ ፈላስፎች ደግሞ ክርስትና

www.ethiopianorthodox.org

የተገኘርዎች ማለት መብት የሌላቸው የተዋረዱ ሰዎች ሥነ ምግባር የባሪያዎች የሞራል ሕግ ነው በማለት በድፍረት ይናገ ራሉ፣ ይጽፋሉም። ግን እውነቱ እንደዚህ አይደለም፡፡ በዓለም ዘንድ የማ ይደገፌው ይህ የክርስቲያኖች የአኗኗር ስልት ያለ ዓላማ ወይም ያለ ምክንያት የሚደረግ አይደለም፤ ውስጡ ጥበበ እግዚአብሔር ያለበት አሠራር ከኅብረተሰቡ መካከል ክፉውን አስወግደን መልካሙን ኑሮ ለማስፈን የም በትዕቢትና በሥልጣን፣ በኃይል በማስገደድና በበላይነት መንፈስ በትሕትናና በፍቅር፣ በትዕግሥትና በየዋህነት በመኖር ነው፡፡ ክርስ በመልካም ኑሮአቸውና አርአያቸው በጥላቻና በክፋት ለተወ ጠረው እርቅና ሰላምን ያወርዳሉ፤ በኅብረተሰቡም መካከል ነፃነትና እኩልነት ድማማችነትና እኅትማማችነት እንዲበረታታ ያደርጋሉ፡፡

ለክፉ ነገር መልካም ነገርን መመለስ ውጤቱ መልካም ነው፡፡ ግን ክፉውን በክፉ መመለስ ክፉ ነገርን ማዛመትና ማባዛት ይሆናል፡፡ ማለት ክፉ ሲበዛ በክፉ ይሆናል የክፉ ክፉ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ በኅብረተሰቡ ዘንድ እየተባዛ እንዳይሄድና ለመቀነስ እንዲቻል ለማድረግ ነገር በአንድ ግለሰብ ላይ ሲፈጸም ወይም ሲከሰት ወደ ሌላ ሰው እንደ በሽታ ተላልፎ እንዳይሄድ ለመግታት የሚያስችል በቅድሚያ መንፈሳዊ ባት አድርጐ መጠባበቅ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ክትባት በመንፈሳዊ የትምህር የምክር አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ግለሰቡም ባገኘው ምክርና ጸሎት ተ ሮ ከመንፈስ ቅዱስ በሚሰጠው ጸጋና ረድኤት የመንፈስና የሞራል ኃይል ጃል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሰው በነገር የተሰቦ በሽታ የተያዘ ተሳዳቢና ጠበኛ ሲያጋጥመው የጠበኛው ክፉ መንፈስ ወደ እርሱ እንዳይጋባ የሚከላከልበት የትዕግሥትና የሰላም መንፈስ ስላለው ጠበኛውን በፍቅርና በትሕትና አስተና በሰላም በእርቅ ሊሸኘው ይችላል፡፡ በዚህ ሁናቴ የጠብ ጫሪውን ክፉ ክርስቲያን የሆነ ሰላማዊ ሰው ሁሉ እንደምንም ብሎ ማቀዝቀዝ ይኖርበ (ምሳሌ 15፥1 እና 4)፡፡ አለበለዚያ አንዱ አንዱን ሲተናኮለው ካልታ ካላሳለፈው ሁለቱም ከመደባደብ ደረጃ ይደርሳሉ፡፡ እነርሱን ያዩ ዘመድና ጓደኛ ሁሉ ወገን በመለየትና በመተጋገዝ ጠቡን ያፋፍሙታል ገላጋይ ከሌለማ የጠቡ ተካፋዮች እየበዙ አምባጓሮው እየከረረና እየተዛመ እንደ ቤት ቃጠሎና እንደ ሰደድ እሳት ሀገሩን ያዳርሰዋል፡፡ እንግዲህ ይህ ነቱ ነገር እንዳይከሰት የቁጣና የበቀል እሳትም እንዳይዛመት ሳይቃጠል በት እንደ ተባለው በቅድሚያ ጠቡ ገና እንደ ተጀመረ ወዲያውኑ ሊከሰ የሚችለው ክፉ ነገር የተፈጸመበት ግለሰብ በክርስቶስ መንፈስ ተጽናን ክፉውን በትዕግሥት ያሳለፈው እንደሆነ ነው፡፡ ያንዳፍታ ስሕተት የዘላለ ፀፀት እንዳይሆንብን ወደ ፈተና እንዳንገባ ከክፉው ሁሉ ወደ ሚያድነን የሰ ማይ አባታችን ተግተን እንጸልይ፡፡ ስለ ክርስቶስ ብለን በግፍ የሚመጣብንን መከራ ታግሠን ክፉውን በክፉ ሳንቃወም በትዕግሥትና በአኮቴት እንቀበለው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንዳለው፡-

> “የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና፡፡ እርሱም ኃጢአት ላደረገም፣ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም፤ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም፣ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ” (1ኛጴጥ.2፥21-23)፡፡

እስከ አሁን ክፉውን በክፉ ባለመቃወም የክፉውን ሰው አሉታዊ እን ቅስቃሴ ለመግታት የምንችልበትን መንገድ በአጭሩ አመልክተናል፡፡ ከዚህ ጋር ደግሞ ክፉውን ሰው የምናሸንፍበት ሌላ መንገድ አለ፡፡ ይኸውም ክፉ ለዋለብን ሰው በክርስቶስ ሆነን ደግ ሥራ በመሥራት የምንፈጽመው ነገር ነው፡፡ በቀ ልንና ፍርድን ለእግዚአብሔር ትተን ይልቅስ ክፉ ለዋለብን ሰው በጐ ነገር አድ ርገንለት ውለታ ቢኖረን ውጤቱ መልካም የሆነ



በክፉ ፈንታ መልካም ካደረግንለት ሊያደርግብን ያሰበውን ወይም የሚያደር ግብንን ክፉ ነገር ሁሉ ይተወዋል ማለት ነው፡፡ እንግዲህ እንደዚህ ብናደርግ ግለሰቡን ከክፉ ሥራ አዳንነው ማለት ነው፡፡ ክፉውን በበጐ አሸነፍነው ማለት ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ በማስመልከት ሐዋርያው ጳውሎስ የሚከተለውን አዲሱን የወንጌል ሥነ ምግባር መመሪያ ሰጥቶናል፡-

> “ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉውን አትመልሱ፤ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆ ነውን አስቡ፡፡ ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ፡፡ ተወዳጆች ሆይ፣ ራሳችሁ አትበቀሉ፣ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፤ በቀል የእኔ ነው፣ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፏልና፡፡ ጠላትህ ግን ቢራብ አብላው፤ ቢጠማ አጠጣው ይህን በማድረግህ በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከምራለህና፡፡ ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ” (ሮሜ. 12፥17-21)፡፡

6 “ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህን ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል፡፡ <u>እኔ ግን እላችኋለሁ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ</u>” በማለት ጌታችን ስሙ ይክበር ይመስገንና የሕግ ሁሉ መፈጸሚያ የሆነውን ሰብአዊነትና ሰላም የሞላበትን እውነተኛና የተቀደሰውን የፍቅር ሕግ ሰጥቶናል፡፡ ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የሚል በሕገ ኦሪት ይገኛል (ዘሌ.19፥18)፡፡ “ጠላትህን ጥላ” የሚለው ግን በኦሪት ተጽፎ ባይገኝም ሰዎች በዘልማድ የሚሠሩበት ሕግ ነበር፡፡ ዛሬም ከሕገ ወንጌል ውጭ የሆኑ ሁሉ በዘልማድ ሲሠሩበት ይታያል፡፡ በሕግ ያልተጻፈ የእግዚአብሔርን ቃል የሚሽር ሌላም ሰው ሠራሽ ወግ እና ሥርዓት በጌታ ዘመን እንደነበረ ይታወቃል (ማቴ.15፥10-20)፡፡ ይህንንና የመሳሰሉትን ከመጽሐፍ ያልተገኙ ሰው ሰውኛ ሥርዓት የሚያራምዱትና የሚያስፋፉት ጸሐፍት ፈሪሳውያን ነበሩ፡፡ እነርሱ “ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ”፡፡ ጌታ ግን ሥራቸውን ሁሉ ተቃውሟቸዋል (ማቴ.23)፡፡ ዛሬም በባሕላችንና በዘመኑ ኅብረተሰብ ውስጥ ቀጥተኛውን የሃይማኖታችንንና የሥነ ምግባራችንን ሕግና ሥርዓት የሚያፋልሱትንና ሕገ ወንጌልን የሚተላለፉትን መቃወምና መቋቋም ክርስቲያናዊ ግዴታችን ነው፡፡

ጌታችን “ጠላቶቻችሁን ውደዱ” ብሎ ሲያዘን ጠላቶቻችን እነማን እን ደሆኑ ለይተን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ፀረ እውነት፣ ፀረ አምላክ የሆነውን እኩይ ነገር ሁሉ ውደዱ ማለት አይደለም፡፡ ጥንተ ጠላታችንን ሰይጣንንና ሠራዊቱን ወይም ገንዘብና ጣዖትን ሁሉ እንድንወድ አልታዘዝንም፡፡ ኃጢአተኞችን መው ደድ እንዳለብን ብናውቅም ኃጢአታቸውንና በደላቸውን ሳይሆን ሰዎቹን ስለምን ወድ ከኃጢአታቸው እስኪለዩ ድረስ ለእነርሱ አስፈላጊውን በጐ ሥራ ሁሉ ከመሥራት አንቆጠብም፡፡ ክፉ የሚያደርግብንን ጠላታችንን የምንወደው ክፋ ቱን ሳይሆን ሰውዬውን መሆኑን አንርሳ፡፡ እንግዲህ መልካም ነገር የምናደርግ ላቸው ጠላቶቻችን እነማን ናቸው?

የጠላት እኮ ዓይነት አለው፣ በሆነ ባልሆነው የሚረግሙን ጠላ ቶች አሉ፤ እነርሱን መልሰን መርገም ሳይሆን መመረቅ ይገባናል፡፡ እንዲሁ ከመሬት ተነሥተው የሚጠሉን ጠላቶች አሉ፤ ጥላቻቸውን ቢያነሡልንም ባያ ነሡልንም ለእነርሱ የሚገባውን መልካም ነገር ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡ በሃይማኖትም ሆነ ወይም በሌላ ምክንያት የሚያሳድዱን ጠላቶች አሉ፤ ስለ እነርሱ መጸለይ አለብን፡፡ ሳናውቀውም ሆነ ወይም በሌላ ምክንያት ተገፋፍተን ራሳችን ለራሳችን ጠላት የምንሆንበት ጊዜ ስላለ ከእንደዚህ ዓይነቱ ፈተና እኛም ለራሳችን መጸለይ ይገባናል፡፡ ጠላትንና ወዳጅን ሳንለይ ለሁሉ ሰው መልካም ካደረግን ለክፉዎችና ለደጐች፣ ለጻድቃንና ለኃጢአተኞች ፀሐዩን የሚያወጣ ላቸው፣ ዝናቡን የሚያዘንብላቸው የሰማዩ አባታችንን እንመስላለን፣ የእርሱም ልጆች እንባላለን፡፡ በጥንተ ተፈጥሮ በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠሩ ልጆች በበደላቸው የጠፉት ጸጋ በክርስቶስ ስለ ተመለሰላቸውና በእርሱም አዲስ

www.ethiopianorthodox.org

ፍጥረት ስለሆኑ እርስ በእርሳቸው በፍጹም ፍቅር ስለሚዋደዱ ፈጣሪያቸው ይመስሉታል፡፡ ፍጹም ፍቅር ያለው እግዚአብሔርን ይመስላል፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍቅር ነውና (1ኛ ዮሐ.4፥8)፡፡ ፍቅር ከሌለን ምን ዋጋ አለን የሚወዱንን ብቻ የምንወድ ከሆንን ሰላምታችንም ከወንድሞቻችን ጋር ብቻ ከሆ ነ ክርስቲያን ካልሆኑ ወገኖች፥ ሕገ ወንጌልን ከማያውቁ ሰዎች በምን እ በልጣለን? እንግዲህ የሰማዩ አባታችን ፍጹም እንደሆነ እኛም ፍጹማን እንድ ሆን ያዘዘን አምላክ፥ ሰውን ሁሉ በመውደድ ይልቁንም ጠላቶቻችን በመውደድ ወደ ተቀደሰውና ወደ ፍጹሙ የወንጌል ሕግ እንድንደርስ እርሱ በጸጋው ይርዳን፡፡

## መ) ክርስቲያናዊ ሕይወት በጾም፥ በጸሎትና በምጽዋት

ምጽዋት፥ ጸሎትና ጾም ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን አስፈላጊ ስለሆኑ ጌታችን በቃለ ወንጌሉ አጽንቷቸዋል፡፡ እነዚህ የአምልኮት መግለጫዎች፥ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ሥራዎች ከዘመነ ብሉይ ጀምሮ የነበሩ ናቸው፡፡ በጌታ ዘመን የነበሩ ጸሐፍት ፈሪሳውያን ግን እነዚህ ሦስቱን ምግባራት አላ ግባብ በመጠቀማቸው ከእውነተኛውና ከመንፈሳዊው ዓላማ ውጭ ሆነው ነበር፡፡ ስለዚህ ጌታ ጸሐፍት ፈሪሳውያን በሰዎች ዘንድ እንዲመሰገኑ በየመንገዱና በየአደባባዩ ለታይታ የሚያደርጉትን ሁሉ በመንቀፍ ለሦስቱም የተለየ አዳዲስ የአፈጻጸም ሥርዓት ሠርቶላቸዋል፡፡ ጌታ ሦስቱም ለክርስቲያናዊ ሕይወ ታችን አስፈላጊ ስለሆኑ አንዳቸውንም ሳያስቀር እንዴት መፈጸም እንዳለብን ለእያንዳንዱ መመሪያ መስጠቱ እየታወቀ ታዲያ ለምንድን ነው አንዳንድ ወገኖች የጾምን ጉዳይ ገሸሽ በማድረግ በሩቅ የሚመለከቱት? ከወንጌል ሥርዓ ት ውጭ እንደሆነ የሚገምቱት? ጌታ እንደ ግብዞች አትጹሙ አትጸልዩ ማለቱ ጾም ጸሎትን መንቀፉ ሳይሆን የእነርሱን የአፈጻጸም ሥርዓት ብቻ መቃወሙ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ እንግዲህ ይህን አውቀን ጌታ በመሠረተልን የአፈጻጸም ሥርዓት እየተመራን ጾም ጸሎትንና ምጽዋትን በተገቢው መንገድ ለማድረግ እንትጋ፡፡ ሥራችንም ዋጋ እንዲኖረው ከሰው ምስጋናን ለመቀበል ሳይሆን በስ ውር ለሚያየን ሰማያዊ አባታችን ስንል እነዚህ ሦስቱን ምጽዋት፥ ጸሎትንና ጾምን እንድንፈጽማቸው ጌታችን በወንጌሉ አስተምሮናል (ማቴ.6፥1-18)፡፡

### 1. ምጽዋት ስለ ማድረግ

ምጽዋት በሕገ ወንጌል ማለት በሕገ ተፋቅሮ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ፍቅር ለራሴ ብቻ ብሎ የሚያስቀረው ነገር የለም፡፡ ሕገ ተፋቅሮ አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን ተካፍሎ መኖርን ያመለክታል፡፡ ይህም ገንዘብና ንብ ረትን ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡ ሀብት ሲባል ከእግዚአብሔር የተሰጠንን ማናቸውንም ስጦታና ችሎታ ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ሰዎችን ሁሉ እንደራስ በመ ውደድ ላጡት ወገኖቻችን ከአለን ነገር ሁሉ ማካፈል ምጽዋት ነው፡፡ እንደ እኔ ይርባቸዋል ይጠማቸዋል ብሎ በማሰብ ለውዳሴ ከንቱ ሳይሆን ለእግዚአ ብሔር ብሎ ከዚህ ከአላፊው ገንዘብ ላይ አንሥቶ ለነዳያን መስጠት እውነተኛ ምጽዋት ይባላል፡፡

ከእግዚአብሔር የተሰጠን ከገንዘብ ሌላ ብዙ ዓይነት ስጦታዎች አሉ፤ ለምሳሌ እውቀትና ሙያ ያላቸው በማስተማር፥ በምክር፥ በሕክምናና በተ መሳሳይ ሥራዎች እንዲሁም ጉልበት ያላቸው በጉልበታቸው ተሠማርተው አገ ልግሎታቸውን ለሚፈልጉት ሁሉ ማበርከት ምጽዋት ማድረግ ነው፡፡ ይኸንን ሁሉ ስናደርግ ጌታችን በሰጠን መመሪያ መሠረት ከሰዎች ምስጋናን በመሻት ሳይሆን በስውር የሚያየንን እግዚአብሔር አባታችንን አምነን ከፈጸም ነው ዋጋችን በመንግሥተ ሰማያት ከፍ ያለ ይሆናል፡፡ የገንዘብም ሆነ የአ



ገልግሎት ርዳታ በምናደርግበት ጊዜ ችግረኞቹ ብቻ እንዲረዱ ለማድረግ ብናስብም ምጽዋቱን በምሥጢር ለመፈጸም ብንሞክርም አንዳንድ ጊዜ ከሰዎች እይታ ውጭ ሊሆን የማይችልበት አጋጣሚ አለ፡፡ ስለዚህ ያዩት ላላዩት በማውራት የበጐ አድራጊው ዝና በብዙዎች ዘንድ ታውቆ ውዳሴ ከንቱን ያስከትላል በማለት ምጽዋትን ማቋረጥ አይገባም፡፡ ምክንያቱም የበጐ አድራጊው ልቡና ውዳሴ ከንቱን በመሻት ሳይሆን ችግረኞች ወገኖቹን በማፍቀር ያደረገው ችሮታ ስለሆነ ነው፡፡ በጐ አድራጊው ውዳሴ ከንቱን ወዶትና ፈልጉት የመጣ ሳይሆን በአጋጣሚ የተፈጸመ ሁኔታ መሆኑን በስውር የሚያየው ሰማያዊ አባቱ አሳቡን ስለሚያውቅ ዋጋውን ያበዛለታል እንጂ አያሳንሰውም፡፡

በስውር ከሚፈጸመው ምጽዋት ሌላ በቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ የገን ዘብና የአገልግሎት እርዳታዎች አሉ፡፡ ከነዚህም አንዳንዶቹ በስውር ሳይሆን በይፋ የሚፈጸሙ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ለበጐ ሥራ አብነት የሚሆኑ ምእመናን መኖራቸው ለኅብረተሰቡም ሆነ ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነቱ ከፍ ያለ ነው፡፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን በስውር የሚደረገውንም ምጽዋት ሆነ ሌሎችንም የአ ስተዋጽኦና የበጐ አድራጐት አገልግሎት ሁሉ በአግባቡ እንዲፈጸም ታሳስባለች፡፡ ቁም ነገሩ ምጽዋታችን እግዚአብሔርንና ሰውን በማፍቀር እንጂ ለታይታና ለውዳሴ ከንቱ እንዳይሆን መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡ ይህን ካደረግን በስውር የሚያየን የሰማዩ አባታችን በግልጥ ይሰጠናል፡፡ የማያልፈውንና በዋጋ የማይተ መነውን ሀብት በመንግሥተ ሰማያት በመላእክቱና በቅዱሳኑ ፊት ያበዛልናል፡፡ (በተጨማሪ በዚህ ምዕራፍ በፊደል (ሠ) ቁጥር 3 ተመልከት)

### 2. ስለ ጸሎት

ጌታችን እንዴት መጸለይ እንደሚገባን የአፈጻጸሙን ሥርዓት አስተም ሮናል፡፡ ከዚህም ጋር የጸሎቱን ዓይነትና ይዘት ገልጾልናል (ማቴ.6፥5-15)፡፡ በሌላም ቦታ እንደምናገኘው ጸሎትን በተመለከተ ጌታ በታሪክና በምሳሌ አስረ ድቶናል፤ ራሱ በመጸለይም አብነት ሆኖናል፤ መመሪያውንም ሰጥቶናል፡፡

በመጀመሪያ ጌታችን ጸሎት ምን ማለት እንደሆነ ሳይገልጽ እንዴት መጸለይ እንዳለብን አስተምሮናል፡፡ እኛም የእርሱን ቃል ተከትለን ጸሎትን እንዴት መፈጸም እንደሚገባን በምናደርገው ጥረት ጸሎት ምን ማለት እንደሆ ነ በተግባር የበለጠ እንድንገነዘበው አስችሎናል፡፡ ከሁሉ በፊት ጌታችን የግብዞ ችን ጸሎት አፈጻጸም የነቀፈው የሰዎችን ምስጋና በመሻት ከመካነ ጸሎት ውጭ በየመንገዱና በየአደባባዩ በመከናወኑ ነው፡፡ ይህም ዓይነት ጸሎት በእግዚአ ብሔር ዘንድ ዋጋ የለውም፤ ዓላማውንም ስቷል፡፡ የእውነተኛ ጸሎት አፈጻጸም ግን በስውር ለሚያየን የሰማዩ አባታችን ብቻ እንዲሆን ጌታችን አስተምሮናል፡፡ በቤተ ክርስቲያን በአፀደ መቅደሱ ከምንፈጽመው ጸሎት በቀር ቤታችንን ዘግተን ወይም በስውር ቦታ ሆነን ሕዋሳታችንን ሰብስበን በሰቂለ ኅሊና በነቂሃ ልቡና ለእግዚአብሔር አምላክ ብቻ ጸሎታችንን እንድናቀርብ በወንጌል የታዘዘ ነው፡፡ እንግዲህ እውነተኛ ጸሎት ማለት ሰው እግዚአብሔርን በማመንና በመፍራት፥ በመውደድና ተስፋ በማድረግ ፥ ፈቃዱን በመፈለግና ደስ የሚሰኝ በትንም በመሻት በፍጹም ልቡናው ወደ ሰማያዊ አባቱ በመንፈስ ቀርቦና ተገናኝቶ ምስጋናውን፥ ንስሐውንና ልመናውን የሚገልጽበት በአጸፋውም ከእግዚአብሔር ጸጋና መጽናናትን የሚያገኝበት ታላቅ የአምልኮት መፈጸሚያ የፍጡርና የፈጣሪ መገናኛ ጊዜ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የክርስቲያን ጸሎት የአ ... ያለውና ግንኙነቱም በአዲስ ቃል ኪዳን የጸና መሆኑን

www.ethiopianorthodox.org

እያሰብን በመንፈስ ቅዱስ ተመርተን መጸለይ ይኖርብናል፡፡ የሚወደን አምላ ችንና አባታችን እንደመሆኑ መጠን እርሱን የሚያስደስተውን ነገር አውቀ ፈቃዱን ለመፈጸም በታዛዥነት መቅረብ ይጠበቅብናል፡፡ ስለዚህም ሁልጊዜ በጸሎታችንና በልመናችን ውስጥ ፈቃድህ ይሁን ማለትን እንርሳ፡፡

## አምላክን "አባታችን" ለማለት ማን መብት ሰጠን?

ከእግዚአብሔር አምላካችን ከሰማዩ አባታችን የጸጋ ልጅነትን ያገኘነው በክርስቶስ ሰው መሆን ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ መሆኑን ላመኑትና ለተቀበሉት ሁሉ የልጅነት መብት ተሰጥቷቸዋል (ዮሐ.1፥12)፡፡ በክርስቶስ አምነው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቁ ሁሉ የሥላሴ ልጅነት አግኝተዋል፡፡ በምሥጢረ ጥምቀት ባገኙት አዲስ ልደት እግዚአብሔርን አባት ብለው የሚጠሩበት የልጅነት መንፈስ ሰላቸው ግንኙነታቸው እንደ አባትና ልጅ ነው (ሮሜ.8፥15)፡፡ ስለሆነም በጸሎት ጊዜ ልባቸው እግዚአብሔርን "አባታችን ሆይ" እያሉ ያመሰግኑታል፥ ይለምኑታል፡፡ ነገር ግን ማንም ሊጠራውና ሊቀርበው የማይቻለውን ኃያል አምላክ በራሳቸው መብትና በራሳቸው ስም እግዚአብሔር አምላክን "አባታችን" ብለው በመጥራት ወደ እርሱ ሊቀርቡና ሊጸልዩ ስለማይችሉ ጌታ በራሱ ሥልጣን በራሱ ስም ችሎታውንና ፈቃዱን በመስጠት በእርሱም ልመናቸውን እንዲያገኙ ደስታቸውም "ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ" (ዮሐ.16፥23-24) ብሎ ባስተማራቸው መሠረት ሐዋርያት ጸሎታቸውን ለኢየሱስ ክርስቶስ አባት ለእግዚአብሔር አብ በማቅረብ በአሐዱ ወልድከ፥ በፍቁር ወልድከ በቅንዉ ወልድከ ወይም በስቁል ወልድከ... በማለት ይለምኑት ነበር (1ዮሐ.5፥14-15 ትርጓሜውን ተመልከት)፡፡ "ዘቦቱ ለከ" በእርሱ (በወልድ) ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ (ለአብ) ይገባል፤ ከእርሱ (ከወልድ) ጋር ከመንፈስ ቅዱስም ጋር ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ፤ አሜን፡፡ የሚለው ቃለ ጸሎት በቤተ ክርስቲያናችን የተለመደ ነው፡፡ "ወንጼውአከ በከመ መሀረነ ቅዱስ ወልድከ እንዘ ይብል አንትሙሰ ሶበ ትጼልዩ ከመዝ በሉ፡- አቡነ ዘበሰማያት..." (የዘወትር ጸሎት ማቴ.6፥9-15)፡፡

## ለእውነተኛ ጸሎት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

ሥርዓተ ጸሎቱን ማወቅ ብቻውን ለጸሎታችን ሥምረት አይሰጠውም፤ የልቡናችን ሁኔታ ወሳኝ ነገር ነው፡፡ የእውነተኛ ጸሎት መነሻው ልብ ነው እንጂ አፍ አይደለም፡፡ ልብ በሌላ አሳብ ተይዞ አፍ ብቻውን ቢያነበንብ ጸሎቱ ዋጋ የለውም፡፡ እንደዚሁም በልቡናው የትዕቢትና የመመጻደቅ አሳብ ካለ እንደ ፈሪሳዊው ጸሎት ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ እርሱ በሳምንት ሁለት ጊዜ እንደሚጸምና አሥራት እንደሚያወጣ፥ የሠራውን የጽድቅ ሥራ ሁሉ እየዘረዘረ ለእግዚአብሔር ካቀረበ በኋላ እንደ ኃጢአተኞች ሰዎች ይልቁንም እንደዚህ ቀራጭ ያላደረግኸኝ አመሰግንሃለሁ እያለ በትዕቢት መንፈስ በመጸለዩ ጌታ ነቅፎታል፡፡ በአንጻሩ ቀራጩ ደግሞ በቅን ልቡና በትሑት ሰብእና ራሱን ዝቅ በማድረግ በንስሐ መንፈስ "አምላኬ ሆይ! እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ!" እያለ በመጸለዩ ተመስግኗል (ሉቃ.18፥9-14)፡፡ የክርስቲያን ጸሎት መሠረት ትሕትናና ተአምኖ ኃጣውእ ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ይቅርታና ምሕረት የመዳናችንንም ጸጋ የምናገኘው በእንዲህ ዓይነት ልቡና ወደ ክርስቶስ በመቅረብ መሆኑን አንርሳ፡፡ እንግዲህ ክርስቲያናዊ ሕይወታችንን በመንፈሳዊ ነገር የበለጸገ እንዲሆን የእምነትና የጸሎት ተጋድሎ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ አጥብቆ መጸለይና (ሉቃ.11፥5-13) ሳይሰለቹ ዘወትር መጸለይ (ሉቃ.18፥1-8)



እንዲገባ ጌታ በምሳሌ አስተምሮናል፡፡ ይልቁንም ወደ ፈተና እንዳንገባ ተግተን እንጸልይ፤ መንፈስ ዝግጁ ነው፤ ሥጋ ግን ደካማ ነውና (ማቴ.26፥41)፡፡

## የእውነተኛው ጸሎት ዓይነትና ይዘት

ጌታ እንዴት፥ ለምንና ለማን እንደምንጸልይ ብቻ ያስተማረን ሳይሆን ምን መጸለይ እንዳለብን እውነተኛውን የጸሎት ዓይነትና ይዘት ገልጾልናል፡፡ ይህንንም ያደረገው ጸሎታችን እንደ አረማውያን ጸሎት እንዳይሆን ነው፡፡ እነርሱ ከንቱ ቃል በመደጋገም የሚለፈልፉና በድግምታቸውም ብዛት እግዚአብሔር የሚሰማቸው ይመስላቸዋል፤ "ስለዚህ አትምሰሏቸው፤ ሳትለምኑት አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃልና፡፡ እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ" በማለት ጌታ የአቡነ ዘበሰማያት ጸሎትን ሰጥቶናል (ማቴ.6፥7-15)፡፡

## አባታችን ሆይ! በሰማያት የምትኖር

(1) ስምህ ይቀደስ
(2) መንግሥትህ ትምጣ
(3) ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን
(4) የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን
(5) በደላችንንም ይቅር በለን እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል
(6) አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን
(7) ከክፉው ሁሉ አድነን እንጂ
መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልና ምስጋና ለዘላለሙ፤ አሜን፡፡

ከላይ በጸሎቱ የተጠቀሱት የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ቃለ ጸሎት ስብሐተ እግዚአብሔርን ያመለክታሉ፤ የተቀሩት አራቱ ደግሞ የእኛን የክርስቲያኖችን የዕለት በዕለት መንፈሳዊና ሥጋዊ ኑሯችንን በማስመልከት በተለይም ክርስቲያናዊ ሕይወታችን በሰማዩ አባታችን ፊት በትክክል ሆኖ እንዲገኝና በመንፈሳዊ ዓላማውም እንዲጸና ለማድረግ የቀረበ ቃለ ጸሎት ነው፡፡ ሰባቱም ቃለ ጸሎት የወንጌልን ምሥጢር በአጭሩ አካተው የያዙ ስለሆኑ እያንዳንዱን ቃል በስፋትና በጥልቀት በማስተዋል ከዕለት በዕለት ኑሯችን ጋር አገናዝበን በተግባር እንድንተረጉመውና በስውር ለሚያየን ለሰማዩ አባታችን ከልብ በመነጨ እምነትና ትኅትና ጸሎታችንን ማቅረብ ይኖርብናል፡፡ እርሱም ከእኛ የበለጠ እኛን ስለሚያውቀን ለእኛ የሚያስፈልገውንና የሚበጀውን ነገር ብቻ መርጦ በግልጥ ይሰጠናል፡፡ ምድራዊ አባት ለሕፃን ልጁ የለመነውን ሁሉ አይሰጠውም፤ በመጀመሪያ ለሕፃን የሚያስፈልገውንና የሚጠቅመውን ብቻ ይሰጠዋል፤ ከዚያም ሕፃኑ ከፍ ሲል እንደ ደረሰበት የእድሜና የእውቀት ደረጃ እያየ እንደ ሁኔታውና እንደ ጊዜው ሊሰጠውና ሊያደርግለት ያሰበውን ሁሉ በቅድሚያ እንደሚያዘጋጅለት እንዲሁም የሰማይ አባታችን ለእኛ ከምድራዊ አባት የበለጠውን ነገር ሊሰጠንና ሊያደርግልን በቅድሚያ አዘጋጅቶልናልና በትዕግሥት እንጠብቀው፡፡ ከስጦታው ይልቅ ሰጪውን እንውደደው፤ "ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነ እንዲሁም በምድር ይሁን" የተባለውን ቃለ ጸሎት ከልባችን እና ኑረው በአፋችንም እንናገረው፡፡

ከላይ በአቡነ ዘበሰማያት ጸሎት ላይ የተጠቀሰው አምስተኛውን ቃል በጽሞና የተመለከቱ ብዙ ሰዎች ይህን ቃል በተግባር ለመፈጸም አዳጋች መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ምክንያቱም ጌታችን ይቅርታን የምናገኝበትን ሁኔታ በገደብ ስለሰጠን ነው፤ "ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ፥ የሰማይ አባታችሁ [illegible] ይላችኋልና፤ ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር

www.ethiopianorthodox.org

ባትሉ፥ አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም (ማቴ.6፥14-15) ... ለት ጌታችን ተናግሯል፡፡ ይህ ኃይለ ቃል በአምስተኛው አንቀጸ ብፁ... "የሚምሩ ብፁዓን ናቸው ይማራሉና" ከሚለው ጋር ይተባበራል (ማቴ.5፥... (ይቅርታ ስለማድረግ ጌታችን በምሳሌ ያስተማረውን በማቴዎስ ወንጌል ምዕ... 18 ከቁጥር 21 እስከ መጨረሻው ተመልከት)፡፡

ስለዚህ እግዚአብሔር አባት በደላችንን ይቅር ብሎ ምሕረትን ... ሰጠን እኛ ለበደሉን ሰዎች ይቅርታ ካደረግን በኋላ ስለሆነ እንግዲህ ለ... ነታችን ስንል ራሳችንን አዘጋጅተን ይሉኝታና አሉባልታን ትተን ያለ ፍርሃ... የጌታን የፍቅርና የምሕረትን መመሪያ ለመፈጸም እንትጋ፡፡ አለበለዚ... ምሕረትንና መዳንን አናገኝም፡፡ ከምሕረት ጋር ከፍቅር ሥራ ጋር ካል... ን በቀር ከኃጢአት መዳን በእምነት ብቻ አይገኝም፡፡ ስለዚህ ነው ሐዋርያ... ቅዱስ ጳውሎስ "በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ፥ በፍቅር የሚሠራ እምነት" ... ደሚጠቅመን የተናገረው (ገላ.5፥6)፡፡ ይኸው ሐዋርያ መዳናችንን በተመለከ... ሲናገር፦ "በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤ ስለ በጐ ፈቃ... መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና" ... (ፊልጵ.2፥12-13)፡፡ እንግዲህ የደኅንነታችንን ሥራ በትጋት በመፈጸም የኃጢአ... ታችንን ሥርየት እንድናገኝ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር እያልን ወደ ሰማዩ አባ... ታችን ብንጸልይ የክርስቶስን ሃይማኖት ብቻ ፈላጊዎች ሳንሆን የጽድቁም ሥራ ተካፋይ በመሆናችን ጸሎታችን በተግባር የተፈተነ እውነተኝነቱ የተረጋገጠ ይሆናል፡፡

## የእውነተኛው ጸሎት ምሥጢር

እንግዲህ የሚጸልይ ሁሉ ወደ ክርስቶስ ይመልከት፤ እርሱ የእው... ነተኛውን ጸሎት ምሥጢር ገልጦልናል፡፡ እንዴት፥ ለምን፥ ለማን፥ ምን እን... ደምንጸልይ በቃልም በተግባርም አብነት ሆኖናል፡፡ ስለዚህ በምንጸልይበት ጊዜ የእርሱን የዋህነት፥ ርኅሩኅና ትኁት ልቡናውን እያሰብን እርሱን በእውነትና በመንፈስ መከተል አለብን፡፡ እርሱ እኛን እንደ ወደደና ይቅር እንዳለን እኛም ሰዎችን ከወደድንና ይቅር ካልን ጸሎታችን ይሠምራል፡፡ በክርስቶስ ስም መጸለይ ማለት ከክርስቶስ መንፈስ ባገኘነው ፍቅርና ርኅሩኅ ልቡና ሆነን በእር... ሱ መንፈስ ተቃኝተን ወደ ሰማያዊ አባታችን ስለ ራሳችንና ስለ ሌሎችም መጸለይ ማለት ነው፡፡ ይህም ብቻ አይደለም፤ በክርስቶስ ስም መጸለይ ማለት እሱ ለሰው ሲል ሰው ሆኖ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳን አፍርሶ ያስታረቀንና ያቀረበን እርሱ በመሆኑ በእርሱ መንፈስ እግዚአ... ብሔርን "አባታችን" ብለን ለመጥራትና ለመጸለይ መቻላችንን ያመለክታል፡፡ መዳናችንና መታረቃችን በእርሱ በኩል ብቻ ስለሆነ ያለ እርሱ ወደ እግዚአ... ብሔር መቅረብ አንችልም፡፡ እርሱ እንደ መምህርነቱ ለእኛ አብነት ለመሆን ጸልዮልናል፤ እንደ ሊቀ ካህናትነቱ ስለ እኛ ኃጢአት ጸልዮልናል፤ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ መሆኑ በእኛ ተገብቶ ጸልዮልናል፤ እንደ አምላክነቱ ደግሞ ዘወትር ጸሎታችንን ይቀበልልናል፡፡

የክርስቶስን ትምህርትና መመሪያ ተከትለን፥ በእርሱ አምነንና ተማፅነን፥ በስሙ ለሰማይ አባታችን ሳንመጻደቅና ሳንሰለች ዘወትር ምስጋናችንና ልመናችንን በአግባቡ ካቀረብን ጸሎታችን ያለዋጋ አይቀርም፡፡ በእንደዚህ ዓይ... ነት ሁኔታ በስሙ ወደ እግዚአብሔር አብ እንድንጸልይ ያስተማረን ጌታ አምላ...



...ችን ክርስቶስ እንደ ፈቃዱ ሆነን ከተገኘን ጸሎታችንን ተቀብሎ ይፈ... ...ምልናል፡፡ "በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ፡፡ ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ" በማለት በማይሻር ቃሉ በእርሱ ያለንን ተስፋ አጽንቶልናል (ዮሐ.14፥13-14)፡፡ ስለዚህም ጌታችን ለጸሎታችንም ...ን ለሌሎች መንፈሳዊ ተጋድሏችን የሚረዳንንና የሚያስፈልገንን "የተስፋውን መንፈስ መንፈስ ቅዱስን" ይሰጠናል፤ "እርሱም የርስታችን (የመንግሥተ ሰማያት) መያዣ (ዐረቦን) ነው" (ኤፌ.1፥13-14)፡፡ ከመልካም ስጦታዎች ሁሉ የላቀውን "በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው?" በማለት ጌታችን አስረድቶናል (ሉቃ.11፥13)፡፡

እንግዲህ የእውነተኛው ጸሎት ምሥጢር በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድነትና ሦስትነት ማለት በምሥጢረ ሥላሴና በምሥጢረ ሥጋዌ ላይ በእምነት ተመሥርቶ የእግዚአብሔር ፍቅርንና የማዳን ሥራውን የወደፊት ተስፋውንም ሁሉ አገናዝቦ የያዘ ነው፡፡ እውነተኛው የጸሎት ምሥጢር የአዲ... ...ሱን ቃል ኪዳን ምሥጢር ተከትሎ በእግዚአብሔር አባትነትና በልጁ መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ይመራል፤ ወደ ምሥራቅ ይመለከታል፤ ሰማያዊውን ሥርዓት ...ጸሎት ይሳተፋል፡፡ ሥርዓተ ምድር ተሠርዓ በሥርዓተ ሰማይ እንደ ተባለ በሰ... ...ማያዊው ዙፋን ፊት እየሰገዱ "ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ" እያሉ ያለ ማቋረጥ በትጋት የሚያመሰግኑትን የሰማይ ሠራዊት እያሰብን እኛም ለሰማያዊ ዙፋን አምሳል በሆነችው በቅድስት ቤተ ክርስቲያን መቅደስ ፊት ለሥሉስ ቅዱስ ምስጋና ማቅረብ ይገባናል (ራእይ 4)፡፡ እኛን ለማዳን በዳዊት ከተማ የተወለደውን የዓለም መድኃኒት ክርስቶስን እያሰብን "ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ" እያልን ከመላእክት ጋር እናመ... ሰግነዋለን (ሉቃ.2፥11-14)፡፡

አልፋና ኦሜጋ "ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፥ ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ" የሚለው ክርስቶስ በሰማያዊው ዙፋንና በኪሩቤል መካከል "እንደ ታረደ በግ ቆሞ" ይታያል፡፡ ...ማንም ማን ያልቻለውን ሰማያዊ ምሥጢር ያለበትን የመጽሐፉን ማኅተም ሊፈታ ችሎታ ላለው ለእርሱ ሱራፌልና ኪሩቤል ይሰግዳሉ፡፡ "እያንዳንዳቸ... ...ውም በገናንና የቅዱሳን ጸሎት የሆነ እጣን የሞላበት የወርቅ ዕቃ" ይዘዋል፡፡ እንዲህም "እያሉ አዲስን ቅኔ ይዘምራሉ"፦

> "መጽሐፉን ትወስድ ዘንድ ማኅተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፥ ታርደሃልና በደምህም ለእግዚአብሔር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከሕዝብህም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግሥትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው በምድርም ላይ ይነግሣሉ፡፡

እልፍ አእላፋት መላእክት ደግሞ በታላቅ ድምፅ እንዲህ እያሉ ያመሰግ... ...ኑታል፦

> "የታረደው በግ ኃይልና ባለጠግነት ጥበብም ብርታትም ክብርም ምስጋናም በረከትም ሊቀበል ይገባዋል"፡፡

"በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእ... ...ነርሱም ውስጥ ያለ ሁሉ" እንዲህ እያሉ አመሰገኑ፦

> "በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋ... ...ኑ ላይ ለተቀመጠው፥ ለበጉም ይሁን"፡፡

"አራቱም እንስሶች ... አሉ፥ ሊቃናቱም ወድቀው ሰገዱ" (ራእይ 5፥6-...

www.ethiopianorthodox.org

## 3. ስለ ጾም

እንደ ምጽዋትና እንደ ጸሎት፥ ጾምም ለክርስቲያናዊ ሕይወት አስፈላጊ
ስለሆነ ጌታችን ክርስቲያኖች ሁሉ እንዴት በወንጌል ሥርዓት መጾም እን
ደሚገባቸው አስተምሯል (ማቴ.6፥16-18)፡፡ ከሌሎች መንፈሳዊ ሥራዎች
ለይቶ ጾምን ማጣጣል ሰው ሰውኛ አስተያየት እንጂ የጌታ ፈቃድ አይደለም፡፡
ጌታስ ለክርስቲያኖች ጾምን በቁም ነገር እንዲይዙትና ሲጾሙም ለሰው እን
ዲታዩ ብለው ሳይሆን በስውር ለሚያያቸው ለሰማያዊ አባታቸው መሆን እን
ደሚገባው በማለት የእውነተኛውን ጾም አፈጻጸም መመሪያ ሰጥቷቸዋል፡፡
በእርግጥ ጌታችን የግብዞችን ጾም ተቃውሟል፤ ይህም ማለት የፈሪሳውያንን
የጾም ዓይነትና ሥርዓት ማለት ነው እንጂ ጾምን ራሱን ተቃውሟል ማለት አይ
ደለም፡፡ ይህማ ቢሆን ኖሮ ጌታ ባልጾመም ነበር፡፡

ለምንድነው የጌታ ደቀ መዛሙርት እንደ ፈሪሳውያንና እንደ መጥምቁ
ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት የማይጾሙት? የሚለው ጥያቄ ጥንትም ሆነ ዛሬም አ
ለ፡፡ የእነርሱ ጾም በብሉይ ኪዳን ሥርዓት ላይ የተመሠረተ ስለሆነ በዓይነቱም፥
በዓላማውም፥ በይዘቱም በሥርዓቱም ከጌታ ጾም ጋር የተለየ ስለሆነ ነው፡፡
ከዚህም ሌላ ጊዜው ከብሉይ ወደ ሐዲስ ሥርዓት መሸጋገሪያ በመሆኑ የጌታ
ደቀ መዛሙርት አዲሱን የወንጌል ሥርዓት በመማር ላይ ነበሩ፤ መንፈስ ቅዱ
ስንም ገና አልተቀበሉም ነበር፡፡ በዚህም ላይ ሙሽራው ከእነርሱ ጋር የነበረበት
ጊዜ ስለሆነ ወቅቱ የደስታ እንጂ የኀዘንና የጾም ጊዜ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም
ለብዙ ዘመናት ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚመጣ ሲጠበቅ የነበረው መሲሕ
ክርስቶስ ሰው ሆኖ በደቀ መዛሙርት መካከል በመገኘቱ የደስታ ጊዜ ስለነበር
ነው፡፡ ስለዚህ ነው ጌታችን "ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎቹ ማዘን
ይገባቸዋልን? ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚለይበት ጊዜ ይመጣል፤ በዚያን
ጊዜ ይጾማሉ" በማለት ከላይ ለተገለጠው ጥያቄ መልስ የሰጠው (ማቴ.9፥14-
15)፡፡ እንግዲህ ለደቀ መዛሙርቱ እንዴት መጾም እንደሚገባቸው ያስተማረ
ጌታ የሚጾሙበትንም ጊዜ ለይቶ አስታውቋቸዋል፡፡

### ምግበ ሥጋና ምግበ ነፍስ

የጌታን ጾም ተከትለው ለሚጾሙ ሁሉ፥ ጥያቄና ፈተና አያ
ጣቸውም፡፡ አንተ ጾመኛ ክርስቲያን ሆይ! ለምንድነው የምትጾመው የምትራበ
ውና የምትጠማው? በጕተራህ እህል ሞልቶ በደጅህ ከብቱ ተሠማርቶ፥ ደግሞ
በጓዳህ እንጀራው ከመሶቡ፥ ወጡ ከድስቱ ወይን ጠጁ ከጋኑ ሞልቶ ተርፎ
እያለ ለምን ትጾማለህ? እግዚአብሔር ልዩ ልዩ መባልዕትን የሰጠን እኮ እየበላን
ና እየተደሰትን ለመኖር አይደለምን? የሚሉትና የመሳሰሉትን ጥያቄዎችና
ፈተናዎች እውነተኛውን ጾመኛ ክርስቲያን አያስጨንቀውም፡፡ ምክንያቱም ሰው
ለመብላትና ለመጠጣት ብቻ የተፈጠረ አይደለምና፡፡"ሰው ለመኖር (ብሎ)
ይበላል እንጂ ለመብላት (ብሎ) አይኖርም" የተባለውን አታስተውልምን! የሰው
ተፈጥሮ እኮ በሥጋ ባሕርይ ብቻ የሆነ አይደለም፡፡ በሰው ሥጋ ውስጥ
የማትሞት ነፍስ አለች፡፡ የምግብና የመጠጥ ዓይነቶች ለሥጋ እንጂ ለነፍስ አይ
ስማማትም ብዙ በመብላትና በመጠጣት ሥጋ እንጂ ነፍስን አያስደስታትም፡፡
በመጠኑ መብላትና መጠጣት ግን ለሥጋም ለነፍስም ይበጃል፡፡ ሁልጊዜ ሥጋ
መብላት ወይን ጠጅ መጠጣት እንኳን ነፍስን ሥጋን ከጉዳት ላይ ይጥለዋል፡፡
ስለዚህ ጾመኛው በመጠኑ የሚኖር፥ ሁሉን መጥኖ የሚያደርግ ስለሆነ የምግቡን
ም ዓይነትና ብዛት እየተቆጣጠረ ወቅቱን እየጠበቀ [illegible]



በሚስማማ ሁኔታ በመጠኑ እየተመገበ ክርስቲያናዊ ሕይወቱን በሥርዓት የሚመራ ነው፡፡ ይልቁንም ከምግብ ሰውነት፥ ከሰውነትም ነፍስ እንደምትበልጥ ስለሚያውቅ እንደ ጌታው ትእዛዝ በቅድሚያ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን ለመፈለግ የምትችለዋን አእምሮ ጠባይዕ ያላትን ሕያዊት ለባዊት ነባቢት የሆነችውን የነፍሱን ደኅንነት ከሁሉም አብልጦ ይፈልጋል፤ የነፍሱን ርሃብ የሚያስወግድለትን ምግበ ነፍስ ይፈልጋል፡፡ በምግበ ሥጋ ረክቶ ዝም ብሎ የሚኖር ሰው የነፍሱን መጕሳቆል አያስተውልም፡፡ ትክክለኛውን ምግበ ነፍስ እስካልተመገብን ድረስ ክርስቲያናዊ ሕይወት የለንም፡፡

እንግዲህ ያለ ምግበ ነፍስ ሰው በምግበ ሥጋ ብቻ ሊኖር አይችል ም፡፡ ምክንያቱም ሰው ከሁለት የተለያዩ ባሕርያት የተፈጠረ ስለሆነ ለሁለቱም የሚያስፈልጋቸው የምግብ ዓይነት መገኘት አለበት፡፡ አለበለዚያ ሥጋውን መግቦ ነፍሱን ያስራበ ሰው በዚህ ዓለም በነፍሱ የጕስቁልናና የቀቢጸ ተስፋ ኑሮ ያጋጥመዋል፤ በሚመጣውም ዓለም ነፍሱ ዘላለማዊ የደስታ ሕይወት አይ ኖራትም፡፡ ስለዚህ ነው ጌታችን ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም ከእግዚአ ብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በማለት የተናገረው (ማቴ.4፥4)፡፡ ጌታ ይህንን ስለ ምግበ ነፍስ ተናገረ፡፡ ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ሳይጠብቅ የሚወደውንና የሚያስጐመጀውን የምግብ ዓይነት በመብላት የዘላለም ደስታን ሊያገኝ አይችልም፡፡ ምናልባት ለጊዜው ደስታ ያገኘ ቢመስለው ውሎ አድ ሮ ሲያየው መሰልቸት፥ ጥላቻና በሽታ እያደረሰበት የደስታው ጊዜ ተለውጦ በኀዘንና በጸጸት ይተካል፡፡ አዳምና ሔዋን ምግበ ነፍስ ሆኖ በጸጋ ይጠብቃ ቸው የነበረውን የእግዚአብሔርን ቃልና ትእዛዝ ትተው ለሥጋዊ ባሕርያቸውና ኑሯቸው የሚስማማውን፥ለመብላት ያማረውን፥ ለዓይን የሚያስጐመጀውን፥ ለጥበብ መልካም የሆነውን (ዘፍ.3፥6) ምግበ ሥጋን በመምረጣቸው ጸጋቸውን ተገፍፈው የደስታቸውን ኑሮ አጥተው ከእነ ልጆቻቸው ጕስቋሎቹ ሆነው ኖሩ፡፡ በጊዜው ጊዜ መጥቶ አዳኛቸው ክርስቶስ የእነርሱን መጕምጀትና ጥጋብ በጾሙና በርሃቡ፥ የእነርሱን ሕግ መተላለፍ በሕግ ፈጻሚነቱ፥ የእነርሱን አለ መታዘዝ በመታዘዙ ያውም እስከ ሞት ድረስ በመታዘዙ (ሮሜ.5፥19፤ ፊልጵ.2፥8) በደሙ ክሶ አድኗቸዋል፤ ሁላችንንም አድኖናል፡፡ ምግበ ነፍስ የሚሆነንን የእግዚአብሔርን ቃል ሰጥቶናል፤ በጥጋብና ባለመታዘዝ ያጣነውንም ጸጋ መልሶልናል፡፡

### ጌታ በሥጋ ከመጣበት ምክንያቶች ሁለቱ

ጌታ ጾሞልናል መከራ መስቀሉን ተቀብሎልናል በማለት እኛ ከጾምና መስቀሉን ከመሸከም ወደ ኋላ የምንልበት ምክንያት የለንም፡፡ ክርስ ቶስ ለእኛ ሲል ሰው ሆኖ በመዋዕለ ሥጋዊው ያደረገውን ነገር ሁሉ ቢያንስ በሁለት መንገድ ልንረዳው ይገባናል፤ የመጀመሪያው እንደ ሰው ሆኖ ሕግን መፈጸሙ ሕማምና መከራን መቀበሉ፥ እንደ ሊቀ ካህናት መጸለዩ፥ እንደ እግዚአብሔር በግ መሠዋቱ ለሰው ልጆች መዳን ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ልንገ ነዘበው የሚገባን ደግሞ ጌታ መጠመቁ፥ መጾሙ፥ መራቡና መጠማቱ፥ መጸለዩ፥ ትዕግሥቱንና ትሕትናውን ፍቅሩንም ማሳየቱ፥ በጎ ሥራን መሥራቱ፥ የመሳሰለውን መልካም ነገር ሁሉ ማድረጉ ለእኛ አብነት ሊሆነንና እኛም እሱን በግብር እንድንመስለው እንጂ እርሱ ሁሉን ነገር ፈጽሞልናል ብለን እጅ እግራችንን አጣጥፈን ለመቀመጥ አይደለም፡፡ አብ እኔን እንደላከኝ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ በማለት ሐዋርያትን ወደ ዓለም ልኳቸዋል፡፡ ስለዚህም እሱን መስለው የእሱን አርአያ በመከተል ኑረዋል፤ ሠርተዋል፡፡ ሐዋርያ ጳውሎስም "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ" ብሏል (1ኛቆ [illegible] ሐዋርያትን፥ ከፍ ብለን ክርስቶስን ከምንመስልባቸው መንፈሳዊ ሥራዎች አንዱ ጾም አይደለምን? ሐዋርያው ጳውሎስስ [illegible]

www.ethiopianorthodox.org

መምን? በእርግጥ ጾሟል (የሐዋ.ሥራ.13፥2-3፤ 14፥23፤ 2ኛቆሮ. 11፥27)።

ከላይ የጠቀስነው ጾመኛ ክርስቲያን አብነት ያደረገው ጌታን ነው። ጌታ ሁሉ በእጁ ሁሉ በደጁ ሆኖ ሳለ እርሱ በፈቃዱ ጠመ፥ ተራበ፥ ተጠማ። ስለዚህም ፈታኙ ዳቦውን ድንጋይ አድርጎ ለምን እንደማይበላ ቢጠይቀው ሰው በእግዚአብሔር ቃል ሁሉ እንጂ በምግብ ብቻ እንደማይኖር ተጽፏል በማለት መልሶለታል (ማቴ.4፥1-4)። ዲያብሎስ ያመጣውን ፈተና ሁሉ ጌታ እንደ ተብሏል እንደዚህ ተጽፏል በማለት በተደጋጋሚ ከቅዱሳት መጻሕፍት ቃል እየጠቀሰ ለጥያቄው ሁሉ መልስ በመስጠት ፈታኙን ድል የነሣው እኛም የርሱ ፈለግ በመከተል ድል በማድረግ ዓለምን እንድናሸንፍ ነው። "በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዟችሁ፥ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ" ብሏል (ዮሐ.16፥33)። እንግዲህ በእግዚአብሔር መንፈስ የተጻፈው ሁሉ ለእኛ ትምህርትና ምክር እንዲሆነን የተጻፈ ስለሆነ (2ኛጢሞ.3፥16-17) ጌታ የ ሰውን ቃለ መጽሐፍ በመመልከት ስለ ጾም የተነገረውን እንማር፦

> " እግዚአብሔርም ለአባቶቻችሁ ወደ ማለላቸው ምድር ገብታችሁ እንድት ት፥ ዛሬ ለአንተ የማዝዘውን ትእዛዝ ሁሉ ታደርጉ ዘንድ ጠብቁ። አም እግዚአብሔር ይፈትንህ ዘንድ፥ በልብህም ያለውን ትእዛዙን ትጠብቅ ወይም ትጠብቅም እንደሆነ ያውቅ ዘንድ፥ ሊያስጨንቅህ በእነዚህ በአርባ ዓመ በምድረ በዳ የመራህን መንገድ ሁሉ አስብ። ሰውም ከእግዚአብሔር አ በሚወጣ ነገር ሁሉ በሕይወት እንዲኖር እንጂ ሰው በእንጀራ ብቻ በሕይ እንዳይኖር ያስታውቅህ ዘንድ አስጨነቀህ፥ አስራበህም፥ አንተም ያላ ኸውን አባቶችህም ያላወቁትን መና አበላህ" (ዘዳ.8፥1-3)።

## የአርባ ዓመት ጾም በበረሓ

የእሥራኤል ሕዝብ ወተትና ማር ያለባትን ምድረ ርስት እስኪወርሱ ድረስ ለአርባ ዓመት ሙሉ ዳቦና እንጀራ፥ ሥጋና የወይን ጠጅ በማያገኙበት በረሓ በነበሩበት ጊዜ የሚመገቡት መናና ውኃ ነበር። አንዳንዴም ሥጋ ለም ነው አግኝተዋል፤ በአንድ ወቅትም ሥጋው ለመቅሰፍት ሆኖባቸዋል (ዘኁ.11፥ 4-35) ሕዝቡ ገና ወደ በረሓው እንደገባ በሁለተኛ ወሩ የበረሓውን ኑሮ በመ ሰቀቅ "በሥጋው ምንቸት አጠገብ ተቀምጠን እንጀራ ስንበላ ስንጠግብ ሳለን በግብፅ ምድር በእግዚአብሔር እጅ ምነው በሞትን!" ብለው እስከ መማረር ደር ሰዋል (ዘጸ.16፥3)። የሰው ነገር አስቸጋሪ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር በችግር ከመኖር ጥሩ ምግብ በልቶና ጠግቦ ከእግዚአብሔር ውጭ በባርነት ምድር መኖርን መረጠ። ከእግዚአብሔር ይልቅ ለሆዱ መገዛትን የመረጠ ሆድ አም ላኩ ይባላል፤ እንዲህ ዓይነቱ ሰው እንኳን ሰማያዊ ምድራዊ ርስትን አያገኝም (ፊልጵ.3፥19-20፤ 1ኛቆሮ.10፥5፤ ዘኁ.11፥33-34)። እግዚአብሔር ግን በሥ ጋው ምትክ መና ከሰማይ አውርዶ ሲመግባቸው ቆየ። እነርሱ ግን ሥጋ በማ ጣታቸው በየጊዜው ያጉረመርሙ ነበር፤ የተመኙትን በልተውና ጠግበው መኖርን መርጠዋልና። ለሆዳቸውም ሲሉ ወደ ግብፅ ምድር ወደ ባርነት ቤት ለመመለስ ይፈልጉ ነበር።

> "በመካከላቸውም የነበሩ ልዩ ልዩ ሕዝብ እጅግ ጐመጁ፤ የእሥራኤል ልጆች ደግሞ ያለቅሱ ነበር፦ የምንበላውን ሥጋ ማን ይሰጠናል? በግብፅ ያለ ዋጋ እን በላው የነበረውን ዓሣ፥ ዱባውንም፥ በጢኹንም፥ ኩራቱንም፥ ቀዩንም ሽን ኩርት፥ ነጩንም ሽንኩርት እናስባለን፤ አሁን ግን ሰውነታችን ደረቀች፤ ዓይ ናችንም ከዚህ መና በቀር ምንም አታይም አሉ" (ዘኁ.11፥4-6)።

መና እንደ ሥጋ ከባድና ገምቢ የምግብ ዓይ ያለ አነስተኛ ነገር "በመሬት

www.ethiopianorthodox.org



መስል . . . እንደ ድንብላል ዘር ነጭ ነው፤ ጣዕሙም እንደ ማር ቂጣ " (ዘጸ. 16፥14 እና 31፤ዘኁ.11፥7-9)፤ የሚጠጣውም ወይን ጠጅ ሳይሆን ንጋይ የፈለቀ ውኃ ነበር። ሕዝበ እሥራኤል በአርባው ዘመን ይመገበው በረው እንደ ሥጋ ጥጋብን የሚያስከትል እንደ ወይን ጠጅ የሚያሰክር አል ረም። ስለዚህ ኑሯቸው የተመጠነ፤ የዕለት ምግባቸው በመስፈሪያ የተለካ እንደ ነበር ተጽፏል (ዘጸ. 16፥16-30)። ለምንድነው ጌታ እግዚአብሔር ለሥጋ ሚመችና በሚደላ ቦታ ሳይሆን ልምላሜ በሌለበት በበርሃ በትኅርምት እን ኖሩ ያስጨነቃቸውና ያስራባቸው? ለሚለው ጥያቄ መልሱ ከላይ በምንባቡ ስጥ ይገኛል። መልሱም በእግዚአብሔር ቃል እንጂ በእንጀራ ብቻ በሕይወት እንደማይኖር እሥራኤልን ለማስታወቅ አስርቦታል፤ የተለየ የምግብ ዓይነትም እንዲበላ ሰጥቶታል፤ የሚል ነው።

የዚህን መልስ እውነተኝነት የምናውቀው ከበስተ ኋላ የነበረውን የሕዝበ እሥራኤልን ታሪክ በመመርመር ይሆናል። ይህ ሕዝብ በምድረ ግብፅ በነበ ረበት ጊዜ ለዚህ ዓለም ገገርዎቻቸው በባርነት ማገልገልና መብላት ብቻ እንጂ የእግዚአብሔርን መንገድ የመንፈሳዊውን አኗኗር አያውቁትም። የጌቶቻቸውን እምነት በመከተል ሰው በእንጀራ ብቻ የሚኖር ይመስላቸው ነበር። እግዚአ ብሔር ግን ይህ እውነት እንዳልሆነ ለማስረዳት በግብፅ አገር ያገኙት የነበረው ፍርቶ እህል ውኃ በሌለበት በረሓ ወስዶ ሕጉንና ቃሉን እያስተማራቸው በትኅ ርምትና በመንፈሳዊ ሥነ ምግባር እንዲሠለጥኑ አድርጓቸዋል። እነርሱ ግን የግብፁ ኑሯቸው የዓለማዊ ሥራቸው ትዝ ትዝ እያላቸው ወደ ኋላቸው ለመመለስ ሲፈልጉ ጌታ እግዚአብሔር ደግሞ እየገሠጸ ሕጉንና ቃሉን እን ዲጠብቁ በሙሴ አማካይነት ያስተምራቸው ነበር። ሙሴ አርባ ቀን በተለየቸው ጊዜ የተነገራቸውን ሕግና ትእዛዝ ትተው ጣዖት አቁመው እየበሉ እየጠጡ ይዘፍኑ ነበር፤ ስለዚህም ብዙዎችን በሞት ቀጥቷቸዋል (ዘጸ.32፥28፤1ኛቆ ሮ.10፥6-7)። እግዚአብሔር ጣዖት ማምለክን ብቻ አይደለም የሚጠላው ያለማቋረጥ በመጐምጀት ሁልጊዜ እየበሉና እየጠጡ ተቀማጥለው የሚኖሩትን ም አይወድም፤ ምክንያቱም እነርሱ እንደ ባለጠጋው ነዌ ታሪክ በዚህ ዓለም ደስታ ብቻ ስለሚኖሩ ነው (ሉቃ.16፥19-31)። ስለዚህም ጌታችን "በመብልና በመጠጥ ብዛት በስካርም በመባከንም ስለ ዓለማዊ ኑሮ በመጨነቅ ልባችሁ እን ዳይዝል ተጠንቀቁ" በማለት የአዲስ ኪዳኑን ሕዝበ እግዚአብሔር በመጠኑና በልኩ እንዲኖሩ አዝዟቸዋል (ሉቃ.21፥34)[73]። በአርባው ዓመት የበረሃ ኑሯቸው መና ብቻ በመብላት ሰውነታቸው እንደ "ደረቀች" በማሰብና በመጨነቅ ሥጋ ለመብላት የጐመጁት ወገኖች በማጉረምረማቸው ለእሥራኤላውያን ሁሉ ታላቅ ፈተና ሆኖባቸው ነበር። ምንም እንኳ እንደ ልመናቸውም የሚበሉት ሥጋ ቢ ሰጣቸው "ሥጋውም ገና በጥርሳቸው መካከል ሳለ ሳያኝኩትም የእግዚአብሔር ቁጣ በሕዝቡ ላይ ነደደ፤ እግዚአብሔርም ሕዝቡን በታላቅ መቅሠፍት እጅግ መታ። የጐመጁ ሕዝብ በዚያ ተቀብረዋልና የዚያ ሥፍራ ስም የምኞት መቃብር ተብሎ ተጠራ" (ዘኁ.11፥4-34)። እነዚህ የጐመጁትን ሕዝብ እንዲህ እየገሠጸ ሕዝበ እሥራኤልን በሕይወት የሚያኖራቸውን የእግዚአብሔርን ቃል እየፈጸሙና መና እየተመገቡ ከእርሱ ጋር እንዲኖሩ የሚወዳቸው አምላካቸው በረድኤቱ አስችሏቸዋል።

የሕዝበ እስራኤል ሕይወትና ሥነ ምግባር ለሕዝበ ክርስቲያንም ትምህርትና መመሪያ ነው (1ኛቆሮ.1-13)። እነርሱ በታዘዙት መሠረት የእግዚአብሔርን ቃል ጠብቀው እንደሆነ እኛም እንደዚሁ መጠበቅ አለብን።

---

73 ... ተተረጐመውን መጽሐፍ ቅዱስ በተለይም የግዕዙን አዲስ ኪዳን

እነርሱ ምድረ ርስት እስኪገቡ ድረስ በመጠንና በልክ እየተመገቡ የኖሩ ነ እኛም እንደዚሁ ከሰማያዊ ርስታችን እስክንገባ ድረስ ከተወሰነልን ሳና በመጠኑና በልኩ መኖር ክርስቲያናዊ ግዴታችን ይሆናል፡፡ በመጠንና በል መኖር ሲባል ምን ማለት ነው? በመጠን መኖር ማለት ቃሉንና ሕጉን እየ በመጠኑና በልኩ እየበሉና እየጠጡ መኖር ነው፡፡ በልኩ መመገብ ማለትስ ማለት ነው? በልክ መመገብ ማለት እስራኤላውያን የዕለት በዕለት ምግባቸ "ጐሞር" በሚሉት መስፈሪያቸው እየለኩና እየቆነኑ እንደተመገቡ እንደ ከመለኪያው ከልኩ በላይ ሳያትረፈርፉና ሳይቀንሱ ለቁመተ ሥጋ የሚያስ ልገውን ያህል አዘጋጅቶ በመጠኑ መመገብ ነው (ዘጸ.16፥16-30)፡፡ እን ጾም ማለት ይህ ነው፤ ይህም ለክርስቲያኖች ጾም ምሳሌ ነው፡፡ ክርስቲያኖ ከምግብ ብቻ ሳይሆን የሚጾሙት ከሌላውም ነገር ሁሉ ጾመው ማለት ተቆጣ በልኩና በመጠኑ ተወስነው በእግዚአብሔር ቃል መኖራቸውን በክርስቲያና ሕይወታቸው መመስከር ይኖርባቸዋል፡፡

## እውነተኛ ጾም ከንስሐና ከበጎ አድራጎት ጋር

ጾም ከምግብ ብቻ መከልከል አይደለም የተባለው አነጋገር እን የሚታለፍ ሳይሆን በቁም ነገር የምንመለከተው ነው፡፡ ጾም ከዓይን አም ከሥጋ ምኞት ከዓለማዊ ነገሮች ሁሉ መከልከልን በጠቅላላው ዓለሙንና ስጡ ያሉትን ሁሉ ከመውደድና ለእነርሱም ከመገዛት ራሳችንን ነፃ የምና በትን መንገድ ያመለክተናል፡፡ በአጠቃላይ ጾም ማለት ራሳችንን ከምድራዊ ሮች ሁሉ የምንከላከልበትና የምንቆጣጠርበት፥ ልባችንን ለእግዚአብሔር ብቻ የምናስገዛበት፥ ለተራቡትና ለተቸገሩትም መልካም ነገርን የምናደርግ መንፈሳዊ መሣሪያ ነው፡፡ ክፉ እያደረጉ ጾም የለም፡፡ ጾማችን ከመልካም ጋር መሆን አለበት፡፡ በጐ ምግባር የጐደለው ጾም እውነተኛ ጾም አይባልም ስለዚህ ነው በዘመኑ የነበሩትን የክፉ ሰዎችን ጾም ነቢዩ ኢሳይያስ የተ መው፡፡ ነቢዩ የግፍ ሥራቸውን ተቃወመ እንጂ ጾም ጸሎትን አልተቃወመም እውነተኛው ጾም ከፍትሕና ከርትዕ ጋር ከሰብአዊ ርኅራኄ ጋር መሆን ዳለበት አስተምሯል (ኢሳ.58፥1-14)፡፡ በክርስቲያናዊ ሕይወታችን ዘመን ሥሐ የጾም ጸሎት ጊዜ እንዲኖረን ያስፈልጋል፡፡ ከዓመፅ ሥራችንና ከኃጢአ በንስሐ ተመልሰን እግዚአብሔርን በጾም ጸሎት ብንለምነው ይሰማናል፡፡

> "አሁንስ፥ ይላል እግዚአብሔር፥ በፍጹም ልባችሁ፥ በጾምም፥ በልቅሶና በዋይ ወደ እኔ ተመለሱ፡፡ ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ፥ ቁጣው የዘገየ፥ ምሕረቱም የበዛ፥ ለክፋት የተጸጸተ ነውና ወደ እርሱ ተመለሱ፡፡ . . . በጽዮን መለከትን ንፉ፥ ጾም ም ቀድሱ . . . የእግዚአብሔርም አገልጋዮች ካህናት እያለቀሱ፦ አቤ ለሕዝብህ ራራ . . . ይበሉ" ካለ በኋላ ነቢዩ ኢዩኤል "እግዚአብሔርም ስለ ምድሩ ቀና ፥ ለሕዝቡም ራራለት . . ." በማለት ይጽፋል (ኢዩ.2፥12-20)፡፡

እንግዲህ እንዲህ ዓይነቱን ጾም ነው እግዚአብሔር የሚፈልገው፡፡ ሕዝቡ በጾ በጸሎት ለንስሐ የሚገባ ፍሬ ካደረጉ ካህናቱም ስለ ራሳቸውና ስለሕዝቡ ሱባኤ ቢገቡ ምሕላ ቢይዙ ከእግዚአብሔር ይቅርታና ምሕረትን እናገኛለን፡፡ የእው ነተኛውን ጾም ጥቅም በዚህ ሁኔታ ልንረዳው ይገባል፡፡ እውነተኛው ጾም ከን ሥሐና ከጸሎት ጋር ይካሄዳል፡፡

እውነተኛው ጾም ሌላም ጥቅም አለው፡፡ ብዙ ከመብላትና ብዙ ከመጠጣት የማይቆጠብ ሰው ለብዙ ኃጢአት የተጋለጠ ነው፡፡ በአንጻሩ ደግሞ በንስሐ ውስጥ ሆኖ የሚጾምና የሚጸልይ ክርስቲያን ከብዙ ፈተናና ኃጢአት ይድናል፡፡ ለዚህም ነበር አንዱ ምክንያት እግዚአብሔር ሕዝቡን እሥራኤልን መናና ውኃ እየመገበ በልክና በመጠን እንዲኖሩ . . .



ክርስቲያኖች በእውነተኛው ጾም ተወስነን መኖር ይገባናል፡፡ ከእግዚአብሔር ቃድ ውጭ ክፉ ከተመኘን በእምቢተኞቹ እሥራኤላውያን ላይ የደረሰው ክፉ ነገር እንዳይመጣብን እንጠንቀቅ፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው፡

> "እሥራኤላውያን ክፉ ነገር እንደ ተመኙ እኛ ደግሞ እንዳንመኝ ይህ ምሳሌ ሆነልን፡፡ ሕዝቡም ሊበሉ ሊጠጡም ተቀመጡ ሊዘፍኑም ተነሡ ተብሎ እንደ ተጻፈ ከእነርሱ አንዳንዶቹ እንዳደረጉት ጣዖትን የምታመልኩ አትሁኑ፡፡ ከእነር ሱም አንዳንዶቹ እንደ ሴሰኑ በአንድ ቀንም ሁለት እልፍ ከሦስት ሺህ እንደ ወደቁ አንሴስን . . . ይህ ሁሉ እንደ ምሳሌ ሆነባቸው፥ እኛንም የዘመናት መጨረሻ የደረሰብንን ሊገሥጸን ተጻፈ፡፡ ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እን ዳይወድቅ ይጠንቀቅ" (1ኛቆሮ.10፥6-12)፡፡

"ነገ እንሞታለንና እንብላና እንጠጣ" የሚለው መመሪያ በክርስቲያኖች ዘንድ ቦታ የለውም (1ኛቆሮ.15፥32-34)፡፡ ይህ፥ ትንሣኤ ሙታንን የማያምኑ ወይም በቀቢጸ ተስፋ የሚኖሩ የዓለማዊ ሰዎች ፍልስፍና ነው፤ እኛ ግን በትን ሣኤ ሙታንንና በዘላለማዊ ሕይወት እናምናለን፡፡ በሞቱ ሞትን ደምስሶ በትን ሣኤው አዲስ ሕይወትን የሰጠንን ክርስቶስን እናምናለን፡፡ እርሱም ስለ እኛ ሲል በሕማሙና በሞቱ ጾዋትወ መከራን ተቀብሎ አድኖናል፡፡ ስለዚህም በመብላትና በመጠጣት ሳይሆን በጾምና በጸሎት ጌታ ለእኛ የተቀበለውን መከራ እያሰብን እናመሰግነዋለን፡፡ ይህም ሙሽራው ከደቀ መዛሙርቱ የሚለይበት ጊዜ ይመጣል፥ ያንጊዜ ይጾማሉ በተባለው መሠረት የሚደረግ ጾም ነው፡፡ ጊዜው ከጸሎተ ኀሙስ ማታ እስከ ትንሣኤ እሑድ ያለውን ይመለከታል፡፡ የዚህ ጾም ምሳሌ በኦሪት ሕግ ተደንግጓል፤ ሊቀ ካህናቱ በዓመት አንድ ጊዜ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በመግባት ስለ እስራኤል ሕዝብ የኃጢአት መሥዋዕት በሚያቀር ብበት ዕለት በሀገሪቱ የሚገኝ ሰው ሁሉ ይጾሙና ራሳቸውንም ያስጨንቋት ነበር (ዘሌዋ.16፥29፤ 23፥27፤ ዘኁ.29፥7)፡፡ በተጨማሪ ሰው ስለ ኃጢአቱ መጾም እንደሚገባው ከጥቅሱ ለመማር እንችላለን፡፡ ሰው በንሥሐ ወደ እግዚአብሔር ሲመለስ ወይም ምሕላ በሚያደርግበት ጊዜ ወይም ሱባኤ በሚይዝበት ጊዜ ሁሉ መጾምና ማዘን ይገባል፤ እንደዚህም በማድረግ በወገንም በአገርም የመጣው መቅሠፍት ይመለሳል (ኢዩ.2፥12-17፤ ዳን.10፥1-14)፡፡

## የጾም ልጓምነት

"ወአሕመምክዋ በጾም ለነፍስየ -- ነፍሴን በጾም አደከምኋት" በረሃብ አስጨነቅኋት ማለት ሲሆን ዓላማው ሥጋን ለመገሠጽና ራስን ለመግዛት ነው (መዝ.34፥13)፡፡ ራስን በጾም ማስጨነቅ ጥቅሙ ምንድነው? የሚለው ጥያቄ በዘመናችን እየበዛ ሄዷል፡፡ እየበላን እየጠጣን እየተደሰትን እምነታችንን ጠብቀን ጸሎትና ምጽዋት ካደረግን ሌላ ምን ያስፈልጋል የሚሉ የስም ክርስቲ ያኖች ጥንትም ዛሬም አሉ፡፡ ይህ ግን ስሕተት ነው፡፡ ሥጋህን ያለልጓም በነፃ ከለቀቅኸው የነፍስህን ነገር ረስተሃል የምትሄድበትንም መንገድ አላወቅኸውም፥ መድረሻህንም በውል አላስተዋልከውም፡፡ ሥጋ ለነፍስ እንደ ጭነት ፈረስ ነው፡፡ ፈረሱ ካልተገራና ልጓም ካልተደረገበት ጋላቢውን ከአደጋ ላይ ይጥለዋል፡፡ ሥጋን እንደ ፍላጐቱ እንዲጋልብ መተው ሳይሆን በጾም ልጓምነት እየተቆጣጠሩ መምራት ለራስም ለሌሎችም ይጠቅማል፡፡ እንደዚህ ካደረግን ሐዋርያው

www.ethiopianorthodox.org

ጳውሎስ "የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ሰቀሉ" ያለው ይፈጸማል (ገላ.5፥24)፡፡[74]

እንግዲህ ክርስቲያናዊ ሕይወታችን የተሟላ እንዲሆን ጸሎ ምጽዋትን ብቻ ሳይሆን ጾምንም አጥብቀን እንያዝ፤ የሦስቱም ዓላማ ተግ ስለ ጾም ጠቃሚነት እንደሚከተለው በፍትሕ መንፈሳዊ ተገልጿል፦

> "ጾምስ የሥጋ ግብር ነው፤ ምጽዋት የገንዘብ ግብር እንደሆነ፡፡ ሕግ ያስወደደው የፈቲው ፆር ትደክም ዘንድ ለነባቢት ነፍስም ትታዘዝ ዘንድ ጸሎትን ያሻው ፈቃድ ለልብ የቁጣ ኃይል እንድትታዘዝ እንደሆነ፡፡ ይረባናል ብለን ከመጸማችን የተነሣ መንፈሳውያንን እንመስላለን፤ ሰልናቸውም የሚመስሉትን ለመምሰል ይቻላል፡፡ ዳግመኛም ጿሚው ችግር ያውቅ ዘንድ ለተራቡትና ለሚለምኑት ይራራላቸው፡፡ ዳግመኛ ፈቃድ ሆኖ ሊመገበው ሥጋውንና ደሙን ይቀበል ዘንድ ነው፡፡ መቀበ በሥጋዊና በነፍሳዊ ትጋት ይሁን፤ ዳግመኛም ከእንስሳዊ ባሕርይ ተለ የጾምን ሥርዓት ጠብቆ ከሰው ወገን ደግሞ በጸሎት የተለየ ሁኖ ስለ በተሠሩት ሕጐች የፀና ሆኖ በሁለንተናው እግዚአብሔርን ያምልከው" ( መንፈሳዊ አንቀጽ 15 ቁ.573-574)፡፡

## ሠ) ክርስቲያናዊ ሕይወት በተአምኖና በምግባረ ወንጌል

በአንቀጸ ብፁዓን የጀመርነው የጌታችን የተራራው ስብከት የመጨረ ክፍል ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን (ማቴ.6፥19-7፥29)፡፡ ይህ ክፍል በቅድሚ በእግዚአብሔር ብቻ ማመንና መታመን እንደሚገባ ይገልጽና ቀጥሎ ከሰዎ ጋር ስላለው ጤናማ ግንኙነትና ስለ ሥራ ፍሬ ወሳኝነት እንዲሁም የእግዚአብ ሔርን ፈቃድና የክርስቶስን ቃል ስለመፈጸም የተሰጠ ትምህርትና መመሪ ነው፡፡ አንቀጸ አሚንና አንቀጸ ምግባር የሚታዩበት የትምህርት ዓይነት ስለሆ ነ በሁለት ክፍለን እናጠናዋለን፡፡

[74] የጥንቷ የምዕራባውያን ቤተ ክርስቲያን አባት አውግስጢኖስ ኑዛዜዎች በሚለው መጽሐፉ የሥጋን ምኞት ስለ መቋቋም በሚናገርበት አንቀጽ፣ እርሱ ራሱ ሰውነቱን ለማስገዛት በየቀኑ የጾም ተጋድሎ እ ደሚያደርግና የዕለት ምግቡንም እንደ መድኃኒት (ለቁመተ ሥጋ ያህል) እንደሚወስድ ከእግዚአብሔር መማሩን ይገልጻል፡፡ ጤንነት፣ ለመብላትና ለመጠጣት ምክንያት መሆኑን በመጥቀስና በማገናዘብ ለጸ የሚያስፈልገው የምግብና የመጠጥ መጠኑ ምን ያህል እንደሆነ በእርግጠኝነት ለማወቅና መለኪያውን በትክክል ለማስቀመጥ አስቸጋሪ መሆኑን አስታውቋል፡፡ ስለ መልካም ጤንነት ብሎ በሚበላበትና በሚጠጣበት ጊዜ አደገኛዋ (ሥጋዊ) ደስታ ራሷን ጓደኛው እንዲሆን የምታደርግ መሆኗን ያስረዳል፡፡ ለጤና ማለት ለቁመተ ሥጋ ብቻ የሚበቃው ምግብ እርካታንና ደስታን ለማስገኘት በጣም እንደሚያንስ ገልጿል፡፡ በየዕለቱ በእንደዚህ ዓይነት ፈተናዎች ውስጥ በማለፍ የመንፈሳዊ ተጋድሎውን፣ ብርታቱንና ድክመቱን በመናዘዝ ከዘረዘረ በኋላ በመጨረሻ ጾመ ልጓሙ በመጠኑ መሆን እንዳለበት አስረድቷል፡፡ "በጉረሮ ላይ የሚደረገው ልጓም . . . በመጠኑ በማላላትና በመጠኑም በማጥበቅ /እጅግም ሳይረግብ እጅግም ሳይወጠር በመካከል ተመጥኖ/ መያዝ አለበት፡፡" ብሏል፡፡
" . . . now this need [eating and drinking] is sweet to me, and against such sweetness I fight, lest I be captured by it, and I wage daily warfare by fasting, more frequently 'bringing my body into subjection' . . . You [God] have taught me this, so that I may come to take food just as I take medicine . . . Since good health is the reason for eating and drinking, a dangerous pleasure makes herself my companion . . . for what is enough for health is too little for pleasure . . . The bridle put upon the throat must be held with both moderate looseness and moderate firmness." St. Augustine, Confessions ,.X, 43-47; translated by John K.Ryan.



## 1. ተአምኗችንና ተስፋችን በእግዚአብሔር ብቻ ይሁን

> "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በሰው የሚታመን ሥጋ ለባሹንም ክንዱ የሚያደርግ ልቡም ከእግዚአብሔር የሚመለስ ሰው እርጉም ነው፡፡ በምድረ በዳ እንዳለ ቁጥቋጦ ይሆናል መልካምም በመጣ ጊዜ አያይም ሰውም በሌለበት ጨው ባለበት ምድር በምድረ በዳ በደረቅ ሥፍራ ይቀመጣል፡፡ በእግዚአብሔር የታመነ እምነቱም እግዚአብሔር የሆነ ሰው ቡሩክ ነው፡፡ በውኃ አጠገብ እንደ ተተከለ በወንዝም ዳር ሥሩን እንደሚዘረጋ ሙቀትም ሲመጣ እንደማይፈራ ቅጠሉም እንደሚለመልም በድርቅ ዓመትም እንደማይሰጋ ፍሬውንም እን ደማያቋርጥ ዛፍ ይሆናል" (ኤር.17፥5-8)፡፡

የእግዚአብሔርን ሀልዎት (መኖር) ማመን ብቻ አይበቃንም፡፡ በእግዚአ ብሔር መተማመንና ተስፋችንንም በእርሱ ብቻ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ነው በመዝሙረ ዳዊት፦ "ይኄይስ ተአምኖ በእግዚአብሔር እምተአምኖ በእጓለ እመሕያው፡፡ ይኄይስ ተሰፍዎ በእግዚአብሔር እምተሰፍዎ በመላእክት" የተባ ለው፡፡ ይህም ማለት "በሰው ከመታመን ይልቅ በእግዚአብሔር መታመን ይሻ ላል፡፡ በገገሮች ተስፋ ከማድረግ ይልቅ በእግዚአብሔር ተስፋ ማድረግ ይሻላል" ማለት ነው (መዝ.117፥8-9)፡፡ ብዙዎቻችን በልዩ ልዩ ምክንያት አው ቀንም ሆነ ሳናውቀው ተአምኗችንን በሰው ላይ ተስፋችንን በባለሥልጣን ላይ አድርገ ነው እንገኛለን፡፡ ይህ ዓይነቱ ነገር ክርስቲያናዊ ሕይወታችንን ከመሠረቱ የሚያፈርሰው ከሥሩ የሚነቅለው ነው፡፡ ስለሆነም ከላይ በጥቅሱ እን ደተመለከተው እንዲህ ዓይነት ሰው "በምድረ በዳ እንዳለ ቁጥቋጦ" ይሆናል፡፡ ነገር ግን ተአምኗችንና ተስፋችን በእግዚአብሔር ብቻ ከሆነ ክርስቲያናዊ ሕይወታችን ይለመልማል፤ በውኃ ዳር እንደ ተተከለ "ፍሬውንም እንደ ማያቋርጥ ዛፍ ይሆናል"፡፡ በሰው መታመን ብቻ አይደለም የተከለከለው በገን ዘብም ሆነ በሌላ ነገር መታመን እንደ ባዕድ አምልኮ ስለሚቆጠር በነቢያትም እንደተነገረው በወንጌልም ፈጽሞ የተወገዘ ነው፡፡ ለቀደሙ ሰዎች በነቢያት የተባለውን ጌታችን በወንጌሉ ፍጹም አድርጉታል፡፡

አንድ አምላክ እግዚአብሔር አባታችንን ብቻ ከማመንና ከመተማመን በቀር ማንም ሰው እምነቱን በሌላ ነገር ላይ እንዳያደርግ ክርስቶስ በቃለ ወን ጌሉ አስጠንቅቆናል፡፡ ነገር ግን የሰው ልጅ እምነቱንና ፍቅሩን ከሚያሳርፍበት ነገር አንዱ የዚህ ዓለም ሀብትና ንብረት እንደሆነ የታወቀ ነው፡፡ የጥንት ሰዎች የወደዱትንና የሚተማመኑበትን ገንዘባቸውን ሰው እንዳያየው ከመሬት ውስጥ ቆፍረው ያስቀምጡታል፤ ሌላውንም ንብረታቸውን ከተሰወረ ቦታ ያከማ ቹታል፡፡ በእንደዚህ ሁኔታ የተንከባከቡለት ሀብት ራሳቸውም ሆኑ ሌሎች ሳይገ ለገሉበት ተበላሽቶና ጠፍቶ የሚቀርበት ጊዜ ብዙ ነበር፡፡ ከዚህም ሌላ በብዙ ጊዜና በብዙ ውጣውረድ ስለ ሰበሰቡት ሀብታቸው ስለ መዝገባቸው ብዙ ያስባሉ፣ ይጨነቃሉ፡፡ ይህን ሁኔታ መነሻ በማድረግ ጌታችን "ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በሚሰርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፤ ነገር ግን" ይህ ሁሉ ጥፋት በማይደርስበት "በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ፤ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ ይሆናልና" በማለት እያስተማረ ይመክራቸው ነበር (ማቴ.6፥19-21)፡፡

### ሁለቱ ብቻ ለፍቅራችን ሌሎቹ ለመገልገያችን ታዝዘዋል

ገንዘባችን ልባችንን ሰርቆ እንዳይወስደውና ምርኮኛ አድርጎ እንዳይ ገዛው መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡ ምክንያቱም ጌታችን እንዳለው "መዝገብህ /ገን [illegible] ደግሞ በዚያው ይሆናልና"፡፡ እንግዲህ ከገንዘብ ምርኮኝነት ነፃ [illegible]

www.ethiopianorthodox.org

መጠቀምና በሥራ ላይ ማዋል እንወቅ፡፡ ክርስቲያኖች መውደድ ያለባቸው ሁለት ነገሮችን ብቻ እንደሆነ የታወቀ ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ እግዚአብሔርን ከሁሉም በላይ መውደድ ነው፤ በሁለተኛ ደረጃ ራስንና ባልንጀራን እኩል በእኩል መውደድ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የሆኑት ማናቸውንም በምድር ላይ የሚገኙትን ማለት መሬቱን፣ ባሕሩን፣ አየሩን፣ እፅዋቱን፣ አዝርዕቱን፣ አትክልቱን፣ እንስሳቱን፣ እህሉን፣ ልብሱን፣ ቤቱን፣ ወርቁንና ብሩን ሌሎችንም የማይንቀሳቀሱና የሚንቀሳቀሱ ሀብትና ንብረት ሁሉ መገልገልና መጠቀም እንጂ እነርሱን መውደድና ማምለክ በእግዚአብሔር ሕግ ተከልክሏል፡፡ ከእግዚአብሔር ይበልጥ የምንወደው ነገር ካለ ያ ነገር ማንም ይሁን ማን፣ ምንም ይሁን የኛ ባዕድ አምልኮ ይሆንብናል፡፡ ፈጣሪን እንጂ ፍጥረትን ማምለክ አይገባንም፡፡ እንዲያውም ሰው በምድር ላሉ ፍጥረታት ሁሉ የበላይ ገዢ እንጂ የእነርሱ ተገዥ ሊሆን አይችልም፡፡ ስለዚህ የሰው ልጅ ከሁሉም በላይ የልቡናው ፍቅር፣ ደስታ፣ እምነትና ተገዢነት ለእግዚአብሔር ብቻ እንጂ ለገንዘብ ወይም ለሌላ ነገር መሆን የለበትም፡፡

እንግዲህ ገንዘባችንን ለእግዚአብሔር አገልግሎት፣ ለራሳችንና ለሰው ጥቅም በሥራ ላይ እናውለው፡፡ እንደዚህ አድርገን ባላፊውና በጠፊው ሀብታችን ቁም ነገር ከሠራንበት ብልና ዝገት ከማያበላሹት ሌቦች ከማይሰርቁት ከሰማያዊ ቦታ ሀብታችንን እናከማቻለን፡፡ አለበለዚያ በተቃራኒው ገንዘባችንን እንወዳለን በገንዘባችንም እንመካለን ለራሳችን እንጂ ለሌላ አገልግሎት አናውለውም በማለት ከጸናን በራሳችን ላይ እባብ መጠምጠማችን ነው፡፡ ለገንዘብ ፍቅር ብለን ራስን ማስገዛት የሚያስከትለው ችግርና ፈተና ብዙ ነው፡፡ ገንዘባችንን አንድ ነገር በነካው ቁጥር ስለ ገንዘባችን ደኅንነት እናስባለን፤ አንዳንድ ጊዜ ብዙ እንጨነቃለን፡፡ ከዚህም የተነሣ የአእምሮ ሰላም እናጣለን፣ በመንፈስ እንታወካለን፣ ዓይነ ልቡናችንም ይታመማል፡፡ ጌታ "የሰውነት መብራት ዓይን ናት" ብሎ በምሳሌ የተናገረው በውስጣችን ስለሚገኘው የልቡናችን ዓይን ስለ አእምሯችን ብርሃን ስለ ዕውቀታችን መብራት ነው፡፡ ይህ ዓይነ ልቡናችን ከላይ በተጠቀሰው ወይም በሌላ ምክንያት ጤንነቱን ሲያጣ የማስተዋል ችሎታው ይጠፋል፣ የእውቀት ብርሃኑ ይጨልማል፤ "እንግዲህ በአንተ ያለው ብርሃን ጨለማ ከሆነ ጨለማውስ እንዴት ይበረታል!" በማለት ጌታ ሁኔታውን በአንክሮ ገልጾታል (ማቴ.6፥23)፡፡ የሰው ልጅ አእምሮ ጠባይዕ የቀና ከሆነ አስተያየቱም እምነቱም የቀና ይሆናል፡፡ አእምሮ ጠባይዑ ያልቀና ከሆነ እምነቱ የቀና አይሆንም፡፡ በፍቅረ ንዋይ ምክንያት የልቡናው ዓይን ጤናማ ያልሆነና አእምሮ ጠባይዑ ያልቀና ሰው ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ ለሁለቱም መገዛት እንደሚቻለው ያስብ ይሆናል፡፡ ጌታ ግን አንድ ሰው ለሁለት ጌቶች መገዛት እንደማይቻለው አስተምሮናል፤ ከሁለቱ ጌቶች "አንዱን ይጠላል፤ ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል፤ ሁለተኛውንም ይንቃል፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም" ብሎናል (ማቴ.6፥24)፡፡

## *እመኑ አትጨነቁ አለ እንጂ አትሥሩ አላለም*

ስለዚህ በአንድ ልቡና ሆነን ለአንድ እግዚአብሔር ብቻ እንድንገዛና በእርሱ መግቦትና ጥበቃ ማመንና መተማመን ይገባናል፡፡ "ጻድቅ በእምነት ይኖራል" እንደ ተባለው ክርስቲያንም በትምህርተ ክርስቶስ ጸንቶ በእግዚአብሔር ታምኖ የዕለት ተዕለት ኑሮውን በሰላም ያከናውናል እንጂ ስለ ኑሮው ብዙ በማሰብና በማሰላሰል አይጨነቅም፡፡ ጌታችን እንዳስተማረው በሰማይ ባለው አባት የሚያምን ክርስቲያን ሁሉ እንደማያምኑት አሕዛብ ስለ ምግቡና ስለ ልብሱ መጨነቅ አያስፈልገውም፡፡ የሰማይ ወፎችን የሚመግብ የሜዳ አበቦችን በልብስ የሚያስጌጥ አምላክ ...

www.ethiopianorthodox.org



ጥበቃው ምን ያህል ይሆን? "እናንተ እምነት የጐደላችሁ እናንተንማ ይልቁን እንዴት?" በማለት ጌታችን በአንክሮ ደቀ መዛሙርቱን ይጠይቃል፡፡ "እንግዲህ ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ፤ ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና፡፡ ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፣ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል" (ማቴ.6፥31-33)፡፡

ጌታ "አትጨነቁ" ማለቱ የሥራ እቅድ እያወጣችሁና እያሰባችሁ የዕለት ተዕለት ተግባራችሁን አትሥሩ ለማለት አይደለም፡፡ ወጥቶ ወርዶ ሳያተርፉ መሥራትማ በምሳሌ መክሊት የታዘዘ ነው፤ ምንም ሳይሠሩና ምንም ሳያተርፉ መሥራትማ በምሳሌ መክሊት የታዘዘ ነው፤ ምንም ሳይሠሩና ምንም ሳያተርፉ መቀመጥማ በፍርድ ያስቀጣል (ማቴ.25፥14-30)፡፡ እቅድ አውጥቶ በቅድሚያ አስቦ መሥራትም ያለ ነው (ሉቃ.14፥28-32)፡፡ በኑሯችንም ሆነ በሥራችን መጨነቅ አያስፈልግም፡፡ ጭንቀት በሕይወታችን ላይ ጉጂ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ስላለው ከዚህ ዓይነቱ የመንፈስና የልቡና በሽታ እንድንድን ጌታ እያስተማረን ነው፡፡ መቼም ቢሆን በመጨነቅ ራሳችንን እንጐዳለን እንጂ የምንጨምረው ነገር የለም፡፡ ስለዚህ ነው ጌታችን "ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማን ነው? በማለት የሚጠይቀን (ማቴ.6፥27)፡፡ ጌታ "ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ፤ አይዘሩም አያጭዱም በጐተራም አይከቱም፣ የሰማይ አባታችሁም ይመግባቸዋል" ያለው እጅ እግራችንን አጣጥፈን ቀኑን ሙሉ ዝም ብለን እንድንቀመጥ አይደለም፡፡ ይህማ ስንፍና ነው፤ ስንፍና ደግሞ ኃጢአት ነው፡፡ ወፎች እኮ ሰነፎች አይደሉም፡፡ እነርሱ ገና ጎሕ ሲቀድ ተነሥተው እግዚአብሔር በሰጣቸው ክንፍ ወዲያና ወዲህ በመብረር ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወሩ ምግባቸውን እየፈለጉና እየለቀሙ ይመገባሉ፤ ጐጆቻቸውንም ይሠራሉ፤ ጫጩቶቻቸውን እየተንከባከቡ በመመገብ ያሳድጓቸዋል፡፡ ሰው ከወፎች ይበልጣል፤ ከእነርሱ የበለጠ ብዙ መሥራትም ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን የልቡናውን ጭንቀት ማስወገድ አለበት፤ በጭንቀቱም ፋንታ የእምነትና የተአምኖን ጸጋ ከእግዚአብሔር ይለምን፡፡ በተአምኖ መኖርና መሥራትን ይማር (ዕብ.11)፡፡ ስለዚህ ነው ጌታችን "ልባችሁ አይታወክ (አይጨነቅ)፤ በእግዚአብሔር እመኑ፣ በእኔም እመኑ" በማለት ደቀ መዛሙርቱን ያጽናናቸው (ዮሐ.14፥1)፡፡

## 2. ቃሉን ሰምቶ የሚያደርገው ለዘላለም ይኖራል

### *አትፍረዱ እንዳይፈረድባችሁ*

የእግዚአብሔር ቃል "አትፍረዱ" ይላል፣ እኛ ግን በወንድማችን ላይ ስንፈርድ እንውላለን፡፡ በዚህ አድራጐታችን ከቀጠልን መልሶ እኛኑ ይጐዳናል፡፡ ምክንያቱም በወንድማችን ላይ በፈረድንበት አኳኋን እኛም ስለሚፈረድብን ነው፡፡ ስለዚህ ነው ጌታችን "እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ፤ በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋልና፣ በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል" ያለው (ማቴ.7፥1-2)፡፡ ይህንንም በዓይን ጉድፍ መስሎ ይገልጻል፡፡ "በወንድምህ ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ፣ በዓይንህ ግን ያለውን ምሰሶ ስለምን አትመለከትም? . . . አንተ ግብዝ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ ከዚያ በኋላ ከወንድምህ ዓይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ በማለት ጌታ መመሪያውን ሰጥቶናል (ማቴ.7፥3-5)፡፡ ስለዚህ በመጀመሪያ ራሳችንን በመመርመር ጥፋታችንና ጉድለታችንን ደካማ ጐናችንንም ተመልክተን መታረም ይገባናል፤ ከዚያ በኋላ በወንድማችን ላይ የምናየውን ጥፋት በፍቅርና በእውነት መንፈስ ሆነን በትምህርትና በምክር ለማረም ጥረት ... እንደዚህ በማድረግ ብዙዎችን ወደ እግዚአብሔር ቃል

ለመመለስ እንችላለን፤ ለብዙዎችም ደኅንነትን እናስገኛለን፡፡ ነገር ግን አንዳን ዶች እንዲህ ዓይነት ምክር ሲሰጣቸው የቃለ እግዚአብሔርን ምክር ተግሣጽ አለመቀበል ብቻ ሳይሆን መካሪዎቻቸውን ቦኀይ መዓት በማየት በቁጣ በመነሣሣት ይጣሏቸዋል፡፡ ስለዚህ ነው "በእግራቸው እንዳይረግጡት ተመልሰውም እንዳይነክሷችሁ፥ የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ፥ ዕንቁቻችሁ ም በእሪያዎች ፊት አትጣሉ" የተባለው (ማቴ.7፥6)፡፡ የተቀደሰውን ወይም ዕ ንቁቻችሁን የተባለው ቃለ እግዚአብሔርና ምክረ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ውሾ ወይም እርያዎች የተባሉት ወደ ትፋታቸው የሚመለሱ ማለት ወደ ኃጢአ የሚመለሱ ታጥበው ጭቃ የሚገቡ፥ መታረምን የማይወዱ ከነኃጢአታቸው መኖር የሚፈልጉ ከዓመፅ ከኃጢአት በቀር መልካሙ ነገር የማይስማማቸው ቅዱሱን መንፈስ የሚሳደቡ የለየላቸው አዕራረ ጽድቅ ስለሆኑ እነርሱ በዚህ ዓ ለም ከክርስቲያናዊ ሕይወት ውጭ የሚኖሩ በኋላም ከመንግሥተ ሰማያት በአ ፍአ የሚቀሩ ናቸው (2ኛጴጥ.2፥22፤ ራእይ.22፥15)፡፡

## ስለ ጸሎትና በፍቅር ስለ መተሳሰብ

ከዚህ ቀጥሎ ጌታችን እንደገና ስለ ጸሎት ያስተምረናል፡፡ ጸሎታችን የግብር ይውጣ ሳይሆን አጥብቀን መጸለይ እንደሚገባን በምሳሌ አስረድቶናል፡፡ ልመናችንና ደጅ ጥናታችን መልስ ሳያገኝ እንደማይቀር አረጋግጦልናል፡፡ ምድራዊ አባቶች ለልጆቻቸው የለመኑትን መልካም ነገርን ይሰጧቸዋል እንጂ ክፉ ነገር አይሰጧቸውም፡፡ "እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታ መስጠትን ካወቃችሁ፥ በሰማያት ያለው አባታችሁ ለሚለም ኑት እንዴት አብልጦ መልካም ነገርን ይሰጣቸው?" በማለት ጌታችን ሰዎች ሊደረግላቸው የሚወዱትን መልካሙን ነገር ሲለምኑ እግዚአብሔር እንደሚ ሰጣቸውና እንደሚያደርግላቸው ከገለጸ በኋላ ሰዎችም እንደዚሁ እርስ በእርሳ ቸው በመንፈሳዊ ፍቅር እንዲተሳሰቡ አስታውቋቸዋል፡፡ "እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው" በማለት ክርስቶስ ሕግንና ነቢያትን ሁሉ የሚፈጽሙበትን ወርቃማውን ሕግ ሰጥቷቸዋል (ማቴ.7፥7-12)፡፡ በጸጋ መንፈስ ቅዱስና በፍቅር ለሚኖሩ ክርስቲያኖች ይህንን ሕግ ለመፈጸም አያዳግታቸውም፡፡ ምክንያቱም እውነተኛ ክርስቲያኖች መምህራቸው ክርስቶስን አብነት አድርገው የሚኖሩ ስለሆነ "እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ" የሚለውንም የፍቅር ትእዛዝ እንደ እርሱ ለመፈጸም የዘወትር ጥረታቸው ነው፡፡ ነገር ግን ብዙዎች ይህንን ሕግና ትእዛዝ ለመፈጸም ስለማያስቡና ስለማይሞክሩ እንዲያው በቸልተኝነትና በግዴለሽነት በትልቁ ጐዳና እንደ ልባቸው ሲመላለሱ፥ በሰፊውም ደጅ ሲገቡና ሲወጡ ይታያሉ፡፡

## ስለ ጠባቡና ስለ ሰፊው መንገድ

ስለዚህ ጌታችን "በጠበበው ደጅ ግቡ" እያለ ሰዎችን ሁሉ ይጠራል፤ ምክንያቱም "ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጁ ሰፊ መንገዱም ትልቅ ነውና፥ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፤ ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጁ የጠበበ መን ገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው" (ማቴ.7፥13-14)፡፡ በዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር እንደምንማረው ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጁ የጠ በበ መንገዱም የቀጠነ የተባለው እውነተኛውን ክርስቲያናዊ ሕይወትና ሥነ ምግባር የሚያመለክት ነው፡፡ ይህንንም የሚያገኙት ጥቂቶች ናቸው የተባለው እንደ አሥሩ ብፁዓን የመሰሉትን፥ በሕገ ወንጌል የሚመሩትን፥ ምጽዋት የሚያደርጉትን፥ በጾም በጸሎት የተወሰኑትን፥ በእምነት የጸኑትን፥ መልካም ሥነ ምግባር ያላቸውን፥ ቃሉን ሰምተው የሚያደርጉትን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ እነዚህን የጽድቅ ሥራዎች ለማድረግ የማይሞክሩት ወይም የማይወዱት ወይም የሚቃወሙት

www.ethiopianorthodox.org



የዚህን ዓለም መንገድ ተከትለው በሕገ እግዚአብሔር ሳይሆን በራሳቸው ፈቃድ እንደ አሻቸው የሚኖሩ፥ መንፈሳዊ ሳይሆኑ መንፈሳዊ የሚመስሉ በስም ክርስቲያኖች ወይም በፈቃደ ሥጋ ብቻ የሚመሩትን ዓለማውያን ሰዎች ሁሉ እንደሆነ ከምሳሌው ለማወቅ ይቻላል፡፡ እንግዲህ በየትኛው መንገድ ላይ እንዳለን ራሳችንን በመመርመርና በማወቅ የሚገባውን ውሳኔና አስፈላጊውን እርምጃ ሳንወስድ በመሐል ሰፋሪነትና በቸልተኝነት ከቆየን ወደ ጥፋት የሚወስደውን ሰፊ መንገድ እንደ መረጥን ይቆጠራል፡፡ ምክንያቱም ሁለት መንገዶች ብቻ እንጂ ሦስተኛ መንገድ የለም፡፡ በየትኛው መንገድ ላይ እን ዳለን የምንመረምረው ራሳችንን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም ጭምር መርምረን ከሁለቱ የየትኛው መንገድ ተከታዮች እንደሆንንና እንደሆኑ በውል ማወቅ ይኖርብናል፡፡ አለበለዚያ የጥፋት መንገደኞች በሕይወት መንገድ የሚሄዱትን መስለው በማታለል ወደ ጥፋት ሊወስዷቸው ይችላሉና ለራሳችንም መጠን ቀቅና ለሌሎችም ማስጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡

> ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው፦ "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጐ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፡፡ ከሄድሁ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ፥ ደቀ መዛሙርትንም ወደ ኋላቸው ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገርን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሡ እኔ አውቃለሁ" (የሐዋ.ሥራ 20፥28-30)፡፡

## ከሐሰተኞች መምህራን ተጠበቁ

እንግዲህ "የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ" በማለት ጌታችን ያስተማረን ከላይ ስለ ተጠቀሰው ጉዳይ ነው (ማቴ.7፥15)፡፡ እነዚህ መስለውና አስመስለው በአማኞች መካከል ገብተው የሚያስቷቸውንና ወደ ጥፋት የሚያገቧቸውን የሐሰት መምህራን እንዴት እንወቃቸው? እናታችን ሔዋንን ያሳተት ሰይጣን በሥጋ ከይሲ ተሰውሮ ደግ ነገር በመሰለ የሽንገላ ቃል በማግባባት እንዳታለላት ገና ከመጀመሪያው የሰው ልጅ ታሪክ የታወቀ ነው (ዘፍ.3፥1-6)፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መታለል የሰው ልጅ ዕድል ፈንታው ሆኗል፡፡ ይልቁንም በዘመናችን በትንቢት እንደ ተነገረው በሃይማኖት ስም አስ መሳዮችና አታላዮች፥ ዓመፀኞችና ከሐዲዎች የበዙበት ጊዜ ነው፡፡ እነርሱ "ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤ የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፡፡ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ" ይላል ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ (2ኛጢሞ.3፥4-5)፡፡ እንደነዚህ ዓይነት አስመሳዮችና ከሐዲዎች "እግዚአ ብሔርን እንዲያውቁ በግልጥ ይናገራሉ፥ ዳሩ ግን የሚያስጸይፉና የማይታዘዙ ለበጐ ሥራም ሁሉ የማይበቁ ስለሆኑ፥ በሥራቸው ይክዱታል" (ቲቶ.1፥16)፡፡ እንግዲህ አስመሳዮቹን የምናውቃቸው ከሆነ ከእነርሱ መሸሽና መራቅ እንጂ በጓደኝነት መቀበልና ማስተናገድ አይገባንም፡፡ የሐዋርያው የቅዱስ ዮሐንስን ማስጠንቀቂያ አንርሳ፥ "ለሚወጣ ሁሉ በክርስቶስም ትምህርት ለማይኖር ሰው አምላክ የለውም፤ በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት፡፡ ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት፤ ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላ ልና" (2ኛዮሐ.9-11)፡፡ በስም ክርስቲያን ሆነው ያሉበትን አካባቢ መስለው የሚያታልሉትን ሰዎች የምናውቅበትን መንገድ ክርስቶስ አስተምሮናል፤ ይኸውም "ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ" በማለት የእውነተኞችና የሐሰተኞች መምህራንን መለየ መስፈርት ሰጥቶናል (ማቴ.7፥16)፡፡

ሰዎችን ማንነት የምናውቀው በሥራ ፍሬያቸው እን

ደሆን ለማሳየት ጌታችን በዛፍ ፍሬ መስሎ አስረድቶናል፡፡ መልካም ዛፍ መል ሙን ፍሬ እንጂ ክፉውን አያፈራም፤ ክፉ ዛፍም ክፉውን እንጂ መል ሙን አያፈራም፡፡ ስለዚህ አስመሳዮችንና ሐሰተኞች መምህራንን በስብ ቸውና በጸሎታቸው ሳይሆን በግል ኑሯቸውና ጠባያቸው በሥነ ምግባር ብል ነታቸው፣ በስውር በሚሠሩት ተንኮላቸው ለማወቅ ይቻላል፡፡ እንደነዚህ ያሉ ሰዎች በሚያታልል ዘዴአቸውና በረቂቅ ስልታቸው የቤተ ክርስቲያንን የመሪነ ሥልጣን እየያዙ በማኅበረ ምእመናኑ ላይ ብዙ ጥፋትን አስከትለዋል፡፡ ምእመናንንም በአንድነታቸው ለማቆየት የሚፈልጉት ለራሳቸው ጥቅም መተዳደሪያ እንዲሆኗቸው አስበው እንጂ ለሃይማኖት ብለው እንዳልሆነ ግል ነው፡፡ በመሪዎቻቸውና በመምህሮቻቸው ምግባረ ብልሹነት ብቻ ሳይሆን እ ነትና መንፈሳዊነት በመጥፋቱ የተነሣ ምእመናኑ አርአያ የሚሆናቸው እውነተ መንፈሳዊ መሪ በማጣት እያዘኑ በአሁኑ ጊዜ በተለይም በብዙ የምዕራብ ሀገሮ ከቤተ ክርስቲያን የቀሩ እጅግ ብዙዎች ናቸው፡፡ ስለዚህም አብያተ ክርስ ያኖቻቸው በየቦታው የተዘጉና ተሸጠውም ለገበያ አዳራሽና ለነዳጅ ማደ ለሌላም ዓለማዊ አገልግሎት ውለዋል፡፡ እንግዲህ እንደነዚህ ያሉ አስመሳይ መን ፈሳዊ መሪዎችና መምህራን ናቸው ጥንትም ሆነ ዛሬ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! እያሉ የጌታን ስም እየጠሩ በአደባባይ የሚሰብኩና በስሙም በመጸለ ታምራት አድርገናል፣ የታመመውን ፈውሰናል የሚሉ፡፡ በሥራቸው ግን እግ ዚአብሔርን የካዱና የርሱን ቃል ሰምተው ያልፈጸሙ፣ በስውር እኩይ ሥራቸውን ከማድረግ የማይቆጠቡ በመሆናቸው በመጨረሻው የፍርድ ቀን መቀጣታቸው አይቀርም፡፡ ምክንያቱም "መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል" በማለት ጌታችን በምሳሌ ትንቢት ተናግ ሮባቸዋልና (ማቴ.7፥19)፡፡

## <u>*መልካም ሰው በንግግሩ ሳይሆን በሥራው ይታወቃል፡፡*</u>

ከዚህም በማያያዝ ጌታችን ስለነዚሁ ስመ ክርስቲያኖች ሲገልጽ "በሰ ማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፣ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም" ብሏል፡፡ በፍርድ ቀንም "ብዙዎች፦ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስም ህስ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን? ይሉኛል፡፡ የዚያን ጊዜም፦ ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፣ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ" (ማቴ.7፥21-23)፡፡ እንግዲህ የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ የሚያስተውል ልቡና ያለው ያስተውል፡፡ የመጨረሻው ተስፋችንንና ሰማያዊ ርስታችንን የምናገኘው የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ እንጂ በቃል በመለፍለፍ ከንፈር በመምጠጥ አቤቱ አቤቱ በማለት ብቻ አይደለም፡፡ በእም ነት ብቻ መንግሥተ ሰማያት እንደማትገኝ ከዚህ ቃለ ወንጌል መማር ይገ ባናል፡፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ትተን በክፉ ሥራችን እየኖርን እምነት አለን በጸጋው ብቻ እንድናለን በማለት በሰፊው ጉዳና የምንሄድ ከሆነ መጨረሻችን ጥፋት ይሆናል፤ መዳኛም የለንም፡፡ ምክንያቱም ያ የምናምነው ጌታ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ እርሱ ራሱ ምስክር እርሱ ራሱ ዳኛ ሆኖ የሚፈርድልን ወይም የሚፈርድብን በእምነታችን መስፈርትነት ብቻ ሳይሆን በዚህ ዓለም ሳለን የፈጸምነው ደግ ወይም ክፉ ሥራ ተመርምሮ እንደሆነ በወንጌሉ አስተምሮናል (ማቴ.25፥31-46፤16፥27)፡፡ "እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክበዋል" ተብሏልና (ሮሜ.2፥6፤ መዝ.61፥12፤ ምሳ.24፥12)፡፡ እምነት ብቻውን የሚያጸድቅ ቢሆንማ ኖሮ ሰይጣን፣ ኢየሱስ ጌታና አምላክ መሆኑን በማመኑ ብቻ ይጸድቅ አልነበረምን? ስለዚህ እምነት ብቻውን ያለ ሥራ እንደማያድን እንወቅ፤ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነውና (ያዕ.2፥14-26)፡፡

ሰው ክርስቶስን በማመን ብቻ ሳይሆን ቃሉንና ትእዛዙን በሥራ ላይ በማዋል ነው የዘላለም መኖሪያ ቤቱን ሊያገኝ የሚችለው...



መልክቶ በምሳሌ ሲያስተምር፦ "ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል፡፡ ዝናብም ወረደ ጐርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት ገፋው በዐለት ላይ ስለ ተመሠረተ አልወደቀም" ብሏል፡፡ ነገር ግን በተቃራኒው ቃሉን ሰምቶ ያላደረገው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል፡፡ መሠረቱም ጥብቅ ስላልሆነ ቤቱ ይወድቃል፤ አወዳደቁም ታላቅ እን ደሆነ በመግለጽ ጌታ የተራራውን ስብከት በነዚህ ሁለት ምሳሌዎች ደምድሞታል (ማቴ.7፥24-27)፡፡

"ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው" ወይም "የማያደርገው" ሲል ጌታችን ካስ ተማረው የወንጌል ቃል ውስጥ የትኛውን ኃይለ ቃል ማለቱ ነው? ብለን ብንጠ ይቅ መልሱ በተራራው ስብከት የተነገረውንና ሌላውንም የወንጌል ቃል ሁሉ ማለት እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ከአንቀጸ ብፁዓን ጀምሮ ስድስቱ ቃላተ ወንጌልን፣ ምጽዋትን፣ ጾም ጸሎትን፣ በእግዚአብሔርና በመግቦቱ መተማመንን፣ ለራስህ የሚያስፈልግህን ለሰዎች ሁሉ ማድረግንና ሌሎችንም የጌታ ቃልና ትእዛዝ ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ መንግሥተ ሰማያት እንደሚገባና የዘላለም ቤቱን እንደሚያገኝ ጌታ በማያሻማ ቋንቋ አረጋግጦልናል፡፡ ስለዚህ መዳን ወይም ጽድቅ በእምነት ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድና የክርስቶስን ቃል በማድረግ እን ደሆነ ከተራራው ስብከት ተምረናል፡፡

## <u>*በክርስቶስ ለመዳንና ለመጽደቅ*</u>
## <u>*የሚያበቁን ነገሮች ወይም "ሁኔታዎች"*</u>[75]

እንግዲህ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው ለመዳንና ለመጽደቅ፣ መንግሥተ ሰማያት ለመግባትና የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት የእግዚአብሔርን ፍቅርና የክርስቶስን የማዳን ሥራ መሠረትና መነሻ በማድረግ እምነትና ጥምቀት ያስፈልጉናል፤ እንደዚሁም ቃሉን ማድረግ ወይም ትእዛዛቱን መጠበቅ ይኖርብናል፡፡ ከሁሉም በፊት ግን እምነት ሃይማኖት ያስፈልገናል፤ ምክንያቱም ሃይማኖት መሠረት ነውና፡፡ ማናቸውም የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ሁሉ በእምነት ላይ ተመሥርቶ የተገነባ መሆኑን የሚረሳ የለም፡፡ ጥምቀት የእምነት መግለጫና ማረጋገጫ ነው፦ ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ጋር አንድ የምንሆንበት፣ ጸጋ መንፈስ ቅዱስንና ልጅ ነትን የምናገኝበት፣ ኃጢአታችን የሚሠረይበት ታላቅ የሃይማኖታችን ምሥጢር እንደሆነ እናምናለን (ሮሜ.6፥3-11)፡፡ "ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም" በማለት ጌታ የተናገረው ስለ ጥምቀት መሆኑ አያጠራጥርም (ዮሐ.3፥5)፡፡ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ጥምቀትን እንድትፈጽም ጌታ ለቤተ ክርስቲያኑ ቀዋሚ ትእዛዝ ሰጥቷታል (ማቴ.28፥19)፡፡ ከጥምቀት ጋርም ሌሎች ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ይፈጸማሉ፡፡ ጥምቀት፣ ሜሮን፣ ንስሐና ቁርባን እነዚህ "አራቱ ምሥጢራት ለእያንዳንዱ አማኝ አስፈላጊ" ናቸው[76]፡፡ በምሥጢራት አማካይነት በጸሎትና ቃሉን በማገልገል በክርስቶስ ላመኑት ሁሉ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ይሰጣል፡፡

---

[75] "በክርስቶስ ደም የመዳን ሁኔታዎች" አራት እንደሆኑ የግብፅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች፡፡ እነርሱም፦ "1. እምነት 2. ጥምቀት 3. ለመዳን የሚያስፈልጉ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን 4. መልካም ሥራዎች" ናቸው፡፡

"Conditions of salvation through the Blood of Christ ... " four essential conditions viz. 1. Faith 2. Baptism 3. Church Sacraments necessary for salvation 4. Good works." H.H. Pope Shenouda III, <u>Salvation in the Orthodox Concept</u> (Dar El Tebaa El Kawmia, December 1990), p.26.

[76] ቄስ ማርቆስ ዳውድ፣ <u>የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት</u>፤ (በእንግሊዝኛ ተጽፎ እ.አ.ዘ.አ.

www.ethiopianorthodox.org

## "ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ... ትእዛዛትን ጠብቅ"

የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት ከእምነትና ከጥምቀት ሌላ የጌታን ትእ
ዛት መጠበቅ እንደሆነ ተረድተናል። ይህንንም በግልጥ ልናውቀው የም
ነው አንድ ሰው የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት ጌታን በጠየቀው ጊዜ ነበ
ጠያቂውም፦ "መምህር ሆይ፥ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነ
ላድርግ?" ባለው ጊዜ ጌታ ሲመልስ "ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ
ትእዛዛትን ጠብቅ አለው። እርሱም፦ የትኞችን? አለው። ኢየሱስም፦ አ
ደል፥ አታመንዝር፥ አትስረቅ፥ በሐሰት አትመስክር፥ አባትህንና እናትህን አ
ብር፥ ባልንጀራህንም እንደራስህ ውደድ አለው" (ማቴ.19፥16-19፤ ሉቃ.10፥2
28)። እንግዲህ በእምነት ብቻ ሳይሆን ትእዛዛትን በመጠበቅ የዘላለም ሕይወ
እንደምናገኝ በጌታ ቃል እናረጋግጣለን። ስለዚህ በእምነት ብቻ መንግ
ሰማያት ለመግባት እንችላለንና ሌላ ነገር አያስፈልገንም እያሉ ከሚናገሩ ሰ
ተጠንቀቁ። እነርሱ ከሐዋርያው ጳውሎስ እንዳገኙት ይናገራሉ። ምናልባ
ሐዋርያው በጥበብ የጻፋቸውን መልእክታት ለመረዳት ስላስቸገራቸው አጣም
ተርጉመውት ይሆንን? (2ኛጴጥ.3፥15-18)።

## እምነት ቢቀድምም ከምግባር አይለይም

እንደ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አባባል "እምነት" የሚለውን ቃ
በትክክል ለመረዳት በምን ዓይነት ስሜት በልዩ ልዩ ምንባብ ውስጥ እንደገ
መርምሮና አገናዝቦ መተርጉም ያስፈልጋል። ሐዋርያው እምነት ሲል በፍቅ
የሚሠራ እምነት ማለቱ እንደሆነ ከላይ ገልጠናል (ገላ.5፥6)። ሐዋርያው እ
ነትን አስቀድሞ ሥራን ያስከትላል። በተቃራኒው ሥራን አስቀድመን እምነት
ማስከተል አንችልም። ምክንያቱም እምነት በተለይም የክርስትና እምነት ለመ
ልካም ሥራ ሁሉ ምንጭና መሠረት ስለሆነች ነው። ምንም እምነት ቀድሞ ሥ
ቢከተል ሁለቱ እንደማይለያዩ አንድ አካል እንዳለው ዛፍ ይመስላሉ። ለዛፍ
ሕይወት መጀመሪያ ሥሩና ግንዱ ነው ከዚያ በኋላ ቅርንጫፎቹና ፍሬዎ
ይከተላሉ። እንደዚሁም ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን መጀመሪያው እምነት
ይቀድማል ከዚያ ቀጥሎ ቀስ በቀስ እምነታችን በፍቅርና በጸጋ መንፈስ ቅዱስ
እያደገ ለዘላለም ሕይወት የሚሆን መልካም ሥራን ለማፍራት የበቃ ይሆናል።
ፍሬ ማፍራት የሚችል ዛፍ፥ ፍሬ ካላፈራ ሥሩና ግንዱ በበሽታ ወይም በልዩ
ልዩ ምክንያት ሥሩ እየደረቀ ነው። መልካም ሥራ የሌለው ሰውም እንደዚሁ
በክህደት ወይም በጥርጥር ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት እምነቱ እየቀዘቀዘና
እየጠፋ ከሄደ ተስፋና ፍቅር አይኖረውም፤ በጐ ነገርንም ለመሥራት አያስብም።
እንግዲህ እምነትና ሥራ የማይለያዩ መሆናቸውን ከዛፉ ምሳሌ ተምረናል።
ክርስቲያኖችም መልካም የሥራ ፍሬ እንዲያፈሩ በክርስቶስ እምነት (ሃይማኖት)
ሥር ሰደው እንደተተከሉ መልካም ዛፎች ናቸው ማለት ይቻላል። ስለዚህ ነው
ሐዋርያው ለኤፌሶን ክርስቲያኖች በጻፈው መልእክቱ በመጀመሪያ በእምነት
(በጸጋው) መዳናቸውን ከገለጸ በኋላ መዳንን ያገኘነው እኛ ሁላችን "መልካሙን
ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን" ያለው።

## ከጥንቱ ከአዳም እዳ በደልና መርገም በእምነትና በጥምቀት በጸጋው ስለ መዳን [77]

ሐዋርያው "ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር
ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም"

[77] በጥምቀት የጥንቱ የአዳም በደል ከአስከተለው መርገም፥ ፍዳና ሞት እኛም ከሠራነው ኃጢአት ሁሉ
እንድናለን። ስለዚህ ነው "ኃጢአትን ለማስተስረይ በአንድ ... ግን እኛ የሠራነው ኃጢአት ብቻ ይሰረይልናል፤ ... ለተፈጸመው አይደለም። (ስለ ጥንተ አብሶ በዚህ መጽሐፍ ... በፊት



ካለ በኋላ ቀጥሎ "እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስ
ቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን"
ሲል ምንማለቱ እንደሆነ እናስተውል (ኤፌ.2፥8-10)። በጥቅሱ መጀመሪያ
ላይ ጸጋው በእምነት አማካይነት እንደ አዳነን የሚያስረዳ ነው። ይህም
የማይታበል ሐቅ ነው። በመሠረቱ ሰው ምንም ዓይነት መልካም ሥራ ይኑ
ረው በሥራው ብቻ ያለ እግዚአብሔር ቸርነትና ጸጋ ለመዳን አይችልም።
ይህማ እውነት ባይሆን ኖሮ ከክርስቶስ በፊት የነበሩት ቅዱሳን ሁሉ በመልካም
ሥራቸው ምክንያት ገነትን ከፍተው በገቡ ነበር[78]። እዚህ ላይ ከሁሉ በፊት
መረዳት ያለብን መዳን ማለት ምን ማለት ነው? መዳን ማለት በመሠረቱ
ከኃጢአትና ከሞት፥ ከሲኦል ግዞትና ከዲያብሎስ ቁራኝነት ነፃ መውጣት
ማለት ነው፤ በአዳም ኃጢአት ከመጣብን ፍዳና በዘር ከወረደው መርገም
መገላገል ማለት ነው። እንግዲህ ሰው በሚያደርገው በማናቸውም የጽድቅ
ሥራ በጥንተ አብሶ ከመጣብን መርገመ ሥጋና መርገመ ነፍስ፥ ሞተ ሥጋና
ሞተ ነፍስ ራሱን አድኖ ገነት መንግሥተ ሰማያት መግባት አይችልም።
ስለዚህ ከእነዚህ ከተጠቀሱት መሠረታዊ ነገሮች የምንድነው በእምነት አማካይ
ነት በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው።

በእግዚአብሔር ጸጋ በእምነት መዳናችን እንደ ተጠበቀ ሆኖ በጥቅሱ
መጨረሻ እንደ ተገለጸው በጸጋው የዳኑት ሁሉ "መልካሙን ሥራ ለማድረግ
በክርስቶስ ኢየሱስ" የተፈጠሩ መሆኑን ያረጋግጣል። ስለዚህ ይህ ጥቅስ
ሁለቱም ማለት እምነትና ምግባር በክርስቲያናዊ ሕይወታችን ውስጥ መከናወን
እንዳለባቸው ያስረዳናል። ሁለቱንም በአንድነት መያዝ ይኖርብናል። አንዱን
ይዞ ሌላውን ማጣጣል ለዘላለማዊ ሕይወት አያበቃንም።

## በጥምቀት ወቅትና በኋላ የመዳንና ያለመዳን ጥያቄ

እንግዲህ ያለ ሥራ በእምነት ድነናል የተባለው በጥንተ አብሶ ማለት
ከመጀመሪያው በአዳም በደልና ኃጢአት ምክንያት ከመጣብን ፍዳና መርገም
ከሞት ሞትም መዳናችንን ለመግለጽ እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል። ይህም
የመዳን ጸጋ በጥምቀት ጊዜ ሲሰጥ የተጠማቂው ኃጢአት ሁሉ ይሠረይለታል።
የአዳም በደል ካስከተለው መርገም ሁሉ በጥምቀት ይድናል። ብፁዕ አቡ
ነ ጎርጎርዮስ ካልእ እንዳስተማሩት፥ ሰዎች ሁሉ በማናቸውም የዕድሜ ክልል
ሲጠመቁ ሕፃናትም "በአርባ በሰማንያ ቀናቸው ሲጠመቁ በዘር ከወረደው
መርገም ይገላገላሉ"።[79] ከዲያብሎስ ቁራኝነት ይላቀቃሉ። በእምነትና
በጥምቀት የምናገኘው መዳን ይህ ነው። በሥራችን ሳይሆን በእምነት አማካይ
ነት በጸጋው የመዳናችን መጀመሪያውና መሠረቱ ይህ ነው። እዚህ ላይ
ተጠማቂው በመልካም ሥራው ሳይሆን በእምነትና በጥምቀት መዳኑን እንገ

[78] "ንጹሕ ይሆን ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ጻድቅስ ይሆን ዘንድ ከሴት የተወለደ ምንድር ነው? እነሆ፥ በቅዱሳኑ ስንኳ አይታመንም፤ ሰማያትም በፊቱ ንጹሐን አይደሉም። ይልቁንስ አስጸያፊና የረከሰ፥ ኃጢአትንም እንደ ውኃ የሚጠጣ ሰው ምንኛ ያንስ?" የተባለውን እናስተውል (ኢዮ.15፥14-16)። "ምሕረትም በፍርድ ላይ ይመካል" የተባለውም በበደላችን የዘላለም የፍርድ ቅጣት ሲገባን ሳለ ጌታ ግን በምሕረቱ ብዛት ይቅርታ በማድረጉ ከፍርዱ ይልቅ የቸርነቱ ሥራ እንዳየለ ያሳየናል (ያዕ.2፥13)። እን ግዲህ ማንም በራሱ የጽድቅ ሥራ ብቻ የዳነ የለም። አብርሃም "ራሱን ስንኳን ከሲኦል ለመርዳት አል ተቻለውም። የበኹር (የበኵር) ልጅሽ ግን በሞቱ ብዙውን አዳነ" የተባለውን ተመልከት (አርጋኖን ዘኀሙስ ምዕራፍ 5)።

[79] ትምህርተ ሃይማኖት ርትዕት፤ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ... ቅዱሳን ትምህርት ክፍል፤ በየሰንበት ት/ቤቶች ለሚማሩ የከፍተኛ ትምህርት ተጽግት ማስተማሪያ የተዘጋጀ፤ መስከረም 1993 ዓ.ም.፤ ገጽ 43 ተመልከት

www.ethiopianorthodox.org

ነዘባለን፡፡ ምክንያቱም ማንም ሰው በበጐ ምግባሩና ትሩፋቱ በገዛ ጉልበቱ ከዲያብሎስ ቁራኝነት ከሲኦል ግዞት ራሱን በራሱ ሊያድን አይችልምና ነው፡፡ እንግዲህ እዚህ ላይ ብቻ ነው ያለ ሥራ በጸጋው በእምነት አማካኝነት መዳናችንን የምንናገረው፤ ይህም ለክርስትና ሕይወታችን መሠረት ነው፡፡ ከእዚህ ጊዜና ወቅት ጀምሮ ነው በሐዲስ ተፈጥሮ አዲስ ልደትን የምናገኘው፤ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት የምንሆነው፡፡ የኃጢአት ሥርየት አግኝተን ከእግዚአ ብሔር ጋር መታረቃችን በክርስቶስ ቤዛነት ስለሆነ የክርስትና ሃይማኖታችን መሠረት በክርስቶስ እምነትና ጸጋ ላይ ጸንቶ ይኖራል፡፡

በእምነትና በጥምቀት ያገኘነው የመዳን ጸጋ ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን መወለድ የአዲስ ልደት መሠረት ሆኖን የክርስቶስን ትእዛዛት እየጠበቅን ካላደግንና ካልኖርን ተስፋና ሕይወት አይኖረንም፡፡ ወዲያው እንደ ተጠመቅን ከዚህ ዓለም በሞት ብንለይ የመዳን ጸጋና የዘላለም ሕይወት አለን፡፡ ነገር ግን ከጥምቀት በኋላ የምንኖረው ሕይወት የክህደትና የዓመፅ ኑሮ ከሆነ የቀደመው እምነትና ጥምቀታችን ብቻውን አያድነንም፡፡ ምክንያቱም የቀደመውን እምነታችንንና የጥምቀቱን ቃል ኪዳናችንን እኛው ራሳችን በራሳችን በማፍረሳችን ነው፡፡ ለዚህም ምሳሌ የሚሆነንን ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት የዳኑትን የሕዝበ እሥራኤል ታሪክ እናስታውስ፡፡ የእምነትና የጥምቀት ምሳሌ የሆነውን ቀይ ባሕርን በተአምራት ከተሻገሩ በኋላ ከባርነት ነፃ አድርጐ ያዳናቸውን የአምላካ ቸውን ትእዛዛት ባለመፈጸማቸው ቃል ኪዳኑን ባለመጠበቃቸው ምድረ ርስት ሳ ይገቡ የቀሩ ብዙዎች ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር ቃልና ትእዛዛቱን የፈጸሙት እሥራኤላውያን ግን ከምድረ ርስት ገብተዋል፡፡ ይህም ታሪክ ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን ምሳሌ እንደሆነ ከሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ተምረናል (1ኛቆ ሮ.10፥1-12)፡፡

በጥምቀት ወቅትና ከዚያም በኋላ ለምንኖረው ክርስቲያናዊ ሕይወት ከላይ ከጠቀስነው ከሐዋርያው መልእክትና ከእሥራኤላውያን የባርነትና የነፃነት ታሪክ ትምህርት መውሰድ ይገባናል፡፡ እሥራኤላውያንንም ሆነ ክርስቲያኖችን ያዳነ አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ የብሉይ ታሪክ ለሐዲሱ ምሳሌና ትምህርት ሆኖ እንዲያገለግለን ተጽፎልናል፡፡ ንጉሡ ፈርዖን እንደ አንጡራ ገን ዘቡ የሚቆጥራቸውን ባሮቹን እሥራኤልን አልለቅም በማለት ለብዙ ዘመናት ቀጥቅጦ ሲገዛቸው ኖሯል፡፡ ኃያል እግዚአብሔር አምላክነቱን ለማሳወቅ በዘጠኝ መቅሠፍት በአሥረኛው ሞተ በኵር ግብፃውያንን መታ፤ ወገኖቹን እሥራኤ ላውያንን ግን በፋሲካው በግ ደም አማካይነት ታድጓቸዋል (ዘጸ.12)፡፡ እሥራኤ ላውያን በዚያች ሰዓት ነፃነታቸውን አግኝተው መንገድ ከጀመሩ በኋላ ባሮቹን አ ለቅም በማለት እንደገና በቁጭትና በንዴት ተነሣሥቶ ወደ ባርነት ሊመልሳቸው በሙሉ ኃይሉ ከነሠራዊቱ እስከ ቀይ ባሕር ድረስ ተከታትሎ በመጣባቸው ጊዜ በእግዚአብሔር ተአምራዊ ኃይል ሁሉም በባሕሩ ውስጥ ሰጥመው አልቀዋል (ዘጸ.14)፡፡ እሥራኤላውያን ግን ከሙሴ ጋር በመተባበር ባሕሩ ተከፍሎላቸው በየብሱ ላይ በሰላም አልፈዋል፡፡ ስለዚህም "አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ፤ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ" ተብሎ ተጽፏል (1ኛቆሮ.10፥1-2)፡፡

ይህ ሁሉ ታሪክ ለእሥራኤል ዘነፍስ ምሳሌ ነው፡፡ የመጀመሪያው አባ ታችን በጥፋቱ ከእግዚአብሔር ከተለየ ጊዜ ጀምሮ እርሱና የእርሱ ዘር ሁሉ በመንጸፈ ደይን ወደቁ፥ በእግረ አጋንንት ተጠቀጠቁ፥ በዲያብሎስ ቁራኝነት ተያዙ፡፡ ዲያብሎስ የአዳምን ዘር ሁሉ እየተቆራኘ [illegible] ዲወርድ ነፍሱ ሲኦል እንድትገባ [illegible]

www.ethiopianorthodox.org



ል ኩ "የዲያብሎስን ሥራ እንዲፈርስ" በማድረግ (1ኛዮሐ.3፥8) አዳምና ልጆቹን አድኖአቸዋል፤ ከዲያብሎስ ቁራኝነት ነፃ አውጥቷቸዋል፡፡ ይህም የተፈጸመው በዕለተ ዓርብ ጌታችን በአፀደ ነፍስ ከሲኦል ወርዶ በሰይጣን ምርኮኝነት ታሥረው የነበሩትን ነፍሳት ከሲኦል አውጥቶ ገነት ባስገባቸው ጊዜ ነበር (1ኛጴጥ.3፥18-19)፡፡ እስከ ስቅለት ዓርብ ድረስ የሞቱት ቅዱሳን አ ባቶች ነፍስ ሁሉ ከሲኦል ሆነው በእደ እግዚአብሔር ተጠብቀው የተስፋውን መምጣት የገነትን መከፈት ሲጠባበቁ ቆይተዋል፤ እግዚአብሔርም ፈጽሞ ላቸዋል፡፡

በዓመተ ኩነኔ ሲኦል ብቻ ለሁሉም ነፍሳት ክፍት ሆና ትገኝ ነበረች፡፡ ከክርስቶስ በኋላ ግን ገነትም ሲኦልም ክፍት ሆነው የሚገባባቸውን ይጠባበቃሉ፡፡ ዛሬ በክርስቶስ አምኖ የተጠመቀ ከሞት ወደ ሕይወት ይሸጋገራል፤ ከፍዳና ከመርገም ይገላገላል፤ ከዲያብሎስ ቁራኝነት ይላቀቃል፡፡ ምንም ሥጋው ወደ መቃብር ቢወርድ በነፍሱ ገነት ይገባል እንጂ ሲኦል አይ ወርድም፡፡ ሥጋውም ቢሆን ከተለየችው ነፍስ ጋር ተዋሕዶ ትንሣኤ ዘለክብርን ይጠብቃል፡፡ እስራኤል ዘሥጋ በሙሴ አማካይነት ባሕሩን እን ደተሻገሩና (ሁሉም ከእርሱ ጋር በመተባበር በደመናና በባሕር በመጠመቅ) ከፈርዖን ቁራኝነት ነፃ እንደወጡ እንደዚሁም እሥራኤል ዘነፍስ የተባልን ክርስቲያኖች በጌታ ስም አምነን ስንጠመቅ ከክርስቶስ ጋር አንድ በመሆናችን ከዲያብሎስ ቁራኝነት ነፃ ወጥተናል፡፡ እንግዲህ ይህ ነፃነትና ደኅንነት በእግዚአብሔር ቸርነት በፍቅሩና በጸጋው ብቻ የተገኘ እንጂ ማንም በሥራው መልካምነት ወይም በራሱ ብርታት አላገኘውም፡፡ በእሥራኤል ዘሥጋ ታሪክ እንደ ተገነዘብነው ከፈርዖን ቁራኝነትና ከግዞት አገር ነፃ የወጡት በእግዚአ ብሔር ተአምራዊ ኃይልና የቸርነት ሥራ ብቻ ነው እንጂ ማንም እሥራኤላዊ በጽድቅ ሥራውና በገዛ ጉልበቱ አላደረገውም፡፡

ለእስራኤል ዘሥጋም ሆነ ለእሥራኤል ዘነፍስ የተፈጸመው የመዳንና የነፃነት ታሪክ በሰው በጎ ሥራና ጽድቅ ሳይሆን በእግዚአብሔር የምሕረትና የቸርነት ሥራ እንደሆነ እናምናለን፡፡ እንግዲህ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ጸጋው በእምነት አድኗችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም" (ኤፌ.2፥8-9) ያለውን በዚህ ታሪካዊ የአምላክ ሥራና ስጦታ እንረዳዋለን እንተረጉመዋለን፡፡ ይልቁንም እግዚአብሔር ሰውን እንደዚሁ በመውደዱ የተነሣ በልጁ ቤዛነት እንዲሁ በጸጋው ማዳኑን ጥቅሱ ያስገነዝበናል፡፡ እረ ለመሆኑ በእግዚአብሔር ምሕረትና ቸርነት ባይሆን ኖሮ፥ በልጁ ቤዛነት ባይሆን ኖሮ ከጥንተ ጠላታችን ከዲያብሎስ ቁራኝነት ማን ያድነን ነበር? የተዘጋችውንስ ገነት ከፍቶ ማን ይሰጠን ነበር? የሰው ሥራማ ገነትን እንድትዘጋ አደረጋት፤ የእግዚአ ብሔር የቸርነቱ ሥራ ግን ዳግመኛ እንድትከፈት አደረገልን፡፡ ስለዚህ ነው ሐዋርያው የመዳናችንን ነገር ሲያስረዳ "የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም" ያለው፡፡ ይህም የሚያሳየን በዘመኑ የነበሩ አይሁዳውያን ክርስቲያኖች መዳንና መጽደቅን በራሳቸው በጎ ሥራ ብቻ እንደሚያገኙ ያስቡ ስለነበር ይህ ነገር እውነት እንዳልሆነ ለማሳመን ሐዋርያው "ማንም እንዳ ይመካ ከሥራ አይደለም" በማለት ይመልስላቸዋል፡፡

እንግዲህ "የእግዚአብሔር ስጦታ" ለሥራችን ዋጋ ሆኖ እንደሚሰጠንና እኛም ለዚሁ ባለመብት እንደሆንን ራሳችንን እንዳንቆጥር ሐዋርያው ትኅትናን ለማስተማር "ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም" አለ እንጂ በጎ ሥራ አያ [illegible] አይደለም፡፡ በሥራችን መመካትን ትተን የታዘዝነውን

"የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ፡ የማንጠቅም ባሪያዎች ነን፤ ልና[...] ገው የሚገባንን አድርገናል በሉ" ሲል ትጎትናን ከሥራ ጋር እንድንይዝ አስ[...] ተምሮናል (ሉቃ.17፥10)።

እስካሁን ለማስረዳት የሞከርነው እኛ ክርስቲያኖች ከፍዳና ከመርገ[...] መዳናችን፡ ከዲያብሎስ ምርኮኝነት ነፃ መውጣታችን በእኛ ኃይልና በጽ[...] ሥራችን ሳይሆን በእግዚአብሔር የምሕረትና የቸርነት ሥራ እንዲሁ በጸጋ[...] ብዛት የተደረገ መሆኑን ለማሳየት ነው። ይህንንም የመዳን ጸጋና ሰማያ[...] በረከት በክርስቲያናዊ ሕይወታችን መጀመሪያ ላይ ለአንድ ጊዜ ብቻ በማ[...] መው በምሥጢረ ጥምቀት አግኝተነዋል። ከጥምቀት በኋላ ግን እምነታችን[...] በሥራ እየገለጽን የእግዚአብሔርን ትእዛዝና ቃል ኪዳን እየጠበቅን መኖ[...] ግዴታችን ነው። ትእዛዛትን ካልጠበቅን በጎ ሥራም ከሌለን የተስፋውን አገ[...] ለመውረስ አንችልም። ይህንንም እንደሚከተለው እናሳያለን።

የጥምቀት ምሳሌ የሆነውን ቀይ ባሕርን ተሻግረው ከባርነትና ከሞ[...] ድነው ነፃ የወጡት እሥራኤላውያን በሙሉ ነበሩ። ነገር ግን ሁሉም ምድ[...] ርስት አልገቡም። የእግዚአብሔርን ሕግና ትእዛዝ የጠበቁት ምድረ ርስት ገብተዋል፤ ያልጠበቁት ግን ምድረ ርስት ሳይገቡ በበረሃ ወድቀው ቀርተዋል። ይህም ለክርስቲያኖች ሁሉ ምሳሌ ሆኗል። በጥምቀት የኃጢአትና የሞት ባሕርን ከተሻገሩ በኋላ ብዙዎች ስመ ክርስቲያኖች በአርባው ዓመት የበረሓ ኑሮ በተመሰለው ምድራዊ ኑሯቸውና በተሰጣቸው ዕድሜያቸው የጌታን ትእዛዛትና ቃል ኪዳን ሳይጠብቁ ወደ ጥንት ጥፋታቸው የሚመለሱት ሁሉ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንደማይገቡ ተጽፏል (1ኛቆሮ.6፥9-10፤ ገላ.5፥19-21፤2ኛጴጥ.2፥19-22)። ትእዛዛቱን የጠበቁት ግን ሰማያዊ ርስትን የዘላለም ሕይወትን ይወርሳሉ (ሉቃ.10፥25-28)። ስለዚህ ነው ጌታችን ወደ ሕይወት ለመግባት የሚፈልግ ሁሉ ትእዛዛትን እንዲጠብቅ ያዘዘው (ማቴ.19፥16-19፤ሉቃ.10፥25-28)። እንግዲህ አምነው ከተጠመቁ በኋላ ሀገረ ሕይወት ገነት መንግሥተ ሰማያትን መውረስ የሚቻለው የጌታን ትእዛዛት በመጠበቅ እንደሆነ ተምረናል። ይህም ማለት በጸጋው ሥር አይደለንም፤ በጸጋውም አልዳንም ማለት አይደለም። በጸጋውና በቸርነቱ ያዳነን አምላክ ትእዛዛትን ደግሞ እንድንጠብቅ ያዘዘን እርሱ ነውና ቃሉን ሰምተን መፈጸም ይገባናል። ትእዛዙን ማለት የጌታን ቃሉን "የሚጠብቅ ቢኖር ለዘላለም ሞትን አያይም" ተብሎ ተጽፏልና (ዮሐ.8፥51)።

እንግዲህ እሥራኤል ዘሥጋ ቀይ ባሕርን መሻገራቸው፡ ከፈርዖን ባርነት ነፃ መውጣታቸው ለመዳናቸው መሠረት ቢሆንም የአዳኛቸውን ትእዛዝ ባለመጠበቃቸው ምድረ ርስት ለመግባት አልጠቀማቸውም። እንደዚሁም ክርስቲያኖች እምነትና ጥምቀት ለመዳናቸው መሠረት ቢሆናቸውም የጌታን ትእዛዛት ባለመፈጸማቸው ግን መንግሥተ ሰማያት ለመግባት አላስቻላቸውም። ይህም ከእኛ ከሰዎች ዳግም ጥፋትና የዓመፅ ሥራ እንጂ ከእግዚአብሔር አይደለም። ስለዚህ እነርሱ በበረሓ ወድቀው እንደቀሩ እኛም እንዳን ወድቅ ሁልጊዜ ተዘጋጅተን እንኑር (ሉቃ.12፥40)። "እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ" (1ኛቆሮ.10፥12)።

ብናውቅበትስ ኖሮ በእምነትና በጥምቀት ያገኘነው ጸጋው ይበቃን ነበር። ብናውቅበት እኮ ከቤተ ክርስቲያን በምናገኘው ጸጋና በረከት ተደግፈን ትእዛዛትን ለመጠበቅና ክርስቲያናዊ ሕይወታችንን ለማጠናከር እንችላለን። የእኛ ችግር አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ አዳልጦን ከወደቅን ተስፋ እን ቆርጣለን። ስሕተታችን ከዚህ ላይ ነው። ጻድቅ እኮ ሰባት ጊዜ ቢወድቅ ተስፋ ሳይቆርጥ ሰባት ጊዜ ይነሣል (ምሳ.24፥16)።

www.ethiopianorthodox.org



እግዚአብሔር እኮ ለዘላለም የታመነ ነው፤ ምሕረቱም ለዘላለም ነው። የእርሱን ታማኝነት አውቀን ብንተማመነው ፍጡሮቹ ነንና ፈጽሞ አይተወንም አይጥለንም፤ ወደማንችለውም ፈተና እንድንገባ አይፈቅድም።

ቅዱስ ጳውሎስ የቆሮንቶስ ምእመናንን ሲያጽናና "ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም" ብሏቸዋል። ቀጥሎም " ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፤ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል" በማለት ለእነርሱ የመከራቸው ምክር ለእኛም መጽናኛ ስለሚሆን በዚህ ቃል ክርስቲያናዊ ሕይወታችንን ማጠናከር ይገባናል (1ኛቆሮ.10፥13)። (ክርስቲያናዊ ሕይወታችን በጸጋ መንፈስ ቅዱስና በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን እንደሚጠናከር በዚህ ምዕራፍ በፊደል (ረ) የተጻፈውን ተመልከት)

ክርስቲያናዊ ሕይወታችን የመዳን ጸጋ ያለበት ሕይወት ነው። ክርስቲያናዊ ሕይወት የተስፋ መንግሥተ ሰማያት ሕይወት ነው። ክርስቲያናዊ ሕይወት ሰማያዊ ርስትን ለመውረስ የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ ነው። ጉዞውም ከጥምቀት በኋላ ይጀምራል።

በእምነትና በጥምቀት ያገኘነው አዲስ ልደትና አዲስ ሕይወት እንደ አዲስ ተክል ስለሆነ ክርስቲያናዊ ሕይወታችን ባገኘው የመዳን ጸጋ ተበረታትቶ እንዲያድግና ለፍሬ እንዲደርስ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለብን። ስለ አዲሱ ክርስቲያናዊ ሕይወታችን አስበን በትጋት መጸለይና መሥራት እንጂ እንዲያው በቸልተኝነት መኖር አይገባንም። "በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ" የተባለውን መመሪያ መከተል ይኖርብናል (ፊልጵ.2፥12)። አዲሱ ሕይወታችን በእግዚአብሔር ቃል ታርሞና ተኰትኵቶ ካላደገ ትእዛዛቱንም በመጠበቅ ካልጸና ለዘላለም ሕይወት የሚያበቃ ፍሬ አይኖረውም። ስለዚህ ለመዳንና ለመጽደቅ፡ መንግሥተ ሰማያት ለመግባትና የዘላለም ሕይወትን ለመውረስ የእግዚአብሔርን ፍቅርና የክርስቶስን የማዳን ሥራ መሠረትና መነሻ በማድረግ በአጠቃላይ ሃይማኖትን ከምግባር ጋር ምግባርን ከሃይማኖት ጋር አስተባብረን መያዝ አለብን፤ ይህም ማለት፡- (1) በእምነት ማለት በሃይማኖተ ክርስቶስ (በሃይማኖተ ወንጌል) መጽናት፡ (2) ከጥምቀት ጋር ሌሎች ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን መፈጸም፡ (3) የፍቅር ትእዛዛትንና ምግባረ ወንጌልን በአጠቃላይ የጌታን አርአያ በመከተል በጎ ነገሮችን ሁሉ በተቻለ መጠን በሥራ ላይ ለማዋል ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።[80] ይህም ሆኖ ለመዳናችንና ለመጽደቃችን ከጥምቀት ጋር እምነት መሠረቱን አይለቅም።

ስለዚህ ነው ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ "እምነት መሠረት ናት ሌሎቹ ደግሞ ግርግዳና ጣራ ናቸው" ያለው። ግርግዳና ጣራ ማለትም ትእዛዛትን ከመጠበቅ ጋር መልካም ሥራዎችን፡ በጎ አድራጎትንና መንፈሳዊ ተጋድሎዎችን ሁሉ ያጠቃልላል። እንግዲህ ያለ ሥራ በእምነት ብቻ መዳናችን ብዙ ቦታ በአጽንኦት የሚነገርበት ምክንያት እምነት ብቸኛ መሠረት መሆኗን

[80] እነዚህ ሦስቱ ለመዳናችንና ለመጽደቃችን በአጠቃላይ በወንጌል ቃልና ሕግ የታቀፉ ናቸው። በአጠቃላዩ ሕግና ትእዛዝ የማይካተቱ አልፎ አልፎ አንድ ወይም ሁለት ተብለው በጣት የሚቆጠሩ ጥቂት የታሪክ ሁኔታዎች ቢገኙ እነርሱን እንደ ማስረጃ ጠቅሶ መከራከር ያለ ማስተዋል ይሆንብናል። ለምሳሌ ፈያታዊ ዘየማን (በጌታ ቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ) ጥምቀትን ሳይፈጽም ትእዛዛትን ሳይጠብቅ ገነት ገብቷልና ለመዳናችንና ለመጽደቃችን እምነት ብቻ ይበቃናል ብሎ መደምደምና መወሰን ከወንጌል እውነት ውጭ ያደርገናል። በመሠረቱ ይህ ታሪክ እንደ ልዩ ነገር ተወስዶ በጌታ የማዳን ሥራ ውስጥ የሚነገር ልዩ ትርጉምና መልእክት ያለው ነው እንጂ እኛ የዘላለም ሕይወት እንድናገኝ ጌታ ያዘዘውን እንዲቃረን አድርጎ መጥቀስ አይገባም። በአጠቃላዩ የወንጌል ሕግና ደንብ ውስጥ የማይመደቡትን በዓይነታቸውና በታሪካዊ ይዞታቸው ልዩ የሆኑትን ነገሮች እየጠቀሱ እንደ መደበኛው የሕግ አንቀጽ አድርጎ [illegible] "Exceptions are not rules" እንደ ተባለው አንዳንድ የተለዩ ነገሮች ወይም [...]ም አጋጣሚዎች ወይም እነዚህን የመሳሰሉ ሁሉ ደንቦችና ትእዛዞች አ[...]

ለመግለጽ ነው እንጂ ሌሎቹ እንደ ግርግዳና ጣራ የመሳሰሉት የ... ሥራዎች አያስፈልጉም ለማለት አይደለም፡፡ ቤት ሲሠራ በመጀመሪያ ... መሠረት ያስፈልገዋል፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ግርግዳውና ጣራው ይሠራል እንጂ ... በመሠረት ብቻ አይቀርም፤ አለበለዚያማ ቤቱ ቤት አይባልም፡፡ ቤቱን ... የሚያሰኘው ከመሠረት እስከ ጣራ ድረስ ያለው ሁሉ ተጠናቆ ሲሠራ ነ... ስለዚህ መንፈሳዊ ቤታችንና ክርስቲያናዊ ሕይወታችን በእምነትና በጥ... ላይ ተመሥርቶ በምግባርና በትሩፋት የተገነባ፡ በንጽሕናና በቅድስና የ... መሆን ይገባዋል፡፡

እንግዲህ "እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አ... ቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠ... የተባለው በእምነታችንና በምግባራችን አኳያ እየተገናዘበ ይተረጉማል (... ፌ.2፥8-10)፡፡ "እኛ ፍጥረቱ ነን" ሲል በጥንተ ተፈጥሮ ያገኘነ... የመጀመሪያውን ልደታችንን ያመለክታል፡፡ "በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠ... ሲል በሐዲስ ተፈጥሮ ያገኘነውን ዳግም ልደታችንን የሚያስረዳን ቃል ነ... በክርስቶስ መፈጠር ማለት በክርስቶስ አምኖ በመጠመቅ በአዲስ ልደት አዲ... ፍጥረት መሆን ማለት እንደሆነ ከሌሎቹ የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክ... ለመረዳት እንችላለን (2ኛቆሮ.5፥17፤ ገላ.6፥15)፡፡ በክርስቶስ የተፈጠርንበት ... ላማ መልካም ሥራ ለማድረግ እንደሆነ ከላይ ከኤፌሶን መልእክት የጠቀስነ... ያረጋግጥልናል፡፡ ስለዚህ በክርስቶስ መፈጠር ማለት በእርሱ አምነንና ተጠም... በአዲስ ልደት አዲስ ሰው መሆናችንን ስለሚያመለክት እንግዲህ በክርስ... የማመናችንና አዲስ ሰው የመሆናችን ዓላማ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘ... ውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ እንደሆነ ለማወቅ እንችላለን፡፡ በሌላ አገላለ... እምነት ይኸውም የክርስትና እምነት በፍቅር የሚሠራ እምነት ስለሆነ የመልካ... ሥራን ዓላማን በውስጡ የያዘ ነው፡፡ ያለ ፍቅር ሥራ (ያለ መልካም ሥራ) ... እምነት አይኖርም፤ ያለ ክርስቶስ እምነት፡ መልካም ሥራ የለም፡፡ ሁለቱን... በአግባቡ መያዝ ክርስቲያናዊ ሕይወታችንን የተሟላ ያደርገዋል፡፡

## ከእምነት ጋር ሰባት ነገሮችን እንያዝ

ክርስቲያናዊ ሕይወታችን በእምነትና በምግባር እንዲሟላና ፍጹም እ... ዲሆንልን በእምነታችን ላይ ሰባት ነገሮችን መጨመር ያስፈልገናል፡፡ "እነዚህን ... ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉምና" ይላል ሐዋርያው ጴጥሮስ፡ በመቀጠልም "ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት መግባት በሙላት ይሰጣችኋልና" በማለት በእነርሱ ምክንያት የተስፋችንን ፍጻሜ እንደምናገኝ ያረጋግጥልናል (2ኛጴጥ. 1፥10-11)፡፡ እንግዲህ በእምነት ላይ የሚጨመሩትን ሰባት ነገሮች እ... ደሚከተሉት ስንዘረዝር እነርሱን ለመፈጸም የሚያስችለንን ጸጋና ረድኤት ከእግዚአብሔር እንደምናገኝ በመተማመን ነው፡-

> "በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፥ በበጎነትም እውቀትን፥ በእውቀትም ራስን መግዛት፥ ራስንም በመግዛት መጽናትን፥ በመጽናትም እግዚአብሔርን መም... ሰል፥ እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን መዋደድ፥ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ፡፡ እነዚህ ነገሮች ለእናንተ ሆነው ቢበዙ በጌታችን በኢ... የሱስ ክርስቶስ እውቀት ሥራ ፈቶችና ፍሬ ቢሶች እንዳትሆኑ ያደርጓችኋልና፤ እነዚህ ነገሮች የሌሉት ዕውር ነውና፥ በቅርብም ያለውን ብቻ ያያል፤ የቀደመውንም ኃጢአቱን መንጻት ረስቷል፡፡ ስለዚህ፥ ወንድሞች ሆይ፤ መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ፤ እነዚህን ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉምና፡፡ እንዲሁ ወደ ዘላለሙ ወደ ጌታችንና መድኃ... ኒታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት መግባት በሙላት ይሰጣችኋልና" (2ኛጴጥ.1፥5-11)፡፡



## 3. ስድስቱ ምግባራተ ወንጌልና አፈጻጸማቸው

የክርስትና ሃይማኖታችን ሐቀኝነት የሚለካውና የሚገመገመው በበጎ ...ራችን ነው፡፡ በፍቅር የሚሠራ እምነት ካለን ክርስቲያናዊ ሕይወታችን ...ለመልማል፥ ያብባል፥ ያፈራል፡፡ ሃይማኖተ ወንጌል ከምግባረ ወንጌል ...ር አንድ ሆኖ በክርስቲያናዊ ሕይወታችን ካልተገለጠ ፍሬ ቢስ፥ ዋጋ ቢስ ...ሆ ይቀራል፡፡ በመጨረሻውም ቀን ከሚሰጠው የፍርድ ቅጣት አናመልጥም፡፡ ...ኸንንም ልናውቅ የቻልነው ጌታችን በመጨረሻው ቀን የፍርድ ውሳኔ በሚ...ጥበት በስድስቱ ቃላተ ወንጌል ወይም ምግባራተ ወንጌል ተብለው በሚጠሩት ...ው (ማቴ.25፥31-46)፡፡

### ስድስቱ ምግባራተ ወንጌል፡-

"(1) ተርቤ አብልታችሁኛልና፥
(2) ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥
(3) እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥
(4) ታርዤ አልብሳችሁኛልና፥
(5) ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥
(6) ታሥሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና" በማለት ከሁሉ ለሚያንሱ ወንድሞች ያደረጉትን ለራሱ እንዳደረጉለት አድርጎ በመቀበል የሰው ልጅ ክርስቶስ ንጉሥ በታላቅ ክብር ከቅዱሳን መላእክቱ ጋር መጥቶ በክብር ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ በቀኙ የቆሙትን ጻድቃንን፡- "እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ...ተ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ" ይላቸዋል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ በግራው የቆሙትን ኃጥአንን ንጉሡ ክርስቶስ እን...ዲህ ይላቸዋል፡-

> "እናንተ ርጉማን፥ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ፡፡ ተርቤ አላበላችሁኝምና፥ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና፤ እንግዳ ሆኜ አል ተቀበላችሁኝምና፥ ታርዤ አላለበሳችሁኝምና ታምሜ ታሥሬም አልጠየቃችሁኝ ምና፡፡ እነርሱም ደግሞ ይመልሱና ጌታ ሆይ ተርበህ ወይስ ተጠምተህ ወይስ እንግዳ ሆነህ ወይስ ታርዘህ ወይስ ታመህ ወይስ ታሥረህ መቼ አይተን አላገለገልንህም? ይሉታል፡፡ ያን ጊዜ እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል፡፡ እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ (ማቴ.25፥41-46)፡፡

እንግዲህ በእምነት ብቻ ገነተ መንግሥተ ሰማያት መግባት እንደማይቻል ከጌታ ቃል እንማራለን፡፡ በክርስቶስ፥ እምነት ብቻ ኖሮን በክርስቶስ፥ የፍቅር ሥራ ከሌለን በእምነት ብቻ መዳን አይቻልም፡፡ ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በክርስቶስ ሆነን በፍቅር የሚሠራ እምነት እንደሚጠቅመን የተናገረው (ገላ.5፥6)፤ ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም "ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው" ያለው (ያዕ.2፡26)፤ ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም ክርስቶስን አብነት አድርጎ እንደሚከተለው የጻፈው፡-

> "እርሱ (ክርስቶስ) ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቷልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል፡፡ ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው፥ ወንድሙም የሚያስፈልገውን ሲያጣ አይቶ ያልራ ራለት ማንም ቢሆን፥ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል? ልጆቼ ሆይ፥ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ" (1ኛዮሐ.3፥16-18)፡፡

www.ethiopianorthodox.org

እንግዲህ በመጨረሻው የፍርድ ቀን የምንጠየቀው ስድስቱ ምግባራት ብቻ ናቸውና ሌላ የጽድቅ ሥራዎች አያስፈልጉንም ማለት እንዳልሆነ እናስተውል፡፡ የጽድቅ ሥራ ሁሉ የሚፈጸመው የክርስቶስን ፍቅርና የእርሱንም የጽድቅ ሥራ ተከትለን ለባልንጀሮቻችን (ጠላቶቻችንም ሳይቀሩ) በምናደርግላቸው የእውነተኛ የፍቅር ሥራ ነው፡፡ ስድስቱ ምግባራተ ወንጌል ሕገ ተፋቅሮ የሚገለጥባቸው የጽድቅ ሥራ ፍሬዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ለክርስትና ሃይማኖት ከእነርሱ የበለጠ የፍርድ መስፈርት ሊኖር አይችልም፡፡ ምክንያቱም ፍቅር በተግባር የሚገለ ረጡመው በእነርሱ ስለሆነ ነው፡፡ ፍቅር ደግሞ ከሁሉ በላይ እንደሆነ እናውቃለን (1ኛቆሮ.13)፡፡ ለምሳሌ አሥሩ ቃላተ ኦሪት የፍርድ መመዘኛ ሊሆን ይችላል፤ አሥሩ ቃላትን የፈጸሙና ያልፈጸሙ በማለት ደጎችና ክፉዎችን ለይቶ ፍርድ መስጠት የቀና ይመስለን ይሆናል፡፡ ነገር ግን ከሁሉ የበለጠው ትልቁ መስፈርት አሥሩ ቃላትን መፈጸም ወይም አለመፈጸም ሳይሆን እያንዳንዱ ሰው ለወንድሙ ያለው ፍቅር ምን ያህል እንደሆነ መመዘኑ ላይ ነው፡፡ ለዚህም እውነተኛውና ትክክለኛው መስፈርት ስድስቱ ምግባራተ ወንጌል ናቸው፡፡ እነርሱን የፈጸመ ሁሉ አሥሩ ቃላትን ከመፈጸም በላይ አልፎ ተርፎ መልካሙን ነገር አድርጓል፡፡ ይህም ማለት ከአሥሩ ቃላት በአብዛኛዎቹ በሰው ላይ ክፉ እንዳናደርግ የሚደነግግ፣ የኃጢአትን ሥራ ብቻ የሚከለክል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ስድስቱ ምግባራት ግን ለተቸገሩ ሰዎች መልካም ነገሮችን፣ የፍቅርና የጽድቅ ሥራዎችን በተግባር ማዋላችንን የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡

## መንግሥተ ሰማያት የሚገቡ ባለጠጎች

አሥሩ ቃላትን (ኢታምልክንና ዘጠኙን) ሁሉም ሰው ሊፈጽመው የሚገባ የመጀመሪያ ደረጃ መሠረታዊ ነገር ነው፡፡ ሆኖም እነዚህን የአሥሩ ቃላትን ትእዛዛት ከወንድሙ ይልቅ ገንዘብን አብልጦ ከሚወደድ (ከፍቅረ ንዋይ) ጋር የምንፈጽማቸው ከሆነ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት አያበቁን ም፡፡ ትእዛዛትን ከልጅነቴ ጀምሮ ፈጽሜአቸዋለሁ ያለው ወጣት ባለጠጋ እንኳ ፍጹምነት ደረጃ ሳይደርስ የቀረበት ምክንያት አንድ ዐቢይ ነገር ስለቀረው እንደ ነበር ታሪኩ በወንጌል ተነግሯል፡፡ ይህም የቀረው ነገር ምግባረ ወንጌል ነበር ማለት ይቻላል፤ ይህም ማለት ገንዘቡን ለተቸገሩ ወገኖች ማካፈል ነበር፡፡ ነገር ግን ወጣቱ ብዙ ሀብትና ንብረት ስለነበረው ገንዘቡን እጅግ ይወድ ስለነበረ ለሌሎችም ማካፈል ስላልፈለገ በጣም አዝኖ ከጌታ ተለይቶ ሄደ (ማቴ.19፥16-30)፡፡ ከዚህም ጋር በማያያዝ ጌታችን "ባለጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል" ያለው ከእግዚአብሔር ይልቅ ገንዘባቸውን ከሁሉም በላይ የሚወዱትንና ከእግዚአብሔር ይልቅ በገንዘባቸው የሚተማመኑትን እንጂ እንደነ አብርሃም የመሳሰሉትን ባለጠጎች አይደለም (ማር.10፥23-31)፡፡ እነርሱማ አሥሩ ቃላትን ወንድምን ከመውደድና ምጽዋት ከማድረግ ጋር ማለት ከምግባረ ወንጌል ጋር የፈጸሙ የእግዚአብሔር ወዳጆች ስለሆኑ መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳሉ፡፡

እግዚአብሔርን ለመውደዳችን ምስክሩ ሰውን መውደዳችን ነው፡፡ "ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል?" ተብሏልና (1ኛዮሐ.4፥20)፡፡ እንግዲህ ስድስቱ ምግባራትን በመፈጸም የምናያቸውን ወንድሞቻችንን እንደምንወዳቸው ስለምናሳይ እግዚአብሔርንም እንደምንወድ በዚሁ ይታወቃል፡፡ ስለዚህ ነው ጌታ በመጨረሻው የፍርድ ቀን "እውነት እላችኋለሁ፣ ከሁሉ ከሚያንሱት ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት" ያለው (ማቴ.25፥40)፡፡ ምግባራተ ወንጌል



ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ በአንድነት እንደተፈጸሙ እናስተውል፡፡

ስድስቱ ምግባራተ ወንጌል ክርስቲያን የተባለውን ሁሉ የሚመለከት እንጂ የተወሰኑ ክፍሎችን ለይቶ የሚያስቀር አይደለም፡፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ የሥራ ዓይነቶችና ልዩ ልዩ አገልግሎቶች እንዳሉ የታወቀ ነው፡፡ ሁሉም እንደ ስጦታው ይሠራል እንጂ ያልተሰጠውን የሥራ ዓይነት ካል ሠራህ አይባልም፡፡ ለምሳሌ የማስተማር አገልግሎት የተሰጠው ሰው ግዴታ በአ ስተዳደር ካልሠራህ ተብሎ አይወቀስም፡፡ ነገር ግን በማስተማር ወይም በሌላ አገልግሎት ላይ የተሠማራ ሰው የተጣለብኝን የሥራ ኃላፊነት ከተወጣሁ በማለት ስድስቱ ምግባራተ ወንጌል አይመለከቱኝም ሊል አይችልም፡፡ ምክን ያቱም በመጨረሻው የፍርድ ቀን እኔ መነኩሴ ነኝ እኔ የቤተ ክርስቲያን አገ ልጋይ ነኝ ወይም እኔ ምእመን ነኝ እኔ ከእሥራኤል ወገን ነኝ እኔ ከአሕዛብ ወገን ነኝ ወዘተ. በማለት ራስን በማግለል ከፍርድ ውሳኔ የሚያስቀር ምክን ያት አይኖርም፡፡ ሁሉም እንደየሥራው ይፈረድበታል፡፡ ስለዚህ ምግባረ ወን ጌልን ይልቁንም ስድስቱን ምግባራትን አለመፈጸም በታላቁ የፍርድ ቀን ያስፈርድብናል፡፡

## የስድስቱ ምግባራተ ወንጌል አፈጻጸም

እንግዲህ በታላቁ የፍርድ ቀን ምንም ዓይነት በጎ ሥራ ሳይኖረን በመ ቅረቱ እንዳናፍር በተለይም ስድስቱን ምግባራት ባለመፈጸማችን እን ዳይፈረድብን ከአሁኑ ጀምረን እነርሱን ለመፈጸም እንትጋ፡፡ ሥራችንም ዋጋ እንዳያጣ አፈጻጸሙን እንወቅበት፡፡ በዘልማድ የሚደረገው የአፈጻጸም ሥርዓ ት አንዳንዱ መልካም ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ችግር የሚያስከትሉ ሆነው ተገኝ ተዋል፡፡ ስለዚህ ከተራ የምጽዋት አሰጣጥ ጀምሮ እስከ ተደራጀው የበጎ አድ ራጎት ሥራ ድረስ ሁሉም ነገር በአግባቡና በሥርዓቱ እንዲፈጸም ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ የሁላችንም ኃላፊነት ነው፡፡ ማናቸውንም ምግባረ ወንጌል ስን ፈጽም በክርስቶስ መንፈስና ትእዛዝ እየተመራን መፈጸም እንጂ የግብር ይውጣ ወይም የውዳሴ ከንቱ እንዳይሆንብን መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡ ምጽዋታችንና በጎ ሥራችን ሁሉ በፍቅረ ክርስቶስና በፍቅረ ቢጽ ብቻ ካደረግነው ዋጋችን በሰ ማይ ከፍ ያለ ይሆናል፡፡ አለበለዚያ ምድራዊ ጥቅምንና ትርፍን እየፈለግንና እየወደድን የምናደርገው ሁሉ በሰማዩ አባታችን ዘንድ ዋጋ አይኖረውም፡፡ እያን ዳንዱ ምግባረ ወንጌል የራሱ የሆነ የአፈጻጸም መንገድ ቢኖረውም ሁሉም ከእው ነተኛ ክርስቲያናዊ ፍቅር የመነጨ እስከ ሆነ ድረስ ዓላማና ግቡ የተሳካ ይሆናል፤ በእግዚአብሔርም ዘንድ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

ስድስቱ ምግባራተ ወንጌልን በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ የመጀመሪ ያዎቹ አራቱ ለሰው ልጆች መሠረታዊ ፍላጎቶችን የሚያሟሉ ሲሆኑ ሌሎች ሁለቱ ደግሞ ሰዎች በግል ጤናቸውና በማኅበራዊ ኑሯቸው የሚያጋጥሟቸውን ችግርና ፈተና ያመለክታሉ፡፡ እንግዲህ እነዚህን በአጭር በአጭሩ እንደሚከ ተለው እንመለከታለን፡፡

### (1) ተርቤ አብልታችሁኛልና፣ (2) ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፡-

የተባሉት ቃላተ ወንጌል የሚያመለክቱት የተራቡትንና የተጠሙትን ወገኖች በአ ግባቡና በሥርዓቱ የመገቡትን በጎ አድራጊዎች ሲሆን ጌታም "ቡሩካኑ ለአቡየ" በማለት መንግሥተ ሰማያትን ያወርሳቸዋል፡፡ "ብፁዓን ዘይሌቡ ላዕለ ነዳይ ወምስኪን" (መዝ.40፥1) እንደተባለ ለተቸገሩ ወገኖች እንደ እኔ ይርባቸዋል እንደ እኔ ይጠማቸዋል በማለት ከልብ አስበው የሚረዱ ሁሉ ብፁዓን ናቸው፡፡ ... ችሮታችንን በአግባቡ ካልፈጸምነው ከጥቅሙ ጉዳቱ

www.ethiopianorthodox.org

ያመዝናል፡፡ አንዳንድ ግለሰቦችና ድርጅቶች ነዳያንን ሃጠቀሙ እየመሰላቸ በአንድ ቀን ግብዣ ከመጠን የበለጠ ሲያበሏቸውና ይልቁንም የሚያሰክ መጠጥ ሲሰጡዋቸው ይታያል፡፡ በዚህም የተነሣ ከነዳያን መካከል አንዳን ቹ አምባጓሮ ለመፍጠር ስለሚችሉ ሁሉም ነገር በመጠኑና በልኩ ማድረግ የተሻለ ይሆናል፡፡ የነዳያንን የጉስቊልና ኑሮ በማየት የምንረዳቸው ሥጋቸው ብቻ ሳይሆን ነፍሳቸውንም ጭምር በሚጠቅም መልኩ መሆን ይገባዋል፡፡ በተናጠል የሚደረገው የዕለት በዕለት ምጽዋት ጠቃሚነቱ በተግባር የታመ ቢሆንም በተደራጀ መልኩ ከመንፈሳዊ ትምህርትና ምክር ጋር ቢፈጸም በጎ አድራጊውን ያስመሰግናል፤ ተጠቃሚውም በአግባቡ ይረዳል፡፡

ረሃብና ጥም ጊዜ አይሰጡም፤በቀጠሮ የሚፈጸም ነገር አይደለም፡፡ ስለዚህ በየዕለቱ በምናደርገው የማዕድ ጸሎት ነዳያንን እያሰብን ለእነርሱ የሚሆን የዕለት ጉርስ እናዘጋጅላቸው፡፡ ይህን ማድረግ እንኳ ባይቻለን ገንዘብ ያላቸውን ባዕለጸጎች አስተባብረን ነዳያንን መርዳት ይገባናል፡፡ ሌላው እንኳ ቢጠፋ ንጹሕ ውኃ እንዲያገኙ እናድርግ፡፡ ቀዝቃዛ ውኃ መስጠት ከፍተኛ ዋጋ እንዳለው ጌታችን አስተምሯል፡፡ "ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ፥እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም" (ማቴ.10፥42)፡፡

ምእመናን በሚያደርጉት ግብዣ ሁሉ ነዳያንን እንዳይረሱ ያስፈል ጋል፡፡ በእግዚአብሔር ስም ወይም በቅዱሳን ስም በሚያደርጉት ዝክር ሁሉ ዘመድ ወዳጅን ብቻ ከመጥራት ይልቅ ነዳያንን መጋበዝ በእግዚአብሔር ዘንድ ከፍ ያለ ዋጋን ያሰጣል፡፡ ስለዚህ በሰንበቴያችንም፥ በማኅበራችንም ወይም በመሳሰለው ሁሉ ድሆችንና አካለ ስንኩሎችን በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ የተያዙትን ነዳያንን ማብላትና ማጠጣት ታላቅ የጽድቅ ሥራ ነው፡፡ የምግባረ ወንጌል አፈጻጸም ማለትም እንደዚህ ነው፡፡

"ምሳ ወይም እራት ባደረግህ ጊዜ፥ እነርሱ ደግሞ በተራቸው ምናልባት እን ዳይጠሩህ ብድራትም እንዳይመልሱልህ፥ ወዳጆችህንና ወንድሞችህን ዘመዶችህንም ባዕለጠጐች ጐረቤቶችህንም አትጥራ፡፡ ነገር ግን ግብዣ ባደረግህ ጊዜ ድሆችንና ጉንድሾችን አንካሶችንም ዕውሮችን ም ጥራ፤ የሚመልሱት ብድራት የላቸውምና ብፁዕ ትሆናለህ፤ በጻድቃን ትንሣኤ ይመለስልሃልና" (ሉቃ.14፥12-14)፡፡

(3) <u>እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና</u>፡- በማለት ጌታ መንግሥቱን እንዲ ወርሱ የጠራቸው ቡሩካን እንደ እነ አብርሃም እንግዳ መቀበልን የሚያዘ ወትሩትን ነው፡፡ በጥንት ጊዜ መንገደኞች ሲመሽባቸው ወደ አቅራቢያው መን ደር በመሄድ እንዲያሳድሯቸው ይጠይቁ ነበር፡፡ ደጋግ ሰዎችም እንግዳውን ተቀብለው እግሩን አጥበው ያሳድሩት ነበር፤ ይህ ባሕል በሀገራችን የታወቀ ሲሆን ዛሬም በአንዳንድ ቦታ እየተሠራበት ይገኛል፡፡ ሆኖም በብዙ ቦታዎች በተለይም በከተማ አካባቢ ሁኔታው የተለዋወጠ ስለሆነ በየሆቴል ቤቱ ገብተው ለማደር የማይችሉት በየመንገዱ በየአደባባዩ ወይም በየበረንዳው ያድራሉ እንጂ ወደ ግለሰብ ቤት ሄዶ ማደር እምብዛም የሚቻል አይሆንም፡፡ ምናልባት አን ዳንድ በጎ አድራጊዎች የእንግዳ ማረፊያ ቤት ኖሯቸው ያሳድሩ ይሆናል፡፡ እን ደዚህም የሚያደርጉ ክርስቲያኖች የክርስቶስን ፈቃድ የፈጸሙ ናቸውና ሊመ ሰገኑ ይገባል፡፡

በተለምዶ አነጋገር ዛሬ እንግዳ መጥቶብኛል ሲባል አብዛኛውን ጊዜ ዘመድ ወዳጅ ብቻ እንደሆነ እንረዳ...

ሰው ነው፡፡ ስለዚህ እንግዳ ስንል በመንገድ ሲሄድ ውሎ የመሸበትን እን ብቻ ሳይሆን መጠለያ የሌላቸውንም ሁሉ ይመለከታል፡፡ ይህም ብቻ አይ ከውጭ ሀገር በልዩ ልዩ ምክንያት ተሰደው የመጡት ስደተኞች ሁሉ እን ናቸው፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ትልቅ የሀገር ችግር ምእመናን ብቻቸውን ሠሩት ስለማይችሉ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተባብረው ሠሩ ከተደረገ ጊዜያዊና ቀዋሚ መጠለያ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ ያም ይህ ሁሉም የክርስቶስን እንግዳ ለመቀበል የተቻለውን ያድርግ፡፡ ከልብ እንባ አይገድምና፡፡

(4) <u>ታርዤ አልብሳችሁኛልና</u>፡- ብሎ ክርስቶስ የመሰከረላቸው ሰዎች በልብስ ምክንያት የተቸገሩ ወገኖችን ያለበሱትን በጐ አድራጊዎችን ይመለከ ል፡፡ እኔ እያማረጥኩ እየደራረብኩ የሞቀ የደመቀ ለብሼ ወገኔ እንዴት ቱን ይሄዳል ብለው ያላቸውን የሚያካፍሉ ምእመናን በእውነት ወገኖቻቸውን ፈቅራሉና በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋቸው ብዙ ነው፡፡ ምክንያቱም "ሁለት ልብስ ያለው ለሌለው ያካፍል" የሚለውን የወንጌል ቃል ፈጽመዋልና (ሉቃ.3፥11)፡፡ አዳምና ሔዋን ጸጋቸውን ከተገፈፉ ጊዜ ጀምሮ ዕራቁታቸውን ስለሆኑ ልብስ አስፈልጓቸዋል፡፡ ስለዚህም "የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው ለእነር ለራሳቸው ግልድም አደረጉ" ይላል ቅዱስ መጽሐፍ (ዘፍ.3፥7)፡፡ በሁላችንም የሚታየው ዕራቁትነት በአዳም በደል የመጣብን ስለሆነ የሥጋ ዕራቁትነታችንን በልብስ፥ የነፍስ ዕራቁትነታችንን በክርስቶስ ጸጋ እንሸፍናለን፡፡ ስለዚህም ነው የአዳም ዘር ሁሉ ዕሩቅ ብእሲ የተባለው፤ ስለዚህም ነው "ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት" የተባለው (ሮሜ.13፥14)፡፡ እንግዲህ ዕራቁቱን የሆ ወገናችንን ስናይ ከአዳም የወረስነው የራሳችን ዕራቁትነት መሆኑን አውቀን ለሥጋው ልብስ፥ለነፍሱ የጽድቅን ጸጋ እንዲለብስ ማድረግ የካህናትና የምእመናን ሁሉ ኃላፊነት ነው፡፡

የታረዙትን የምናለብሰው ያጌጠና ያሸበረቀ፥ የደመቀና የሞቀ ልብስ ገዝቶ በማልበስ ሳይሆን ኀፍረታቸውን ለመሸፈኛና ብርድን ለመከላከል ያህል ይበቃቸዋል፡፡ ስለ መብልና መጠጥም ከላይ እንደተገለጸው ሁሉ ስለ ልብስም በመጠኑና በልኩ ሆኖ እርዳታው ዘላቂነት እንዲኖረውና ለብዙዎችም እንዲዳረስ ማድረጉ ይመረጣል፡፡

(5) <u>ታምሜ ጠይቃችሁኛልና</u>፡- በማለት ጌታ ሕሙማንን መጠየቅ እን ደሚያስፈልግ ያስተምረናል፡፡ በልዩ ልዩ ሕማምና ደዌ የተያዙትን ወገኖች መጠየቅ ማለት አንድ ጊዜ ብቻ ሄዶ መጠየቅ አይደለም፡፡ ሁሉም እንደ ስጦ ታው አቅሙ በሚፈቅድለት መንገድ የተቻለውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ የተያዙትን ሕሙማን በመንፈስ ከማጽናናት እስከ ገን ዘብ ድጐማ ድረስ፥ ሐኪም ከመፈለግ መድኃኒት እስከ ማግኘት ድረስ ልዩ ልዩ ርዳታ ማድረግ ክርስቲያናዊ ግዴታችን ነው፡፡ ካህናትም ከመንፈሳዊ ትምህር ትና የምክር አገልግሎት እስከ ምሥጢረ ቀንዲል ድረስ ያለውን ለሕሙማን ይፈጽማሉ (ያዕ.5፥14-16)፡፡ ከዚህም ሌላ ካህናት ከምእመናን ጋር በመተባበር ለሕሙማንና ለቤተሰቦቻቸው አስፈላጊው ነገሮች ሁሉ እንዲሟሉ ማድረግ የሐዋርያዊ ተልዕኳ ቸው አንዱ ክፍል ነው፡፡ በተለይም በዘመኑ በሽታ ችግር የደረሰባቸውን ወገኖች ለመርዳት ቤተ ክርስቲያንና ኅብረተሰቡ በአንድነት እን ዲሠሩ እያደረግን ችግሩን ለመቅረፍ ሁላችንም ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ ይኖርብናል፡፡

www.ethiopianorthodox.org

(6) ታሥሬ ወደ እኔ መጥታችሁ ጠይቃችሁኛልና፦ በማለት ከታሠሩት ወገኖች ጋር ራሱን አንድ በማድረግ ስለ እነርሱ ይናገርላቸዋል ከተቸገሩት ጋር መቸገርና ለችግሩም መፍትሔ መፈለግ የክርስቲያናዊ ምልክት ነው። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "የወንድማማች መዋ ይኑር። እንግዶችንም መቀበል አትርሱ" ካለ በኋላ "ከእነርሱ ጋር እንደ ሆናችሁ እሥሮችን አስቡ፤ የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እን ሆናችሁ አስቡ" በማለት ምግባረ ወንጌል እንዲጠናከር ያደረገው (ዕብ.13፥1-3)።

እንግዲህ ፍቅራችን ያለግብዝነት ይሁን፤ ለታሠሩት ወገኖችም ከለ እናስብላቸው። ይልቁንም ረዳት ለሌላቸው የበለጠ ለማድረግ እንሞክር። ታችን ከታሠሩ በኋላ ብቻ ሳይሆን ገና በምርመራና በፍርድ ቤት በሚቆሙ ጊዜ ጠበቃና ዋስ እንሁናቸው ወይም እንፈልግላቸው። ከታሠሩም በማጽናናትና ስንቅ በማቀበል እንዲሁም ያዘኑትን ቤተሰቦቻቸውን በመንፈሳ ትምህርትና ምክር በማበረታታትና ለኑሯቸውም የሚያስፈልገውን ሁሉ በተ መጠን ርዳታ በማድረግ ከጐናቸው እንቁም። በክርስቶስ ስም ወዳጃቸውና አለ ታቸው እንሁን። ሌላ ጥቅምና ትርፍ ሳንፈልግ ለክርስቶስ መንግሥትና ለጽድ ብለን የሚገባንን ከፈጸምን በሰማዩ አባታችን ዘንድ ዋጋችን ከፍ ያለ ይሆናል።

## ማጠቃለያ

እንግዲህ ስድስቱ ምግባራተ ወንጌልና የመሳሰሉትን በመፈጸም የክርስቶስን መንግሥት ለመውረስ የበቃን ያደርገን እንላለን። አለበለዚያ ግን በእምነት ብቻ ያለ በጐ ሥራ እንጸድቃለን ማለት እንደማንችል ተምረናል። በመጨረሻው የፍርድ ቀን እምነት ብቻ ኖሯቸው "ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ" እያሉ የእግዚአብሔርን "ፈቃድ" የማይፈጽሙትን፤ የክርስቶስን ቃል ሰምተው የማያደርጉትና የፍቅር ሥራ የሌላቸው ሰዎች ሁሉ እጣ ፋንታቸው ለሰይጣንና ለመላእክቱ ከተዘጋጀው ቦታ ይሆናል (ማቴ.7፥21-29፤ 25፥41)። ምክንያቱም እነርሱ በእምነትም በምግባርም እርሱን ስለሚመስሉት ነው። ሰይጣን እምነት ብቻ እንጂ በጐ ሥራ የሌለው ወንጀለኛ በመሆኑ ተፈርዶበታል (ያዕ.2፥19)።

> "ወንድሞቼ ሆይ እምነት አለኝ የሚል ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን? ወንድም ወይም እኅት እራ ቁታቸውን ቢሆኑ የዕለት ምግብንም ቢያጡ ከእናንተ አንዱ በደህና ሂዱ እሳት ሙቁ ጥገቡም ቢላቸው ለሰውነት ግን የሚያስፈልጉትን ባትሰጧቸው ምን ይጠቅማቸዋል? እንደዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው" (ያዕ.2፥14-17)።

እንደ ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ "ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው፤ ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ፤ በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነቱን መጠበቅ ነው" (ያዕ. 1፥27)። ይኸው ሐዋርያ "እንግዲህ በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው" ብሎናልና ያወቅነውንና ያመነውን በሥራ ለመተርጐም የልዑል እግዚአብሔር ጸጋና ረድኤት እንዳይለየን ዘወትር መጸለይ ይገባናል (ያዕ. 4፥17)። ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ካልተለየን መልካሙን ሐሳባችንና እቅዳችንን ይባርክልናል፤ ክርስቲያናዊ ሕይወታችንን በእውነተኛና በትክክለኛው ሃይማኖት እስከ መጨረሻው ያጸናልናል፤ ምግባራተ ወንጌልንም ... የበቃን ያደርገናል።



## ()) ክርስቲያናዊ ሕይወት በጸጋ መንፈስ ቅዱስና በቤተ ክርስቲያን

የተራራውን ስብከት መሠረት በማድረግ ሌሎችንም የቅዱሳት መጻሕፍት ቃል በመጨመር ከላይ ከ(ሀ) እስከ (ሠ) የተማርነውን የጌታን ቃል መፈጸም ክርስቲያናዊ ግዴታችን መሆኑን አውቀናል። በጠቅላላው ክርስቲያናዊ ሕይወታችን በሃይማኖተ ወንጌል፤ በሕገ ወንጌልና በምግባረ ወንጌል መታነጽ እንዳለበት እናምናለን። እያንዳንዱን የጌታን ቃል ሰምተን በሥራ ላይ ለማዋል ጥረት ካላደረግን ክርስትናችንን ሐቀኝነት የጐደለው ያስመስልብናል። ስድስቱ ቃላተ ወንጌልንና አሥሩ ቃላትን ሌሎችንም የጌታ ትእዛዛት ሁሉ ሰምተን በተግባር ለመፈጸም በተቻለን አቅምና በሙሉ ኃይላችን መንፈሳዊ ተጋድሎ ማድረግ ነው እንጂ ወደ ኋላ ማፈግፈግ አያስፈልግም። እንግዲህ ክርስቲያናዊ ሕይወት የተጋድሎ ኑሮ ነው። ስለሆነም ተጋድሏችንን በድል እንድንወጣ የሚረዳንን ጸጋ በቅድሚያ እግዚአብሔር ስላዘጋጀልን ብቻችንን እንደሆንን በመገመት መጨነቅ የለብንም። እርሱም ቃሉን ሰምተን እንድናደርገው ያዘዘን ጌታችን ጸጋውና ረድኤቱን ይሰጠናል። ኃይሉን በሚሰጠን በክርስቶስ ሁሉን እንችላለን (ቆላ.4፥13)። ስለዚህ በቃሉ ተወስነን ክርስቲያናዊ ሕይወታችንን በእርሱ ላይ መሥርተን "ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን፤ የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፤ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ" (ዕብ.12፥1-2)።

የወንጌል ሕግና ትእዛዝ፤ ምግባርና ትሩፋት ከባድ ነው በሚል ሽፋን ሌላ ስላችና አቋራጭ መንገድ መፈለግ አያዋጣንም። ምክንያቱም ዓለሙ ሁሉ ወደ ሚጓዝበት ሰፊ መንገድ ሊወስደን ስለሚችል ነው። እኛ ትእዛዛትን ለመፈጸም የምንችለው ከሁሉ በፊት የእግዚአብሔር እምነትና ፍቅር ሲኖረን ነው፤ ይህ ካለን የዓለም ፍቅር ይጠፋልናል፤ ስለዚህም ዓለምን ለማሸነፍ እንችላለን። እግዚአብሔርን መውደድ ማለት ትእዛዛትን መፈጸም ነው፤ ትእዛዛቱንም መፈጸም ዓለምን ማሸነፍ ነው። እንግዲህ ትእዛዛቱም ከባድ እንዳልሆኑና ዓለምንም በምን ለማሸነፍ እንደምንችል ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ የሰጠንን ማሳሰቢያ እንመልከት፦

> "ትእዛዙን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና፤ ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም። ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና፤ ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው። ኢየሱስም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ከሚያምን በቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማን ነው?" (1ኛዮሐ.5፥3-5)።

ከዚህ ምንባብ የምንማረው የጌታ ትእዛዛት ከባድ እንዳልሆኑና ዓለምንም ለማሸነፍ የምንችለው በእምነታችን እንደሆነ ነው። ትእዛዛትን ለመፈጸም እምነት ያስፈልገናል፤ እምነትም ከትእዛዛትና ከምግባር ሁሉ ይቀድማል። እውነተኛና ጠንካራ እምነት ካለን ትእዛዛትን መፈጸም አይከብደንም፤ ትእዛዛቱንም ከፈጸምን ዓለምን አሸነፍን ማለት እንችላለን። እንግዲህ የማሸነፋችን መሠረቱ እምነት እንደሆነ አውቀናል። ነገር ግን የትኛው ዓይነት እምነት እንደሆነ በውል ለይተን ማወቅ አለብን። ከጥቅሱ እንደምንማረው በወልደ እግዚአብሔር በክርስቶስ ከሚያምነው በቀር ማንም ይህንን ዓለም በድል አድራጊነት ሊወጣው አይችልም። ስለዚህ በክርስቶስ እምነት ላይ ልቡናችንን ካሳረፍን እርሱ ደግሞ የኛን የደካሞቹን ሸክም ወስዶ ያሳርፈናል። ስለዚህ ነው ጌታችን፦

> "እናንተ ... ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፤ ወደ እኔ ኑ፤ እኔም አሳርፋችኋለሁ። ቀንበሬን በ...ችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፤ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፤

www.ethiopianorthodox.org

ይህ ኃይለ ቃል ለሁላችንም መጽናኛ ነው፡፡ ቀንበር የተባለች ሕገ ወንጌል ሕግ ናትና፤ ትእዛዙም ቀሊል ነውና፡፡ ሆኖም ሕገ ወንጌል ቀኝ ጉንጭህን ለሚመታህ ግራ ጉንጭህን አዙርለት . . . ጠላትህንም ውደድ ትላለች፤ ከዚህ የከበደ ምን አለና ነው ጌታ እንዲህ ያለው ቢሉ አደርገዋለሁ ብሎ በቆረ ጎሊና ለተነሣ ሰው ቀሊል ነውና በማለት ሊቃውንት አባቶች ያስረዳሉ፡፡ "አ ድም፥ለወጣንያን ክቡድ ቢሆን ለፍጹማን ቀሊል ነውና፤ አንድም፥ከሕገ ኦሪ ሲለይ ነው፡፡ ኦሪት ውጉሩ ስቀሉ ብላ ካሰናበተች በኋላ ምላሽ የላትም፡፡ ወንጌል ግን በንስሐ ትላለች፡፡ ንስሐውን ቅሉ ስብእ በበስብእ ትላለችና፡፡ ሕግሰ ሲሐዊት ተራጎርኃት እንዲል፡፡ አንድም፥ኦሪት ፈጽማችሁ ጽደቁ ትላለች፤ ወን ጌል ግን በክርስቶስ ፈጻሚነት ትላለችና" (ማቴ.11፥30 ትርጓሜ ወንጌል)፡፡

"ወንጌል ግን በክርስቶስ ፈጻሚነት ትላለች" የተባለው ክርስቶስ የኦሪትን ሕግ ሁሉ ለእኛ መዳን ሲል መፈጸሙን የሚያመለክት እንጂ ጌ ሕግን ፈጽሞልናልና እኛ ከሕግ ጋር ምንም ግንኙነት የለንም ማለት አይደ ለም፡፡ ይህማ ቢሆን ኖሮ ጌታ ስድስቱን ቃላተ ወንጌል ባልጠሰን ነበር፡፡ አዳም ሕግን ተላልፎ ያመጣብንን ፍዳና መርገም ከዚያም ሕገ ኦሪትን በመተላለፍ ሰው ሁሉ በደለኛ በመሆን በየጊዜው በበደል ላይ በደል እየጨመረ በመሄዱ ሁለተኛ አዳም የተባለ ጌታ ሕግን በመፈጸም ከፍዳና ከመርገም ከኃጢአትና ከሞት አድኖናል፡፡ መዳንም የሚገኘው ሕግ በፈጸመልንና ስለ እኛ ኃጢአተ ቤዛ በሆነልን በክርስቶስ በማመንና በስሙም በመጠመቅ ነው፡፡ እንግዲህ ይህን የጌታን የማዳን ሥራ ለመግለጽ ክርስቶስ ሕግን ስለ እኛ ፈጽሞታል እንላለን እንጂ በስሙ አምነው የተጠመቁትና የዳኑት በአዳኛቸው እምነት ብቻ የሚኖሩ ስለሆነ ሕገ እግዚአብሔርን መጠበቅና መፈጸም አያስፈልጋቸውም ማለት አይ ደለም፡፡ ስለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ "ሕግን በእምነት እንሽራለን? አይ ደለም፤ ሕግን እናጸናለን እንጂ" በማለት የተናገረው (ሮሜ.3፥31)፡፡

ለክርስቲያኖች የእምነትና የጥምቀት ምሳሌ የሆነውን ባሕረ ኤርትራን ሕዝበ እሥራኤል ከተሻገሩ በኋላ ሕገ እግዚአብሔርን ባለመጠበቃቸው ከተስፋው ሀገር ሳይገቡ በመንገድ ላይ ሙተው ቀርተዋል፡፡ እኛም ካመንና ከተጠመቅን በኋላ ሕገ እግዚአብሔርን በመጠበቅ ከክፉ ነገር እንድንጠነቀቅ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን የተጠቀሰውን ታሪክ ለእኛ ተግሣጽ እንዲሆነን የተጻፈ መሆ ኑን አስረድቶናል (1ኛቆሮ.10፥1-13)፡፡ እንደዚህም ስለ ተባለ እንደ ጥን ቶቹ አይሁድ ከሕገ ኦሪት በታች ነን ማለት አይደለም፡፡ ይኸው ሐዋርያ በክ ርስቶስ ያመኑት ሁሉ በክርስቶስ ጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች እንዳልሆኑ ይገልጻል (ሮሜ.6፥14)፡፡ ምክንያቱም በክርስቶስ ያሉ ሁሉ ሰውነታቸውን ለጽድቅና ለቅድስና ስለሚያስገዙ በሕገ ተፋቅሮም ስለሚኖሩ የሕገ ኦሪት ትእዛዝ ከሚጠይቀው በላይ የፈጸሙ ስለሆነ በክርስቶስ ጸጋ እንጂ ከሕገ ኦሪት በታች አይደሉም፡፡ በክርስቶስ ያገኘነው ጸጋ ከሁሉ በላይ እንጂ በታች አለመ ሆኑን የምናውቀው የጸጋ ምንነትን ስንረዳ ነው፡፡ ጸጋ ለመዳናችንና ለክርስ ቲያናዊ ሕይወታችን መሠረት መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ እምነት እን ዲኖረንና በእምነትም እንድንጸና የሚያደርግ ጸጋ እግዚአብሔር እንደሆነ ሁሉ በጐ ምግባርን ለመፈጸምና ትእዛዛቱንም ለመጠበቅ የሚያስችለን አሁንም ደግሞ ጸጋው ነው፡፡

## 1. የጸጋ አጋዥነት ለክርስቲያናዊ ሕይወት መጠናከር

የጸጋ አመጣጥ በኃጢአት ምክንያት ከፈጣሪው የተጣላውንና ከደስታ ኑሮው የተፈናቀለውን ሰው ከኃጢአትና ከሞት አድኖ ...



ክብሩ ለመመለስ እግዚአብሔር በቸርነቱና ሰውን በመውደዱ ከጥንት ጀም ሮ ካዘጋጀው የመዳን ምሥጢር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ይህም የመዳን ጸጋ በክርስቶስ ሰው መሆን ተገለጠ፡፡ በርሱም አማኞች በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥ ቷቸዋል (ዮሐ.1፥16)፡፡ ነገር ግን የመዳን ጸጋ ለዓለም ሁሉ በግልጥ የተ ሰጠው በመስቀል ላይ ካሣ ከተፈጸመ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ በወረደ ጊዜ ነበር (የሐዋ.ሥራ2፥1-40)፡፡ በትንቢተ ኢዩኤል (2፥28-29) እን ደተነገረው በዚያን ቀን እግዚአብሔር መንፈሱን በሕዝቡ ላይ ባፈሰሰ ጊዜ ሁሉም ልባቸው ወደ እግዚአብሔር ተመለሰ፡፡ እነርሱም ምን እናድርግ? ብለው ሐዋርያትን በጠየቋቸው ጊዜ በክርስቶስ አምነው እንዲጠመቁና መን ፈስ ቅዱስንም እንደሚቀበሉ ነገሯቸው፤ በዚያን ቀን ብቻ ሦስት ሺህ አማ ኞች ከጉባኤ ሐዋርያት እንደገቡ ተጽፏል (የሐዋ.ሥራ2፥41)፡፡ እንግዲህ እናስተውል፤ በዚያን ቀን የተደረገውን ብንመረምር ከሌሎች ሃይማኖቶች በተለየ አኳኋን የክርስትና ሃይማኖት አጀማመር ታሪክ በእግዚአብሔር ጸጋ አጋዥነት እንደሆነ ከማንም አይሰወርም፡፡ ከሐዋርያት ቋንቋ መገለጥ ጀምሮ የሕዝቡ ልብ ወደ እግዚአብሔር መመለስና ማመን በጸጋ መንፈስ ቅዱስ ኃይልና አጋዥነት የተፈጸመ ታላቅ ተአምራዊ ድርጊት ነበር፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ለሚነሡት አማኞች ጸጋ መን ፈስ ቅዱስ ይሰጣል፤ ይህም ጸጋ በክርስቶስ ሕማምና ሞት የተገኘው የመዳን ተስፋ በምእመናን ልቡና ሠርፆ እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ደኅንነትና የዘላለም ሕይወት በሚገኝበት እምነት ጸንተው የበጎ ሥራ ፍሬ እንዲያሳዩ የሚረዳቸው ጸጋ ነው፡፡ ስለሆነም ስለ ጸጋ ምንነትና ሥራ በመጠኑም ቢሆን እንደገና ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡

## የጸጋ ምንነት-ጥቅሙና አገልግሎቱ

እንግዲህ ጸጋ ማለት ሰውን ከወደቀበት ጥፋትና ከደረሰበት ጉዳት ለማዳን ታስቦ ከእግዚአብሔር ለሰው ልጆች እንዲሁ ያለ ዋጋ የሚሰጡትንና የሚደረጉትን ልዩ ልዩ ስጦታዎችና ድርጊቶችን ሁሉ በማጠቃለል የሚያመ ለክት ቃል ነው፤ የቃሉም ትርጉም መልካም ስጦታ፥ ሀብት፥ ይቅርታ፥ ሥርየት፥ ያለ ዋጋ የሚሰጥና የሚደረግ የቸርነት ሥራ ሁሉ ነው፡፡ ጸጋ፥ ልቡናችንን በማነቃቃት መልካሙን እንድንመኝና እንድናስብ እንዲሁም መልካሙን እንድናደርግ ብርታትንና ችሎታን ይሰጠናል፡፡ ጸጋ የተባለውም መንፈስ ቅዱስና ልዩ ልዩ ስጦታዎቹ ናቸው፡፡ መንፈስ ቅዱስ አካሉ አንድ ሲሆን ስጦታው ብዙ ነው (1ኛቆሮ.12፥4)፡፡ የጸጋ መንፈስ ቅዱስ የመጀ መሪያ ሥራ የሰውን ልቡና ወደ ፈጣሪው መመለስና በእርሱም እንዲያምን ማድረግ ነው፡፡ ስለሆነም ከማናቸውም መንፈሳዊ ሥራ ሁሉ ከልብ መመ ለስና ማመን ይቀድማል፡፡ ትክክለኛውን ሃይማኖት እንድንይዝ የሚያደርገንና የሚያጸናን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ ስለ ኢየሱስ ማንነት፥ ስለ ጌትነቱና መሲሕነቱ፡ ስለ አዳኝነቱና አምላክነቱ ማንም ሰው በገዛ ራሱ ተነሣሥቶ የሚመሰክር የለም፡፡ ጌታ ሐዋርያትን ስለ ራሱ ማንነት በጠየቃቸው ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ ብሎ የመለ ሰው ከራሱ ልቡና አንቅቶ የተናገረው አልነበረም፡፡ "በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህም" በማለት ጌታችን የተናገረው የዚህ ሐዋርያ እምነት የእግዚአብሔር ስጦታ እንደሆነ ያመለክታል (ማቴ. 16፥17)፡፡ የአይሁድ እምነት አራማጅ የነበረው ሳውል (ጳውሎስ) በእግዚአ ብሔር ጸጋ የእውነተኛው የክርስትና እምነት መሪ ሐዋርያ ሆኗል (የሐዋ. ሥራ9፥1-30)፡፡

www.ethiopianorthodox.org

የመጀመሪያው የጸጋ ስጦታ እምነት ነው፤ እምነትም ጸጋ ነው፡፡ በአ ያልተገኘ እምነት ለጽድቅ አያበቃም፡፡ በጸጋ መንፈስ ቅዱስ የተገኘ እም ግን የመዳን ተስፋ አለው፤ አማኞችንም በሕይወት መንገድ ይመራል፡፡ እ ግዲህ የክርስቲያናዊ ሕይወታችን መሠረት የሆነው ትክክለኛው እምነት ግለ ርትዕት ሃይማኖት በጸጋ መንፈስ ቅድስ የተሰጠ መሆኑን እናምናለን፡፡ የመ ፈስ ቅዱስ ረቂቅ ሥራ ከዕለት በዕለት ኑሯችን ክብደት ተጽእኖ የተነሣ ባና ውለውም እርሱን እስካልካድነው ድረስ እርሱ ለእኛ የሚጠቅመውን ከመ ራት አያቋርጥም፡፡ እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ ደግሞ በልዩ ልዩ ሁኔታ በሕ ልምም፥ በራእይም ወይም በገሃድ በሚታይ ሰማያዊ ብርሃንም ወይም በሌላ ተአ ምራዊ ኃይል በመገለጥ እምነታችንን ከመቼውም የበለጠ እንዲጸና ያደርግ ናል፡፡ ይልቁንም በጸሎት የጸጋ መንፈስ ቅዱስ አጋርነት የበለጠ ይታወቃል፡፡ በርትዕት ሃይማኖትና በእውነተኛ አምልኮት እንድንጸና ያደረገን መንፈስ ቅዱስ ለማን እንደምንጸልይና እንዴት መጸለይ እንደሚገባን ለማናውቀው ለእኛ ያስተምረናል፤ "እንዲሁም ደግሞ . . . ድካማችንን ያግዛል" (ሮሜ.8፥26)፡፡

በዚህ ዓለም ውስጥ ስንኖር ክርስቲያናዊ ሕይወታችንን የሚፈታተኑ ብዙ ነገሮች ያጋጥሙናል፡፡ ስለዚህ ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን የሚረዳን አስ ተማሪና መካሪ አጽናኝና አጋዥ እንዲሆን ጌታችን መንፈስ ቅዱስን ለሐዋር ያትና ለቤተ ክርስቲያኑ ሰጥቷል፡፡ እርሱ የጌታን ቃል እንድናስታውስ እየረዳን ይመክረናል፤ በችግራችንም ያዝንልናል፤ በፈተናችንም ጊዜ ያጽናናናል፡፡ በሐ ሰትም ነገር እንዳንሳሳት ወደ እውነት ሁሉ ይመራናል፤ ምክንያቱም እርሱ የእውነት መንፈስ ነውና፡፡ ስሙም እንደ ግብሩ "አጽናኝ" ወይም በግሪክ ጰራ ቅሊጦስ ይባላል - "መጽንኒ መንጽሒ ናዛዚ ከሣቲ መሥተፍሥሒ መስተሥር ዪ ማለት ነው" (ዮሐ.14፥15-17፤15፥26፤16፥7-15)፡፡

በክርስቶስ አምነው የሚጠመቁትን ሁሉ መንፈስ ቅዱስ የኃጢአት ሥርየትንና የጸጋ ልጅነትን በመስጠት የእግዚአብሔርን ጽድቅና ቅድስና ተካ ፋዮች እንዲሆኑ ያበቃቸዋል፤ በጥምቀትም ከክርስቶስ ጋር አንድ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡ የክርስቶስን ሕማማት በመካፈል ለኃጢአት የሞትን (የተለየን) እንድንሆን የሚያስችለንና በትንሣኤውም ተባባሪ ለመሆን ትንሣኤ ልቡናን ሰጥቶ በአዲስ ሕይወት ለእግዚአብሔር እንድንኖር ኃይልን ለእኛ ለክርስቲያኖች የሰጠና የሚሰጥ መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ እንግዲህ በጸጋው አጋርነት የምትኖሩ ምእመናን ሁሉ "ለኃጢአት እንደ ሞታችሁ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቁጠሩ" (ሮሜ.6፥11)፡፡ ያለፈው የድንቁርናና የኃጢአት ኑሯችን ይበቃናል፤ አሁን በጸጋ መንፈስ ቅዱስ ከኃጢአት ነጽተናል ይቅርታም አግኝተናል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳለው "ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ /ከክርስቶስ/ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን፤ የሞተስ ከኃ ጢአቱ ጸድቋልና፡፡ ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንድንኖር እናምናለን" (ሮሜ.6፥6-8)፡፡

## ስለ አሮጌውና ስለ አዲሱ ሰው

ከላይ "አሮጌው ሰዋችን" የተባለው እንደ ሥጋ እንጂ እንደ መንፈስ ፈቃድ የማይኖሩትን በቀድሞው ዓለማዊ አስተሳሰባቸው ሳይለወጡ የሚገኙትን ስመ ክርስቲያኖች ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡ እንደ እነዚህ የመሳሰሉትንም ሐዋርያው ጳውሎስ ሲመክር፦ "ፊተኛ ኑሯችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ" ... እምሯችሁም መንፈስ ታደሱ ለእ... እንደ

www.ethiopianorthodox.org



እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ" ብሏል (ኤፌ.4፥22-24)፡፡ ከውኃና ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ አዲስ ልደት አለው (ዮሐ.3፥5)፡፡ አዲስ ልደትም ያለው አሮጌውን አስወግዶ አዲሱን ሰው ለብሷል፤ በክርስቶስም አዲስ ፍጥረት ሆኗል (ገላ.6፥15፤ 2ኛ.ቆሮ.5፥17)፡፡ አዲሱ ሰው በመንፈስ ይኖራል፤ በመንፈስም ይመራል፤ በሕይወቱም የመንፈስ ፍሬ ይታይበታል፤ እነሱም ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው፡፡ እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም" (ገላ.5፥22-23)፡፡ ስለዚህ አዲሱ ሰው ከሕግ በታች አይደለም፡፡ ምክንያቱም እርሱ በጸጋ መንፈስ ቅዱስ እየተመራ ሕግ ከሚጠይቀው በላይ በሕገ ተፋቅሮና በበጐ ነገር ሁሉ የጸና ስለሆነ የሕግ ትእዛዛት እርሱን አይመለከተውም፡፡ ሕግ አጥፊዎችን ለመቆጣጠርና ለመቅጣት የተሠራ ስለሆነ ሕግ ክፉ አድራጊዎችን እንጂ በጐ አድራጊዎችን አይመለከትም፡፡ ስለዚህ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ "በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም" ያለው (ገላ.5፥18)፡፡

እንግዲህ ምእመናን ሁሉ አሮጌውን ሰው በማስወገድ በክርስቶስ አዲሱን ሰው በመከተል በጸጋ መንፈስ ቅዱስ እየታገዝን ክርስቲያናዊ ሕይወታችን የተሟላና ፍጹም እንዲሆን ጥረት እናድርግ፡፡ ይህንንም በጸጋ መንፈስ ቅዱስ አጋርነት በመተማመን እንፈጽመው፡፡ በአዲሱ ሕይወታችን ጾንተን በጸሎት ተግተን ከኖርን የእግዚአብሔር ጸጋና በረከት አይለየንም፡፡ ይልቁንም ከእናታችን ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሳንለይ ከእርሷ ጋር በመኖር የእግዚአብሔር ጸጋ ይበዛልናል፡፡

## "የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል ያጸናችሁማል"

ክርስቲያኖች በዚህ ዓለም ሲኖሩ ብዙ መከራና ፈተና ስላለባቸው በተለይም በጥንተ ጠላታችን በዲያብሎስ የሚደርስባቸውን ችግርንና ጭንቀትን ለመወጣት የሚችሉት ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ለኃያሉ አምላክ ለእግዚአብሔር በመስጠት ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ስለዚሁ ሲያስተምር፦ "እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ፤ እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት" ብሎናል (1ኛጴጥ.5፥6-7)፡፡ ይህም ማለት ራሳችን በችሎታችንና በጥበባችን ብቻ ተመክተን ጭንቀታችንንና ችግራችንን ለማስወገድ ስለማንችል ራሳችንን በማዋረድ ማለት በትሕትና ራሳችንን በማስገዛት ኃያሉ እግዚአብሔርን ብንቀርበው እርሱ ይረዳናል ማለት ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ በክርስቲያናዊ ሕይወታችን ውስጥ ለምናደርገው መንፈሳዊ ተጋድሎ ለእግዚአብሔር ረድኤት ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው አምነን በዚህ አሳብ መኖርና መሥራት ይገባናል፡፡ ጌታችን "ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል" ብሎናልና (ዮሐ.15፥5)፡፡

የእግዚአብሔር ረድኤት እንደ ተጠበቀ ሆኖ የእኛን ድርሻ ደግሞ በማስመልከት ሐዋርያው፦ "በመጠን ኑሩ ንቁም" እያለ ወደ ፈተና እንዳንገባ በቅድሚያ ያስጠነቅቀናል፡፡ ምክንያቱም "ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጐ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና" በማለት የችግራችን ሥር መሠረት የሆነውን የፈተናችንና የጭንቀታችን ምንጭ ማን እንደሆነ ገልጾልናል፡፡ የጨለማው ዓለም ገዢ ዲያብሎስ የሚያመጣብንን ፈተናና መከራ አውቀን እን ድንቋቋመው ሐዋርያው፦ "በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት" በማለት ... ሰጥቶናል (1ኛጴጥ.5፥8-9)፡፡

ይኸው ሐዋርያ ከጥቂት መከራ በኋላ እግዚአብሔር "የጸጋ ሁሉ አምላክ" ፍጹማን እንደሚያደርገንና እንደሚያግዘን ሲያስረዳ፦ "በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል ያጸናችሁማል ያበረታችሁማል" ብሎአናል፡፡ ስለዚህ ሁልጊዜ በፈተናችንና በመከራችን የሚያግዘን የጸጋ ሁሉ አምላክ ጠላታችን ዲያብሎስን እንድንቋቋመው ኃይል ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና እናቀርባለን፡፡ "ለእርሱ ክብርና ኃይል እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን፤ አሜን" (1ኛጴጥ.5፥10-11)፡፡ እንግዲህ ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን መሳካት እርዳታ የምናገኝበትን የእግዚአብሔርን ጸጋና በረከት ከቤተ ክርስቲያን በጸሎት፥ በቃሉ አገልግሎትና በምሥጢራት አማካይነት ስለሚሰጠን ስለዚህ ጉዳይ ቀጥሎ ያለውን እንመለከታለን፡፡

## 2. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኖርና ማገልገል

ክርስቲያናዊ ሕይወታችን ሊያድግና ሊለመልም፥ ሊያብብና ሊያፈራ የሚችለው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስንኖር ነው፡፡ በእምነትና በጥምቀት የተወለድነውና ጸጋ መንፈስ ቅዱስን የተቀበልነው፥ በትምህርትና በሥነ ምግባር ታንጸን ልናድግ የቻልነው በእናት ቤተ ክርስቲያናችን አማካኝነት ስለሆነ ምንጊዜም ልንለያት አይገባም፡፡ ካደግን በኋላም ከእርሷ ጋር እስከ ሞት ድረስ ጸንቶ መቆየት ከእግዚአብሔር ዋጋን ያስገኛል፡፡ ነገር ግን አንዳንዶች ይህን ዘንግተው ከቤተ ክርስቲያን በመቅረት በግለኝነት አስተሳሰባቸው በገዛ ፈቃዳቸው ለብቻቸው መኖርን መርጠዋል፡፡ እንደነዚህ ዓይነት ግለሰቦች ከማኅበረ ምእመናኑ ጋር ኅብረት ስለሌላቸው ክርስቲያናዊ ሕይወታቸው ማደጉን አቁሞ ሃይማኖታቸውና መንፈሳዊነታቸው እየዘቀዘቀ ሄዶ ከመጥፋት በቀር ምንም የሚያገኙት ጥቅም የለም፡፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ጸጋና ዋጋ የሚገኝባትን፥ የመንግሥቱንና የጽድቁን መግለጫ የሆነችውን፥ ክርስቶስ በደሙ የመሠረታትን ቤተ ክርስቲያኑን በመተዋቸው ነው፡፡ ተወልደው ያደጉባት ቤተ ክርስቲያናቸውን መተዋቸው ብቻ ሳይሆን ወደ ተቃዋሚዎች ጐራ ገብተው ፀረ ክርስቲያን አቋም በመያዝ የተቀበሉትን የሕይወት ቃልና የጸጋውን መንፈስ በማክፋፋትና የተቀደሰውንም የክርስቶስ መሥዋዕትነት በማጥላላት ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ጋር በግብር የሚመስሉትን የዕብራውያንን ሰዎች ሐዋርያው ጳውሎስ ሲመክርና ሲያስጠነቅቅ እንዲህ ይላል፦

> "ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፤ በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደሆነው፥ መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ፡፡ የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢአት መሥዋዕት አይቀርልንምና፥ የሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ፡፡ የሙሴን ሕግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሦስት ቢመሰክሩበት ያለርኅራኄ ይሞታል፤ የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደርኩስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያክፋፋ፥ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል?" (ዕብ.10፥24-29)፡፡

ከዚህ ጥቅስ ሁለት ነገሮችን እንማራለን፡፡ በመጀመሪያ በቤተ ክርስቲያን መሰብሰባችን እርስ በርሳችን እንድንበረታታ እንድንመካከር ለመልካምም ሥራ እንድንነቃ የሚጠቅመን ስለሆነ ወደፊት አብልጠን እንድሰበሰብ የሚያሳስበን ነው፡፡ ይህን ብናደርግ ክርስቲያናዊ ሕይወታችን እንደሚታነጽ የተሰጠ ምክር ነው፡፡ በጥቅሱ ሁለተኛ ክፍል ...



የተቀደሰው ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ላይ የንቀትና የስድብን ነገር የሚናገሩትን፥ በክርስትና ሃይማኖት ቆይተው ኋላ የወጡትን አይሁዳውያንንና አረማውያንን ይመለከታል፡፡ እንግዲህ እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ዛሬም በዘመናችንና በዓለሙ ሁሉ ተንሠራፍቶ ስለሚታይ የተቀደሰው እምነታችንን የሚያስተሐቅሩ ስለሆነ ከከሃድያንና ከመናፍቃን እርሾ ተጠብቀን ከማስጠበቅ በቀር አማራጭ የለንም፡፡ በጌታ ስቅለት በዕለተ ዓርብ ለኃጢአት ሥርየት የፈሰሰውን ደሙን የማያምኑ፥ በጸሎተ ኀሙስ የተሠራውን የምሥጢረ ቁርባን ሥርዓት የሚክዱ፥ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን የሚያጣጥሉ ስለሆነ የሐዋርያው ጳውሎስ ማስጠንቀቂያና ፍርድ ይጠብቃቸዋል፡፡ በተለይም መንፈስ ቅዱስን የሰደበ ሁሉ ኃጢአቱ አይሥረይለትም (ማቴ.12፥32)፡፡

እኛ ግን ክርስቶስ በደሙ በመሠረታት በመንፈስ ቅዱስ ባጸናት ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ሕጓንና ሥርዓቷን አክብረን እንኖራለን፡፡ አንድ ጊዜ በዕለተ ዓርብ የፈጸመው የማዳን ሥራ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ታስቦ እንዲኖር ለማድረግ ጌታችን በጸሎተ ኀሙስ ያቋቋመልንን ሥርዓተ ቁርባን እንፈጽማለን (ማቴ.26፥26-28፤ 1ኛቆሮ.11፥23-26)፤ በስሙ ወንጌልን እየሰበክንና እያሳመንን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እናጠምቃለን (ማቴ.28፥19-20፤ ዮሐ.1፥43)፡፡ ከዚህም ሁሉ ጋር ሌሎች ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በመካፈል ክርስቲያናዊ ሕይወታችንን እናጠናክራለን፡፡ እነዚህንና ሌሎችንም ትእዛዛት ጌታ ለሐዋርያቱ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ እንዲጠብቋቸው ያደረገው በጸሎት፥ ቃሉን በማገልገልና በምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት አማኞች ሁሉ በተሰጣቸውና በሚሰጣቸው ጸጋ መንፈስ ቅዱስ እንዲጸድቁና እንዲቀደሱ በማድረግ የመንግሥቱ ወራሾች እንዲሆኑ ነው፡፡

## የእግዚአብሔር መንግሥቱና ጽድቁ በቤተ ክርስቲያን

ያለ ቤተ ክርስቲያን መንግሥተ ሰማያት አትታወቅም፡፡ ያለ ተስፋ መንግሥተ ሰማያትም ክርስቲያናዊ ሕይወት አይኖርም፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር በዓለም ላይ መንግሥቱንና ጽድቁን ለማብሠር ዓለሙንም ለማዳን አሰቦ አንድ ልጁን ክርስቶስን ላከው፡፡ ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስም ሰው ሁኖ በሰዎች መካከል እየተመላለሰ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ወንጌልን ከሰበከበት ጊዜ ጀምሮ መንግሥተ ሰማያት በምድር ላይ በክርስቶስ ስም እንድትታወቅ ሆናለች፡፡ ጌታ ራሱ እንደ አስተማረን፦ "ሕግና ነቢያት እስከ ዮሐንስ ነበሩ፤ ከዚያ ጀምሮ የእግዚአብሔር መንግሥት ይሰበካል፤ ሁሉም ወደ እርስዋ በኃይል ይገቡባታል" ብሏል (ሉቃ.16፥16)፡፡ በእርሱ ስም ላመኑትና ለተከተሉት ደቀ መዛሙርት መንግሥተ ሰማያት እንደምትሰጣቸው ነግሯቸዋል፡፡ "አንተ ታናሽ መንጋ መንግሥትን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነውና አትፍሩ" ብሏቸዋል (ሉቃ.12፥32)፡፡ እንዲያውም የመንግሥተ ሰማያትን ቁልፍ በአደራ ለሐዋርያቱ ሰጥቷል፤ ቁልፍ የተባለውም የሐዋርያትን ሥልጣንና ኃላፊነትን ያመለክታል፡፡ ጌታ ይህን ኃላፊነት ከመስጠቱ በፊት በመጀመሪያ በራሱ በጴጥሮስ (በጠንካራው ዐለት) ላይ ቤተ ክርስቲያኑን እንደሚመሠርት አስታውቋቸዋል (ማቴ.16፥18-19፤ ዮሐ.1፥43)፡፡ ምክንያቱም ያለ ቤተ ክርስቲያን ስለ መንግሥተ ሰማያት ማወቅ አይቻልምና፡፡ መንግሥቱና ጽድቁ ሊታወቅና ሊታመን የሚቻለው በሰዎች መካከል በተግባር ተፈጻሚነት ሲኖረው ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ጌታ የመንግሥተ ሰማያትን ኃላፊነት በሰጣቸው በሐዋርያት ላይ በደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያኑን ሠርቷል፤ መሥርቷልም፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ስንል በሐዋርያት ጉባኤ የተሰበሰቡት አማኞችንና ከዚያም በኋላ ... ማለት በአንብሮተ እድ የተሠየሙትን፡ በታሪክ

www.ethiopianorthodox.org

የታወቁትንና ሐዋርያዊ መንበር ያላቸውን ብቻ ማለታችን መሆኑ መ ወቅ አለበት፡፡

## ከልደት እስከ ሞት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ

እንግዲህ ሐዋርያዊት መንበርና ትውፊት ባላት ቤተ ክርስቲያ ውስጥ በመኖርና በማገልገል፡መንፈሳዊ ጥሪያችንን በማክበርና ክርስቲያና ሕይወታችንን በተግባር በማስመስከር የክርስቶስ መንግሥት ተካፋዮች ለመሆ እንበቃለን፡፡ የክርስቲያን ሕይወት ከልደት እስከ ሞት ድረስ ከቤተ ክርስቲያ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ወላጆች ሕፃናትን ክርስትና ከማስነሣት ጀምሮ በመ ፈሳዊ ትምህርትና በሥነ ምግባር ታንጸው እንዲያድጉና ከቤተ ክርስቲያን መ ፈሳዊና ማኅበራዊ ሕይወት ተካፋዮች እንዲሆኑ ለማድረግ ልጆቻቸውን ከስ በት ት/ቤት እንዲገቡ፥ ከጸሎተ ቅዳሴ እንዳይለዩ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለ ባቸው፡፡ ክርስቲያናዊ ሕይወት የሚጀምረው ከቤተሰብ ስለሆነ በቃል ሆነ በሥራ ወላጆች ልጆቻቸውን ማስተማርና ለመልካም ነገር ሁሉ አርአ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ልጆችም ሲያጠፉ ቀስ ብሎ ያጠፉት ነገር ምን እ ደሆነ በማስረዳት ከፉና ደጉን በክርስትና ትምህርት አኳያ ለይተው እ ዲያውቁት ማስተማርና ከዚያም ቀጥሎ ጥፋቱ እንዳይቀጥል ማስጠንቀቅና መገሠጽ፥ ቅጣትም አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ቅጣቱን በአግባቡ መፈጸም እንጂ ልጆችን እንዲያው በከንቱ ከመሬት ተነሥቶ መደብደብና ማስቆጣት ካልጠበቀ ነው ጉዳት ላይ ይጥላቸዋል፡፡ "እናንተም አባቶች ሆይ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጓቸው እንጂ አታስቆጧቸው" የተባለውን መመሪያ እንከተል (ኤፌ.6፡4፤ቆላ3፡21)፡፡

"ልጆች ሆይ፡ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ ይህ የሚገባ ነውና" የተባለው በዕድሜ ልጆች የሆኑትን ብቻ ሳይሆን ወጣቶችንና አዋቂዎችን ሁሉ ይመለከታል (ኤፌ.6፡1)፡፡ ምክንያቱም አዋቂዎችም ለወላጆቻቸው ልጆች ናቸውና፡፡ ወጣቶች ለወላጆቻቸው እየታዘዙ ሰውንም ሁሉ እያከበሩ መኖር የመጀመሪያ ግዴታቸው ይሆናል፡፡ "የጭንቀት ቀን ሳይመጣ በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ" የተባለውን መመሪያ በመከተል ወጣት ምእመናንም የወጣትነት እድሜ ከሚያጋጥመው ፈተና ሁሉ ራስን ጠብቆ ከቁም ነገር መድረስ ታላቅ መንፈሳዊ ተጋድሎን ይጠይቃል (መክ.12፡1)፡፡ አንድ በአን ድ ጸንቶ ሥርዓተ ጋብቻን በተክሊል መፈጸም ከሁሉም ምእመናን የሚጠበቅ ታላቅ ቁም ነገር ነው፡፡ ለጋብቻም ሆነ ለሌላም ጉዳይ የትምህርትና የምክር አ ገልግሎት ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አባቶች ጠይቀው በመረዳት ክርስቲያኖች ሁሉ በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን መኖር ይገባቸዋል፡፡ ድንቁርናና ክፋት በበዛበት ዓለም የሚኖሩ ምእመናን በቀላልም ሆነ በከባድ ኃጢአት ሲወድቁ ሳይውሉ ሳያድሩ ንስሐ መግባት ነው እንጂ ወደፊት አደርገዋለሁ በማለት ላልተወሰነ ጊዜ መቅጠር ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም፡፡ ንስሐ ገብቶ በየጊዜው ሥጋ ወደሙን መቀበል ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ያሰጣል፤ ለልቡናችን ም ከፍተኛ መንፈሳዊ ደስታንና እርካታን ያስገኝልናል፤ በኅሊናችንም ሰላምና መረጋጋት ይሰፍናል፡፡

ምእመናን ሁላችን በመከራና በደስታም ጊዜ ቢሆን ወይም በአልጋ ቁራኛ በደዌ ዳኛ በተያዝንም ጊዜ ቢሆን ሁሉንም ለቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህናት እናስታውቅ በተለይም ጸሎት እንዲያደርጉልን ቀሳውስትን እንጠይቅ፡፡ ስለዚህ ጉዳይ የጌታ ወንድም ሐዋርያው ያዕቆብ የሰጠውን መመሪያ አውቀን እንድንፈጽመው ከዚህ በታች ጽፈነዋል፡-



"ከእናንተ መከራን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ይጸልይ፤ ደስ የሚለውም ማን ም ቢኖር እርሱ ይዘምር፡፡ ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ቀሳውስት ወደ እርሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩ ለት፡፡ የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል፤ ኃጢአትም ሠርቶ እንደሆነ ይሠረይለታል፡፡ እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ፥ ትፈወ ሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች" (ያዕ.5፥13-16)፡፡

በዘመነ ሐዋርያት ይፈጸም የነበረው ይህ ዓይነቱ ሥርዓተ ጸሎት ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን ምሥጢረ ንስሐና ምሥጢረ ቀንዲል ተብሎ እየተሠራበት ይገኛል፡፡ ምእመናን መንፈሳዊ ልደታቸውን ካገኙበት ከጥምቀት ጀምሮ በሞተ ሥጋ ከዚህ ዓለም እስከሚለዩበት ጊዜ ድረስ ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ ምሥጢራትን በመፈጸም ለሥጋና ለነፍስ የሚያስፈልገውን ጸጋ እግዚአ ብሔር ምእመናን እንዲያገኙ ታደርጋለች፡፡ በዕለተ ሞታቸውና ከዚያም በኋላ ጸሎተ ፍትሐት በማድረስ ስለ ነፍሳቸው ደኅንነት ትጸልያለች፡፡ ስለዚህ ከእናታችን ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን መለየት ማለት የነፍሳችንን ደኅንነት ማጣት ማለት ነው፡፡ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ የመዳን ጸጋ የለምና እንግዲህ ለነፍሳችን ደኅንነት፥ ለኃጢአታችን ስርየት፡ ለተስፋችን ጽንዓት፡ ለክርስቲያ ናዊ ሕይወታችን እድገት፡ ለመንፈሳዊና ለማኅበራዊ ሥራችን ሥምረት እን ድናገኝ እያንዳንዱ ምእመን ቢያንስ ቢያንስ የሚከተሉትን ሰባት መመሪያዎች መፈጸም ይኖርበታል፡-

## ሰባቱን መመሪያዎች በመከተል አገልግሎታችንን እንፈጽም

1. እያንዳንዱ ምእመን እሑድ እሑድ ከቤተ ክርስቲያን በሰዓቱ ሄዶ ጸሎተ ቅዳሴውን ይካፈል፥ ተሰጥዎውን በመቀበል ያስቀድስ፡ቃለ ጸሎቱንና ትምህ ርተ ወንጌሉን በማስተዋልና በትጋት ተከታትሎ ይስማ፤ በደዌ ወይም ከአ ቅም በላይ በሆነ ችግር ካልሆነ በቀር በዚች ዕለት ማንም ሰው ከቤተ ክርስቲያን አይቅር፡፡ ይህች ዕለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን የተ ነሣባት የተቀደሰች የክርስቲያኖች ሰንበት ናትና፡፡
2. እያንዳንዱ ምእመን በዓመት ውስጥ በተወሰኑ ጊዜያት ንስሐ ገብቶ ሥጋ ወደሙን ይቀበል፡፡ ዓመቱን ሙሉ አንድ ጊዜ እንኳ ሳይቆርብ ጊዜውን ማሳ ለፍ አይገባውም፡፡
3. ለሞት ቀጠሮ የለውምና ለንስሐ ቀጠሮ አንስጠው፥ እያንዳንዱ ምእመን ሁልጊዜ ራሱን ይመርምር፤ በማወቅም ባለማወቅም የሠራው ኃጢአት ቢኖር ንስሐ ይግባ፤
4. ክርስቲያናዊ ሕይወትን በየቀኑ ከሚያጠናክሩት መንፈሳዊ ነገሮች አንዱና ታላቁ ጸሎት ስለሆነ እያንዳንዱ ክርስቲያን በየቀኑ ሳያቋርጥ አዘውት ሮ ይጸልይ፤ ነቢዩ ዳዊት "ስለ ጽድቅህ ፍርድ ሰባት ጊዜ በቀን አመሰግን ሃለሁ" እንዳለ እንደዚሁ በየጊዜያቱ ለእግዚአብሔር ምስጋና ያቅርብ፤ ሐዋርያ ጳውሎስም "ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ" እንዳለ እንደዚሁ ክርስ ቲያን ሁሉ እግዚአብሔርን ሁልጊዜ ያመስግን፤ ይጸልይ፤ በማያመች ጊዜና ቦታ እንኳ ቢሆን በልቡ ያመስግን፤ የኅሊና ጸሎት ያድርስ፡፡
5. ጾምም እንደ ጸሎት ለመንፈሳዊ ሕይወት አስፈላጊ መሆኑ ከላይ ተገልጿል፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱ ምእመን በቀኖና ቤተ ክርስቲያን በተደነገገው መሠረት ይጹም፤
6. ሰንበት እንዲከበር የታዘዘው በዚያች ዕለት እግዚአብሔርን እያሰብን ስሙን ለመቀደስና መልካም ሥራ ለመሥራት ነው፡፡ እንደዚሁም በዓላትን የምንአ ከብረው ጌታችን ለእኛ ሲል የፈጸመልንን ቸርነትና በጐ ሥራ እያስታወስን ... ግንበትና በእርሱ ያለንን እምነት፥ ተስፋና ፍቅር

www.ethiopianorthodox.org

የምናጠናክርበት ዕለት ነው፡፡ ስለዚህ ማናቸውም ክርስቲያን በፍትሕ መን ፈሳዊ የተደነገጉትን በዓላት ያከብር፡፡

7. በአንቀጸ ምጽዋት በተገለጸው መሠረት እያንዳንዱ ምእመን ይመጽውት፤ ስዕለቱንና መባውን ሁሉ ለቤተ እግዚአብሔር ያግባ፤ የቤተ ክርስቲያንም መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት የተሟላ እንዲሆን በቅዱሳት መጻ ሕፍትና በሕገ ቤተ ክርስቲያን በተደነገገው መሠረት በየጊዜው አስተዋጽኦ ማድረግን አያስታጉል፡፡

ማናቸውም አማኝ ክርስቲያናዊ ሕይወቱ መሟላቱንና መንፈሳዊ ጥረ መፈጸሙን የሚያውቀው ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ዳርዳሩን ወይም ማዶ ማዶ ውን ወይም አግድም አግድሙን በመሄድ ሳይሆን በውስጥዋ በመኖሩ ነው፤ በውስጥዋ መኖሩን ደግሞ የሚያረጋግጠው ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን በተግባር በመፈጸም ይሆናል፡፡ በመመሪያው የታዘዙት መንፈሳዊ ሥራዎች ሁሉ፥ ጊዜንና ዘመንን እየጠበቁ በየቀኑ፥ በየሳምንቱ፥ በየወሩና በየዓመቱ የሚመላለሱ ስለሆነ የቤተ ክርስቲያንን የጊዜ መቁጠሪያ በቅድሚያ አውቆና ጠብቆ እያን ዳንዱ አማኝ መንፈሳዊ መርሐ ግብር አዘጋጅቶ ክርስቲያናዊ ሕይወቱን በሥነ ሥርዓት መምራት ይጠበቅበታል፡፡

ከዚህም ሌላ በቤተ ክርስቲያን የሚዘጋጀውን የመንፈሳዊና የማኅበ ራዊ አገልግሎት በይበልጥ እንዲስፋፋ ለማድረግ ምእመናን በሙሉ ልባቸው የአገልግሎቱ ተሳታፊ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ለሃይማኖታችንና ለቤተ ክርስቲያ ናችን ስንል ራሳችንን ሳንቆጥብ በሙሉ ኃይላችን ከሠራን ጥቅሙና ውጤቱ ለቤተ ክርስቲያናችን እድገት ብቻ ሳይሆን ለሀገርና ለወገንም ይተርፋል፡፡ ስለዚህ በሕገ ቤተ ክርስቲያንና በቃለ ዓዋዲው መሠረት በሰበካ ጉባኤ አስ ተዳዳርና በልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች ገብተው የሚያገለግሉትን አባላት መምረጥ ወይም በአባልነት መመረጥ የካህናትና የምእመናን ሁሉ መብትና ግዴታ መሆኑን አውቀን በይበልጥ በትጋት መሥራት የሁላችንም ኃላፊነት ነው፡፡ ይልቁንም በአሁኑ ጊዜ የስብከተ ወንጌሉ ሥራ እንዲስፋፋ፥ የሰንበት ት/ቤቱ እንዲጠናከር፥ የትምህርት ክፍሉ በሥርዓተ ትምህርት እንዲዘጋጅ ለማድረግ የካህናትንና የምእመናንን ያልተቆጠበ የጋራ ጥረት ይጠይቃል፡፡



# ምዕራፍ ሁለት

## ክርስቲያናዊ ሕይወትና ሥነ ምግባር በሁለቱ የፍቅር ትእዛዛት በአሥሩ ቃላት

### መ ግ ቢ ያ

በምዕራፍ አንድ የተራራውን ስብከት መሠረትና መነሻ በማድረግ ክርስቲያናዊ ሕይወታችንና ምግባራችን በሃይማኖተ ወንጌል፥ በሕገ ወንጌልና በምግባረ ወንጌል ላይ መገንባት እንዳለበት አመልክተናል፡፡

ሕገ ኦሪት በሕገ ወንጌል እንዴት ተተርጉሞ ለክርስቲያኖች መመሪያ ሆኖ እንደተሰጠ በ፰ቱ ቃላተ ወንጌል ተምረናል፡፡ በምዕራፍ ሁለት የአሥሩ ቃላት ትምህርታችንም በዚሁ መንገድ ይቀጥላል፤ በተለይም በሕገ ተፋቅሮ መሠረትነት በዝርዝር ይቀርባል፡፡

አሥሩ ቃላት ለዕለት በዕለት ሥራችንና ለማኅበራዊ ኑሮ ግንኙነታችን የሚረዳ የሥነ ምግባር መመሪያ ብቻ አይደለም፡፡ ለመዳናችንና ለመጽደቃችን ወደ ዘላለም ሕይወትም ለመግባታችን ከእምነትና ከምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ጋር ትእዛዛትን መፈጸም አስፈላጊ እንደሆነ ከላይ በክፍል ሦስት በምዕራፍ አንድ (ሠ) ተመልክተናል፡፡ ለዚህ መረጃ የሰጠነው "ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ . . . ትእዛዛትን ጠብቅ" የሚለውን የጌታን ቃል ነው፡፡ ጌታም ትእዛዛቱን እንደሚከተሉት ዘርዝሯቸዋል፦

- "አትግደል
- አታመንዝር
- አትስረቅ
- በሐሰት አትመስክር
- አባትህንና እናትህን አክብር
- ባልንጀራህንም እንደራስህ ውደድ" የሚሉ ናቸው (ማቴ.19፥16-19)፡፡

እነዚህ ከሕገ ኦሪት ከአሥሩ ቃላት የተውጣጡት ትእዛዛት ከላይ እንደጠቀስነው ወደ ሕይወት ለመግባት የሚያስፈልጉን ስለሆኑ ጌታ እንዳዘዘን በትጋትና በጥንቃቄ ልንጠብቃቸው ይገባናል እንጂ ሕግን መፈጸም እንደማይቻልና እንደማያስፈልግ አድርጐ መናገር የጌታን ቃል ማስተሐቀር ይሆናል፡፡ ሕግን ፈጽሞ እንድንፈጽም ያዘዘን ጌታ አምላክ ሕጉን እንድንጠብቅ የሚረዳንን ጸጋ መንፈስ ቅዱስ እንደሰጠን ከላይ በምዕራፍ አንድ (ረ) ገልጸናል፡፡ በጸጋው ሥር ነንና እምነት እንጂ ሕግ አያስፈልገንም ማለት አይገባንም፡፡ ምክንያቱም ሐዋርያው ጳውሎስ እንዳስተማረን "እንግዲህ ሕግን በእምነት እንሽራለን? አይደለም፤ <u>ሕግን እናጸናለን እንጂ</u>" ብሎናልና (ሮሜ.3፥31)፡፡

ይኸው ሐዋርያ ስለ ሕግ በተናገረበት በሮሜ ምዕ.7 ሕግን ለመፈጸም የሰውን ውስጣዊ ትግል አሳይቶ በመጨረሻም ሕገ እግዚአብሔርን የሚቃወም በሥጋ ባሕርያችን በሰውነታችን ውስጥ የሚገኝ ሕገ ኃጢአት እን [illegible] ይህ ሕገ ኃጢአት ሕገ እግዚአብሔርን እንዳንፈጽም

www.ethiopianorthodox.org

የሚዋጋንና የሚማርከን በውስጣችን የሚገኘው ፈቃደ ሥጋ እንደሆነ የታመ ነው (ገላ.5፥16-26)። ሰው በራሱ ጥረት ብቻ ሕግን ሊፈጽም እንደማይችል ከዚህ እንማራለን። ሕገ እግዚአብሔርን ካልፈጸመ ደግሞ ይፈረድበታል። እንግዲህ ሰው ያለ እግዚአብሔር ረድኤት ምንኛ ጐስቋላ እንደሆነና ከዚህ የኃጢአት ምርኮኝነትና የሞት ፍርድ ማን ነፃ ሊያወጣውና ሊያድነው እንደሚችል ሐዋርያው በአንክሮ ይጠይቅና "እኩት እግዚአብሔር በእንተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ" በማለት ይመልሳል። ይህም ማለት እግዚአብሔር "የባሕርይ ልጁ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሰዶ (ልኮ) አዳነኝ፤ ያዳነኝ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን" ማለት ነው (ሮሜ.7፥21-25 ትርጓሜውን ተመልከት)።

ይህን ካለ በኋላ ሐዋርያው "እንግዲያስ እኔ በአእምሮዬ ለእግዚአብሔር ሕግ፥ በሥጋዬ ግን ለኃጢአት ሕግ እገዛለሁ" ማለቱ ምን ይሆን ብለን እንጠይቅ ይሆናል (ሮሜ.7፥25)። በክርስቶስ መምጣት ኃጢአታችን ተወግዶ በጸጋው ካዳነን በኋላም በሰውነታችን በሥጋችን ውስጥ ሕገ ኃጢአት ማለት ፈቃደ ሥጋ እንደማይጠፋ ለማመልከት ሐዋርያው ይህን ተናገረ እንጂ ክርስቲያን ሁሉ ለሁለቱ ሕጐች እየተገዛ ይኖራል ወይም ተገዝቶ መኖር ይገባዋል ለማለት አይደለም። ክርስቲያኖች ያለ መንፈሳዊ ትግል እንዲሁ እንዲቀመጡ ሐዋርያው አላስተማረም፤ ይህንንም ለማስረዳት በሚቀጥለው ምዕራፍ በሮሜ ምዕ.8 ገልጾታል። በፈቃደ መንፈስ ቅዱስ በመመራት ሕገ ኃጢአትን ወይም ፈቃደ ሥጋን መታገል እንዳለብን ከተጠቀሰው ምዕራፍ በሰፊው ለመማር እንችላለን። "እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኃጢአትን በሥጋ ኰነነ" በማለት በክርስቶስ ሞት መዳናችንን አብሥሮናል። በመቀጠልም የሁለቱ ዓይነት ሰዎች ሁኔታ ምን እንደሆነ እንደሚከተለው ይገልጽልናል።

> "እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያስባሉና እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር ያስባሉ። ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፥ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው። ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፥ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፥ መገዛትም ተስኖታል፤ በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም" ካለ በኋላ መልእክቱን ሲያጠቃልል፦ "እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም። የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም" ብሏል (ሮሜ.8፥3-9)።

የክርስቶስ ወገን ያልሆነ የእግዚአብሔር መንፈስ የለውምና እንደ ሥጋ እንጂ እንደ መንፈስ ፈቃድ አይኖርም። ከላይ እንደ ተጠቀሰው "ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛም፥ መገዛትም ተስኖታል" የተባለው በሥጋ ያሉትን ያመለክታል። በክርስቶስ መንፈስ የሚኖሩ ግን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ረድኤት ስላላቸው ሕገ ኃጢአትን እየተቋቋሙ ለሕገ እግዚአብሔር ብቻ ተገዢ ሆነው ይኖራሉ። ያለፈው ኃጢአታቸውንና ሕግ መተላለፋቸውን ይቅር እንዳላቸው፥ ከሚመጣውም እንዲጠብቃቸውና የጸጋውን አጋርነት እንዲያበዛላቸው "እኩት እግዚአብሔር በእንተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ፦ በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን" እያሉ ከማመስገንና ከመጸለይ አያቋርጡም።

በመንፈስ ሆነን ሕገ ኃጢአትን መታገል እንጂ እኔ በሥጋዬ ለኃጢአት ሕግ ተገዢ ነኝ (ሮሜ.7፥25) ያለውን ንባብ ብቻ ይዞ ያለምንም መንፈሳዊ ተጋድሎ መቀመጥ የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ ማስተጓጐል፥ ያደረገልንንም ታላቅ ውለታ መዘንጋት ይሆንብናል። ስለዚህ ቀጥሎ

www.ethiopianorthodox.org



የተመለከተውን የሐዋርያውን የትግል መመሪያ እንከተል።

> "እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፥ ዕዳ አለብን፥ እንደ ሥጋ ፈቃድ ግን እንኖር ዘንድ ለሥጋ አይደለም። እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና፤ በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ። በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና" (ሮሜ.8፥12-14)።

ከጥቅሱ ላይ "በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት ትኖራላችሁ" የተባለው ምንድን ነው? መንፈሳዊ ተጋድሎን እያስተማረን አይደለምን? "የሰውነት ሥራ" የተባለው ፈቃደ ሥጋ ያለበት ሕገ ኃጢአት ስለሆነ እርሱን በመንፈስ ኃይል እንድንገድለው ማለት በጸጋ መንፈስ ቅዱስ አጋዥነት ሁልጊዜ እንድንታገለው የተሰጠን የክርስቲያናዊ ሕይወት መመሪያችን ነው። በሥጋ ባሕርያችን በጥንተ ተፈጥሮ ያለው ሕገ ኃጢአት አሁንም እየሠራብን ነው። በሐዲስ ተፈጥሮ በክርስቶስ ያገኘነው መንፈስ ቅዱስ ግን ወድቀንና ተስፋ ቆርጠን እንዳንቀር እያጽናናን፥ ወደ ንስሐ እየመራን፥ ይቅር እያለንና የተጋድሎ ጸጋን እየሰጠን እስከ ሞት ድረስ በትዕግሥትና በእምነት እኛን አጽንቶ በመጨረሻ ድልን በጸጋው እንድንቀዳጅ ያበቃናል። ስለዚህ ነው ሕገ ኃጢአትን ማለት የሰውነትን ሥራ በመንፈስ ኃይል ተጋድሎ እንድናደርግ ከላይ ከምንባቡ የተጠቀሰው። እንግዲህ ሕገ ኃጢአትን በሕገ እግዚአብሔር፥ ፈቃደ ሥጋን በፈቃደ ነፍስ እየተዋጋን በመንፈስ እንድንኖርና በመንፈስ እንድመራ "እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መከራን" እንድንቀበል በሐዋርያት ቃል ታዝዘናል (ገላ.5፥16-25፤ ቆላ.3፥5-11፤ 1ኛጴጥ.4፥1-19፤ ያዕ.4፥1-10)።

መቼም ቢሆን መሰናክል በማይቀርበት፥ ውጣ ውረድ በበዛበት መከራና ፈተና በማይለይበት ዓለም ስንኖር መንፈሳዊ ተጋድሎ እንጂ ድል አድርጐ በእፎይታና በሰላም መቀመጥ አይቻልም። የነፍስ ድል በሥጋ ላይ ሙሉ በሙሉ የሚገኘው በትንሣኤ ዘጉባኤ ነው። በዚህ ድንኳን ሰውነታችን እስካለን ድረስ እንቃትታለን፤ መልካሙን እንመኛለን፥ በጎውን ለማድረግ እንሞክራለን። ነገር ግን አምነን ከተጠመቅን ከዳንም በኋላ እንኳ የኃጢአት ቅሬታ ከውስጣችን አይጠፋም። ምንም እንኳ በእምነትና በጥምቀት ጥንተ አብሶና እኛም የሠራነው ኃጢአት ተደምስሶልን[80.1] ከነፍስ ሞት (ከዳግም ሞት) ድነን ለገነት ለመንግሥተ ሰማያት የታደምን ብንሆንም አንዳንድ ጊዜያዊ የኃጢአት

[80.1] ጥንተ አብሶ (የመጀመሪያው የአዳም በደል) መደምሰሱ እንዴት ነው? ጌታ በመስቀል ላይ ሳለ በደሙ ፈሳሽነት ካሣ ከፍሎ ለዓለም ሁሉ ቤዛ ሆኖ የማዳን ሥራውን በዕለተ ዓርብ በመፈጸም ከመጀመሪያው አዳም ጀምሮ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ የሚነሡትን የሰው ዘር ሁሉ ከኃጢአትና ከሞት አድኗቸዋል። በዚህ ጊዜ ነበር በዘር የተላለፈውን ጥንተ አብሶ ጌታችን ለአንዴና ለዘለዓለም የደመሰሰው። ሆኖም ጥንተ አብሶ ተወግዶ የኃጢአት ሥርየትና የዘለዓለም ሕይወት ጸጋ የተሰጠው ለሚያምኑት እንጂ ለማያምኑት አይደለም። ምንም የዕለተ ዓርቡን የማዳን ሥራና ጸጋ እግዚአብሔር ለዓለም ሁሉ የሰጠው ቢሆንም ክርስቶስንና ጸጋውን የሚክዱትና የሚቃወሙት ግን ከመጀመሪያው አዳም እዳ በደልና መርገም ነፃ አይሆኑም። በዳግማዊ አዳም በክርስቶስ የተገኘውን ጸጋ አምነው አልተቀበሉምና በመጀመሪያው አዳም መርገም ሥር እንደሆኑ ይቀራሉ። በንሙ ኮንኑ እንደነበሩ ሰዎች ይቆጠራሉ። ምክንያቱም እነርሱ የመዳኛቸውን ጸጋ የተሰቀለውን ክርስቶስን በመካዳቸው ነው። ሙሴ የሰቀለውን የናስ እባብ ያዩት ብቻ እንጂ ያላዩት አልዳኑም። የተሰቀለው የናስ እባብ ለእሥራኤላውያን በሙሉ ሆኖ ሳለ ከእባቡ መርዝ የዳኑት ግን የሙሴን ቃል አምነው የታዘዙት ብቻ ነበሩ። እንደዚሁም ጌታ የተሰቀለው ለዓለም ሁሉ ቢሆንም ሞትን ካመጣው ከእባቡ ከዲያብሎስ የኃጢአት መርዝ ማለት ከጥንተ አብሶ የዳኑት ግን ያመኑትና የተጠመቁት ብቻ ናቸው (ዘኁ.21፥5-9፤ ዮሐ.3፥14-19፤ ዘፍ.3)።

እንግዲህ ለኃጢአት መደምሰሻ ለመንግሥተ ሰማያት መውረሻ እግዚአብሔር ለዓለም ሁሉ ያዘጋጀው የመስቀል መድኀኒት ለሁሉም በመለኮታዊ እጥፎ ተሰጥቷል። ሆኖም መድኀኒቱን አምነን ካልተቀበልነው መስጠቱ ብቻ አያድነንም። ለምሳሌ ሐኪም ያዘዘው መድኀኒት ካልተወሰደና ከሰውነታችን ገብቶ ካልተዋሐደ በስተቀር በውጭ መኖሩ ብቻ ፈውስ አያስገኝም። ስለዚህ እውነተኛው ሐኪም ጌታችን በመስቀል ላይ ለቤዛ ዓለም የሰጠው ሥጋውና ደሙ እውነተኛ መድኀኒት መሆኑን አምኖ የተቀበለው ብቻ ከኃጢአትና ከሞት ይድናል፥ የዘለዓለም ሕይወትን ጸጋ ይጎናጸፋል፤ ያልተቀበለ ግን እንደተጻፈው «የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቈጠረ [illegible] ... ስለሆነ ከጥንተ አብሶ መርገም ስለማይድን የሞት ሞት ይፈረድበታል (ዕብ. 10፥29-31 [illegible])።

www.ethiopianorthodox.org

ውጤቶች ርዝራዦች በውስጣችን ይቀራሉ፤ በጉስቋላው የሥጋ ባሕርያችን ይገኛሉ፡፡ እነርሱም ድካምና መከራ፥ ሕማምና ሞት እንደዚሁም በዚህ ዓለም ሕይወታችን የሚታየው የጠባይ ደካማነትና ሥጋዊ ምኞች፥ ለሐሰት ነገር ለፈተና በቀላሉ መጋለጥና ለእነርሱም እጅ በመስጠት መስማማትና መማረክ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ፈቃደ ሥጋ ማለት የሥጋ ምኞት የኃጢአት ዝንባሌ ጥንትም ሆነ ዛሬ ሊፈትነን ከእኛ ጋር ይኖራል፡፡ ከእኛ ጋር በመኖሩም ኃጢአት አይሆንብንም፤ እንደ ባላንጣ፥ እንደ ማይላቀቀት ባለጋራ ሁልጊዜ ስለሚሞግተን ሁልጊዜ መታገል ይኖርብናል፡፡ ለእርሱ እጅ በሰጠን ጊዜ ብቻ ኃጢአት ይሆንብናል እንጂ እርሱ ከእኛ ባሕርይ ውስጥ በመኖሩ ብቻ ኃጢአት አይሆንብንም፡፡ ስለዚህ እኔ እየጾምኩና እየጸለይኩ ለምን የሥጋ ፈቃድ በውስጤ ይገኛል ለምን ልማደ ሰብእ አይጠፋልኝም ብሎ መጨነቅ ሳይሆን ዘወትር ፈቃደ ሥጋን፥ ፍትወታት እኩያትን በእግዚአብሔር አጋዥነት እስከ ዕለተ ሞት መታገል ያስፈልጋል፡፡ የሰው ተፈጥሮ እንደ መልአክ ተፈጥሮ ስላልሆነ በዚህ በጉስቋላ ሰውነታችን እስከ አለን ድረስ ከፈቃደ ሥጋ ጋር ያላሠለሰ ትግል እያደረግን መኖር እንጂ ትግል አልባ የሆነ ፍጹም ሰላማዊ ኑሮ አይገኝም፡፡ ነገር ግን ትግሉ ወደፊት ለሚመጣው ሰላምና ደስታ መንገድ ያዘጋጅልናል፡፡

ከፈቃደ ሥጋ ጋር ባለማስማማት በክርስቶስ ጸጋ ሆነው በቆራጥነት የሚታገሉት አይጐዱም፡፡ ካልታገሉ ፈተናውን ማለፍ አይችሉምና፡፡ መታገል ማለት ደግሞ እንዲያው በከንቱ አይደለም፡፡"ነፋስን እንደሚጐስም ሁሉ እንዲሁ አልጋደልም" በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ እውነተኛው ተጋድሎ አስረድቶናል፡፡ በመቀጠልም "ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጐሰምሁ አስገዛዋለሁ" ብሏል (1ኛቆሮ.9፥26-27)፡፡ "ደግሞም በጨዋታ የሚታገል ማንም ቢሆን፥ እንደሚገባ አድርጐ ባይታገል፥ የድሉን አክሊል አያገኝም" (2ኛጢሞ.2፥5)፡፡ እንግዲህ ባጋጠመን ፈተና ብዙ አንጨነቅ፡፡ "ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና አልደረሰባችሁም" ተብሎ ተጽፏልና፡፡ "ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው፥ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል" (1ኛቆሮ.10፥13)፡፡

እንግዲህ ተጋድሏችን ሕገ እግዚአብሔርን ለመፈጸም ነው፡፡ እግዚአብሔር ሕጉን ለሰው ልጆች የሰጠው ከአምልኮ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ ሊመልሳቸው ነው፡፡ "ተገሐሥ እምእኩይ ወግበር ሠናየ" ማለት ከክፉ ነገር እንድንከለከል መልካሙን እንድናደርግ ሕጉ ይመራናል (መዝ. 33፥14) ፡፡ በሕገ እግዚአብሔር አንፃር ጸጋ እግዚአብሔር አለ፡፡ ስለሆነም በሕጉ መርቶ በጸጋው ደግፎ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚያገባን እርሱ ነው፡፡ ስለዚህ እርሱን አምነን በእርሱ ታምነንና ተስፋችንን በእርሱ ጥለን ሕጉን ለመፈጸም ያልተቆጠበ ጥረት እናድርግ፡፡

ሕገ እግዚአብሔርን መፈጸም ማለት ለአሥሩ ቃላት መታዘዝ ነው፡፡ አሥሩ ቃላት ደግሞ በፍቅር ትእዛዛት ይጠቃለላሉ፡፡

> "እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ፥ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታልና፡፡ አታመንዝር፥ አትግደል፥ አትስረቅ፥ በውሸት አትመስክር፥ አትመኝ የሚለው ከሌላይቱ ትእዛዝ ሁሉ ጋር በዚህ፡ ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቃልሉአል፡፡ ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው" (ሮሜ.13፥8-10)፡፡



እንግዲህ ፍቅር የአሥሩ ቃላት ሁሉ ማጠቃለያ ነው፡፡ ስለዚህም ነው ጌታችን በማቴዎስ ወንጌል ምዕ.19፥18-19 ትእዛዛትን ከዘረዘረ በኋላ በመጨረሻ "ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ" ያለው፡፡ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንትም ይህን ይዘው የአሥሩ ቃላት የመጨረሻና የማጠቃለያ ትእዛዝ እንዲሆን አድርገውታል፡፡

የፍቅርን ትእዛዝ በመፈጸም የዘላለም ሕይወትን ለመውረስ እንደሚቻል ጌታ በወንጌል አስተምሮናል፡፡ ከላይ ከተጠቀሰው (ማለት ማቴ. 19፥16-19) ሌላ አንድ የሕግ አዋቂ ስለዘላለም ሕይወት ጌታን ሲጠይቅ፦ "የዘላለምን ሕይወት እንድወርስ ምን ላድርግ? አለው፡፡ እርሱም በሕግ የተጻፈው ምንድር ነው? እንዴትስ ታነባለህ?አለው፡፡ እርሱም መልሶ፦ ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም ኃይልህም በፍጹም ሐሳብህም ውደድ፥ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው"፡፡ ኢየሱስም፦ "እውነት መለስህ፤ ይህን አድርግ በሕይወትም ትኖራለህ አለው..." (ሉቃ.10፥25-37)፡፡ እንግዲህ ከዚህ ከጌታ ቃል በተለይም ከርኅሩኁ ሳምራዊ በጐ አድራጐት የምንማረው ሰው ሊድንና የዘላለም ሕይወት ሊወርስ የሚችለው አንዳንድ ወገኖች እንደሚሉት ያለ ምንም ሥራ በእምነት ብቻ አይደለም፡፡ በእርግጥም ሰው በመጀመሪያ እምነት ሊኖረው የግድ ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ብቻ መንግሥተ ሰማያት መግባት ስለማይቻል ፍቅርንና በጐነትን በእምነት ላይ ጨምረን መያዝ ይኖርብናል (2ኛጴጥ.1፥5-7፤ ገላ.5፥6)፡፡ ከእምነት ጋር የፍቅርን ትእዛዛት በመፈጸም ለዘላለም ሕይወት የበቃን እንሆናለን፡፡

ስለዚህ ክርስቲያናዊ ሕይወታችን በፍቅር ትእዛዛት መጠናከር ያስፈልገዋል፡፡ የመጀመሪያውና ታላቁ ፍቅራችን ከሁሉም በላይ እግዚአብሔርን መውደድ ይሆናል፤ ቀጥሎም ሰውን ሁሉ ከራስ ጋር አስተካክሎ መውደድ እንደሆነ ተረድተናል፡፡ እንግዲህ ክርስቲያናዊ ሕይወታችን በሁለት ወገን የተያያዘ የፍቅር ሕይወት ነው፤ በፍቅረ እግዚአብሔርና በፍቅረ ቢጽ ተመሥርቶና ተዋቅሮ በአሥሩ ቃላት የተገነባ መንፈሳዊና ማኅበራዊ ሕይወት ነው፡፡ ይህ ጣምራ የፍቅር ሕይወት በአሥሩ ቃላት ተዘርዝሮ በተግባር ይገለጣል፡፡ በፍቅረ እግዚአብሔርና በፍቅረ ቢጽ ሕግና ነቢያት ሁሉ ይፈጸማሉ (ማቴ.22፥37-40)፡፡ ከዚህ ቀጥሎ አሥሩ ቃላትን በሁለቱ የፍቅር ትእዛዛት ከፍለን እንመለከታለን፡፡

የመጀመሪያውና ታላቁ ትእዛዝ ማለት ፍቅረ እግዚአብሔር ከአሥሩ ቃላት በመጀመሪያዎቹ በአራቱ ሲገለጽ ስድስቱ ደግሞ ሁለተኛውን ትእዛዝ ማለት ፍቅረ ቢጽን ይመለከታሉ፡፡ አራቱ ለእግዚአብሔር ልናደርግ የሚገባንና የማይገባንን ይደነግጋሉ፡፡ የትእዛዛቱም አፈጻጸም በፍቅረ እግዚአብሔር መሠረትነት ይወሰናሉ፡፡ የተቀሩት ስድስቱ ትእዛዛት ለሰዎች ልናደርግ የሚገባንና የማይገባንን ስለሚደነግጉ ትእዛዛቱ በፍቅረ ቢጽ መሠረትነት ይፈጸማሉ፡፡ እንግዲህ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር በእነዚህ በሁለቱ የፍቅር ትእዛዛት ላይ የተመሠረተ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

በአጠቃላይ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር በእምነት፥በተስፋና በፍቅር ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ መጀመሪያ ነው ከክፉ መራቅም ማስተዋል ነው እንደተባለው እምነትና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው ሰው ትእዛዙን ለመጠበቅ ይተጋል፡፡ ስለዚህ ነው እምነት የክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ምንጭ ነው የሚባለው፡፡ ስለእግዚአብሔር የማያውቁና እርሱንም [illegible] ትና ለኃጢአት ሥራ ፈጽሞ የተጋለጡ ናቸው፡፡ እግዚአ

www.ethiopianorthodox.org

ብሔርን ማመንና ማፍቀር ግን ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን ለሥነ ምግባራ ሥምረት ይሰጠዋል፤ የጽድቅን ሥራ ያጠናክረዋል፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ እ ነትና አምልኮት.ስለሚያስፈልግ የአሥሩ ቃላት የመጀመሪያው ትእዛዝ እ ምልክ ነው፡፡ ኢታምልክ ለዘጠኙ ሁሉ መነሻና መሠረት ነው፡፡

ስለዚህ አሥሩ ቃላት እንደሌሎቹ የሥነ ምግባር መመሪያ ሰዎች ለሰዎች ለሚያደርጉት ማኅበራዊ ግንኙነት ብቻ ተወስኖ የሚቀር አ ደለም፡፡ የአሥሩ ቃላት ትእዛዛት በእግዚአብሔር አምልኮት ላይ የተመሠረ ነው፤ ከማኅበራዊ ግንኙነቱም በፊት አምላካዊ ግንኙነት ይቀድማል፤ ሁለቱ እንደ አንድ አካል አንድ ስለሆኑ አይለያዩም፡፡ ስለዚህ በአሥሩ ቃላት የእ ነትና የምግባር ትእዛዛትን በአንድነት እናነባለን፤ እነርሱ የምግባርና የሃ ማኖት ሕግ ሆነው ተሰጥተውናልና፡፡

እንግዲህ እነዚህን በእግዚአብሔር ጣት የተጻፉትን የቃል ኪዳ ምስክር የሆኑትን የአሥሩ ቃላትን ትእዛዛት መጠበቅና ማስጠበቅ የሁላችን ግዴታ ነው፡፡ ቃሉን ሰሚዎች ብቻ ሳንሆን ፈጻሚዎችም መሆን ይኖርብናል፡፡ ከትእዛዛቱ ሁሉ አንዱን ብንሽር ሁሉንም እንደሻርን ይቆጠራልና ከእያንዳን የሕግ ቃል ጋር የራሳችንን እምነትና ምግባር እየመረመርንና እየለካን ድ ጉናችንን እየመዘንና እየገመገምን በዚያ ላይ ትኩረት ሰጥተን የእርም እርምጃ መውሰድ ይገባናል (ያዕ.1፥22፤ 2፥10) ፡፡

አሥሩ ቃላት የእግዚአብሔር የማዳኑ ሥራ በታሪክና በምሳሌ ከተፈጸመ በኋላ ማለት ከግብፅ የባርነት ቤት በነፃነት ለወጡት ወገኖች የተሰ ትእዛዛትና የቃል ኪዳኑ መግለጫዎች ናቸው (ዘጸ.24፥1-8፤ ዘዳ.4፥13፤ 5፥33)፡፡ ለእኛም ለክርስቲያኖች እንደዚሁ ከኃጢአትና ከሞት ለዳነ ከዲያብሎስ ባርነት ነፃ ለወጣነው ወገኖች በአዳኛችን በክርስቶስ በሕገ ወንጌል ፍጹም ሆነውና ተጠናክረው ተሰጥተውናል (ማቴ.5፥17-48)፡፡ ስለዚህ የአሥሩ ቃላትን ትእዛዛት ደስ እያለን ምሕረት ያደረገልንንና ተስፋ የሰጠንን እግዚአ ብሔርን እያመሰገንን፥ የቸርነቱን ሥራ እያሰብንና ውለታውን ሁሉ እያስ ወስን በመንፈሳዊ ቅንዓት ተነሣሥተን በትጋት ለመፈጸም ያልተቋጠበ ጥረትና ትግል እናድርግ፤ በሕጉ እየተመራን፥ እንዳንወድቅ በጸጋው እየተደገፍን፤ በእርሱ እንኑር በፍቅሩ እንኑር፥ ቃሉም በእኛ ይኑር፥ እኛም በቃሉ እንኑር፤ ያለእርሱ በሕይወት ለመኖር አንችልምና፥ ያለእርሱ ምንም ምን ለማድ ረግ አንችልምና (ዮሐ.15፥1-17)፡፡ በእርሱ መኖር በመንፈስ ቅዱስ መኖር ነው፡፡ "ከመንፈሱ ስለሰጠን፥ በእርሱ እንድንኖር እርሱም በእኛ እንዲኖር በዚህ እናውቃለን" (1ኛ ዮሐ.4፥13)፡፡

እንግዲህ ራሳችንን ለሁለቱ የፍቅር ትእዛዛት አስገዝተን ክርስቲያናዊ ሕይወታችንን ለመምራት እንድንችል የአሥሩ ቃላትን ትእዛዛት አጥንተንና አው ቀን ለመተግበር እንዲመቸን በሕገ ተፋቅሮ መሠረትነት በሁለት ክፍለ በሚከተለው አኳኋን አስቀምጠናቸዋል፡፡ (የአሥሩ ቃላትን ዝርዝር በክፍል ሦስት መግቢያ ውስጥ እንዲሁም በምዕራፍ ሁለት የአርእስት ማውጫ ላይ ተመልከት)፡፡

### ሀ) የመጀመሪያውና ታላቁ የፍቅር ትእዛዝ፦

### "ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ"

ይህ የፍቅር ትእዛዝ ለእኛ ከመሰጠቱ በፊት እግዚአብሔር እኛን በቅድሚያ በፍጹም ፍቅር ወድዶናል፡፡ ፍቅሩንም በማዳን ሥራው ገልጾታል፡፡ በመጀመሪያ በታሪክና በምሳሌ እ

www.ethiopianorthodox.org



ግብፅ ከባርነት ቤት ነፃ በማውጣቱ፥ በኋላም በክርስቶስ ነፍሳትን ከሲኦል ከሰይጣን ግዞት ነፃ አውጥቶ በማዳኑ "እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር አው ቀናል፥ አምነንማል" (1ኛዮሐ.4፥14-16)፡፡ እንግዲህ እሱ እኛን እንደወደደን እኛም እሱን እንወደዋለን፡፡ እሱ እኛን መውደዱን በተግባር እንደ ገለጸልን እኛም እርሱን በፍጹም ኃይላችን መውደዳችንን በተግባር መግለጽ ይኖር ብናል፡፡ ይህንንም ለማድረግ የምንችለው የአሥሩ ቃላት ትእዛዛትን በመፈጸም ነው፡፡ ከወደድነው ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክን ማምለክ የለብንም፡፡ ከወደድ ነው ስሙን በከንቱ ወይም በሐሰት መጥራት አይገባንም፡፡ ከወደድነው የእርሱ የሆነውን ሁሉ ማክበርና ቃሉንም መጠበቅ ይኖርብናል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በፍቅረ እግዚአብሔር ውስጥ የሚጠቃለሉትን የመጀመሪያዎቹን አራቱን የአሥሩ ቃላትን ትእዛዛት እንመለከታለን፡፡

### ፩ኛ. "እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ"

የዚህን የመጀመሪያውን ትእዛዝና የሌሎችንም ትእዛዛት ቃል በቃል አጥንተን በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ውስጥ ተግባራዊ በማድረግ ክርስ ቲያናዊ ሕይወታችንን በቃለ እግዚአብሔር ማጠናከር ይገባናል፡፡ ከአሥሩ ቃላት ሁሉ በሰፊው የተገለጸና በተለይም በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በብዛት የተነገረና የተተረጐመ የመጀመሪያው ትእዛዝ ነው፡፡ ስለዚህ የትእዛዙን ሙሉ ቃል ከተመሳሳዩ የወንጌል ቃል ጋር እንደሚከተለው እናቀርባለን፡፡

> "ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ፡፡ ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ" (ዘጸ.20፥2-3)፡፡ "ለጌታህ ለአ ምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏልና" (ማቴ.4፥10)፡፡

ይህ የመጀመሪያው ትእዛዝ የምግባርና የሃይማኖት መሠረት ነው፡፡ ያለ እርሱ ክርስቲያናዊ ሕይወት አይኖርም፡፡ ሁሉ ነገር ከእግዚአብሔር እንደተገኘና እኛም በእርሱ ስለ ተፈጠርን ከሁሉ ነገር አስቀድመን እርሱን ማወቅና ለእርሱ መገዛትም ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ በመጀመሪያ ህልዎቱን ቀጥሎ ማንነቱን ማለት ጠባይዓቱን ከዚያም ትእዛዛቱን አውቀን ለእርሱ መገዛትና እርሱን ብቻ ማምለክ እንደሚገባን እንመለከታለን፡፡

### 1. "እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ" "ያለና የሚኖር እኔ ነኝ" - ህልዎቱ

አሥርቱ ቃላት የምግባር መመሪያ ብቻ ሳይሆን በይበልጥ የሃይማኖት ሕግ ያለበት እንደሆነ ከላይ በመግቢያው ጠቅሰናል፡፡ ከምግባር ሃይማኖት ስለሚቀድም የአሥሩ ቃላት የመጀመሪያው አንቀጽ የእግዚአብሔርን ህልዎት (መኖር) የሚገልጽ ነው፡፡ ከህልዎቱ ጋር ደግሞ አድኅኖቱንና ፍቅሩን፥ ክብሩንና ምስጋናውን ማወቅና ማመን አስፈላጊና ጠቃሚ ስለሆነ ከብዙው በጥቂቱ እንደሚከተለው ለማየት እንሞክራለን፡፡

### በቅድሚያ የእግዚአብሔርን ህልዎትና አድኅኖት ማወቅና ማመን

በልብ መታሰቡ በቃል መነገሩ ከፍ ከፍ ይበልና ሰውን የሚወድድ እግዚአብሔር በታላቅ መለኮታዊ መገለጥ በሲና ተራራ ላይ በሚነደው እሳት መካከል ሆኖ በተራራው እግር ሥር ለተሰበሰቡት ወገኖቹ ለእሥራኤል ሕዝብ ... ም በድንጋይ ጽላት ላይ ጽፎ የሰጣቸው የመጀመ

ሪያው አንቀጽ፦ " አነ ውእቱ እግዚአብሔር አምላክከ" ማለት "እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ "የሚል ነበር፡፡ " እኔ ነኝ" የሚለው የመጀመሪያው የዕብራይስጡ ቃል ለሙሴ የተገለጸውን ስመ አምላክ ያመለክታል፡፡ ይኸውም "አነ ውእቱ ዘሀሎ ወይሄሉ" "ያለና የሚኖር እኔ ነኝ" የሚለውን ኀቡዕ ስም ያስገነዝበናል (ዘጸ.3፥13-14)፡፡ ይህ ስያሜ የሀልዎቱ የህልውናው ስም ነው፡፡ በዕብራይስጡ ያህዌህ (Yahweh) ይባላል፡፡

ያህዌህ የሚለውን ቃል በቀላሉ ለመተርጐም ያስቸግራል፡፡ ቃሉ የሚያመለክተን "ያለና የሚኖር እርሱ ነው" ለማለት ነው፡፡ እንደ ሰባው ሊቃናት ትርጉም "እኔው አንዱ እኔው ነኝ" ወይም "እኔ ያው እኔው ነኝ" ማለት ይሆናል፡፡ ካለመኖር ወደ መኖር ለመጣው ነገር ሁሉ መንሥኤና አስገኝ እርሱ ብቻ ነው ማለት ሲሆን በአጠቃላይ ሀልዎቱንና አስገኝነቱን (ፈጣሪነቱን) የሚገልጽ ቃል እንደሆነ ሊቃውንት ያስረዳሉ፡፡ እግዚአብሔር ራሱ ለራሱ የሰጠው ልዩ ስም ስለሆነ በዕብራውያን ዘንድ የተቀደሰ ስመ አምላክ ነው፡፡ ስለዚህም እርሱን ሁልጊዜ በዚህ ስም አይጠሩትም፡፡ በምትኩ አዶናይ ማለት ጌታ (እግዚእ) በሚለው ቃል ይጠቀማሉ፡፡ በግሪኩ ኪሪዮስ ይባላል፤ ትርጉሙም ጌታ (እግዚእ) ማለት ነው፡፡

የሥነ ፍጥረት ሁሉ መገኘት ወይም መኖር በእርሱ መኖር ነው፡፡ የመኖር ሁሉ መሠረቱና ምንጩ እርሱ ስለሆነ ሁሉም ከእርሱ ሀልዎት ይገኛል፡፡ ሀልዎቱ በሕገ ልቡና ማለት ፈጣሪ በፍጥረቱ ለፍጥረቱ የታወቀ ቢሆንም ለአበው ቅዱሳን ግን በተአምራዊ ሁኔታ በመገለጡ ህልውናው (መኖሩ) በተረጋገጠ መንገድ ታውቋል፡፡ (ስለ ሀልዎቱ የትምህርተ ሃይማኖት መቅድምንና በክፍል አንድ አንቀጽ አንድ በፊደል (ሀ) ያለውን ተመልከት)

ለሙሴ ሀልዎቱን የገለጸለት አምላክ፥ እሥራኤልን ከግብፅ የባርነት ቀንበር ነፃ ለማውጣት አስቦ ነው እንጂ እንዲያው ሀልዎቱን መኖሩን ለማሳወቅ ብቻ አልነበረም፡፡ ስለሆነም ወዲያውኑ ሙሴን ወደ ምድረ ግብፅ ልኮ እስራኤልን በጽኑ ክንዱ በኃይሉና በተአምራቱ አድኗቸዋል፡፡ እንግዲህ ስለዚህ ነው የመጀመሪያው ትእዛዝ ሀልዎቱንና አድኅኖቱን በአንድነት ብማገናዘብ ያዳናቸውን ወገኖች የእግዚአብሔርን መኖር ብቻ አውቀውና አምነው ለእርሱ ብቻ እንዲገዙና እርሱን ብቻ እንዲያመልኩ የሚደነግገው፡፡ ይህም ማለት የመጀመሪያው አንቀጽ፦ " ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ" ሲል እግዚአብሔር መኖሩን አምላክነቱን የገለጸው፥ እርሱነቱን ያስታወቀው ከማዳን ሥራው ጋር እሥራኤልን ነፃ ከማድረግ ጋር እንደሆነ ያስገነዝበናል ማለት ነው፡፡

"ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ" የሚለው ቃል ለእሥራኤል ሕዝብ ብቻ የተነገረ መስሎን ራሳችንን ማግለል አይገባንም፡፡ ይህ ቃል እሥራኤል ዘነፍስ ለተባለች ለቤተ ክርስቲያን በምሳሌነት ይነገራል፡፡ የጥንት እሥራኤላውያንን ከግዞትና ከባርነት ነፃ ያወጣና ያዳነ አምላክ በዘመኑ ፍጻሜ ደግሞ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በስሙ የታመኑትን ሁሉ በነፍስም በሥጋም ታድጓቸዋል፡፡ እኛን ክርስቲያኖችን ከዲያብሎስ ግዛት ከኃጢአት ባርነት ነፃ በማድረግ አድኖናል፤ ከሞት ወደ ሕይወት አሻግሮናል፤ ከሲኦል ወደ ገነት አግብቶናል፡፡ ስለዚህ ቸርነቱንና የማዳን ሥራውን እያሰብን በፍቅርና በምስጋና ልናመልከውና ልንሰግድለት ይገባናል፡፡ እዚህ ላይ እግዚአብሔር ሕጉና ትእዛዙን ከመስጠቱ በፊት አስቀድሞ የቸርነቱንና የማዳን ሥራውን እንደፈጸመልን እናስተውል፤ እሥራኤልን ከግብፅ ባርነት ነፃ ካወጣ በኋላ ነው ሕጉና ቃል ኪዳኑን የሰጣቸው (ዘጸ.19-20)፡፡



እንግዲህ የሕግ የመጀመሪያው ቃል ሀልዎተ እግዚአብሔርን፥ ቀጥሎ የቸርነቱን ሥራና ፍቅሩን አውቆና አምኖ መኖርና ለእርሱ ብቻ መገዛት ነው፡፡ እግዚአብሔርን ልናስደስት የምንችለው መንፈሳዊ አመለካከታችንና አስተያየታችን በጽኑው ሕገ ሃይማኖት ላይ ተመሥርቶ በእርሱ እምነትና ተስፋ በምንኖርበት ጊዜ ነው፡፡ ማመናችንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳስተማረን መጀመሪያ በሀልዎቱ ከዚያም እርሱን ለሚፈልጉት ሁሉ ዋጋ በሚሰጥበት በተስፋው ይሆናል፡፡ ይህንንም ሐዋርያው ሲገልጽ " ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም" ካለ በኋላ በሚከተለው ሐረግ፦ "ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ" ማለቱ ሀልዎቱን (መኖሩን) ለማመልከት ነው፡፡ ቀጥሎም "ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና" ያለው ደግሞ ተስፋውን ያሳያል (ዕብ.11፥6)፡፡

ይልቁንም እኛ ክርስቲያኖች ከጥንቶቹ እሥራኤላውያን በበለጠ የእግዚአብሔርን ሀልዎት ከማመን ጋር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገልንን ቸርነትና ምሕረት ማመንና በፍቅሩም መኖር ይገባናል፡፡ ውለታውን እያሰብን ለእርሱ በፍቅርና በትኅትና መገዛት ያስፈልገናል፡፡ ከብሉይ መገለጥ የሐዲሱ መገለጥ የበለጠ እንዲሆን የሚያደርገው ራሱ አምላክ ወልደ አምላክ ሰው ሆኖ እኛን ለማዳን በሥጋ በመምጣቱ ነው፡፡ ይህም የሥጋዌ ምሥጢር መገለጥ የእግዚአብሔርን ሀልዎት ከማጠናከሩ በላይ አድኅኖቱን አጉልቶ ያሳየናል፡፡ በልጁም አማካይነት ከመርገምና ከዘላለም ሞት አድኖ በጸጋው ከወደቅንበት አንሥቶ ከፍ ከፍ አድርጐናል፡፡ በተሰጠንም ተስፋ እየተደሰትን ከእርሱ ጋር በመንፈስ ቅዱስ ሱታፌ በእምነትና በፍቅር፥ በትኅትናና በትዕግሥት እንድንኖር በጸጋው አብቅቶናል፡፡

## ለወደደንና በጎ ላደረገልን እግዚአብሔር ምን እንከፍለዋለን?

እንግዲህ የሁላችንንም ነፍስና ሥጋ የፈጠረ እውነተኛው አምላክ፦ እስራኤል ዘሥጋን ከግብፅ የባርነት ቀንበር፥ እሥራኤል ዘነፍስን ከሲኦል ከዲያብሎስ ቁራኝነት ያዳነኩ "እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ" ይለናል፡፡ ጥንትም ዛሬም ሁልጊዜም እንዲህ የሚለን እንዲህም የሚናገረን እርሱ ማን ነው? እርሱስ ለአደረገልን በጎ ነገር ሁሉ ለውለታውስ የምንሰጠው ምላሽ አጸፋው ምንድን ነው? በመጀመሪያ እርሱ ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ ለመመለስ ከላይ እንደ ተማርነው፦ "ያለና የሚኖር" አንድ አምላክ ጥንትም ዛሬም ለወደፊትም ሰዎችን ሁሉ የሚያድን እርሱ ብቻ ነው እንላለን፡፡ በሐዲስ ኪዳንም "አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ" (ኤፌ.4፥6) የተባለው ያው አንድ እግዚአብሔርን የሚገልጽ ቃል ነው፡፡ እንግዲህ "ያለና የሚኖር" "አንድ አምላክ የሁሉም አባት" ዓለምን ያዳነና የሚያድን እርሱ ብቻ እንደሆነ እናምናለን፡፡ እርሱም የሰማይ አባታችን ነው፡፡

"አባታችን" ብለን የምንጠራው አንድ አምላክ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን በአንድነት ነው፡፡ ምንም ለአጠይቆ አካላት ሦስት ብንል በአምላክነት በህልውና፥ በባሕርይ፥ በመፍጠር፥ በማዳን፥ በሥልጣን፥ በአገዛዝ፥ በመግቦት . . . አንድ ናቸው (ክፍል አንድ ምሥጢረ ሥላሴን ተመልከት)፡፡ ከእግዚአብሔር ሀልዎት ጋር አባትነቱና አዳኝነቱ በይበልጥ የታወቀው ዓለምን ሊያድን በመጣው በክርስቶስ ሰው መሆን ነው፡፡ ስለዚህ ከብሉይ በበለጠ በሐዲስ ኪዳን የእግዚአብሔርና የሰዎች ግንኙነት ምን ያህል እንደ ተቀራረበና እንደ ተዛመደ "አባታችን" የሚለው ቃል ያስረዳናል፤ እግዚአብሔር እንደ አ[illegible] ለመሆን በቅተናል፡፡ ይህም የሆነው በእግዚአብሔር
[illegible] ልጅ በክርስቶስ በተገኘ ጸጋና በረከት ነው፤ በክርስቶስ ስም ላመ[illegible]

www.ethiopianorthodox.org

ኑት ሁሉ የኃጢአት ሥርየትና የጸጋ ልጅነት በመስጠቱ ነው (ዮሐ.1፥12)።

በዘመነ ሐዲስ "ያለና የሚኖር" እግዚአብሔር አምላክ፥ በቸርነቱ በፍቅሩ እኛን አድኖን በጸጋ ልጆቹ እንድንሆን እርሱም አባት እንዲሆነን ካም ፈቃዱ ሆኖልናል። ከእንግዲህ ወዲህ በፍቅር ሆነን የባሕርይ ልጁ እ ዳስተማረን "አባታችን ሆይ!" እያልን እንጠራዋለን። ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ሁሉ አባ አባት ሆይ! እያሉ ያንኑ አንዱን አምላክ በልጁ ስ ስላደረገላቸው ቸርነት ሁሉ ዘወትር ያመሰግኑታል። ይልቁንም "አባታች ሆይ" በሚለው የዘወትር ጸሎት "ስምህ ይቀደስ" እያልን ስሙን እናወድሳለ እናከብራለን። እንግዲህ ለወደደንና በጎ ላደረገልን እግዚአብሔር የምንሰጠ ምላሽ ፍቅርና ምስጋና ነው እያልን ከላይ የተነሣውን ጥያቄ በዚሁ እንመልሳ ለን።

እግዚአብሔር እኛን ያዳነን እንዲሁ ስለ ወደደን ብቻ ነው እንጂ ሌላ እኛን የሚወድበት ምክንያት ኖሮት አይደለም (ዮሐ.3፥16)። እንግዲህ የፍቅር ምላሹ ወይም አጸፋው ፍቅር ነው። የፍቅርንም ምላሽ እንድንሰ ያስተማረን እርሱው ራሱ ነው። ሳይወደን ውደዱኝ አላለም፤ አስቀድሞ እርሱ ነው የወደደን። ስለዚህ የፍቅር ምላሽ ፍቅር ስለሆነ ታላቁንና የመጀመሪያውን የፍቅር ትእዛዝ ሰጠን። እርሱም በኦሪት የተጻፈ በወንጌል የጸና ለአንድ አም ላክ ለእግዚአብሔር ብቻ የሚቀርብ ፍቅር ነው።

"እሥራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአ ብሔር ነው፤ አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ" የሚለውን የፍቅር ትእዛዝ በመፈጸም ነው እያንዳንዱ አማኝ ለወደደውና ለአዳነው አምላክ ምላሽ መስጠት የሚገባው (ዘዳ.6፥4-5፤ ማር.12፥29-30)። የእግዚአብሔር ፍቅር በክርስቶስ የማዳን ሥራ ስለተገለጸ (1ኛ ዮሐ.4፥9-10) ክርስቲያኖች ይህን እያስታወሱ እግዚአ ብሔርን በክርስቶስ ስም የበለጠ እንዲያፈቅሩት ያደርጋቸዋል። እውነተኞች ክርስቲያኖችን ከእግዚአብሔርና ከልጁ ፍቅር የሚለያቸው ነገር አይኖርም። "ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ወይስ ጭንቀት፥ ወይስ ስደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥ ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን?" ያለው ቅዱስ ጳውሎስ፥ ምንም ነገር ቢሆን ከቶ "በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ" በማለት በልቡናው በሕይወቱ ሥር ሰዶ ያለውን ፍጹም ፍቅር ገልጾልናል (ሮሜ.8፥35-39)።

ፍቅረ እግዚአብሔር ፍቅረ ክርስቶስ ስንል ምን ማለታችን እንደሆ ነ በትክክል መረዳት ያስፈልገናል። በስመ ፍቅር ለእግዚአብሔርና ለሰው የምናሳየው ፍቅር አንድ አይደለም። ፍቅረ እግዚአብሔር ከፍቅረ ቢጽ (ከባልንጀራ ፍቅር) በዓይነትም በይዘትም በደረጃም ይለያያል። ሰው ባልን ጀራውን እንደ ራሱ እንዲወደው ታዟል። ስለዚህ እኔ ባልንጀራዬን መውደዴን የምገልጸው ለእኔ የሚያስፈልገኝ ለእርሱም ያስፈልገዋል በማለት ለእርሱ የሚያስፈልገውን ሁሉ በማድረግ ነው። እንደ እኔ ይርበዋል ይጠማዋል በማለት የተራበው ባልንጀራዬን በመመገብ እውነተኛ ፍቅሬን በተግባር እገልጽለታለሁ። ለእግዚአብሔር የምናሳየው ፍቅር ግን ከዚህ የላቀና የተለየ ነው። እግዚአብሔርን የምንወደው ፈጣሪያችንና ገዢያችን፥ አዳኛችንና ጠባቂያችን እንደሆነ በማመን ነው። ስለዚህ እግዚአብሔርን በፍጹም ልብ መውደድ ማለት የእርሱን አምላክነትና አዳኝነት አውቆ እርሱን ብቻ ማምለክና ለእሱ መገዛት፥ እርሱን ማክበርና መፍራት፥ ትእዛዙንና ፈቃዱን ሁሉ መፈጸም እስከ መጨረሻውም በታማኝነት ማገልገል ማለት ነው። እን ግዲህ እግዚአብሔርን መውደድ እነዚህን ሁሉ ያካትታል። ደረጃውም ከፍቅረ



ቢጽ እጅግ የበለጠ ነው። ባልንጀራችንን የምንወደው ከራሳችን ጋር አስተካ ክለን ነው። እግዚአብሔርን የምንወደው ግን ከራሳችንና ከባልንጀራችን በአ ጠቃላይ ከሁሉም በላይ ነው። እግዚአብሔርን ከሁሉም በላይ በፍጹም ፍቅር ከልብ እንድንወደው የሚያደርገን በልጁ በክርስቶስ በተግባር የተገለጠው የፍቅር ሥራው እንደሆነ መርሳትና መዘንጋት የለብንም። "እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቷልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል" (1ኛዮሐ.3፥16)። በሐዲስ ኪዳን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብ ልንወደው የምንችለውና የሚገባን በክርስቶስ ፍቅር በምንኖርበት ጊዜ ነው (ዮሐ.15፥9-11)። ስለዚህ ይህንን ታላቅና ጥልቅ ፍቅር ቸል ሳንል በልቡናችን ውስጥ ለዘላለም እንዲኖር ማድረግ ይገባናል። በመንፈስ ቅዱስ በልቡናችን የፈሰሰው ፍቅሩ የተስፋችን ማስረጃ መሆኑን አውቀን እንደ ቀላል ነገር በመቁጠር ሳንዘነጋ በክብር ጠብቀን እንያዘው (ሮሜ.5፥5)።

እንግዲህ ይህንን የእግዚአብሔር ፍቅር ሳንረሳ እንድንጠብቀው ምን ምልክት ወይም ምን መታሰቢያ እናድርግለት? የጥንት እሥራኤላውያን ለአን ድ አምላክ የሚገባውን የፍቅር ትእዛዝ ለመጠበቅ ብዙ ጥረት እንዲያደርጉ የሚከተለው መመሪያ ተሰጥቷቸዋል፦ "እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ። ለልጆችህም አስተምረው፥ በቤትህም ስትቀመጥ፥ በመን ገድም ስትሄድ፥ ስትተኛም፥ ስትነሣም ተጫወተው። በእጅህም ምልክት አድ ርገህ እሰረው፤ በዓይኖችህም መካከል እንደ ክታብ ይሁንልህ። በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው" (ዘዳ.6፥6-9)።

በጌታ ዘመን የነበሩ ፈሪሳውያን ይህንን ምልክት ለውዳሴ ከንቱ ስለተጠቀሙበት ተወቅሰዋል (ማቴ.23፥5፤ ዘጸ.13፥9፤ ዘኁ.15፥38-41)። ዛሬም እኛ የእግዚአብሔርንና የክርስቶስን ፍቅር ለማሰብና ለማስታወስ የምን ጠቀምባቸው ምክልቶች የራሳችንንና የሌሎችንም ክርስቲያናዊ ሕይወት የሚ ያንጹ እንጂ የሚያፈርሱ እንዳይሆኑ እንጠንቀቅ። ይህንንም ስንል ምልክት ማድረግ አይጠቅመንም ማለታችን አይደለም።

ይልቁንም በዛሬው የመሳሳትና የመታለል፥ የመዘንጋትና ስለ ኑሮ የማሰብና የመጨነቅ ነገር በበዛበት ዓለም የምንኖር ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ፍቅር ከልቡናችን እንዳይጠፋና ፈጽሞ እንዳንረሳው በልዩ ልዩ መንገድና ምልክት ማስታወሻ እንዲኖረን ያስፈልጋል። በቤታችን ግዳግዳ ላይ የቃለ እግዚአብሔር ጥቅሶችንና ሥዕሎችን በማድረግ ቅዱሳት መጻሕፍትም በማንበብና ከቤተሰብና ከጓደኞች ጋር መወያየት ይጠቅማል። በተለይም የእግዚአብሔርን ፍቅርና ውለታውን የምናስብበትና ለእርሱም ምስጋና የምና ቀርብበት በየዕለቱ የጸሎት ጊዜ እንዲኖረን ማድረግ አማራጭ የሌለው መንገድ ነው። "እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት፥ ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ፥ በእርሱ /በክርስቶስ/ እናቅርብለት"። ከዚህም ጋር "መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና" (ዕብ.13፥15-16)።

እንግዲህ ሰው የወደደውን ያመሰግናልና ለእግዚአብሔር የምስጋና መሥዋዕት ከማቅረብ ቸል አንበል። እንደሚገባን ደስ እያለን ካላመሰገንነው ፍቅሩ በልቡናችን የለም ማለት ነው። አመስግን ቢሉት አላመሰግንም ይልቅስ እኔን አመስግኑኝ በማለት ራሱን የምስጋና ባለቤት በማድረጉ ሰይጣን በትዕቢቱ ከቀደመው ክብሩ ተዋርዷል፤ ከጨለማ ጉድጓድ ወድቋል (መቅድመ ወንጌል ተመልከት)።

www.ethiopianorthodox.org

## "እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን" አለማክበርና አለማመስገን ለክፉ ነገር ይዳርጋል፡፡

የፈጠረንና የአዳነን አምላካችንና መድኃኒታችን እንደ ወደደን እኛም እየወደድነው እንዳንኖርና እንደሚገባንም እንዳናከብረውና እንዳናመሰግነው የሚያስረሳን ልዩ ልዩ መከራና ፈተና በግል ሥራችንና በማኅበራዊ ኑሯችን ውስጥ ያጋጥሙናል፡፡ በቤተሰብና በዘወትር የሥራ ጉዳዮች ላይ ቀኑን ሁሉ በመያዝና ለማኅበራዊ አገልግሎት በመውጣትና በመውረድ ጊዜያችን ያል ፋል፡፡ ይልቁንም በዘመናችን እያደገና እየተስፋፋ በመጣው በመገናኛ ብዙኀን የምንሰማውና የምናየው ነገር ሁሉ ከመቼውም ይበልጥ ልቡናችንና አእ ምሯችንን እየተቆጣጠረው ትርፍ ጊዜያችንንም እየተሻማው ይገኛል፡፡ በመሆ ኑም አንዳንድ ምእመናን እግዚአብሔርን በግላቸው በጸሎት የሚያስቡበት ሰዓ ት እያጡና እንደዚሁም ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱበት ጊዜ እየተጣበበባቸው በመሄድ ላይ ነው፡፡ ይህ ነገር ከቀጠለ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ላይ አደገኛ ውጤት ያስከትልባቸዋል፡፡ በየዕለቱና በተለይም በየሰንበቱ ለእግዚአብሔር የምንሰጠው ጊዜ ከሌለ ከእርሱ ጋር ያለን ግንኙነት እየነሰና እየደከመ ሄዶ ፈጽሞ ከመጥፋት ደረጃ ላይ ይደርሳል፡፡ ከዚያ በኋላ የመንፈሳዊ ዓላማችንና ክርስቲያናዊ ሕይወታችን ፈጽሞ ይረሳና የጽድቁን መንገድ ስተን ዓለሙ ሁሉ በሚሄድበት በሰፊው ጎዳና ጭልጥ ብለን በመሄድ ከሰይጣን አሽከላ ውስጥ በመውደቅ ነፍሳችን መውጫ አጥታ በወጥመድ ውስጥ ተይዛ እንደ ቀረች ወፍ እንሆናለን፡፡

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሰው አደገኛ ሁኔታ እንዳይከሰት "እግዚአ ብሔር አምላክህ እኔ ነኝ" ያለውን ፈጣሪና አዳኝ አምላክ መማፀን ይኖር ብናል፡፡ ወደፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ የተባለውን መመሪያ በመከ ተል ዘወትር ሳንታክት መጸለይ ይገባናል፡፡ ከቀኑ ጊዜያችን ቀንሰን በየዕለቱ እርሱን የምናስብበት ሰዓት እንዲኖረን ያስፈልጋል፡፡ በክፉዎች ጎዳና ርቀን ሳንሄድ በቶሎ በንስሐ ተመልሰን የተጉሳቆለውን ክርስቲያናዊ ሕይወታ ችንን እናድሰው፡፡ ስለ እግዚአብሔር ሀልዎትና አድኅኖት ያለንን እውቀትና እምነት የምንጠብቀው በጸሎትና ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ቃሉንም በመስማት ነውና ይህን ከማድረግ ቸል አንበል፡፡

ነገር ግን በልቡናችን ደንዳናነትና ጽናት የተነሣ ከስሕተትና ከጥፋት ጎዳና ሳንመለስ እንዲያው ስናመነታ ልዑል እግዚአብሔርንና በጐ ሥራውን እያወቅን የሚገባውን ክብርና ምስጋና ካላቀረብን በዚህ ምትክ ክፉ ነገር ይደርስብናል፡፡ አሕዛብ የማይታየውን አምላክ በሥነ ፍጥረቱ አማካይነት መኖ ሩን እያወቁ ለእርሱ የሚገባውን ክብር ባለማቅረባቸው ምክንያት በክፉ ነገር ላይ እንደ ወደቁ ተጽፏል፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሕገ ልቡና የሚመሩ አሕዛብ ስለ እግዚአብሔር ህልዎት እንደሚያውቁ ሲገልጽ፡- "የማይ ታየው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን እያወቁ" ይልና ቀጥሎ፡- "እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩትና ስላ ላመሰገኑት የሚያመካኙት አጡ፤ ነገር ግን በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተ ውለውም ልባቸው ጨለመ፡፡ ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ፣ የማይጠፋውን ም የእግዚአብሔርን ክብር በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር በአላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መስለው ለወጡ" በማለት ያስረዳናል (ሮሜ.1፥19-23)፡፡ እዚህ ላይ እናስተውል፡፡ አሕዛብ በሕገ ልቡና ፈጣሪ እግዚአብሔርን በትክክል እያወቁት ግን በቸልተኝ



ባለማቅረባቸው ማለት እንደ ሐዋርያው አባባል "እንደ እግዚአብሔርነቱ ስላላከበሩትና ስላላመሰገኑት" በአሳባቸው ከንቱነት በባእድ አምልኮ ላይ እንደ ወደቁ እናያለን፡፡ መቼ ይህ ብቻ፣ ከትክክለኛው አምልኮት ውጭ እንደሄዱ እንዲሁም ከእውነተኛው ሥነ ምግባር ውጭ በመውጣት በሥጋቸው ምኞት በመመራት ከርኩሰትና ከልዩ ልዩ ኃጢአት ውስጥ ወድቀዋል፡፡ "ይህም የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለለወጡ በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ ነው" (ሮሜ.1፥25)፡፡ ስለዚህ እነርሱ "እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው" (ሮሜ.1፥28)፡፡

አሕዛብ በሕገ ልቡና የሚያውቁትን እግዚአብሔርን ባለመውደዳቸውና ክብር ባለመስጠት ቸል በማለታቸው ምክንያት እንደዚህ ዓይነት ክፉ ነገር ከደረሰባቸው ይልቁንም ክርስቲያኖች በቸርነቱና በምሕረቱ በልጁ ሰው መሆን የተገለጠውን እግዚአብሔርን እንደሚገባን በመውደድ ካላከበርነውና ካላመሰገ ነው ምንኛ የበለጠ ክፉ ነገር ያጋጥመን ይሆን? እንግዲህ እግዚአብሔርን በዘ ነት የማዳኑንም ጸጋ እያወቁ በተውትና በናቁት ክርስቲያኖች ላይ የበለጠ የፍርድ ቅጣት እንደሚመጣባቸው እንወቅ፡፡ ምክንያቱም ብዙ ነገር ከተሰጠው ብዙ ነገር ይጠበቃልና ነው፡፡ ስለዚህም "ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት ተነሥቶ የሚጀመርበት ጊዜ ደርሷልና አስቀድሞም በእኛ የሚጀመር ከሆነ ለእግዚአ ብሔር ወንጌል የማይታዘዙ መጨረሻቸው ምን ይሆን? ጻድቅም በጭንቅ የሚድን ከሆነ ዓመፀኛውና ኃጢአተኛው ወዴት ይታይ ዘንድ አለው? ስለዚህ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መከራን የሚቀበሉ፣ መልካምን እያደረጉ ነፍሳቸውን ለታመነ ፈጣሪ አደራ ይስጡ" (1ኛ ጴጥ.4፥17-19)፡፡

እንግዲህ እስካሁን ስለ እግዚአብሔር ሀልዎት በምናጠናበት ጊዜ በተጨማሪ ከሀልዎቱ ጋር የማይለያየውን የአድኅኖቱን ነገርና የፍቅሩን ሁኔታ እንዲሁም ፍርዱ ከራሱ ቤት ጀምሮ በዓለም ሁሉ ላይ እንደሚሆን ከላይ በጥቂቱ ተመልክተናል፡፡ እነዚህ ሁሉ ማለት ፍቅሩ፣ ማዳኑ፣ ፍርዱና የመሳ ሰሉት ሁሉ የእግዚአብሔርን ማንነትና ባሕርዩን የሚገልጹልን ጠባይዓቱ ናቸው፡፡ እያንዳንዱ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ሀልዎቱን ብቻ ሳይሆን ማን ነቱን የሚገልጹትን ጠባይቱን ማወቅ እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው፡፡ ምክን ያቱም ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ምን መሆን እንዳለበትና በእንዴት ዓይነት አኳኋን መከናወን እንደሚገባው የሚወስኑት ጠባይዓቱ ናቸው፡፡ ስለዚህ ማንነቱ የሚታወቅባቸው የባሕርዩ መገለጫዎች ጠባይዓቱን ከቅዱሳት መጻሕፍት በማውጣጣት ዋና ዋናዎቹን ቀጥሎ በሚገኘው ርእሰ ትምህርት እናጠናቸዋለን፡፡

## 2. የእግዚአብሔር የባሕርዩ መገለጫዎች - ጠባይዓቱ

እግዚአብሔር በቸርነቱ ራሱን በገለጠ ጊዜ ሀልዎቱን ማለት መኖሩን ብቻ በማወቅ ሳይወሰነን ባሕርዩንም ደግሞ በመጠኑ እንድናውቅ ፈቅዶልናል፡፡ ስለዚህ የባሕርዩ መገለጫዎችን ማለት ጠባይዓቱን የተቻለንን ያህል አውቀን ማሳወቅ ግዴታችን ነው፡፡ የማይታየውን ባሕርዩን በባሕርዩ የሰወረውን የእግዚአብሔርን ማንነት፣ የባሕርዩን ምንነት በትክክል ለመረዳት በጥያቄና መልስ በቀላሉ የምንማረው ነገር አይደለም፡፡ ምክንያቱም የነገረ መለኮት ምሥጢር ከተፈጥሮ አእምሯችን በላይ ስለሆነ ረቂቁን ምሥጢር ለማስተዋልና ለመገንዘብ ስለሚያዳግተን ነው፡፡ እግዚአብሔር በታላቅ ቸርነቱ ሰውን ለማዳን ራሱን ለሰዎች ልጆች ስለገለጸ ስለ ባሕርዩ አንዳንድ ነገሮችን በመጠኑ ... ስለዚህ የአንድ እግዚአብሔር የባሕርዩ መገለጫዎች

www.ethiopianorthodox.org

ናቸው ተብለው ከታወቁት መካከል ዋና ዋናዎቹን እንመለከታለን፡፡ ከዚ... በፊት ግን የእግዚአብሔር ባሕርይ ምን እንደሆነ ለማወቅ ስለሚያስቸግር... ጥቂት ግንዛቤ ለማግኘት፣ እንዲረዳን ስለባሕርዩ ምንነት የባሕርዩን መገለጫዎችና ሁኔታዎች በንዕዕር መልክ በአጭሩ እንገልጻለን፡፡

## የእግዚአብሔር ባሕርይ ሲባል ምን ማለት ነው?

የዚህን ጥያቄ መልስ በሰው ጠባይ መስለን ለመመለስ እንሞክራለን፡፡ ለሰው፣ ጠባይ እንዳለው ሁሉ ለእግዚአብሔርም ባሕርይ አለው፡፡ እንግዲህ በ... ዕዕር ለማጥናት ስለ አንድ ሰው ደግነትና ለጋሥነት ወይም ጠንቃቃነትና ቁጠ... ነት ወይም ብርታትና ትዕግሥት ስንናገር የሰውየውን ጠባይ መግለጣችን ነው፡፡ እንደዚሁም ስለ እግዚአብሔር ኃያልነትና ዘላለማዊነት ስለ ፈታሒነቱና መሐሪነቱ ስናስረዳ ባሕርዩን ማለት ጠባይዓቱን ማመልከታችን ነው፡፡ ስለዚህ ... ባሕርይ ማለት ጠባይ ማለት ነው ብለን በቀላል የምናስበው ሳይሆን የእግዚአ... ብሔር ባሕርይ ረቂቅ፣ አኗኗሩም ምጡቅ ስለሆነ በሰው ባሕርይና ጠባይ... የሚለካ አይደለም፡፡ ከሰው ተፈጥሮና ጠባይ ጋር የሚነፃፀርና የማይነፃፀር አለ፡፡ ምንም ሰው በነፍሱ ሕያው ሆኖ ቢፈጠርም በሥጋው ይወለዳል፣ ያረጃል፣ ይሞታል፡፡ እግዚአብሔር ግን ከዘላለም እስከ ዘላለም የሚኖር ስለሆነ ጥንት... የለውም ፍጻሜም የለውም፤ አያረጅም፣ አይለወጥም፣ አይሞትም፤ ለዘላለም ሕያው ነው፡፡

እንግዲህ "ባሕርይ" ስንል የእግዚአብሔር ሀልዎትና መለኮታዊ ባሕርዩ የሚገለጽባቸው ሕያውነቱ፣ ዘላለማዊነቱ፣ ከሃሊነቱ፣ ቅድስናው፣ ጥበቡና እውቀቱ፣ ጥበቃውና መግቦቱ፣ ትክክለኛ ፍርዱ፣ ምሕረቱ፣ ፍቅሩ እና የመሳ... ሰሉትን ጠባይዓት የሚያመለክት ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ የታወቁት እግዚአብሔር ሕልውናውን ሲገልጥ ባሕርዩንም ማለት ጠባይዓቱን አብሮ ስለ ገለጠ በመጠ... ስለ ባሕርዩ (ጠባይዓቱ) ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተለይም ሕግን በመስጠቱ፣ ቃል ኪዳን በመግባቱ፣ ልጁን በመላኩ የእግዚአብሔር ባሕርይ የሆነውን ፍቅርና ምሕረቱን ትክክለኛ ፍርዱንም በግልጽ ለመረዳት በቅተናል፡፡ ስለዚህ ባሕርይ ስንል የአንድ አምላክ የሀልዎቱ፣ የመለኮቱና የባሕርዩ መገለጫዎችና መታወቂያዎች የሆኑትን ሁሉ የሚያጠቃልል እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡

የእግዚአብሔርን ባሕርይ ማወቅ ለክርስቲያን ሁሉ ይጠቅማል፡፡ ባሕር... ዩን ካወቅን ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ እንችላለን፡፡ ለማክበርና ለመፍራት፣ ለመውደድና ተስፋ ለማድረግ፣ እርሱንም በመንፈስና በእውነት ለማምለክ የበቃን እንሆናለን፡፡ እንደ ባሕርዩም በጸሎት ልናነጋግረውና እንደ ባሕርዩም ፈቃዱን መፈጸም ይኖርብናል፡፡ ለምሳሌ አንድ ልጅ አባቱን የሚያስደስተው በመጀመሪያ ጠባዩን በትክክል አውቆ በጠባዩ መሠረት የሚገባውን ሲያደር... ግለት ነው፡፡ አለበለዚያ የአባቱን ጠባይ የሚጻረር ነገር የሚፈጽም ልጅ ወደ አባቱ ቀርቦ ለመነጋገርና የሚፈልገውንም ለማግኘት በጣም ያዳግተዋል፡፡ ስለዚህ እኛም የእግዚአብሔርን ባሕርይና ፈቃድ አውቀን ብንጸልይ እግዚአ... ብሔርንም አስደስተን እራሳችንንም እንጠቅማለን፡፡

## ስለ ባሕርዩ አለመረዳት ስሕተትን ያስከትላል

የእግዚአብሔርን ባሕርይ በቅዱሳት መጻሕፍት በተጻፈው መሠረት ለመረዳት አለመሞከር በሃይማኖት ላይ ስሕተትን፣ በሕይወት ላይ ጉዳትን ያስከትላል፡፡ አንዳንድ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ... መሐሪነቱን ብቻ ይዘው ሌሎችን የባሕርይ መገ...

www.ethiopianorthodox.org



ዳንዶች፦ "ኃጢአት ብንሠራ ምን አለበት እርሱ መሐሪ ነው ይምረናል" በማለት ኃጢአትን ሳይፈሩ ለመሥራት ይደፋፈሩ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ይህ ታላቅ ስሕተት ነው፡፡ ምክንያቱም ፍትሕና ርትዕ፣ ቅድስናና ጽድቅ የእግዚአ ብሔር የባሕርዩ ስለሆኑ በምንም መንገድ በሰማይም ሆነ በምድር ኃጢአ ተኛውና ዓመፀኛው ሳይፈረድበት የማይቀር በመሆኑ ነው፡፡ እግዚአብሔር ንስሐ በማይገቡ ዓመፀኞችና በደለኞች ላይ ቊጣው እንደ እሳት እንደምትነድና እነር ሱንም በዘላለም ሥቃይ የሚቀጣቸው ትክክለኛ ፈራጅ እንደሆነ የማያምን ቢኖር ስለ እግዚአብሔር ማንነትና ባሕርይ ገና አልተረዳም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን እየተከታተለ የሚያጠቃና የሚደመስስ መለኮታዊ ኃይል ብቻ አድርገንም መገመት አይገባን ም፡፡ እግዚአብሔር የሰውን መመለሱን ማለት ልማቱን እንጂ ጥፋቱን አይ ወድም (ሕዝ.18፥23፤ 25-32)፡፡ ስለዚህ ሰው ከጥፋቱ የሚመለስበትን መን ገድ አዘጋጅቶለታል፡፡ ከጥፋቱና ከኃጢአቱ የሚድንበትን ሁኔታ ማዘጋጀቱ ፍቅርና ምሕረትም የባሕርዩ መሆኑን ያሳስቡናል፡፡ እንግዲህ እግዚአብሔር በቸርነቱ ለኃጢአተኞች ያዘጋጀውን የመዳን ጐዳና በመከተል ከእግዚአብሔር ምሕረትን እናገኛለን፤ በኃጢአተኞችም ላይ ከሚመጣው ቊጣና ፍርድ እን ድናለን፡፡

እግዚአብሔር፣ እሥራኤልን ከግብፅ ሀገር፣ ከባርነት ቤት አውጥቶ በሲና ተራራ በእሳት መካከል ራሱን የገለጸላቸው ሕጉንና ትእዛዙን በመስጠት ነበር (ዘጸ.19-20)፡፡ ይህንን በማድረጉ እግዚአብሔር የሕግና የፍትሕ አምላክ መሆ ኑን ያስገነዝበናል፡፡ በሲና ተራራ ላይ በሚያስደነግጥ ሁኔታ ሲገለጽ ሰዎች እግዚአብሔርን ፈርተው ትእዛዛቱን እንዲፈጽሙ ከኃጢአትም እንዲርቁ ለማድረግ ነው (ዘጸ.20፥18-20)፡፡ በእውነትም እግዚአብሔር የሚያስፈራና የሚያስገርም ስለሆነ መለኮታዊ ባሕርዩን መረዳት፣ ገናናነቱንና ኃያልነቱን ማመን፣ እንዲሁም በሕግና በፍርድ የሚቀጣና የሚያድን፣ ለሁሉም እንደ የሥራው ዋጋውን የሚከፍል መሆኑን ማወቅ የሃይማኖታችን ተቀዳሚ ተግባር መሆን አለበት፡፡ ስለዚህም የትምህርታችንና የጥበባችንም መጀመሪያ እግዚአ ብሔርን በመፍራትና ለእርሱም በመገዛት ላይ ይመሠረታል (መዝ.110፥10)፡፡ እንግዲህ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ማወቅ ብቻ ሳይሆን በኃጢአታችን ምክን ያት ከሚመጣው መዓትና ከዘላለም ኲነኔ እንድናመልጥና ምሕረቱንም እን ድናገኝ በተዘጋጀልን በንስሐና በደኅንነት ጐዳና መሄድ ይኖርብናል፡፡

የእግዚአብሔር ሕጉና ፍርዱ በኦሪት እንደ ታወቀ እንደዚሁም ፍቅርና ምሕረቱ በወንጌል የምሥራች ቃል በግልጽ በክርስቶስ እንዲታወቅ ሆኗል፡፡ ስለ እግዚአብሔር ፍርድና ምሕረት ስንናገር በአንድ ሣንቲም ላይ እንደሚታዩ ሁለት ገጽታዎች ሊመሰሉ ይችላሉ፡፡ ይህም ማለት ፍርዱና ምሕረቱ የማይለያዩ ናቸው ለማለት ነው፡፡ በአንድ በኩል እግዚአብሔር በትክክለኛ ፈራጅነቱ ኃጢአተኛውን ይቀጣዋል እንጂ አይምረውም (2ኛ. ጴጥ.2፥4-10)፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ስለሰዎች መዳን ባዘጋጀው መንገድ ለኃጢአተኞች ምሕረትን ይሰጣል፡፡ እነዚህ ሁለቱ የባሕርይ መገለጫዎች ማለት ፍርዱና ምሕረቱ በነገረ መስቀል ተገልጸው ይታያሉ፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ዓለምን ያዳነው፣ ምሕረቱንም ያወረደው ስለ ኃጢአተኞች በደል ካሣ ለመክፈልና በእነርሱም ምትክ የሞትን ፍርድ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለተቀበለ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ፍርድና ምሕረት በክርስቶስ መስቀል እን ደተፈጸመ እናስተውል፡፡ ሰውም የዳነው በእግዚአብሔር ትክክለኛ ፍርድ እን ... ...ዚህ ነው ቅዱስ ቄርሎስ "ወአድኅነነ በፍትሕ ጽድቅ ... ምሕረቱ" ብሎ የለመነ፡፡

እንግዲህ ስለ እግዚአብሔር ማንነትና ስለ መለኮታዊ ባሕርዩ ስናስ ከኀናናነቱና ከኀያልነቱ እንዲሁም ከቅድስናው ክብር የተነሣ ከዙፋኑ ፊት የሚ ነደው እሳት ኃጢአትንና ክፋትን ሁሉ የሚያቃጥል መሆኑን በመገንዘብ ነው ይህም ለፍጥረት ሁሉ በተለይም ለኃጢአተኞች ምን ያህል እንደሚያስፈራ እንደ ሚያስደነግጥ ግልጥ ነው:: የሰማይ ሠራዊትም በዙፋኑ ላይ ላለው በፍርሀት እንደሚሰግዱለትና እንደሚያመሰግኑት በማሰብ ስለ ባሕርዩና ክብ ገናናነት በመጀመሪያ ደረጃ ማወቅ ይኖርብናል (ኢሳ.6፡1-7፤ ራእይ 4)። "የዙፋንህ መሠረት ጽድቅና ፍርድ ነው፤ ምሕረትና እውነት በፊት ይሄዳሉ" (መዝ.88፡14) የተባለውን ሳንዘነጋ ሌሎችንም የባሕርዩ መገለ ጫዎችን በአንድነት ማወቅና ማመን አለብን እንጂ አንዱን ይዘን ሌላው መተው መሠረተ ሃይማኖትን እንደ ማፋለስ ስለሚቆጠር ሁሉንም በተንቃቄ ማጥናትና መያዝ ለክርስቲያናዊ ሕይወታችን ይጠቅመናል::

## የአምላክ ባሕርይ መገለጫዎች ጠባይዓት [81]

ከእግዚአብሔር ጠባይዓት መካከል አንዳንዶቹ በተወሰነ መንገድ በእ ተሰጥተው በሥነ ፍጥረት የሚገኙና የሚታዩ ቢሆኑም በእግዚአብሔር ዘንድ ግን በምልዓትና ያለ ወሰን ያለምንም ጉድለት በፍጹምነት ይገኛሉ:: በፍ ፈጥሮ የሚታዩት ጠባይዓት ግን በአንፃራዊነትና በውሱንነት ሁኔታ ነው ከነዚህም ጠባይዓት መካከል - ኃይል፡ ጥበብ፡ ዕውቀት፡ ፍቅር፡ ይቅር ማድረግ፡ መስጠት . . . ወዘተ. የተባሉትን ይመለከታል::

እግዚአብሔር ጥበበኛ ነው፤ ብዙ ሰዎችም ጥበበኞች ናቸው:: የእግዚአ ብሔር ጥበብ ገደብ፡ ወሰን የለውም፡ ፍጹም ነው:: የሰዎች ጥበብ ግን እግዚአ ብሔር በሰጣቸው እውቀትና ማስተዋል መሠረት የተወሰነና የተመጠነ ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ጠባይዓት ለእግዚአብሔር ብቻ ገንዘቡ ስለሆነ ከፍጥረት ወገን ማንም ምንም አይጋራውም:: እነዚህም የእግዚአብሔር ፍጹማን የሆኑ ጠባይዓቱ ለእርሱ ብቻ የሚነገሩ ናቸው::

ስለ እግዚአብሔር ጠባይዓት ከላይ የተገለጸውና ከታችም በግርጌ ማስታ ወሻ የቀረበው በግብፅ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚሰጥ ትምህርት ነው::[82]

ከዚህ ቀጥሎ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለእግዚአብሔር ብቻ የሚነገሩትን ጠባይዓቱንና ሌሎችንም ጠባይዓቱን ሳንከፋፍልና ደረጃ ሳናወጣ ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ብዙ ጊዜ ከሚያጋጥሙን መካከል ጥቂቶቹን መርጠን በአ ሥር ተራ ቁጥሮች መድበን በአጭር በአጭሩ እንደሚከተለው አቅርበናል::

---

[81] Attributes - የሚባለው የእንግሊዝኛ ቃል "ጠባይዓት" በሚል ተተርጉሟል::

[82] ለእግዚአብሔር ብቻ ከሚነገሩት ጠባይዓቱ መካከል God's Exclusive Attributes በሚለው ርእስ ሥር ጥቂቶቹ ተጠቅሰዋል፡- God is Eternal - እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው . . . God is the Creator - እግዚአ ብሔር ፈጣሪ ነው፤ God is Almighty - እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ (ከሃሌ ኩሉ) ነው፤ God is Omni Present - እግዚአብሔር በሁሉ ቦታ ይገኛል (ምሉእ በኩለሄ)፤ God Knows Everything - እግዚአብሔር ሁሉን ያውቃል፤ God is boundless - እግዚአብሔር ውሱንነት የለበትም፤ God is unchangeable - እግዚአ ብሔር አይለወጥም:: H.H. Pope Shenouda III, God And Man (Cairo, Dar El Tebaa El Kawmia, Dec. 2000) pp.10-15.

በተጨማሪ - ዓሥራት ገብረ ማርያም፥ ትምህርተ መለኮት (አዲስ አበባ፥ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ ሁለተኛ እትም፣ 1991) ከገጽ 12-38 "የእግዚአብሔርን ህላዌ የሚያመለክቱ ጠባዮች" እና "ከፍጥረቱ ጋር ባለው ግንኙነት የእግዚአብሔር ጠባዮች" ተብለው በአጠቃላይ በሁለት ክፍል ተመድበው በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎችና እንዲሁም በቅዱሳን አባቶች ምስክርነት ተብራርተው የቀረቡት ትምህርቶች ስለ እግዚአብሔር ማንነትና ጠባይዓት በስፋትና በጥልቀት ስለሚያስተምሩን በማስተዋል እናንብባቸው::



1. **እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣** በሁሉም ጊዜና በሁሉም ቦታ ይገኛል:: እንደ ሰው በግዙፍ አካል በአንድ ቦታ የተወሰነ አይደለም:: እግዚአ ብሔር መንፈስ ነው ሲባል የሚታይ የሚዳሰስ ግዙፍ አካል የለውም ለማለት ነው:: እግዚአብሔር መንፈሳዊና መለኮታዊ የሆነ ረቂቅ ባሕርይ እንዳለው ለማመልከት ነው:: ይህንን መንፈሳዊ ህላዌ በትክክል ለመግለጥ ባይቻልም እኛ ከምናውቀው ከሥጋዊ ሰውነትና ከቁስ አካል የተለየ መሆኑን እንገነዘባለን:: የእግዚአብሔርን መንፈስነት ልንገነዘብ የምንችለው በሥጋዊ የስሜት እውቀታችን ሳይሆን በረቂቁ የማስተዋል መንገድ ነው:: ሰውም በአርአያ ሥላሴ ስለ ተፈጠረ ነፍሳዊና መንፈሳዊ ተፈጥሮ በባሕርዩ ስላለ በዚህም አኳያ የመንፈስን ባሕርይ ለማስተዋል ይቻላል:: እንግዲህ እግዚአብሔር መንፈስ መሆኑን አውቀን እኛም እር ሱን ለመቀበል በመንፈሳችን መዘጋጀት አለብን:: ወደ እርሱም በመን ፈስና በእውነት ቀርበን እንድንጸልይና እንድናመልከው እንድንሰግድለትም ይገባናል:: ጌታችን እንደዚህ አስተምሮናልና:: "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈል ጋቸ ዋል" (ዮሐ.4፡24):: ጌታም መንፈስ ነው ወደ እርሱም እንጸልያለን፤ መንፈስ ባለበት በዚያ ነፃነት አለ (2ኛቆር.3፡17)::

2. **እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው::** መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው በዘመናት ሁሉ የሚኖር፣ የማያረጅ፣ የማይሞት፣ የማይለወጥ ሁሉን አሳ ልፎ የሚኖር ማለት ነው:: ጊዜ የማይወስነው፣ ጊዜን የሚወስን፣ ጊዜንም የፈጠረ መሆኑን መግለጽ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነት መናገር ነው:: እግዚአብሔር ለሙሴ የዘላለም ስሙን ሲገልጽለት "ያለና የሚኖር እኔ ነኝ" በማለቱ ዘላለማዊነቱን ያስረዳናል (ዘፀ.3፡14):: እንደዚሁም በዮሐን ስ ራእይ ተጽፏል:: "ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ፡ አልፋና ኦሜጋ እኔ ነኝ ይላል" (ራእይ 1፡8):: ስለ እግዚአብሔር ዘላለማዊነት በመዝሙረ ዳዊት ይገኛል:: "አቤቱ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፣ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው:: እነርሱ ይጠፋሉ፣ አንተ ግን ትኖራለህ፤ ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ፣ እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፣ ይለወጡማል፤ አንተ ግን ያው አንተ ነህ፣ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም" (መዝ.101፡25-27):: ይህንና ይህንን የመሳሰሉትን የእግዚአብሔርን ዘላለማዊነት እያሰብን "ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ የነበረውና የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ ያለው አምላክ እያሉ ቀንና ሌሊት" ሳያርፉ ከሚያመሰግኑት ጋር አብረን የዘላለም ስሙን ለማመስገን እንድንበቃ እግዚአብሔርን መለመን ይኖርብናል (ራእይ 4፡8)::

3. **ሁሉን የያዘ እግዚአብሔር ሁሉን ለማድረግ የሚችል ኃያል (ኤል ሻዳይ) ነው** (ዘፍ.17፡1):: ይህን ማድረግ ያውከዋል፡ ያንን መሥራት አይችልም የሚባለው ለፍጡር ብቻ እንጂ ለፈጣሪ ከቶ የሚሳ ነው ነገር የለም:: ዘይክል ኩሎ ወአልቦ ዘይሰአኖ የተባለው አምላክ ፈጣሬ ፍጥረታት ዓለምን ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ እርሱ ለመለኮታዊ ኃይሉ ፈጽሞ ወሰንና ገደብ የለውም:: በዚህ ዓለም የሚኖሩትን ፍጥረታት ሰዎችንም እንስሳትንም ዕፅዋትንም፡ ሁሉን በሚችል ኃይሉ እንደ ባሕርያቸው ሕይወት የሰጣቸው ስለሆነ ሁሉንም በልዩ ልዩ መንገድ ይመግባቸዋል፡ ይጠብቃቸዋል፡ ይረዳቸዋል:: በመጽሐፍ ቅዱስ ከሃሊነቱን ማለት ሁሉን ቻይነቱን የሚያስረዱ ብዙ ታሪኮች አሉ:: ሠለስቱ ደቂቅን ከእሳት ውስጥ ያወጣ፣ እሥራኤልን

www.ethiopianorthodox.org

ባሕር ከፍሎ ያሻገረ፣ መና ከሰማይ አውርዶ ሕዝቡን የመገበ እግዚአብሔር ሁሉን ማድረግ ይቻለዋል። መኸን ለነበረችውና በዕድሜ ብዛት ላረጀችው ለሣራ ልጅ የሰጠ እግዚአብሔር አይደለምን? "በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?" (ዘፍ.18፥14፤ ዘፀ. 14፥21-31፤ ዳን.3፥25)። እንግዲህ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር በሰማይም በምድርም እንደሌለ የታመነ ነው። ዛሬም ፈቃዱን ለሚፈጽሙ ወገኖቹ፣ ሁሉን የሚችል አምላክ እጁን ይዘረጋላቸዋል። ከታላቅ ፈተናና ችግርም በተአምራቱ ያድናቸዋል። በሰዎች ዘንድ አይቻልም፣ ከተፈጥሮ ሕግ በላይ ነው የተባለውን ነገር እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ እንዲፈጽሙ ሁሉን ለማድረግ በሚችል ኃይሉ ረድቷቸዋል። ለዚህም የነቢያት የሐዋርያት ሥራና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሁሉ ምስክሮች ናቸው። መንግሥተ ሰማያት ለመግባት ጭንቅ የመሰላቸው ደቀ መዛሙርት ጌታን ጠየቁት፦ "እንግዲህ ማን ሊድን ይችላል? አሉ። እርሱ ግን በሰው ዘንድ የማይቻል በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል አለ" (ሉቃ.18፥26-27)። ከሃሊ ኩሉ የሆነ አምላክ እኛን ለማዳን ታላላቅ ድንቅ ሥራዎችንና ተአምራትን አድርጎልናል። እንግዲህ ይህን ሁሉ እያሰብን ኃያሉን አምላክ ማክበርና ማመስገን ይኖርብናል።

4. <u>እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂና ፍጹም ጥበበኛ ነው።</u> ዓለምንና በውስጧ የሚገኙትን ሁሉ በጥበቡ ፈጠረ። ሁሉንም የፈጠረ ስለሆነ የሁሉንም ህላዌና አሠራር ያውቃል። ከእርሱ የእውቀት ዓይኖች የሚሰወር ነገር የለም። የማይታየውን ነገር ሁሉ በጥልቀት ያስተውላል። ፍጥረታት ከዳር እስከ ዳር ይታዩታል። የተሸፈነ ነገር ለእርሱ አይሰወርም። እኛ በእርሱ ዘንድ ራቁታችንን እንታያለን። ጨለማ ወይም ግርግዳ የእርሱን እይታ አይገታውም። እግዚአብሔር የተጋረደውን ነገር ብቻ ማየት ሳይሆን በነፍሳችን በልቡናችን የሚመላለሰው አሳብ ምን እንደሆነ ያውቃል። ምኞታችንና አስተያየታችንን ሳንገልጸው በፊት እርሱ ያውቀዋል። የልባችንን ዝንባሌና ወደፊት የምናስበውንም ጭምር ያውቃል። ያለፈውና የሚመጣው ሁሉ አሁን ከሚደረገው ጋር በአንድነት ይታየዋል። "አቤቱ፥ መረመርኸኝ፣ አወቅኸኝም። አንተ መቀመጤንና መነሣቴን አወቅህ፤ አሳቤን ሁሉ ከሩቅ አስተዋልህ። . . . መንገዶቼን ሁሉ ቀድመህ አወቅህ" . . . አቤቱ፣ አንተ እነሆ የቀድሞውንና የኋላውን አወቅህ" (መዝ.138፥1-5)። ይህን ሁሉ ስለሚያውቅ ፍርዱ ትክክለኛ ነው፤ አይመረመርም። መንገዱም ረቂቅ ስለሆነ ማንም አያውቀውም።

ሐዋርያው ጳውሎስ "የእግዚአብሔር ባለጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው፤ ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው፥ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም። የጌታን ልብ ያወቀው ማን ነው? ወይስ አማካሪው ማን ነበር?" በማለት ስለ እግዚአብሔር ጥበብ በማድነቅ ያስገነዝበናል (ሮሜ.11፥33-34)። ዳዊት በመዝሙሩ እግዚአብሔር አያይም የሚሉትን ሰነፎች ከተግሣጽ ጋር እንዲህ ይላቸዋል። "እግዚአብሔር አያይም፣ የያዕቆብም አምላክ አያስተውልም አሉ። የሕዝብ ደንቆሮች ሆይ፥ አስተውሉ፤ ሰነፎችማ መቼ ይጠበባሉ? ጆሮን የተከለው አይሰማምን? ዓይንን የሠራው አያይምን?" (መዝ.93፥7-9)። ሐዋርያው ጳውሎስም የእግዚአብሔር ዓይኖች እንደሚያዩን ያስተምረናል። "እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖች ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ፥ በእርሱ ፊት የተሰወረ



እንግዲህ በልባችን የተሰወረ ነገር ቢኖር የእግዚአብሔር የማወቅና ሁሉን የማየት ባሕርዩን ተገንዝበን ልባችንን ግልጽና ንጹሕ አድርገን ወደ እርሱ ብንቀርብ እንጂ እግዚአብሔር አያይም ብለን ተሸፋፍነን የልባችንን ሰውረን፥ በግብዝነት ብንቀርብ ጸሎታችን ተሰሚነት አያገኝም። እንዲያውም እግዚአብሔርን መፈታተን ይሆንብናል። ይህም አድራጎት በበደል ላይ በደልን መጨመር ነው። ስለዚህ ልባችንን ገልጸን፥ ምሥጢራችንን አውጥተን ሁሉን ለሚያይ አምላክ ብንናዘዝ እንደ ባሕርዩ ሁኔታ ወደ እርሱ የቀረብን ስለሆነ ጸሎታችንን ሰምቶ ይቅር ይለናል።

5. <u>እግዚአብሔር በፍጥረት ሁሉ ሙሉ በመሆን በሁሉም ቦታ ይገኛል።</u> ምሉዕ በኩለሄ፥ ማለት በኃለሙ ሙሉ በአንድ ጊዜ ለመገኘት የሚችል የእግዚአብሔር ባሕርይ ብቻ መሆኑን እንመለከታለን። እግዚአብሔር መንፈስ ነው። ስለዚህ በሁሉ ቦታ ይገኛል። "ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ?" ይላል ዳዊት በመዝሙሩ "ወደ ሰማይ ብወጣ፥ አንተ በዚያ ነህ፤ ወደ ሲኦልም ብወርድ፥ በዚያ አለህ። እንደ ንሥር የንጋትን ክንፍ ብወስድ፥ እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር፥ በዚያ እጅህ ትመራኛለች፥ ቀኝህም ትይዘኛለች" (መዝ.138፥7-10)። ነቢዩ ኤርምያስም ስለዚሁ የእግዚአብሔር ባሕርይ ያስተምረናል። "እኔ የቅርብ አምላክ ነኝ እንጂ የሩቅ አምላክ አይደለሁም። ሰው በስውር ቢሸሸግ፥ እኔ አላየውምን? ሰማይን ምድርንስ የሞላሁ እኔ አይደለሁምን? ይላል እግዚአብሔር" (ኤር.23፥23-24)። እንግዲህ ይህንን የመለኮት ባሕርይ ባለማወቅ ወደአልታወቀ ሀገር በመሄድ መደበቅና መሰወር አይቻልም። ነቢዩ ዮናስም ሊያመልጥ እንደተሳነው ከታሪኩ መማር ይገባናል (ዮናስ 1፥1-4)። ስለዚህ እግዚአብሔር የማይገኝበት ቦታ እንደሌለና የእርሱም ዓይኖች እንደሚያዩንና እንደሚቆጣጠሩን ብናውቅና በየጊዜውም ይህንን ብናስታውስ ከብዙ ስሕተቶች ለመዳን ያስችለናል።

6 <u>የእግዚአብሔር መግቦቱና ጥበቃው</u> ቸርነቱ የሚታወቅበት የባሕርዩ መገለጫ ነው። መመገብና መጠበቅ አንድ ወገን ሆኖ እግዚአብሔር የፈጠረውን ዓለም የተወውና የረሳው ሳይሆን ሁልጊዜ እንደሚመለከተውና እንደሚንከባከበው የሚያስረዳን መለኮታዊ ባሕርይ ነው። አንድ አባት ቤቱን ንብረቱን ቤተሰቦቹን ሁሉ፥ ትንሹንም ትልቁንም ክፉዎችንም ደጎችንም ቤተ ዘመዱን፥ የቤት እንስሶችንም ጭምር እንደሚመግብና እንደሚያስተዳድር እንዲሁም እግዚአብሔር ሥነ ፍጥረቱንና በመሬት ላይ የሚኖሩትንም የሰዎች ልጆችንና እንስሳትን ሁሉ ይመግባል፥ ይጠብቃል፥ ዝናቡን ያዘንባል፥ ፀሐዩን ያወጣል፥ ለደጎችም ለክፉዎችም ያስተዳድራልም። (ማቴ.5፥45) እንደ አባትነቱ ይመግባል፤ እንደ ባል ተብሎ እንደ ተጻፈ በመቅጣት ያርመዋል መሪነቱ ያስተዳድራል። እንደ ዳኝነቱ ያጠፋውን ማንም ጠፍቶ ተረስቶ እንዲቀር አይወድም። ሆኖም ሁሉ ሰው እንደ ፈቃዱ በዚህ ዓለም በነፃነት እንዲኖር ፈቅዶለታል። ይህም የሰው ነፃነት ከአዳም ጀምሮ የጥፋቱና የውድቀቱ ምንጭ ስለሆነ በዚህ ዓለም ላይ ክፋት ተንሰራፍቶ፥ ፈተናና ችግር ተስፋፍቶ እንመለከታለን። ይህንንም ሁኔታ የእግዚአብሔር ጥበቡና ፍርዱ ይቆጣጠረዋል። የእግዚአብሔር ጌታ ባወቀ በማይመረመር ጥበቃ ባይኖር ኖሮ ክፋት አመዝኖ ዓለም በጠፋች ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር የዓለም መንግሥታትንና አሕዛብን ሁሉ እንደሚቆጣጠርና እንደሚያስተዳድር ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዱናል። የፈርዖን፥ የናቡከደነፆር፥ የቂሮስ፥ የቆስጠንጢኖስና የሌሎችም ታሪክ ሁሉ ይህንኑ ያረጋግጡልናል። ክፉዎችን ለመቆጣጠር መልካ እግዚአብሔር የዓለምን ሕዝብ ይገዛል። እርሱ ባወቀ በየጊዜው የመንግሥታት መሪዎችን

www.ethiopianorthodox.org

ይቀያይራል፤ ይሾማል፤ ይሽራል (ዘፀአ.7-14፤ ዳን.4፡24-37፤ 2ኛ ዜና 36፡22-23፤ ዕዝራ 1፡1፤ ኢሳ.44፡28፤ 45፡1-13፤ ሮሜ 13፡1-7)፡፡

ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ምንም ምን የሚደረግ ነገር የለም፡፡ በእግ በዕድል በአጋጣሚ ተደረጉ የሚባሉት አልባሌ ነገሮች ሁሉ ሳይቀሩ ከእግዚአብሔር እውቀትና ቁጥጥር ውጭ አይደሉም፡፡ ይልቁንም አማኞች የእግዚአብሔር ጥበቃው እንደማይለያቸው አምነው ለሚያደርጉት መልካም ተግባር ሁሉ ያለ ፍርሃትና ስጋት በተአምኖ መሥራት ይገባቸዋል፡፡ ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ሳይፈሩ እንዲያስተምሩና እንዲመሰክሩ በማጽናናት ያለሰማያዊ አባታቸው ፈቃድ ምንም ነገር እንደማይፈጸም በምሳሌ አስረድቶ በመለኮታዊው ጥበቃው እንዲተማመኑ አድርጓቸዋል፡፡ እንዲህም አላቸው፡ "ሁለት ድንቢጦች በአምስት ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ ያለ አባታችሁ ፈቃድ በምድር ላይ አትወድቅም፡፡ የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቆጥሯል፡፡ እንግዲህ አትፍሩ፤ ከብዙ ድንቢጦች እናንተ ትበልጣላችሁ (ማቴ.10፡29-31)፡፡

ስለዚህ በእግዚአብሔር መጋቢነትና ጥበቃ በመተማመን ማድረግ የሚገባንን የዕለት ሥራችንን መሥራት እንጂ በሆነው ባልሆነው መጨነቅ አያስፈልግም፡፡ "እንግዲህ ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ፤ ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና፡፡ ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፡ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል" (ማቴ.6፡31-32)፡፡

7. <u>ቅድስና</u> እጅግ ከታወቁት ከእግዚአብሔር የባሕርዩ መገለጫዎች አንዱ ነው፡፡ ቅድስና ማለት ከኃጢአት፡ ከርኩሰት ስሜትና ከክፉ ሐሳብ፡ ከአስጸያፊ ነገሮች ሁሉ የራቀና የተለየ፡ ፍጹም ንጹሕ የሆነ፡ እንከን፡ ጉድለት፡ ድክመት፡ ነቀዕ የሌለበት ማለት ሲሆን ይኸውም ንጹሕ እምንጹሐን ቅዱስ እምቅዱሳን የሆነውን የመለኮትን ልዑል ባሕርይ የሚያመለክት ነው፡፡ ስለዚህ በእግዚአብሔር ዘንድ ኃጢአትና ርኩሰት፡ አጸያፊ ነገሮች ሁሉ የተጠሉና የተወገዙ ናቸው፡፡ እግዚአብሔር ቅዱስ ነው፡፡ በእርሱ ፊት ፍጹም ንጹሕ ነገር የለም፡፡ ሰማያትም እንኳ በእርሱ ፊት ንጹሕ አይደሉም (ኢዮብ 15፡15)፡፡ ስለሆነም ፍጥረት ሁሉ ለእርሱ ቅድስና ይንበረከካሉ፤ ቅድስናው የሚያስፈራና ድንቅ ነው፡፡ በሱራፌልም የሚቀርበው የቅድስና ምስጋና ድምፅ ሥር መሠረትን ያናውጣል፡ ክብሩም በሰማይም በምድርም የሞላ ነውና (ኢሳ.6፡1-4)፡፡ የእግዚአብሔር ቅድስና የተገለጠለት ነቢዩ ኢሳይያስም በቅድስናው ዙፋን ፊት ራሱን እንዳረከሰ ሰው ቆጠረው፡፡ ስለ ራሱም እንዲህ አለ፡ "እኔም፡ ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው በመሆኔ፡ ከንፈሮቻቸውም በረከሱባቸው ሕዝብ መካከል በመቀመጤ ዓይኖቼ የሠራዊትን ጌታ ንጉሡን እግዚአብሔርን ስለ አዩ ጠፍቻለሁና ወዮልኝ! አልሁ፡፡ ከሱራፌልም አንዱ እየበረረ ወደ እኔ መጣ፤ በእጁም ከመሠዊያው በጉጠት የወሰደው ፍም ነበረ፡፡ አፌንም ዳሰሰበትና፡ እነሆ፡ ይህ ከንፈሮችህን ነክቷል፤ በደልህም ከአንተ ተወገደ፡ ኃጢአትህም ተሰረየልህ አለኝ" (ኢሳ.6፡5-7)፡፡

እንግዲህ ስለ እግዚአብሔር የቅድስና ባሕርይ ማወቅ ብቻ አይጠቅመንም፡ ፈሪሃ እግዚአብሔርን ከእውቀት ጋር መያዝ ይኖርብናል፡፡ ስለዚህ እኛም እንደነቢዩ ወደ ቤተ እግዚአብሔ



ስለርኩሰታችንና በደላችን ወዮልን ብለን በንስሐ ብናዝንና ብንናዘዝ እግዚአብሔር መልእክተኛውን ካህኑን ልኮ ኃጢአታችንን ያስተሥርይልናል፤ ከመሠዊያው ላይ ያለውንም ያሳትፈናል፡፡ ከበደላችን ሁሉ ንጹሕ እንሆናለን፡ ከእግዚአብሔርም እንታረቃለን፡ ወደ እርሱም ለመቅረብና ባለሟልም ለመሆን እንችላለን፡፡

እግዚአብሔር ንጹሐ ባሕርይ ነው፤ ፈጽሞ ቅዱስ ነው፡፡ እኛም ቅዱስ እንድንሆን ታዘናል፡፡ "እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝና፤ ሰውነታችሁን ቀድሱ፤ ቅዱሳንም ሁኑ፤ እኔ ቅዱስ ነኝና" ተብሎ ተጽፏልና (ዘሌዋ. 11፡44)፡፡ "ስለዚህ የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃችሁና በመጠን ኖራችሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ የምታገኙትን ጸጋ ፈጽማችሁ ተስፋ አድርጉ፡፡ እንደሚታዘዙ ልጆች ባለማወቃችሁ አስቀድሞ የኖራችሁበትን ምኞት አትከተሉ፡፡ ዳሩ ግን፡ እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ በኑሯችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ" (1ኛጴጥ.1፡13-16)፡፡

8. <u>ፍጹም ጽድቅና ትክክለኛ ፍርድ፤ ፍትሕ ርትዕ</u> የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቡ ነው፡፡ እግዚአብሔር ፍጹም ጻድቅና እውነተኛ ፈራጅ ነው ስንል ከሰዎች ጋር ያለውን ሕጋዊና ግብረ ገባዊ ግንኙነት ያመለክታል፡፡ ፍጹም ጻድቅና ሁሉን አዋቂ በመሆኑ የሚሰጠው ውሳኔ ሁሉ፤ ፍትሕ ርትዕ የሞላበት ነው፡፡ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ይከፍለዋል፡፡ ለጻድቅ ሰው የጽድቅን ዋጋ ይከፍለዋል፤ ለኃጥኡ የኃጢአቱን ፍዳ ይሰጠዋል፡፡ የእግዚአብሔር ትክክለኛ ፍርድ የሚፈጸመው ሕጉን ና ኪዳኑን ለሰጣቸው አማኞች ብቻ አይደለም፡፡ እርሱ አሕዛብን ሁሉ በሕገ ልቡና መሠረት ይፈርድ ባቸዋል ወይም ይፈርድላቸዋል (ሮሜ.2፡12-16)፡፡ በዚያች በምታስፈራ በመጨረሻይቱ ቀን እግዚአብሔር የመጨረሻውን ይግባኝ የሌለበትን ፍርድ ይሰጣል፡፡ እስከዚያች ቀን ድረስ ግን በምድር ላይ ያሉት ሰዎች ከጥፋታቸው እንዲመለሱ በልዩ ልዩ ፈተናና ችግር ይገሥፃቸዋል፣ ይቀጣቸዋልም፡፡ የሰውን ልማቱን እንጂ ጥፋቱን የማይወድ አምላክ በታላቅ ትዕግሥቱ ለማንኛውም ሰው ከነኃጢአቱ ከመሞቱ በፊት የንስሐ ዕድል ይሰጠዋል፡፡ በእያንዳንዱ ላይ ከመፍረዱ በፊት የንስሐ ጥሪ ያደርግለታል (ሕዝ.18፡30-32)፡፡ ስለዚህ ነው "አዎን ፡ ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፤ ፍርዶችህ እውነትና ጽድቅ ናቸው" ተብሎ የተጻፈው (ራእይ 16፡7)፡፡

እግዚአብሔር ጠባቂያችንና መጋቢያችን አስተዳዳሪያችንም እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ድሆችን የሚበድሉትን፣ በንጹሐን ላይ ግፍ የሚውሉትን፣ በትዕቢትና በተንኮል ተነሣሥተው የወንድማቸውን ነፍስ የሚያጠፉትን ወንጀለኞች ሁሉ ዝም ብሎ አይመለከትም፤ ይከታተላቸዋል እንጂ አይተዋቸውም፡፡ በመጨረሻም አድልዎ የሌለበት ትክክለኛ ፍርዱን ይሰጣል፤ ግፈኛውን ይቀጣዋል፤ ቅዱሳኑን ይጠብቃል፤ የንጹሐንን ደም ይበቀላል፡፡ "እግዚአብሔር ፍርድን ይወዳልና" ተብሎ እንደ ተጻፈ (መዝ.36፡28)፡፡

9. <u>እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ ምሕረቱም ለዘላለም ነው፡፡</u> የእግዚአብሔር ባሕርይ በፍጹም ፍቅር ይገለጻል፡፡ ፍቅር ሲባል በዓለም የምናየው ሥጋዊና ስሜታዊ ፍቅር አለመሆኑን የማያውቁ ቢኖሩ በቅድ ማወቅ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ፍጹም ፍቅር ስንል እግዚአብሔር የሰውን

www.ethiopianorthodox.org

ዘር ሁሉ የወደደበት፣ መለኮታዊ ፍቅሩን ርኅራኄውንና አዘኔታውን፣ ቸ ነቱንና በጎ ሥራውን ሁሉ የሚያመለክት ነው። በዚህ ፍቅሩ እግዚአ ብሔር ዓለ ምን አድኖበታል። በምሕረቱም ለደካሞችና ለኃጢአተኞ ያዝናል፣ ከሞት ፍርድና ከእርግማን የሚድኑበትን መንገድ አዘጋጅቷል። በፍቅሩ ብዛት የተነሣ "ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና" ተብሎ እንደ ተጻፈ እናስታውስ (ዮሐ.3፥16-17)። እንግዲህ የዚህ እውነተኛ ፍቅር ትርጉ በልባችን ውስጥ ያለው ፍቅር ሳይሆን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን በልጁ ጸጋ ያስተሠረየበትን፣ የምሕረቱን ሥራ የፈጸመበት የእግዚአብሔር የባሕርይ ፍቅሩ እንደሆነ ከሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት እንማራለን። "እግዚአብሔር ፍቅር ነውና። በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፣ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና። ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እር ሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተሥረያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አ ይደለም" (1ኛዮሐ.4፥8-10)።

እንግዲህ እግዚአብሔር ልጁን ለኃጢአታችን መሥዋዕት እስከ ማድረግ ድረስ የወደደን እኛን ከክፋው ሁሉ አድኖ የዘላለም ሕይወትን መንግሥተ ሰማያትን ሊያወርሰን አስቦ ነው። ስለዚህ እኛም ፍቅሩን እያሰብን ማለት እኛ ሳንወደው በፊት እርሱ እንዲሁ እንደ ወደደን በማወቅ ወንድማችንን ማለት ሰውን ሁሉ እንዲሁ መውደድ እንደሚገባን የእግዚአብሔር ፍቅሩ ያሳስበናል። እንደዚሁም እንድናደርግ ተጽፏልና። "እርሱ አስቀድሞ ወዶ ናልና እኛ እንወደዋለን። . . . እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን" (1ኛዮሐ.4፥19-21)።

10. ***ያለ መለወጥ*** አንዱ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው። መለወጥ፣ መለዋወጥ፣ መቀነስ፣ መጨመር፣ ማሻሻልና ማረም የሰዎችን ጠባይና ሥራ የሚገልጽ እንጂ በእግዚአብሔር ባሕርይ ውስጥ የሚገኝ አይ ደለም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ፍጹም ስለሆነ በባሕርዩ ላይ መለዋ ወጥ ፈጽሞ የለም። "እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም" ተብሎ እንደ ተጻፈ እግዚአብሔር በፍጹምነቱ ለዘላለም ይኖራል (ሚል.3፥6)። ፍቅሩና ምሕረቱ ለዘላለም ነው፣ ቃሉም ለዘላለም የጸና ነው፣ ብልየት አልፈት የለበትም። "ሰማይና ምድር ያልፋሉ፣ ቃሌ ግን አያልፍም" በማለት እርሱ ባለቤቱ መስክሯል (ማቴ.24፥35)። በጎ ስጦታን የሚሰጠን ሰማያዊ አባታችን መለወጥ የሌለበት መሆኑን ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ ያረጋግጥልናል። "በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፣ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ" (ያዕ.1፥17)።

እንግዲህ እግዚአብሔር በባሕርዩ የማይለወጥና ፍጹም የሆነ ባሕርዩም ከዘላለም እስከ ዘላለም እንደጸና እንደሚኖር እናምናለን። "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለምም ያው ነው" ተብሎ እንደ ተጻፈ፣ እኛም በእርሱ እምነትና ፍቅር ያለመለወጥ ለዘላለም ጸንተን እንድንኖር በጸጋው ይርዳን (ዕብ.13፥8)።

እስካሁን ስለ ባሕርዩ ስለ ጠባይዓቱ ስንማር እግዚአብሔር ሰውን አፍ ቃሪ፣ ቸርነቱ የበዛ መሐሪና ይቅር ባይ እንደዚሁም ጻድቅና እውነተኛ ፈራጅ፣ ፍጹም ንጹሕና ቅዱስ መሆኑን እርሱ ራሱ ባለቤቱ የገለጸልን እን ዲያው እንድናውቀው ብቻ አይደለም። ነገር ግን እኛም በብዙ መንገድ እር ሱን እንድንመስለውና እንድንከተለ



ምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ካገኘነው ጋር የተካከለ የክብር እምነት ላገኙ" የጥንት ክርስቲያኖች ሲጽፍላቸው እግዚአብሔርን ስለ መምሰልና በተስፋው ቃል የእግዚአብሔር የባሕርዩ የክብሩ ተካፋዮች መሆናቸውን እንደሚከተለው ገልጾላቸዋል፣

> "የመለኮቱ ኃይል በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለ ሰጠን በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ እውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ። ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እን ድትሆኑ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን" (2ኛጴጥ.1፥1-4)።

"እግዚአብሔርንም የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው" ተብሏልና በእምነታችን ላይ ጨምረን "እግዚአብሔርን መምሰል" እንደሚገባን ተጽፏል (1ኛጢሞ.3፥16፤ 2ኛጴጥ.1፥6-7)። ስለዚህ ነው "እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደሆነ እናንተ ደግሞ በኑ ሯችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ" የተባለው (1ኛጴጥ.1፥15-16)። እርሱ ሰውን ሁሉ ወዳጅ እንደሆነ እኛም ሰውና እግዚአብሔርን መውደድ ይገባናል። እርሱ መሐሪና ይቅር ባይ፣ እውነተኛ ጻድቅና ትክክለኛ ፈራጅ እንደሆነ እኛም በነዚህና በመሳሰሉት ጠባይዓቱ እርሱን መምሰል ይኖርብናል። እንግዲህ ከኃጢአትና ከዓመፅ ሥራ ሁሉ በዚህም ዓለም ከሚገኙ ክርክሶችና ከክፉ ነገር ከሐሰትም ሁሉ ራሳችንን ጠብቀን የጽድቅ ፍሬን ለማፍራትና በአጠቃላይ እር ሱ ቅዱስ እንደሆነ እኛም ቅዱሳን እንድንሆን የሚያዘጋጀንን መመሪያና ሥርዓ ት ሠርቶልናል። ይኸውም ፈቃዱና ቃል ኪዳኑ የሚገለጽበት ለዘላለም ጸንቶ የሚኖረው የእግዚአብሔር ቃሉ ሕጉና ትእዛዙ ነው። ስለዚህም ከሀልዎቱ ጋር ጠባይዓቱን አውቀን ሕገ እግዚአብሔርን እንድንፈጽመው ከዚህ ቀጥሎ የተቀደ ሱትን ትእዛዛቱን እናጠናለን።

## 3. "ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ፥ እርሱንም ብቻ አምልክ" - ትእዛዛቱ

ይህ ርእስ የአሥሩ ቃላትን የመጀመሪያውን ማለት "ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ" የሚለውን ድንጋጌ በአዎንታዊ አገላለጽና አባ ባል አትልቶ የሚያሳየን ታላቅ ትእዛዝ ነው። ጌታ በፈተናው ወቅት ዲያብሎስ የዚህን ዓለም መንግሥታትና ክብራቸውን ካሳየው በኋላ ለእርሱ ቢሰግድለት ይህን ሁሉ እንደሚሰጠው ቢነግረው "ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏልና" ብሎ በመመለስ ድል ነስቶታል (ማቴ.4፥8-11)። እኛም ዛሬ በሰይጣን አማካይነት ከዓለሙ ውስጥ የሚመጣብንን አም ልኮተ እግዚአብሔርን የሚያስተወንን ፈተና ሁሉ በተጻፈው ቃል ጸንተን እን ድንቋቋመው ጌታ አብነት ሆኖናል። ጌታ የአሥሩ ቃላትን የመጀመሪያውን ትእዛዝ በዚህ ሁኔታ ፈጽሞ እኛም እንድንፈጽመው የሚያስችለንን ጸጋና ረድኤት ከእርሱ አግኝተናልና ከጥንቶቹ እሥራኤላውያን በበለጠ መንገድ ትእዛዛቱን ሁሉ ለመፈጸም በእርሱ መንፈስ እንበረታታለን።

"ኢታምልክ" ወይም " ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ" የተባለው ሌላ አምላክ ኖሮ ወይም ሌሎች አማልክት ኖረው ሳይሆን የሰው ልጆች ለፈጣሪ የሚገባውን አምልኮና ፍቅር ለፍጡር በመስጠታቸው ነው። በዚህ ዓለም ውስጥም ሆነ ውጭ የሚታየውም ሆነ የማይታየው ከመጠን በላይ ... ነገር የአምላክን ቦታ ይወስዳል። በፈጣሪ ሳይሆን ... ፍቅር ያደረበት ሰው ቢኖር በእንደዚህ ዓይነት ሰው

www.ethiopianorthodox.org

ልቡና ውስጥ ባዕድ አምልኮ ነግሷል፡፡ በዚህም የመጀመሪያውን ትእዛዝ "አ... ምልክን" ተላልፏል፡፡ አንዳንድ ሰው ከሁሉ በላይ አብልጦ ገንዘብን ይወ... ይሆናል፤ ባለው ጊዜ ሁሉ አገልግሎቱም፡ መገዛቱም ለገንዘብ ብቻ ከሆነ እ... ደዚህ ዓይነቱ ሰው በፍቅረ ንዋይ ተሸንፏል፡፡ እግዚአብሔርንም ረስቷል፡፡ እግዚአብሔርንና ገንዘብን ጐን ለጐን ለማገልገል አይቻልም፡፡ አንድ ሎሌ ለሁለት ጌቶች መገዛት አይቻለውምና (ማቴ.6፡24)፡፡

በአባይ ጥንቆላ፡ በኮከብ ቆጠራ፡ በአስማት ሥራ እና በመሳሰሉት ሁሉ የሚታመን ሰው እውነተኛውን የእግዚአብሔር አምልኮት ትቷል፡፡ ከእግ... ዚአብሔርም ርቋል፡፡ የክሕደት ኃጢአትም ፈጽሟል፤ ፈጣሪውንም በድሏል፡፡ እግዚአብሔር በአምልኮቱ ቀናተኛ አምላክ ስለሆነ ከፍተኛ ቅጣት ያገኘዋል፡፡

በዘመናችን እንደሚታየው በሳይንስና በምርምር በተገኙ ውጤቶችና መላምቶች ላይ ብቻ በመመሥረት የእግዚአብሔርን ቃል በማቃለል እምነታ... ቸውንና ትውክልታቸውን በራሳቸውና በእውቀታቸው ላይ ብቻ ያደረጉት ሰዎች... ሁሉ ከእግዚአብሔር ይልቅ ራሳቸውንና እውቀታቸውን ያስበለጡ ስለሆ... ነ የክሕደትና የትዕቢት ኃጢአት እንደፈጸሙ ይቆጠራል፡፡ ሃይማኖት አልባ የሆኑ ሰዎች ለእግዚአብሔር መገዛትን ትተው ለራሳቸው ስሜት በመገዛት ስለሚኖሩ ከጥንቶቹ ጣዖት አምላኪዎች ተለይተው አይታዩም፡፡ ሁሉም የመጀመሪያውን ሕግ ኢታምልክን ተላልፈዋልና፡፡ ይህና የመሳሰሉት ሁሉ ከባድ ኃጢአት በመሆናቸው በእግዚአብሔር ዘንድ የተወገዙ ናቸው፡፡ በሠለጠ... ነው ዓለም ውስጥ ከሚታየው ባዕድ አምልኮ አንዱ በሳይንስ እውቀት ሰበብ በተፈጥሮ ከተከሰተው ከቁስ አካል ሀልዎት በቀር መንፈሳዊ እውነታዎች እንዲ... ረሱ በመሆናቸው ብዙ ሰዎች ተሰናክለዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሳይንስን ለሰ... ብአዊ አገልግሎት በማዋልና ለሃይማኖት ተልዕኮ ማስፈጸሚያ መሣሪያ እን... ዲሆኑ በማድረግ አምልኮታችንን ለማስፋፋትና ለማጠናከር ይረዳናል፡፡

ከእግዚአብሔር የበለጠ ወይም ከእርሱ እኩል የምንወደውና የምን... ገዛለት ነገር መኖር የለበትም፡፡ ስለዚህ ከራሳችን ጀምረን ገንዘባችንን ወይም ዕውቀታችንን ወይም ጉልበታችንን ወይም ውበታችንን ወይም ሥራ... ችንን ወይም ሌሎች ይህንን የመሳሰሉ ነገሮችን በማድነቅ ይበልጥ እንወዳቸው... እንደሆነ ኀሊናችንን እንመርምር፡፡ ዓለም በእጁ ለሠራውና ለአዘጋጀው ነገር መገዛቱ ልማድ ነውና ምናልባት ራሳችንንና ጊዜያችንን የሚቆጣጠሩ "ትንንሽ እግዜሮች" በየቤታችን አብጅተን እንደሆነ እንመርምር፡፡ ምናልባት ከአንድ እግዚአብሔር ሌላ ልቡናችን የያዘው ካለ ወይም በስውር ለምንወደው ባእድ ነገር በስውር በደባልነት አክራይተነው እንደሆን ራሳችንን እንጠይቅ፡፡ በን... ስሓም ተመልሰን ስግደትና አምልኮት ለሚገባው ለእግዚአብሔር አምላክ ብቻ እንገዛ፡፡ እርሱን ብቻ እንውደድ፡፡ ከአምላክ ቀጥሎ የሚወደድ ሰው ብቻ ነው፡፡ ሌሎችን ነገሮች እንድንገለገልባቸው ተፈጠሩ እንጂ እንድናፈቅራ... ቸው አልታዘዝንም፡ የታዘዝነው ፍቅረ እግዚአብሔርና ፍቅረ ቢጽ ብቻ ነው፡፡ ይህንንም ብናደርግ ኢታምልክና ሌሎችንም ትእዛዛት ሁሉ በሚገባ ፈጽመናል፡፡

## *ለጌታ ለእግዚአብሔር አምልኮና ስግደት፥ ክብርና ምሥጋና ለቅዱሳንና ለመላእክት*

የአምልኮት ስግደት ለእግዚአብሔር ብቻ ነው፤ ይህም ማለት ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ለአንድ አምላክ ብቻ እንጂ ለመሳእክትና ለቅዱሳን አልታዘዘም፡፡ ምክንያቱም እነርሱ ፍጡራን በመሆናቸው ... የሚገባውን አምልኮት ለእነርሱ አናደ...



መልእክተኞችና አገልጋዮች፡ ወዳጆችና ባለሟሎች፡ በመንፈስ ቅዱስም የጸጋውና የክብሩ ተካፋዮች ለእኛም አማላጆች በመሆናቸው ስለ ክብራቸውና ስለ ቅድስናቸው የክብር ሰላምታና የጸጋ ምስጋና እናቀርብላቸዋለን፡፡ ከላይ እንደ ገለጽነው እንደ ፈጣሪ የአምልኮት ስግደት ሳይሆን ለቅዱሳን የሚገባው የሰላምታ፡ የክብርና የጸጋ ስግደት ነው፡፡ ይህም ማለት ለእግዚአብሔር ስንሰ... ግድ አምላክነቱን ፈጣሪነቱን አዳኝነቱን በማሰብ ጸጋውን እንዲሰጠን፡ ምሕረት እንዲያደርግልን እየጸለይን ነው፤ ለቅዱሳን ግን የሰላምታ የክብርና የጸጋ ስግደት ስናቀርብ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ሁሉ አብልጦ የፈጠራቸውና የመረጣቸው ክብርንና ሥልጣንን የሰጣቸው ወዳጆቹ ባለሟሎቹ መሆናቸውን እያሰብን ከእግዚአብሔር ይቅርታን ምሕረትን እንዲያሰጡን እንለምናቸዋለን፡፡

በሀገራችን ይትበሃል አንድ ሰው ለሌላው ሰላምታ ሲያቀርብ ከአንገቱ ደፋ ወይም ከወገቡ ጐንበስ ብሎ እጅ ይነሳል፡፡ በድሮ ጊዜም በእጅና በጉልበት መሬት በመንካት ለነገሥታት ሰላምታ ማቅረብ የተለመደ ነበር፡፡ ይህም የሰላምታ ወግ ለአምላክ የሚገባውን ስግደትን ስለሚመስል ብዙዎች ተቃውመውታል፡፡ የቤተ መንግሥቱም ወግ፡ የሰላምታውም ሥርዓት ከቀድሞ ነገሥታት ጋር አብሮ ያለፈ ስለሆነ በአሁኑ ጊዜ ጉዳዩ እምብዛም አያሳስበን ም፡፡ ሆኖም ቤተ ክርስቲያናችን አምላክ አማልክት ንጉሠ ነገሥት ለሆነው ሰማያዊ አባታችን የምታቀርበው የአምልኮት ሥርዓት ለፍጡራን የማይሰጥ መሆኑን አበክራ ለምእመናን ታስተምራለች፡፡ እግዚአብሔርም ለአምልኮቱ "ቀናተኛ አምላክ" መሆኑን ታስታውቃለች፡፡ ቃለ እግዚአብሔርንና የቤተ ክርስቲያንን ትምህርት በመቃወም የመጀመሪያውን ትእዛዝ ኢታምልክን የተላለፈ ሁሉ ከፍተኛ ቅጣት ይጠብቀዋል፡፡

በዘመናችን የምዕራባውያን አስተሳሰብና ባሕል እየተስፋፋ በመምጣቱ በሥርዓተ አምልኮት ላይ ችግር አስከትሏል፡፡ ስግደት የሚለው ቃል በእነርሱ ቋንቋ ለእግዚአብሔር ብቻ እንጂ ለሌላ የማይሰጥ ነው፡፡ እነርሱ ስግደት[83] የሚሉት የአምልኮት ስግደትን ብቻ ስለሆነ ሌላ ዓይነት ስግደት አያውቁም፡፡ ለባለሥልጣንም ሆነ ለጓደኞቻቸው የሚያቀርቡት ሰላምታ ሁሉ በእጅ ንቅናቄ ብቻ የሚፈጸም ነው፡፡ በሀገራችንና በባሕላችን ግን ከላይ እንደ ተጠቀሰው ለነገሥታትና ለንግሥታት፡ ለልዑላንና ለልዕልታት ወይም እነርሱን ለመሳ ሰሉት ሁሉ የሚሰጠው ሰላምታ በጣም ዝቅ ብሎ በእጅ መሬት በመንካት አን ዳንዴም ጫማቸውን ወይም መሬቱን በመሳም ይፈጸማል፡፡ ይህ ሁኔታ ከሰላ ምታ ያለፈ የስግደትን ቅርጽ የያዘ ስለሚመስል ቀደም ባለው ጊዜ በአገራችን በንጉሡ ዙፋን ችሎት አካባቢ የሚመጡ ሁሉ በተለይም ጐንበስ ቀና ማለቱ የሰለቻቸው አንዳንድ ሰዎች እንደ ስቅለት በዓል ኪራላይሶን መስሎ እን ደታያቸው በሐሜት ይናገሩ የነበረው ዘመናዊው የምዕራባውያን ባሕል ወደ አገራችን መግባት ከጀመረበት ወዲህ ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ በይበልጥ የምዕ ራባውያን አመለካከት እያደገ በመሄዱ ይልቁንም በሃይማኖት ተቃዋሚ ወገኖች በኩል ነገሩ እየተጠናከረ ሄዶ ወደ ቤተ ክርስቲያን እየገባ ነው፡፡

በአገራችን የክብር ሰላምታና የአምልኮት ስግደት በውጭ በሚታየው

83 በእንግሊዝኛ worship የሚለው ቃል መስገድ ወይም ስግደት ተብሎ ቢተረጐምም ለእግዚአብሔር ብቻ የሚቀርበውን ጠቅላላ ሥርዓተ አምልኮትን በማቴ.4፥10 እና በዮሐ.4፥23-24 እንደ ተገለጸው ያሳ ያል እንጂ እንደ ግዕዙና እንደ አማርኛው ቃል ቀጥተኛ ፍቺ መሠረት በተለይ ጉልበትን ወይም ግን ባርን መሬት አስነክቶ የሚደረገውን ስግደት አጉልቶ አያመለክትም፡፡ እንደዚህ ዓይነቱን ስግደት ማለት በአካል ንቅናቄ የሚደረጉትን የስግደት ዓይነቶች የሚገልጹ ሌሎች ተጨማሪ ቃላት አሉ፡፡ ከእ ነርሱም መካከል genuflexion የሚለው ቃል በጉልበት መንበርከክ ማለት ሲሆን prostration ደግሞ በግን ባር ... (... ሙሉ ሰውነትን መሬት አስነክቶ) መስገድ ነው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

መልካቸው ስለሚመሳሰሉ ተቃዋሚዎች ቤተ ክርስቲያናችንን ለፈጣሪና ለፍጡር እኩል ወይም አንድ ዓይነት ስግደት እንደምታደርግ ያስባሉ፤ በመቃወምም ይናገራሉ፡ ይጽፋሉም፡፡ እየማተብን ለቤተ ክርስቲያንና ለቅዱሳን ሥዕል ጉንበስ ቀና እያልን ስንሳለም ሲያዩን ለእግዚአብሔር ብቻ የሚገባውን የአምልኮት ስግደት የፈጸምን ይመስላቸዋል፡፡ ምንም አፍአዊው (ውጭአዊው) ድርጊት (ጉንበስ ቀና ማለቱ) አንድ ቢመስልም የሚለይበት ሁናቴው በእምነታችንና በአሳባችን ውስጥ ይገኛል፡፡ ለእግዚአብሔር ስንሰግድ ሁሉን ፈጥሮ የሚገዛ አንድ አምላክ አምልኮና ስግደት የባሕርዩ መሆኑን በማመን ሲሆን ለቅዱሳን ደግሞ የክብርና የሰላምታ የጸጋ ስግደት እናቀርባለን፡፡

እንግዲህ የሃይማኖቱ ነገር በባሕላዊው መንገድ እንዴት እንደ ተገለጸ ወይም መገለጽ እንዳለበት ማስተዋል ይገባናል እንጂ የተመረጡትንና የሚያከብራቸውን ቅዱሳኑን መንቀፍ ያከበራቸውን እግዚአብሔርን መንቀፍ ይሆንብናል፡፡ እንኳን ቅዱሳን ቀርቶ ከአባት ከእናት ጀምሮ ሰውን ማክበር የታዘዘ አይደለምን? በእነርሱ ላይ ክፉ ማሰብና ማድረግ የእግዚአብሔርን ተግሣጽ ይጋብዛል፡፡ "ወገሥጸ ነገሥተ በእንቲአሆሙ፤ ወኢትግሥሡ መሢሐንየ፤ ወኢታሕስሙ ዲበ ነቢያትየ" ተብሎ ተጽፏልና፡፡ ይህም ማለት "የቀባኋቸውን አትዳስሱ፡ በነቢያቴም ክፉ አታድርጉ ብሎ፡ ሰው ግፍ ያደርግባቸው ዘንድ አልፈቀደም፡ ስለ እነርሱም ነገሥታትን ገሥጸ" ማለት ነው (መዝ.104፡14-15)፡፡ ለዚህ ዓለም ገዢዎች ማለት በበላይ ላሉት የመንግሥት ባለሥልጣኖች እንኳ እንድንገዛና "መፈራት ለሚገባው መፈራትን፡ ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ" አልተባለምን? (ሮሜ.13፡1-7)፡፡

እንግዲህ ከእግዚአብሔር በታች ለቅዱሳን ክብር ይገባቸዋል ስንል በመንግሥተ ሰማያት ያላቸውን ክብርና ጸጋ በማሰብ ነው፡፡ እኛም ወደ እነሱ ክብር ለመድረስ አርአያቸውን በመከተል በጸሎታቸው እንዲያስቡን ከእግዚአብሔርም ጸጋና ረድኤት ምሕረትም እንዲያሰጡንና እንዲያማልዱን እንለምናቸዋለን፡፡ የቅዱሳን ፈጣሪና አምላክ ለሆነው ለአንድ አምላክ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ የባሕርይ ስግደትና አምልኮት እያቀረብን ለቅዱሳን ግን የጸጋ ስግደት በማቅረብ እናከብራቸዋለን፡፡ እንግዲህ ስግደት የሚለውን ቃል በማጠቃለል በሁለት ለይተን መተርጉም አለብን፤ የመጀመሪያው ለአምላክ የሚቀርበው የአምልኮት፡ የባሕርይ ስግደት ይባላል፤ ሁለተኛው ለቅዱሳን የሚቀርበው የጸጋ ስግደት ነው፡፡ እመቤታችንን ግን ከቅዱሳንና ከመላእክት የበለጠ ክብርና ጸጋ ከፈጣሪዋ የተሰጣት ስለሆነ እርስዋን ከፈጣሪ በታች ከቅዱሳን በላይ በተለየ ማዕረግ እናከብራታለን፡፡ ምክንያቱም እርስዋ የአምላክ እናት ሆናለችና፡፡ ለእመቤታችን ክብርና ምስጋና ለልጅዋ አምልኮና ስግደት ይገባል፡፡ "ላቲ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወለወልዳ አምልኮ ወስግደት"፡፡



## ፪ኛ "የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፤ አትስገድላቸው አታምልካቸውም"

ይህ ሁለተኛው ትእዛዝ ከመጀመሪያው ጋር የተያያዘ ነው "ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ" ያለው አጠቃላይ ሕግ ሲሆን ሁለተኛው ትእዛዝ ግን በተለይ ቅርጽንም ምሳሌንም እንዳናደርግ ይከለክላል፡፡ የትእዛዙ ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ነው፡፡

> "በላይ በሰማይ ካለው፡ በታችም በምድር ካለው፡ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ አትስገድላቸው አታምልካቸውምም በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ ለሚወዱኝ ትእዛዜን ም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአ ብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና (ዘጸ.20፡4-6)፡፡
>
> "አምላክ በሰው ብልሃትና አሳብ የተቀረጸውን ወርቅ ወይም ብር ወይም ድንጋይ እንዲመስል እናስብ ዘንድ አይገባንም" (የሐዋ.17፡29)፡፡
>
> "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል" (ዮሐ.4፡24)፡፡

ቅርጽንም ምስልንም ምሳሌ የሆነውን ነገር ሁሉ ከአምልኮተ እግዚአብሔር
ውስጥ እንዳናስገባው መከልከላችን እንደ ቀላል ሕግ መመልከት የለብንም፡፡ በአ
ሁኑ ጊዜ ቅርጽንና ምስልን ማድረግ የአምልኮት ችግር የሚያስከትል አይመ
ስልም፡፡ በጥንት ጊዜ ግን እንደዚህ አልነበረም፡፡ ይህንን የሚያደርጉ ጣዖት አም
ላኪዎች ነበሩ፡፡ በእነርሱም ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይነድ ነበር፡፡ እግዚአ
ብሔር በአምልኮቱ የሚመጡበትን ሳይፈርድባቸው አይተዋቸውምና፡፡ ስለዚህም
ይህ ትእዛዝ እግዚአብሔርን የሚወዱትንና የማይወዱትን የሚለይ ሕግ ነው፡፡

ይህ ትእዛዝ ከምድረ ግብፅ ከባርነት ቤት ላወጣቸው ለእሥራኤል ሕዝብ
የተሰጠ ቃል ኪዳን ስለሆነ ከባርነት ቀንበር ከፈርዖን እጅ ነፃ ያወጣቸውን አም
ላካቸውን በመጥላት ሕጉን ያፈረሱትን እስከ ሦስትና አራት ትውልድ ድረስ
መርገምን ያመጣባቸዋል፡፡ ለሚወዱትና ትእዛዙን ለሚጠብቁት ግን እስከ ሺህ
ትውልድ ድረስ ምሕረትን የሚያደርግ ቀናተኛ አምላክ እንደሆነ እርሱ ባለቤቱ
ገልጾልናል፡፡ "ቀናተኛ" መባሉ በአሉታዊ መንገድ ሳይሆን የመረጣቸውንና የአ
ዳናቸውን ወገኑን ርስቱን እንደ ልጅ የሚከባከበውን የእሥራኤል ሕዝብ እጅግ
ስለሚወዳቸው እነርሱ ደግሞ በአፀፋው እርሱን መውደድ ይገባቸዋል፡፡ ነገር ግን
በፍቅሩ ምትክ እርሱን ጠልተው ያደረገላቸውን ውለታ ረስተው በሐሰት ጉዳና
በመከተል አምላክ ላልሆነው ባዕድ አምላክ በመገዛታቸው እግዚአብሔርን እው
ነተኛ አምላካቸውን ያስቀናዋል፡ ያስቆጣዋልም፤ በቃል ኪዳኑም የሰጣቸውን
ተስፋ ያስቀርባቸዋል፡፡ እንግዲህ የእግዚአብሔር ቀናዒነት ለበጐ ነገር ነው፤
በእውነተኛው አምልኮት እንድንጸና የሚያደርገን ነው፡፡

ከላይ በሰማይ ያለውን የፀሐይን፡ የጨረቃንና የከዋክብትን፡ በምድርም
ካለው የሰውን የእንስሳትን፡ የአራዊትን፡ የአእዋፍን፡ ከምድርም በታች በውኃ
ካለው የዓሣን፡ የአዞንና የመሳሰሉትን ሁሉ በሥዕልና በቅርጽ ሠርተው እነርሱን
እንዳያመልኩና ለእነርሱ እንዳይሰግዱ እሥራኤላውያን ታዘዋል፡፡ ጥንት አሕዛብ
ያደርጉት ከነበሩት ከእንጨት ተቀርጸው ከድንጋይ ተጠርበው ከብረት ቀልጠው
የተሠሩትን ምስሎችና ሐውልቶች እሥራኤላውያን እንዳያመልኩ የሁለተኛው
ትእዛዝ ይደነግጋል፡፡ ምክንያቱም ሐዋርያው ጳውሎስ ጣዖታትን ያመልኩ የነበ
ሩትን የጥንት ግሪኮችን ሲያስተምር "አምላክ በሰው ብልሃትና አሳብ የተቀረ
ጸውን ወርቅ ወይም ብር ወይም ድንጋይ እንዲመስል እናስብ ዘንድ አይገባን
[illegible] (... 17፡29)፡፡
እዚህ ላይ [illegible]ዴት አእምሮ ጠባይዕ ያላቸው ሰዎች በገዛ ፈቃዳቸው

www.ethiopianorthodox.org

ተነሣሥተው በእጃቸው የሠሩት ምስልና ጣዖት እንደ እግዚአብሔር ለ... ሩት አሰቡ የሚል ጥያቄ በአእምሯችን ይጉላላ ይሆናል፡፡ በጽሞና ለተመለ... ጉዳዩ እጅግ የሚያስገርምና የሚያሳዝን ነው፡፡ ከዛሬ ሰዎች የጥንት ሰዎች አ... ዋቆች ሆነው አይደለም ለብዙ አማልክት ተገዢዎች የሆኑት፡፡ በሕገ ል... ፈጣሪ ለፍጥረቱ በፍጥረቱ ቢታወቅም በዚህ እውቀታቸው ሳይጸኑ ጣዖት አ... ኪዎች ሆኑ፡፡ ለዚህም ምክንያት አለው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እግዚአ... ብሔር በአሕዛብም ዘንድ የታወቀ መሆኑን ሲገልጥ "የሚታየው ባሕርይ እ... ሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠ... ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና" ካለ በኋላ የስሕተታቸውን ምክንያት ደግ... ሲያስረዳ "እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከበሩ... ስላላመሰገኑት . . . በአሳባቸው ከንቱ ሆኑ የማያስተውለውም ልባቸው ጨለመ" ብሏል፡፡ ስለሆነም "ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ " እግዚአብሔርን "በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መል... መስለው ለወጡ" (ሮሜ.1፥20-23)፡፡

አምላክን በባሕርዩ በሥዕልና በምሳሌ ማሳየት አይቻልም፤ ም... ያቱም እግዚአብሔር ከእይታ ውጭ ነው፡፡ "መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም" (ዮሐ.1፥18)፤ አይቶትም ሰው በሕይወት ሊኖር አ... ችልም፡፡ በመሠረቱ "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል" (ዮሐ.4፥24)፡፡ መንፈስን በምድራዊ ቁሳ... ቁስ ተቀርጾና ተቀናብሮ በተሠራ ምስል ወይም ሥዕልና ምሳሌ ማሳየት ካለመ... ቻሉም በላይ ወደ ባእድ አምልኮ የሚያመራ የሐሰት መንገድ ነው፡፡ እግዚአ... ብሔር መንፈስ ስለሆነ ይህን ወይም ያንን ይመስላል ብለን ለመናገር የመለኮ... ባሕርይ አይፈቅድልንም፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለው፦

> "እንግዲህ እግዚአብሔርን በማን ትመስሉታላችሁ? ወይስ በምን ምሳሌ ታስተያ... ዩታላችሁ? የተቀረጸውንስ ምስል ሠራተኛ ሠርቶታል፥ አንጥረኛም በወርቅ ለብጦታል፥ የብሩንም ሰንሰለት አፍስሶለታል . . . እንግዲህ እተካከለው ዘንድ በማን መሰላችሁኝ? ይላል ቅዱሱ፡፡ ዓይናችሁን ወደ ላይ አንሡታችሁ ተመልከቱ፤ እነዚህን የፈጠረ ማን ነው? ሠራዊታቸውን በቁጥር የሚያወጣ እርሱ ነው፥ ሁሉንም በየስማቸው ይጠራቸዋል፤ በኃይሉ ብዛትና በችሎቱ ብርታት አን... ድስ እንኳ አይታጣውም፡፡ . . . እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ፥ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው፤ አይደክምም፥ አይታክትም፥ ማስተዋሉም አይመ... ረመርም" (ኢሳ.40፥18-28)፡፡

ስለዚህም ጉዳይ ቀደም ብሎ ሊቀ ነቢያት ሙሴ ሕዝበ እሥራኤልን ሲያስጠ ነቅቅ፦ "እግዚአብሔር በኮሬብ /በደብረ ሲና/ በእሳት ውስጥ ሆኖ በተናገራችሁ ጊዜ መልክ ከቶ አላያችሁምና እጅግ ተጠንቀቁ እንዳትረክሱ፥ የተቀረጸውን ምስል የማናቸውንም ነገር ምሳሌ . . . እንዳታደርጉ" በማለት ሁለተኛውን ትእዛዝ በተለየ መንገድ አጠናክሮታል (ዘዳ.4፥15-18)፡፡ የእሥስራኤል አምላክ ለሕዝቡ በሲና ተራራ ላይ ሲገለጥ ድምፁ ተሰማ እንጂ መልክና ቅርጽ ያለው ነገር አልታየም፡፡ የታየ ነገር ቢኖር እሳትና ጢስ፥ ደመናና ጨለማ፥ የመብረቅ ብርሃንና ነፀብራቅ ሌሎችም እነዚህን የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እርሱ ግን ባሕርዩ ረቂቅ አኗኗሩ ምጡቅ ስለሆነ መልክ ኖሮት የሚታይና የሚጨበጥ ነገር አይደለም፡፡ ስለዚህ የእሥራኤል አምላክ ይህን ይመስላል ተብሎ የተሣለ ሥዕል በብሉይ ኪዳን ታሪክ አይገኝም፡፡

ከላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ሥዕልና ምሳሌም የተፈቀደበት ጊዜና ቦታ አለ፡፡ ይኸውም አሥሩ ቃላት የተጻፉበት ሁለቱ ጽላት የሚቀመጡበት በወርቅ የተለበጠው ታቦትና በታቦቱም መክደኛ ላይ "ከተቀጠቀጠ ወርቅ" የተሠራው የኪሩቤል ምስልና ሌላም ተቀርጸ... ነው (ዘጸ.25፥10-21፤ 37፥7-9፤ 1ኛ...



ሆነው ክንፋቸውን በዘረጉት ሁለት ኪሩቤል መካከል ጌታ ራሱ በጻፈው በምስክሩ ጽላት ላይ ባለው በሥርየት መክደኛው በረድኤት በመገኘት የእስራኤልን ልመና እንደሚሰማቸውና እንደሚያነጋግራቸው ተጽፏል፡፡ "በዚያም ከአንተ ጋር እገናኛለሁ፤ የእሥራኤልንም ልጆች ታዝዝ ዘንድ የምሰጥህን ነገር ሁሉ፥ በምስክሩ ታቦት ላይ ባለው በሁለት ኪሩቤል መካከል፥ በሥርየት መክደኛውም ላይ ሆኜ እነጋገርሃለሁ" (ዘጸ.25፡22)፡፡

እንግዲህ እዚህ ላይ እናስተውል፡፡ የእግዚአብሔር ድምፁ እንጂ መልኩና ቅርጹ አይታይም፡፡ ስለዚህ የኪሩቤል ሥዕል እንጂ ለእግዚአብሔር ሥዕል አልተሠራለትም፡፡ ቀደም ሲል እንደ ጠቀስነው አሁንም በታቦቱ ዙሪያ የእግዚአብሔርን ቃልና ድምፅ ከመስማት በቀር መልኩና ገጹ አይታይም፥ አይታወቅም፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ቃሉን በተጨባጭ ሁኔታ የሚገልጥበት ጊዜ እንደሚመጣ ለማሳወቅ ሲል አንድ ምሥጢራዊ ሥዕልና ምሳሌን እንዲሠራ ሙሴን አዘዘው፡፡ ሙሴም የነሐስ እባብ ሠርቶ በዓላማ ላይ ሰቀለው (ዘኁ.21፡4-9)፡፡ ይህም የምሥጢረ ሥጋዌን የመስቀሉን ነገር ይገልጣል (ዮሐ.3፡14-15)፡፡ የኃጢአት መርዝ የእግዚአብሔር ቃል ሰው ሆኖ በግልጥ የሚመጣና በሰይጣን የታመሙትን የሚያድንበትን ሁኔታ የሚያስረዳ ቀጥተኛ ትንቢት ነው፡፡ በሥጋ ብእሲ ከይሲ የመጣውን የዲያብሎስን ሥራ አካላዊ ቃል ክርስቶስ በሥጋ በመገለጥ አፍርሶታልና (1ኛዮሐ.3፡8፤ ራእይ 20፡2)፡፡ እንግዲህ ትንቢቱ ሲፈጸም በዘመነ ሥጋዌ ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ሥጋን ለብሶ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት በመገለጡ የእርሱን ሥዕልና ምሳሌ መሥራት ተቻለ፡፡ ምክንያቱም ሥግው ቃል በዓይን የሚታይ በእጅ የሚዳሰስ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የአምላክ ወልደ አምላክ የክርስቶስንና የእናቱን የእመቤታችንን፥ የመላእክትንና የቅዱሳንን ሥዕል ትቀበላለች፤ በአክብሮትም ትመለከተዋለች፡፡ በተቀደሰውም ቦታ ታስቀምጠዋለች፡፡

እስካሁን እንደ ተመለከትነው አንድ እግዚአብሔርን በሥዕልና በምስል ወይም በልዩ ልዩ ምሳሌ ቀርጾና ሠርቶ ማሳየትና ለእነርሱም መስገድ የተከለከለ መሆኑን ከሁለተኛው ትእዛዝ ተምረናል፡፡ ሆኖም የኪሩቤልን ሥዕልና የነሐሱን እባብ ምስል ደግሞ ስንመለከት ሥዕልና ምሳሌ በዘመነ ብሉይም እንደ ነበሩና እነርሱንም በአግባቡ እንድንጠቀምባቸው እንጂ እንድናመልካቸው የተሰጡን እንዳልሆኑ እንገነዘባለን፡፡ ንጉሡ ሰሎሞን ባሠራው ቤተ መቅደስ በውጭም በውስጥም ዙሪያውን ሥዕለ ኪሩቤል ነበረ፡፡ "በቤቱም ግንብ ሁሉ ዙሪያ በውስጥና በውጭ የኪሩቤልና የዘንባባ ዛፍ የፈነዳም አበባ ምስል ቀረጸ" ተብሎ ተጽፏል (1ኛነገሥ.6፡29)፡፡ ዛሬም የመላእክትና የቅዱሳን ሥዕል በሐዲስ ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ይገኛል፡፡ ቤተ ክርስቲያን አምሳለ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት እንደ መሆኗ መጠን እውነተኛ ገጸ ባሕርይዋ የሚታወቀው ከመላእክትና በአካለ ነፍስ ካሉት ቅዱሳን ጋር በአንድነት በመሆን ነው፡፡ ስለዚህም በምድር ያለችው ቤተ ክርስቲያን ብቻዋን እንዳልሆነች ለአማኞቿ የምታስተምረውና የምታስታውቀው ከእግዚአብሔር ጋር በሰማያዊው ሥፍራ የሚገኙትን ባለሟሎቹን በልዩ ልዩ ሥዕልና ምሳሌ በማሳየት ሲሆን ለእነርሱም የሚገባውን ክብርና ምስጋና በአግባቡ ታቀርባለች፡፡

ከሁሉም በላይ በዓላማ ላይ በተሰቀለው የነሐስ እባብ የተመሰለው የሚያድነን ጌታችን የዓለም መድኃኒት ሆኖ በመልዕልተ መስቀል ላይ መሰቀሉን የሚያሳይ መለከት ትንቢት ነው (ዘኁ.21፡4-9፤ ዮሐ.3፡14-15)፡፡ ስለሆነም በዘመነ ሥጋዌ የመዳናችን ምልክት ሆኗል፡፡ መስቀሉም የጌታችን ሥዕለ አድኅኖ በልዩ መልክ ተሥሎ ይገኛል፡፡ ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን ትእምርተ መስቀሉን ማዋና ዓላማዋ አድርጋዋለች፡፡ በመስቀሉም ምልክትነት ነገረ መስቀሉን በማስተማር ሰዎች ሁሉ በዓይናቸው "ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ...ፎቱና እርሱንም በማመን እንዲድኑ ማድረግ የቤተ

www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያን የዘወትር ተልዕኮዋ ነው (1ኛቆሮ.1፡18-25፤ 2፡2፤ ገላ.3፡1፤ኢፌ 2፡14-16፤ ቆላ.2፡14)።

እንግዲህ በዘመነ ሥጋዌ ከጌታችን ጀምሮ የእመቤታችን፣ የመላእክትና የቅዱሳን ሥዕሎችን ቤተ ክርስቲያን በከፍተኛ አክብሮት ጠብቃ ታስጠብቃለች። ለመስቀልና ለሥዕል ክብር የሚሰጠው የመስቀሉንና የሥዕሉን ባለቤት ማለት በሥዕሉ ላይ የተገለጸውን ነገር ማክበር እንደሆነ እንገነዘባለን። እንደ ሌሎቹ የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ቤተ ክርስቲያናችንም በሥርዓተ አምልኮት ትውፊት መሠረት ለሥዕል የአምልኮ ስግደት ሳይሆን የክብርና የጸጋ ስግደት እንደሚገባ ታምናለች። ስለዚህም ጉዳይ በሊቃውንት ጉባኤ የተጻፈውን እንደሚከተለው አቅርበናል።

"በሥዕል ፊት ቆሞ መጸለይ ከባለ ሥዕሉ ረድኤትን፣ በረከትን መለመን፣ መማጠን ነው። ለሥዕል የጸጋ ስግደትን መስገድ፣ ሥዕልን መሳለም፣ በሥዕሉ አማካይነት ለሥዕሉ ባለቤት ክብርንና ፍቅርን ለመግለጥ ነው። ይኸውም የቤተ ክርስቲያን ህልውና ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ የነበረ ጥንታዊ ትውፊት ነው።

"በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ለተግሉና በጸሎት ለከበሩ የጌታ፣ የእመቤታችን፣ የቅዱሳን መላእክት፣ ጻድቃንና ሰማዕታት ሥዕሎች የጸጋ፣ የአክብሮት ስግደት፣ አስተብርኮና አድንኖ ማቅረብ እንደሚገባ ቤተ ክርስቲያናችን ታምናለች፣ ታስተምራለች።"

"ቅድመ ሥዕልኪ እሰግድ፣ ወለሥዕለ ወልድኪ እገኒ፤
ማርያም ድንግል ማርያም እመ አዶኒ" (መልክዐ ሥዕል)[84]

ከላይ ደጋግመን እንደ ተመለከትነው ለሥዕል የምናቀርበው የአክብሮት እንጂ የአምልኮት ስግደት እንዳልሆነ ቤተ ክርስቲያን ከማሳሰብ አልተቆጠበችም። ይህም ሆኖ አንዳንድ ወገኖች የሥዕልን ነገር ጭራሹኑ አይቀበሉትም። እንደ እነርሱ አመለካከት አክብሮት እንኳ መስጠት እንደ ማያስፈልግ ይናገራሉ። ይህ የማይገባ ተቃውሞ ነው። ኧረ ለመሆኑ ሰው የወዳጁንና የዘመዱን ፎቶ እንኳ በደኅና ሁናቴ በመከባከብ ይዞ በተዘጋጀለት ቦታ በአክብሮት የማያስቀምጠው ማነው? ይልቁንስ ከማንም ሰው ይበልጥ የሚወደንን ወዳጃችንን፣ አዳኛችንን፣ ባለ ውለታችን የክርስቶስን ሥዕል እንዴት የበለጠ አናከብርም! ሥዕሉን የምናከብረው እኮ የሥዕሉን ባለቤት በማክበራችን ምክንያት ነው። ከሰማይ ወርዶ ከድንግል ተወልዶ በመስቀል ተሰቅሎ ያዳነንን የእሱን ሥዕል እንዴት በአክብሮት አንመለከተውም! የመድኃኒታችንን የልደት ሥዕል ከድንግል እናቱ ጋር (ምስለ ፍቁር ወልዳ)፣ የማዳኑን ሥራ በሥዕለ አድኅኖ (በሥነ ስቅለት) በማሳየትና በአክብሮት መጠበቅ ይገባናል። የክርስቶስን ወንጌል ለዓለም ያስተማሩትን ቅዱሳን ሐዋርያቱን፣ ስለ ስሙ በመመስከር መከራ የተቀበሉትን፣ በእሳት በስለት የሞቱትን ኃያላን ሰማዕታቱን ከነታሪካቸው በክብር እናስታውሳቸው ዘንድ ሥዕላቸውን እንጠቀማለን።

የተጻፈውን የቅዱስ መጽሐፍ ቃል አንብበን እግዚአብሔርንና የቸርነቱን ሥራ እንድናውቅና እንድናከብረው እንደሚረዳን እንደዚሁም የቤተ ክርስቲያንን

[84] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክር... (ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ሐምሌ 1988 ዓ.ም.)፤ ገጽ 97።



ሥዕሎች በማየት እግዚአብሔርንና የማዳን ሥራውን በቀላሉ ተረድተን አምላካችንን ለማክበርና ለማመስገን ያተጋናል። ስለዚህ የሥዕል ዓላማውና ጥቅሙ ቀላል አይደለም። "ሥዕል በቤተ ክርስቲያን ሁለት ዓይነት መልእክት" እንዳለው ከሊቃውንት ጉባኤ እንማራለን።

"ከእነዚህም አንዱ . . . የቅዱሳት መጻሕፍትን ታሪኮች ማንበብ ለማይችሉ ሰዎች ለማስረዳት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ማንንም ሳይፈሩና ሳያፍር ስለ ሃይማኖቱ መስክሮ በሰማዕትነት የሞተ ወይም ስለ ዓለምና ስለ ራሱ በመጸለይ መላ ሕይወቱን ከፍትወታት እኩያት ከአጋንንት ጋር በመጋደል ያሳለፈውን ሰማዕት ወይም ጻድቅ በሥዕል ለማስታወስ በሥዕሉም አማካይነት እያንዳንዱ ምእመን ለሥዕሉ ባለቤት ያለውን ክብርና ፍቅር ለመግለጥ ነው"[85]።

እንግዲህ የሥዕል እውነተኛ ጥቅምና አገልግሎት ከላይ እንደ ተገለጸው ሆኖ ሳለ ከመካከላችን አንዳንድ አማኞች ባለማወቅ ሥዕልን አላግባብ ሲጠቀሙበት ይታያል። ቤተ ክርስቲያን የማታውቀውንና የማትቀበለውን ሥዕል ሁሉ መጠቀም ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። አንዳንድ አጉል ሥዕል የሥዕሉን ባለቤት በማክበር ፈንታ የሚያስንቅ እንዲሆን ያደርገዋል። በተለይም በአላዋቂ ሠዓሊ የተሠራ ከሆነ፣ ከቃለ እግዚአብሔርና ከታሪክ ጋር ያልተገናዘበ ከሆነ ይህ ዓይነት ሥዕል ዋጋ የለውም። ዛሬ ለንግድ ተብሎ በብዛት የሚመረተው ሥዕላ ሥዕል እንደ ሸቀጥ ዕቃ በአልባሌ ቦታ ተደርድሮ ሲታይ ለሥዕል የሚሰጠውን አክብሮት እንዲቀነስ አድርጎታል። በቤተ ክርስቲያን ያልታወቀና ያልተፈቀደ ይህንን ዓይነት ሥዕል በመግዛትና በቤታቸው በማኖር አላግባብም በመጠቀማቸው የተነካ ብዙዎችን እያሳሳተና እውነተኛውን ሥርዓተ አምልኮት እያሰናከለ ይገኛል።[86]

ስለዚህ ምእመናን በቤተ ክርስቲያን የታወቀውንና በጸሎተ ቡራኬ የከበረውን ሥዕል መጠቀም እንዳለባቸው ካህናት ማስተማርና መምከር ይገባቸዋል። ምእመናንም ትምህርቱን ሰምተው መፈጸም እንጂ በገዛ ስሜታቸው የፈለጉትን በማድረግ ወደ ስሕተት እንዳይገቡ ይጠንቀቁ። ሥዕል የተፈቀደው የሥዕሉን ባለቤትና ታሪኩን ምእመናን ሁሉ እንዲያውቁትና እንዲያከብሩት

[85] ከላይ የተጠቀሰውን ተመልከት

[86] ሠዐሊዎች ሥዕሎቻቸው መንፈሳዊና ትምህርታዊ መልእክት እንዲኖራቸው ለማድረግ ቅዱሳት መጻሕፍትን እያነበቡ ታሪኩን እየተረዱ ሊቃውንትን እየጠየቁ በጥንቃቄ መሥራት ይገባቸዋል። ለ በለዚያ በምእመናንና በውጭ ተመልካቾች ዘንድ ሲታይ ሥዕሎቹ የተዛባ መልእክት ስለሚያስተላልፉ ለነቀፌታ የተጋለጡ ይሆናሉ። ነገረ መለኮትንና መንፈሳውያን ምሥጢራትን በሥዕል ለመግለጽ ያዳግታል፤ በተለይም ምሥጢረ ሥላሴን በሥዕል መግለጽ አይቻልም። የአንድነትንና የሦስትነትን ምሥጢር እንደ ቀላል ነገር በሰሌዳ ላይ ሥሎ ፈጣሪያችን ይህን ይመስላል ብሎ ማሳየት ለተቃዋሚዎችና ለተቺዎች መንገድ መስጠት ይሆናል። ምክንያቱም በሥዕሉ ላይ የሚንፀባረቀው የአካል ሦስትነት እንጂ የባሕርይና የመለኮት አንድነትን ለማሳየት ስለማይቻል ነው። በአንፃሩ ደግሞ የምዕራባውያን ሠዓሊዎች የመለኮት አንድነትን አጉልቶ ለማሳየት ሲሉ በአንድ ራስ ሦስት የሰው ገጾች ያሉትን ሥዕል ይሥላሉ። "The Trinity is shown with one head and three faces." Roland H. Bainton, The Church of Our Fathers (Philadelphia, The Westminster Press, 1950) p.42

ምሥጢረ ሥጋዌን ማለትም በሥጋ የተገለጠውን የክርስቶስን ታሪክ ግን በሥዕል ማሳየት ይቻላል፤ ማሳየትም ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም አንዳንድ የክርስቶስንና የቅዱሳኑን ታሪክና ትምህርት በቀላሉና በአጭሩ በሥዕል ለማስረዳት ስለሚቻል ነው። እንግዲህ መንፈሳውያን ሥዕሎች ጥራት ... ተፈላጊውን የቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርትና መልእክት በትክክል ለምእመናን እንዲያስተላልፉ ... ክርስቲያንን አይኮኖሎጂ (Iconology) ከማወቅ ጋር መንፈሳዊነት ያላቸው እንዲሆኑ ይገባል። Joseph ...arangatt (Dr.), "East as the Homeland of Iconology and Iconography: An Ecclesiologi-

www.ethiopianorthodox.org

እንጂ ሥዕሉን እንዲያመልኩት አይደለም። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ሥዕልንና ምስልን የሚያመልክ ማንም ቢኖር የአሥርቱ ቃላትን ሁለተኛ ትእዛዝ እንዳፈረሰ ይቆጠራል። "አትስገድላቸው፤ አታምልካቸውም" የተባለውን ሕግ ይተላለፋል (ዘጸ.20፡4-5)።

በሥዕል መገልገል አምልኮ የሚሆንብን በእንዴት ዓይነት ሁኔታ ስንጠቀም ነው? ሥዕል እንደ አምልኮ የሚቆጠርብን በእግዚአብሔር ፊንታ እምነታችንንና ትውክልታችንን በዓይነ ሥጋ በሚታየው በሥዕሉ ላይ ብቻ በምናደርግበት ጊዜ ነው። አማናዊውን ትተን፣ አማናዊ ባልሆነው፣ ለአማናዊው ነገር ምልክትና ምሳሌ በሆነው በሥዕሉ ላይ ብቻ በማተኮር ጸሎታችንና ተማጽኖችን እዚሁ ላይ ካከተመ እውነተኛው ሥርዓተ አምልኮ ይፋለሳል። እንዲህ ዓይነቱ መንገድና ከቃለ እግዚአብሔር ውጭ በግል ስሜት በመነሣሣት የሚፈጸመው ተማፅኖና አምልኮት ራስ ወደ ሆነው ወደ ክርስቶስና ወደ እግዚአብሔር አያደርስንም። ስለዚህ ሥዕልን ከምልክትነቱና ከምሳሌነቱ አልፎ ተርፎ እንደ አማናዊ ነገር ሳንቆጥረው ለሥዕሉ ባለቤት ጸሎታችንን ማቅረብ ይገባናል። ለሥዕሉ ባለቤት ስንልም ሥዕሉን እናከብረዋለን።

በሙሴ ዘመን በእባብ መርዝ የተነደፉ እሥራኤላውያን በዓላማ ላይ የተሰቀለውን የነሐስ እባብ በሚያዩበት ጊዜ ይድኑ ነበር (ዘኍ.21፡4-9፤ ዮሐ.3፡14-15)። በአርዌ ብርቱ (በነሐሱ እባብ) ምሳሌነት የክርስቶስን ማዳን ሙሴ ማስተማሩ ነበር እንጂ ከነሐስ ቀልጦ የተሠራው የእባብ ምስል ለዘላለም አማናዊ መድኃኒት አድርገው እንዲገለገሉበት አልተሰጣቸውም። ነገር ግን ይህን ባለመረዳት አንዳንድ እሥራኤላውያን የማዳኑ ኃይል ከእግዚአብሔር ሳይሆን ከምስሉ እየመሰላቸው በኮረብታው ላይ እጣን እያጠኑ ለብዙ ዘመናት ሲያመልኩት እስከ ንጉሡ ሕዝቅያስ ድረስ ቆይተዋል። ሕዝቅያስ ግን "አባቱ ዳዊት እንዳደረገው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገርን አደረገ፤ በኮረብታም ያሉትን መስገጃዎች አስወገደ፣ ሐውልቶችንም ቀለጣጠመ፤ የማምለኪያ ዐፀዶችንም ቆረጠ፤ የእሥራኤልም ልጆች እስከዚህ ዘመን ድረስ ያጥኑለት ነበርና ሙሴ የሠራውን የናሱን እባብ ሰባበረ፣ ስሙንም ነሑሽታን ብሎ ጠራው" (2ኛ ነገሥ.18፡3-4)።

ነሑሽታ የሚለው ስያሜ የተሠራበትን ነገር ያሳያል፤ ኔሐሼት ማለት ነሐስ ማለት እንደሆነና እንደዚሁም ናሐሽ ሲል ደግሞ ትርጉሙን ማለት እባብ መሆኑን እንደሚያመለክት የብሉያትና የዕብራይስጥ ቋንቋ መምህራን ያስተምራሉ። ሙሴ ለመልካም ነገር የሠራው አርዌ ብርት ዓላማውን ስቶ ከጊዜ በኋላ ለክፉ ነገር መዋሉ እጅግ ያሳዝናል። ታሪክ ራሱን እየደገመ ነውና ዛሬም እንዳንሳሳት እንጠንቀቅ። ከላይ እንደ ጠቀስነው ጥንትም ሆነ ዛሬ ሰዎች የሚሳሳቱት ማዳን የፈጣሪ መሆኑን ረስተው በፍጡር ላይ እንደሆነ አድርገው በሚያስቡበትና በሚያምኑበት ጊዜ ነው። የጥንት እሥራኤላውያን አርዌ ብርቱን በማየት ብቻ አልዳኑም፤ የእግዚአብሔርን ቃል በመከተልና እግዚአብሔርን በማመን ዳኑ እንጂ።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ መጽሐፈ ጥበብ በግብፅና በእሥራኤል ላይ የወረደውን የእግዚአብሔር ቅጣት በማነፃፀር የፊተኛው መዳን የሌለበት የሞት መቅሠፍት ሲሆን የኋለኛው ማለት የእሥራኤል ግን ሕገ እግዚአብሔርን እንዳይዘነጉ ለማሳሰብ የመዳን ምልክት ያለበት ጊዜያዊ ቅጣት እንደነበረ ያስረዳናል። መዳንም በዓላማው ላይ የተሰቀለውን የነሐስ እባብ "በማየት ብቻ" ሳይሆን በእግዚአብሔርና በቃሉ [illegible] ርዌ ብርቱ ለሥዕሉ ለምስሉ ያጠ[illegible]



ሁሉ የተነቀፉ ናቸው። ምክንያቱም እውነተኛውን ሥርዓተ አምልኮት አፋልሰዋልና፤ በተለይም የአሥሩ ቃላት ሁለተኛውን ትእዛዝ ተላልፈዋልና (ዘጸ.20፡4-6)። ስለዚሁ ጉዳይ በመጽሐፈ ጥበብ ምዕራፍ 16 ከቁጥር 5 እስከ 13 የሚገኘውን ምንባብ በማስተዋል እንመልከት፡

> "ክፉዎች የሚሆኑ የአራዊት ቁጣ ቢመጣባቸው ክፉዎች በሚሆኑ በምድር አውሬዎች[87] እንኳ ቢያልቁ ጥቂት ወራት ይቀጡ ዘንድ ታወኩ እንጂ ለዘለዓለሙ የጸናባቸው አይደለም የሕግህን ሥርዓት ያሳስባቸው ዘንድ ይህም ምልክት ድኅነት ሆናቸው። ከነዚህ ድኅ የተመለሰ ሰው ሁሉን የምታድን ሆይ ባንተ ስለ አመነ ዳነ እንጂ በማየት ብቻ የዳነ አይደለም፤ በዚህ ፈተንካቸው። . . . በልጆችህ በእሥራኤል ግን መርዝ ያለው የእባቦች ጥርስ በታዘዘ ጊዜ ቸርነትህ መጥቶላቸዋልና አዳናቸው። ሕግህን ለማሰብ ይህንን መከራ ተቀምሰዋልና፤ ፈጥነው በጽኑ ክህደት እንዳይወድቁ ተአምራትህን ከማሰብ ወጥተው በመከራና በሌላ ሥራ እንዳይወድቁ ፈጥነው ዳኑ። አቤቱ ሁሉን የሚያድን ቃልህ አዳናቸው እንጂ የሚጠጡት እንጨት የሚቀቡት አስማት ያዳናቸው አይደለም። ለሕይወትና ለሞት ሥልጣን አለህና ወደ መቃብር ታወርዳለህ ከመቃብርም ታወጣለህ" (ጥበብ 15፡5-13)።

## ፫ኛ. "የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ"

"የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና" በማለት የሦስተኛው ትእዛዝ ስሙን ከመቀደስና ከማመስገን በቀር በዋዛ ፈዛዛ በተርታ ነገር ሁሉ ስሙን ከመጥራት እንድንቆጠብ ያስጠነቅቀናል።

የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ከምንጠራበት መንገድ አንዱ መሐላ ነው። "እግዚአብሔር ይመስገን" ከማለት በስተቀር የእግዚአብሔርን ስም በየመንገዱና በየጨዋታ ቦታ ሁሉ ስሙን መጥራት ፈጽሞ የተከለከለ ነው። እንኳን በቀልድ በቁም ነገር ጊዜም እንኳ ቢሆን የተቀደሰውን ስም መጥራት አይፈቀድም። ይልቁንም በሆነ ባልሆነው መማል የእግዚአብሔርን ስም ማቃለል የተቀደሰውን ስሙን ማርከስ ስለሆነ ከባድ ኃጢአት ነው።

መሐላ ምን ማለት ነው? መሐላ ማለት አንድን ነገር ለማረጋገጥ ወይም ተስፋ የተሰጠው ነገር እንደሚፈጸም ለማስረዳት እግዚአብሔርን ምስክር፣ ዳኛና ዋስ እንደማድረግ ነው። ስለዚህ መሐላ በማይረባ የሰዎች ጉዳይ ውስጥ ኃያሉን እግዚአብሔርን በምስክርነት መጥራት የእግዚአብሔርን ክብር ማዋረድ መሆኑን አንርሳ። በእውነተኛ ነገሮችም እንኳ ቢሆን መሐላ አይፈቀድም።

ጌታችን በ፳ቱ ቃላተ ወንጌል ከቶ እንዳንምል አዝዞናል። በሰማይም በምድርም በታላቁ ከተማ በኢየሩሳሌምም ቢሆን በራሳችንም ቢሆን መሐላ ፈጽሞ የተከለከለ ነው። ስለዚህ ነገራችን ሁሉ እውነት ከሆነ እውነት! እውነት! እያልን እናረጋግጥ፤ ውሸት ከሆነ ውሸት! ውሸት! ነው በማለት ነገራችንን በዚህ እንግታው። ከዚህ የተረፈ ግን የክፉዎች መንገድ ነው። ክርስቶስ ያዘዘን "ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን፤ ከነዚህ

87 "በምድር አውሬዎች" የተባለው አርዌ ምድርን ወይም በብዙ ቁጥር አራዊተ ምድርን ወይም እንደ [illegible] የሚባል እባብ እሥራኤላውያንን በበረሓ በመርዙ እየነደፈ የፈጃቸው [illegible] ዌ ምድር እንደሆነ ከጥቅሱ ለመረዳት ይቻላል (ጥበ.15፡5)። እንደገና ስለ አርዌ ምድር በዚሁ ምዕራፍ ዝቅ ብሎ በቁጥር 10 ተጠቅሷል።

www.ethiopianorthodox.org

የወጣ ከክፉው ነው" (ማቴ.5፡33-37፤ ያዕ.5፡12)።

እንግዲህ ወጣቶችም ሆኑ ጐልማሶች በየመንገዱና በጨዋታ ላይ ሁሉ የክርስቶስን ትእዛዝ እያስታወስን የጌታን ስም በከንቱ እንዳንጠራ፣ በማናቸውም ስም መሐላ እንዳናደርግ መጠንቀቅና ሌሎችንም መምከር ይኖርብናል። በየቦታው የጌታን ስም የእመቤታችንን የመላእክትንና የጻድቃንን ስም በመጥራት የሚምሉና የሚገዘቱ ምእመናን ባለማወቅ ስለሆነ ካህናት እንዲያስተምሩና እንዲገሥጹ ምእመናንም የካህናቱን ማስጠንቀቂያ ሰምተው ከመሐላ በመራቅ የክርስቶስ ትእዛዝ ተፈጻሚነት እንዲያገኝ ቤተ ክርስቲያን ሁለቱንም ወገን አደራ ትላለች።

እንግዲህ የእግዚአብሔርን ስም የምንጠራው በግልና በማኅበር ጸሎት ጊዜ ይሆናል። ይህም ስሙን ለመቀደስ ስለሆነ የታዘዘ ነው። በሰላምታም ጊዜ "እግዚአብሔር ይመስገን" ማለት ከመልካም ባሕላችን አንዱ ነው። ከዚህ በተረፈ የእግዚአብሔርን ስም የምንጠራው በፍርድ ቤት በዳኛው ትእዛዝ ብቻ ይሆናል። ይኸም ቢሆን አስፈላጊ ሲሆንና ሌላ አማራጭ ሲጠፋ ብቻ ነው። ስሙን ጠርተን የምንመሰክረው ነገር ፍጹም እውነት መሆኑን መሐላችንን ከመስጠታችን በፊት ማረጋገጥ ይኖርብናል። እንደ ተጻፈው የሙግት ሁሉ መፈጸሚያው መሐላ ነውና (ዕብ.6፡16)።

የእግዚአብሔርንና የቅዱሳንን ስም በመጥራት መሐላ እንደ ተከለከለ ሁሉ፤ ማንም ሰው በራሱ ስም ሆነ በዘመዶቹ ወይም በታወቀ ነገር መማልም አልተፈቀደም። "እኔ ልሙት" "እከሌ ይሙት" እያሉ በየንግግሩ ውስጥ መማልና መገዘት መጥፎ ልማድ መሆኑን ተገንዝበን ራሳችንን ማረም ይኖርብናል። ግዴታ ሳይኖርብን ለማይጠቅምና ለማያስፈልግ ነገር ሁሉ በየንግግሩ መካከል ጣልቃ እያገቡ በከንቱ መማል ተናጋሪውን ይጐዳዋል እንጂ አይበጀውም። ምክንያቱም አንደበቱን የማይቆጣጠር እግዚአብሔርንም ራሱንም ሰውንም ይበድላል (ያዕ.3፡1-12)።

የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ የምንጠራበት ሌላው መንገድ በስድብና በርግማን ነው። ሳያስቡበት እንዲሁ በዘልማድ የእግዚአብሔርንና የቅዱሳንን ስም በመጥራት ሰዎችን በግልጽ ሲሰድቡና ሲያዋርዱ ይሉኝታ የሌላቸውና የማያፍሩ አንዳንድ ሰዎችን እንሰማለን። እንዲያውም "እግዚአብሔር . . . እንዲህ ያድርግህ . . . እንደዚያ ያድርግህ" እያሉ ሰውን በሚጐዳ በክፉ ቃል የሚሳደቡና የሚራገሙ እንዳሉ የታወቀ ነው። ስለዚህ ለእንደዚህ ዓይነት ሰዎች አዝነን በትምህርትና በምክር እየረዳናቸው ልቡናቸው በፍቅርና በትዕግሥት እንዲታረምና ጠባያቸውም እንዲሻሻል ካህናትም ሆኑ ምእመናን የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል። በተለይም ካህናት ትምህርትና ሥነ ምግባር የጐደላቸውን ምእመናን በማስተማርና በመገሥጽ ንስሐ እንዲገቡ በመምከርና ስለ ኃጢአታቸውም እንዲፀፀቱና የበደሉት ሰውም ካለ ካሣ እንዲከፍሉ ቀኖናም እንዲሰጣቸው ማድረግ የካህናት ሁሉ መንፈሳዊ ተልዕኮና አገልግሎት ነው።

በከንቱ ሳይሆን በቁም ነገር የእግዚአብሔርን ስም የምንጠራበት መንገድ አለ። ይህም አማኞች በእግዚአብሔር ፊት የሚያደርጉት ስዕለት ነው። ስዕለት በጸሎት አማካይነት በግልም ሆነ በማኅበር በብፅአት ወይም በመሐላና በቃል ኪዳን ለእግዚአብሔር ቃል የሚገባበትና ተስፋ የሚሰጥበት እምነት ከምግባር ተገናዝቦ በድርጊት የሚገለጽበት ልዩ መንገድ ነው ማለት ይቻላል።



ስዕለት ከማድረግ በፊት የሚቻልና የማይቻለውን ነገር ሁሉ ከመረመረ በኋላ ስዕለት ተሳዩ ሊፈጽም በሚችለው ነገር ብቻ መሳል ይኖርበታል። አለበለዚያ ስዕለቱን መፈጸም ካልቻለ መሐላውን እንዳፈረሰ የእግዚአብሔርንም ስም በከንቱ እንደ ጠራ ተቆጥሮ ከበደል ነፃ አይሆንም።

ለስዕለት የምናቀርባቸው ነገሮች በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያላቸው የተቀደሱ መሆን አለባቸው እንጂ አንዳንድ ትምህርት እንደ ጐደላቸው ሰዎች አይጡን ጉርጡን የማይረቡ አልባሌ ነገሮችን ሁሉ በቅድመ እግዚአብሔር ማቅረብ በደል ነው። ለጓደኛ በስጦታ መልክ ሊበረከት የማይገባውንና የሚያጸይፈውን ነገር በስዕለት ለእግዚአብሔር ወይም ለቅዱሳን ማቅረብ የተቀደሰውን ስም ማዋረድ ወይም ማርከስ መሆኑን እንዲገነዘቡና ይህንን ዓይነት ስዕለት የሚያገቡት ሰዎች ከዚህ አድራጐታቸው እንዲቆጠቡ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ስም ለምእመናን ሁሉ ታሳስባለች።

ማናቸውም ሰው ስዕለት ሲያገባ የስዕለቱን ዓይነት፣ የስዕለቱን መጠን ማለት ከባድና ቀላል መሆኑን መርምሮ፣ ግዴታውንም ለመወጣት መቻል አለመቻሉን አቅሙን መዝኖ ከንስሐ አባቱ ምክር ጠይቆ መፈጸም ይኖርበታል። ይህ የሆነ እንደሆነ ስዕለቱ ይሠምራል፤ የእግዚአብሔር ስም ይከበራል። አለበለዚያ አጉል ጸሎት ወይም አጉል ስዕለት ለቅሥፈት የተባለው ይደርስበታል።

አኗኗራቸውንና አገልግሎታቸውን በተመለከተ ብፅአት የገቡ ቃል ኪዳናቸውን በመሐላ ያጸኑ ለተቀደሰ ዓላማ ሲሉ የእግዚአብሔርን ስም የጠሩ ሁሉ ብፁዓን ናቸው። ጋብቻቸውን በምሥጢረ ተክሊል የፈጸሙ ምእመናን፣ የምሥጢረ ክህነትን ጸጋ በመቀበል እግዚአብሔርንና ምእመናንን ለማገልገል ቃል የገቡት ካህናት እንደዚሁም በምንኩስና ሥርዓት የገቡ በድንግልናና በተባሕትዎ በምናና የሚኖሩ መነኮሳት ሁሉ የቤተ ክርስቲያን እውነተኛ አባሎችና አገልጋዮች ናቸው። በገቡት ብፅአት የእግዚአብሔርን ስም አከብረውታልና፤ ለሰዎች ሁሉ አርአያ በመሆን የሰማይ አባታችንን አስመስግነውታልና (ማቴ.5፡16)።

## ፬ኛ. "የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ"

ስድስት ቀን ሠርተን ሰባተኛውን ቀን (ቅዳሜ) እንድናርፍ ታዘናል። ምክንያቱም "እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንም፣ ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ዐርፏልና፤ ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበትን ቀን ባርኮታል ቀድሶታልም" (ዘጸ.20፡8-11፤ ዘፍጥ.2፡1-3)።

በዚህ ትእዛዝ ውስጥ በመጀመሪያ የምንማረው፣ ሥራ የታዘዘ መሆኑን ነው። "ስድስት ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ" ይላል (ዘጸ.20፡9)። ከእረፍት በፊት ሥራ መታዘዙን እናስተውል። ማናቸውም ሰው በዘወትሩ ቀን ስንፍናን አስወግዶ የሥራን ክቡርነት አምኖ መሥራት ግዴታውና መብቱም ነው። ሥራ በርግማን የመጣ አይደለም። "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔደን ገነት አኖረው" (ዘፍ.2፡15) ተብሎ እንደ ተጻፈው ሰው ገና ሲፈጠር የሥራ ኃላፊነት ተሰጥቶታል። ሆኖም አዳም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በማፍረሱ ከእርሱ የተነሣ ምድር ተረገመች፣ እሾህና አሜከላ እንድታበቅል ሆነች። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በፊቱ ወዝ እንጀራ እንዲበላ ሆኗል። ይህም ሁናቴ የሥራ ብዛትንና [illegible] እንጂ ሥራ ቀድሞውንም የታዘዘ ነው። እግዚአብሔርም [illegible] ከረገመው በኋላ "ምድርንም ባረስህ ጊዜ እንግዲህ

www.ethiopianorthodox.org